**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Folklore/Cultural Studies Thesis and Dissertations

2011-06

# þÿ 9 9 è ¥ 3 d c L z ¥ “ J í ò ` ¥ “ - ¥ “ Í

# þÿ È ( ò : : p › ñ * ¨ I ë è @ ( ` % “

þÿ 5 “ u , è í •

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/14069

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

# ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ

## ፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል

# ‹‹ የህልም እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ››

## ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

**በ ስለናት የላይነህ**

ሰኔ 2011 ዓ.ም

<u>ባህርዳር</u>

# ‹‹የህልም እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ››

ባህር ዳር ዩንቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

ፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል

ድኅረ-ምረቃ መርሃ ግብር

ለፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በስለናት የላይነህ

አማካሪ፡- ዶ/ር አስቴር ሙሉ

ሰኔ 2011 ዓ.ም

<u>ባህር ዳር</u>

**ባህር ዳር ዩንቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ**

**ፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል**

**ድኅረ-ምረቃ መርሃ ግብር**

**በስለናት የላይነህ**

**ሰኔ 2011 ዓ.ም**

**ባህር ዳር**

**የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ**

**አማካሪ፡-** ………………………………………. **ፊርማ**………………...

**የውስጥ ፈታኝ፡-** ……………………………… **ፊርማ**………………

**የውጭ ፈታኝ፡-** ……………………………….. **ፊርማ**………………

# ማረጋገጫ

የህልም እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ በሚል ርዕስ  በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በፎክሎር( ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል የድኅረ-ምረቃ መርሃ ግብር፤ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**ስም ----------------------------------------- ፊርማ ---------------------------------ቀን -----------------**

## ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን እድል እንደአገኝ ላመቻቸልኝ ለመቀሌ ዩኒቨርስቲ ላቅ ያለ ምስጋና ይድረሰው፡፡ በመቀጠልም ከርዕሰ ጉዳዩ መረጣ ጀምሮ በምሰራበት ጊዜ አቅጣጫውን በማሳየት፣ የተጣመመውን በማቃናት፣ ለጥናቴ የሚጠቅሙ መረጃዎችን በመስጠት እና በማመላከት ስለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ፣ በተጣበበ ሰአት እየመጣው ሳስቸግር እንኳን እርዳታዎ ከፈገግታ እና ከሳቅ ጋር ሳይለየኝ ለአገዙኝ ለውድ አማካርዬ ለዶ/ር አስቴር ሙሉ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ፈጣሪ የሆድዎትን በጀርባዎ አድርጎሎትና በሰላም ተገላልለው ለማየት ያብቃኝ፡፡ በዚቺ አጭር የትምህርት ቆይታዬ ከእናንተ ትምህርታዊ እውቀትን ብቻ ሳይሆን ትህትናን፣ ታዛዥነትንና አስተዋይነትን ያስተማራችሁኝ ዶ/ር ዋልተንጉስ መኮንን፣ ዶ/ር ጥላሁን በጅቷል እና ዶ/ር ሶሎሞን ተሾመ መምህሮቼ ከምገልጸው በላይ አመሰግናሉ፡፡

በሰራሁት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠት እና አይዞታችሁ ላልተለኝ ለመምህር ታምሩ ደለለኝ፣ ለመምህር ሞገስ ሚካኤል፣ ለጋዜጠኛ ሀይማኖት ተስፋዬ ፣ ጋዜጠኛ ታደሰ ፀጋ እና የቅኔ መምህር ለሆኑት መ/ሪ መንክር ተስፌ እንዲሁም ሌሎች ስማችሁን ያልጠቀስኳችሁ በዚህ ስራ ላይ ሃሳባችሁን እና እጃችሁን ያሳረፋችሁ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳቹሁ፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ በወጣሁበት ጊዜ የራሳችሁን ስራ በመተው የምፈልገው መረጃ እንዳይቀር ቆላውን በመውረድ እና ደጋ በመውጣት አቅማችሁን እና ችሎታችሁን በማሚጠጥ የረዳችሁኝ በተለይም ውድ ጓደኛዬ ቦሰና ይግረም፣ ኤርሚያስ ስበር፣ ለተማሪ አባተ አንበል ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ለገነሜ የባህር ዳር የህዝብ ላይበራሪ እና ሰራተኞች በላይራሪያችሁ ስም እጅግ አድርጌ አመሰግናቹኋለሁ፡፡

መረጃ ለመሰብሰብ የወጣሁት መረጃ ሰጪ እንዳለ አስቤ ነውና ይህ ጥናት ከግብ እንዲደርስ ያደረገው እናንተ የሰጣችሁኝ መረጃ ስለሆነ በትህትና እና በአስተዋይነት መረጃ የሰጣችሁኝ ሁሉ ለመስጋናዬ ወደር የለውም፡፡ በመጨረሻም ከልጅነቴ ጀምራቹሁ የእናትነት እና የአባትነት የህትነት እና የወንድምነት ፍቅራቹሁ ላልተለየኝ አሁንም በስስት በማየት እና ጥንካሬ እንዲኖረኝ ለምታበረታቱኝ ቤተሰቦቼ ለውድ እናቴ ለታዘቢው እንየው፣ ለእኔ መምህር አባቴ ለየላይነህ ጀንበሬ፣ ልዩ ለሆንሽው እህቴ ታምሬ የላይነህ፣ የህጻን አንደበት በማይመስለው አንደበትህ ለእኔ ያለህን አይዞታህ ሳዳምጥ ብዙ ደረጃዎችን እራመዳለሁ እና ውድ ወንድሜ አበባው የላይነህ፣ ሃብታም የላይነህ እና ብርቱካን የላይነህ ምጋናዬ ከልብ ነው፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**

ምስጋና ........ ii
ማውጫ ........ iii
ከመጽሃፍት የወጡ ምዕጻረ- ቃላት ........ vi
ከማህበረሰቡ የተገኙ ሙዳዬ ቃላት ጥቂቶቹ ........ vii
አጠቃሎ ........ viii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 2
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4
1.3 የጥናቱ አላማ ........ 5
1.3.1 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች ........ 5
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 6
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 6
1.6 የጥናቱ አደረጃጀት ........ 7
ምዕራፍ ሁለት ........ 8
የጥናቱ ስነ-ዘዴ ........ 8
2.1 መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 8
2.1.1 ቃለ-መጠይቅ (interview) ........ 8
2.1.2 ቡድን ተኮር ውይይት (focus group discussion) ........ 10
2.2 መረጃ መሰብሰቢያ መቼት ........ 11
2.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 11
2.4 መረጃ መተንተኛ ዘዴ ........ 12
2.5 የመረጃ መተንተኛ ቲወሪ (ንድፈ ሃሳብ) ቅኝት ........ 13
2.5.1 ስነ-ልቦናዊ ንድፈ ሃሳብ ........ 13
2.5.1.1 አእምሮን /ስነ-ልቡናን/ የመገንባት፤የማነቃቃት ቲዮሪ (Drive or structural theory) ........ 15
2.5.2 ስነ-ፍቺ ንድፈ ሀሳብ ........ 18

2.5.3 ተግባራዊ ንድፈ-ሃሳብ (functionalism Theory) ..... 20
2.6 የመስክ ተሞክሮ ዘገባ ..... 21
2.7 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ..... 24
ምዕራፍ ሶስት ..... 25
ክለሳ ድርሳን ..... 25
3. የፅንሰ-ሀሳብ ቅኝት ..... 25
3.1 ሀገረሰባዊ ልማድ ..... 25
3.1.1 የሀገረሰባዊ ልማድ ክፍሎች ..... 27
3.1.1.1 ሀገረሰባዊ እምነት ..... 27
3.1.1.1.1 የህልም ምንነት ..... 28
3.1.1.1.1.1 የህልም አይነቶች ..... 45
3.2 የተዛማጅ ጹሁፍ ቅኝት ..... 46
ምዕራፍ አራት ..... 52
4.1 አካባቢያዊ ዳራ ..... 52
4.1.1 የወረዳው ስያሜ ..... 53
4.1.1.1 የወረዳው ቋንቋ እና ሃይማኖት ..... 54
ምዕራፍ አምስት ..... 55
5. መረጃ ትንተና ..... 55
5.1 ለእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ምንድን ነው? ..... 55
5.2 በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የህልም መወከያ ትዕምርቶች ምን ምን ናቸው? ..... 59
5.2.1 ምግብ እና መጠጦች በህልም ውስጥ ..... 60
5.2.2 አልባሳት በህልም ውስጥ ..... 71
5.2.3 ቁሳቁሶች በህልም ውስጥ ..... 81
5.2.4 እንስሳት በህልም ውስጥ ..... 88
5.2.5 እፅዋት በህልም ውስጥ ..... 96
5.2.6 ሰብሎች በህልም ውስጥ ..... 101
5.2.7 የሰዎች ቀለም፣ ግብር፣ እድሜ እና ፆታ በህልም ውስጥ ..... 105
5.2.8 የሰው ስሞች በህልም ውስጥ ..... 108
5.2.9 ሌሎች ነገሮች በህልም ውስጥ ..... 111

5.2.10 ህልም ምን ገጽታ አለው? ........ 122
5.3 በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ማን ያያል? ........ 123
5.3.1 የህልም ማያ ወሳኝ ጊዜ መቼ ነው? ........ 126
5.4 በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ፈቺ ማን ነው? መቼ ይፈታል? ........ 128
5.4.1 የህልም ፈቺዎች ማህበራዊ ደረጃ ........ 131
5.4.2 የህልም ፈቺዎች የለመዳ ሁኔታ ........ 133
5.5 የህልም ፋይዳ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ........ 134
5.5.1 የህልም ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ........ 134
5.5.2 የህልም ማህበራዊ ፋይዳ ........ 137
5.5.3 የህልም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ........ 137
5.4.4 የህልም ፖለቲካዊ ፋይዳ ........ 138
6. ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳብ ........ 140
6.1 ማጠቃለያ ........ 140
6.2 ይሁንታ ሃሳብ ........ 144
ዋቢ-መጽሀፍት ........ 146
አባሪ1፡-ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ የምርምር ጥቄዎች ........ 150
አባሪ2፡- አብይ መረጃ ሰጭዎች ........ 151
አባሪ3፡- ንዑሳን መረጃ ሰጭዎች ........ 152
አባሪ 4፡- ያልተተነተኑ የማህበረሰቡ ህልሞች ........ 153
አባሪ5፡- በመረጃ ስብሰባው ጊዜ የተነሱ ፎቶዎች ........ 155

## ከመጽሃፍት የወጡ ምዕጻረ- ቃላት

| ምዕጻረ-ቃላት | ፍቺ (ትርጉም) |
|---|---|
| መክ፡- | መክብብ |
| ማቴ፡- | ማቴወስ |
| ሐ.ሥ፡፡- | የሀዋርያት ስራ |
| ዘፍ፡- | ዘፍጥረት |
| ዳን፡- | ዳንኤል |
| ዘዳ፡- | ዘዳግም |
| ግዕ፡- | ግዕዝ |
| ዕብ፡- | ዕብራይስጥ |
| ዐረ፡- | ዐረብ |
| ኦ.ዘፍ፡- | ኦሪት ዘፍጥረት |
| ት.ዳን፡- | ትንቢተ ዳንኤል |
| ዐ.ኪ.ን፡- | አዲስ ኪዳን |
| ብ.ኪ.ን፡- | ብሉይ ኪዳን |
| አል.የሱፍ | የመጀመሪያው የሱፍ |

## ከማህበረሰቡ የተገኙ ሙዳዬ ቃላት ጥቂቶቹ

| ቃላት (ሀረጋት) | አውዳዊ ፍቺ (ትርጉም) |
|---|---|
| ዱዬ፡- | ጨምሬ |
| ባህር ሆዴን፡- | ዋናውን ሆዴን |
| ፈጅ፡- | በጎጥ ለተለያዩ ስራዎች አሰሪነት የሚሾም |
| ሰይጣን፡- | ጥሩ ያልሆነ መንፈስ ስም(መጠሪያ) |
| ወትሮ፡- | ድሮ፣ ጥንት |
| ጨዋ፡- | ቄስ ያልሆነ |
| ደንታ፡- | ግድ የለሽ መሆን |
| ቀፈት፡- | ገመድ |
| ጉብሳን፡- | ጻዲቅ |
| ሌማት፡- | ድግስ |
| ታርሳ፡- | ሴት ወልዳ ስትነሳ |
| በተ-ስኪያን (ቤተ-ክስያን)፡- | ቤተ-ክርስቲያን |
| ማጨት፡- | መጠየቅ |
| ውሬዛ፡- | ሰውን የሚቃወም መንፈስ |
| የሽብ የሽብ፡- | በጋራ |
| ከምንጣፉ ጠፍታ፡- | ከስታ |
| ንሺ፡- | እንቺ፣ ውሰጅ |
| ውቃቤ፡- | ልማዳዊ የአምልኮ አይነት |
| ፈላስማን፡- | ፈላስፋ |
| ሳሰማራ | ወደ መስክ ስወስድ |

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ‹‹ የእናርጅ እናውጋን ማህበረሰብ የህልምን እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳ መመርመር›› ላይ ያተኮረ ሲሆን ለዚህ አላማ መሳካት ደግሞ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ህልሞች፣ ፍችዎቻቸው እና በውስጥ የያዟቸው ትዕምርቶች ምን ምን ውክልና እንዳላቸው ማወቅ፣ ተጠኚው ማህበረሰብ ህልምን በመጠቀም ያለውን የህይዎት ፍልስፍና፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ የአኗኗር ዘይቤ ወ.ዘ.ተ በአጠቃላይ የማንነቱን መሰረት እንዴት እንደሚገልጽ ማወቅ፣ በማህበረሰቡ የህልም ማለሚያ (ማያ) ወሳኝ ጊዜያትን መመርመር፣ ህልም የሚያዩት (የሚያልሙት) እነማን እንደሆኑ እና ከምን አንጻር እንደሚያዩት፣ ህልም ፈችዎች እነማን እንደሆኑ እና እንዴት እንደሚፈቱ ማወቅ የሚሉ ንዑሳን አላማዎች ያካተተ ጥናት ነው፡፡

እነዚህን አላማዎች መሰረት ያደረጉ መረጃዎች ከቀዳማይ እና ካላዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበው በስነ-ልቦናዊ፣ በስነ-ፍቺ እና በተግባራዊ ቲዎሪዎች መረጃ መቀንበቢያነት በገለጻ እና በይዘት ትንተና ስልቶች መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱ የእናርጅ እናውጋን ማህበረሰብ ይወክላሉ የተባሉ አራት የገጠር ቀበሌዎችን በመምረጥ የመስክ መረጃዎችን የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም በቃለ-መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት በሃያ ስድስት አብይ /ቁልፍ/ መረጃ አቀባዮች እና በሃያ ንዑሳን መረጃ አቀባዮች መረጃው ተሰብስቧል፡፡

በመረጃ ትንተናው የህልም ማያ (ማለሚያ) ወሳኝ ጊዜያት እንዳሉ፣ ህልም በቀዳሚነት የአላሚውን ማንነት የሚለካ እና የሚገልፅ እንደሆነ፣ህልም አወንታዊ እና አሉታዊ ገጽታ እንዳለውና ገፅታውም ከፍቺው እና ከአደራረሱ የተወሰደ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ጥናት የህልምን ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የሆነ አወንታዊ እና አሉታዊ ማህበራዊ እና ግለሰባዊ ተፅእኖ እንዳለው መርምሮ ህልም ማለም አለብኝ ተብሎ ታቅዶ ይታለማል ከሚለው መደምደሚያ ሃሳብ ላይ ተደርሷል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር ህይወቱን ለማኖር የሚያስፈልጉት እና የማያስፈልጉት፣ ሲኖር የሚገጥሙትን ጥሩ እና መጥፎ ክስተቶችን የሚያስተናግድ ፍጡር ነው፡፡ ይህን ክስተት በመቃወም ሆነ በመቀበል ስሜትን የሚገልጽበት የተለያዩ መንገዶች አሉት፡፡ እነዚህ መንገዶችም የራሱን አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ ርዕዮተ አለም፣ ሃዘን፣ ደስታ፣ ፈጠራ፣ ጥላቻ፣ ፍቅር፣ ማሽነፍ፣ ማግኘት፣ ማጣት፣ መሸነፍ፣ እምነት፣ ሃይማኖት፣ ስራ፣ አምልኮ….ወዘተ የመሳሰሉ ጉዳዮችን የሚገለጹ ናቸው፡፡ የአገላለጹ መሰረትም ከማህበራዊ፣ ከባህላዊ፣ ከኢኮኖሚያዊ፣ ከፓለቲካዊ እና ከስነ-ልቦናዊ አንጻር ሊታይ ይችላል፡፡ እነዚህ ደግሞ እያንዳንዳቸው በውስጣቸው ሰፊ ጉዳዮችን ያካተቱ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል ስነ-ልቦናን ብንመለከት ከላይ ያሉትን በማካተት የሰው ልጅ ማለቂያ የሌለውን ውስጣዊ ፍላጎት እና ምኞት መለኪያ የሆኑትን ነገሮች ይመለከታል፡፡

የሰው ልጅ ፍላጎት እና ምርጫ በአኗኗር ውስጥ ድርሻ ይይዛል፡፡ ይህ ፍላጎት ደግሞ መሟላት እና አለመሟላት በሰው ህይወት ዘንድ አወንታዊ እና አሉታዊ ተጽዕኖ አለው፡፡ የተጽእኖዎቹ ጥቅም እና ጉዳት በተለያዩ የፎክሎር ቡድን ቅርጾች (ሎሮች) ይወጣሉ፡፡ ከእነዚህ ሎሮች መካከልም ተረቶች፣ አፈታሪኮች፣ ሚቶች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ፌስቲቫሎችና ከበራዎች፣ የእጅ ስራዎች፣ ህልሞች፣ ባህላዊ መድሃኒቶች፣ በአላት….ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከእነዚህ የማህበረሰብ ሎሮች መካከል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ህልም ነው፡፡ ስለሆነም የጥናቱ አቅጣጫ ህልምን መሰረት በማድረግ የእናርጅ እናውጋን ማህበረሰብ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ የህይወት ፍልስፍና፣ እምነት፣ የኗኗር ዘይቤውን…..ወዘተ የመሳሰሉትን ነገሮች እንዴት ይገልጻል የሚለውን ጉዳይ መርምሯል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

እያንዳንዱ ግለሰብ በዚህ ምድር ሲኖር የተለያዩ ፍላጎቶች አሉት። በኑሮው በሆነ ጉዳይ ፈፃሚ እና አስፈፃሚ የመመረጥ፣ የሆነ ፈጠራ የመፍጠር ተሰጥኦ ያለው ሰው ብቻ ነው። ተፈጥሮን መልክ ማስያዝ እና ትርጉም መስጠት፣ ተፈጥሮን በተለያየ መልክ መጠቀም የሚችል የሰው ፍጡር ነው። ይህን ሃሳብ በተመለከተ ‹‹አምስቱ አዕማደ ሚስጢር›› በሚለው መጽሃፍ በሰፊው ተገልጾ የምናገኘውን ከጥቃቅን ነፍሳት እስከ ሰው ልጅ ፍጥረት አፈጣጠር ያትታል። ይኸውም ፈጣሪ 22 ፍጥረታትን እንደፈጠረ እና 22ኛው ፍጥረት የሰው ልጅ እንደሆነ የሚያትት ሲሆን የሰው ልጅ በሀያ አንዱ ፍጥረት ንጉስ፣ ገዥ፣ አስተዳዳሪ፣ ተጠቃሚ እና አዛዥ አድርጎ እንደሾመው ይገልጻል። ስለዚህ ሰው ከሌላው ፍጡር በተለየ እልቆ ቢስ የተጠቃሚነት ፍላጎት እንዳለው ያሳያል። ይህ የተጠቃሚነት ፍላጎት እና ስሜት ሊሟላ እና በአንድም በሌላም ምክንያት ላይሟላ ይችላል። የተሟሉትን እና ያልተሟሉትን የሰው ልጅ ፍላጎት መግለጫ መንገዶች በርካታ ናቸው። አንዳንዶቹ አወንታዊ ሲሆኑ ደስታን መግለጫ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ አሉታዊ ሲሆኑ ሀዘንን መግለጫዎች ናቸው። እነዚህ መገለጫዎች በማህበረሰቡ የተበጁ እና ለትውልድ የሚያስተላልፏቸው ናቸው። ከእነዚህ መካከልም በተለያዩ የፎክሎር ዘውጎች ውስጥ የምናገኘውን መንፈሳዊ እና ቁሳዊ የማንነት መገለጫዎችን መጥቀስ ይቻላል። እነርሱም የእጅ ስራዎች፣ ዳንስ፣ ተረቶች፣ ሚቶች፣ አፈታሪኮች፣ ህልሞች ይገኙበታል። ይህን በተመለከተ Freud በስነ-ልቦናዊ ንድፈ ሃሳብ ህልሞች እና ሌሎች ከበራዎች፣ ስርዓቶች እንዱሁም ‹‹ሀራም›› የሆኑ ጉዳዮች በሰው ልጅ ኢ-ንቁው የአእምሮ ክፍል ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተሸሽገውና ታምቀው የቆዩ ድብቅ ፍላጎቶችን የሚገልፁ መሆናቸውን አሳይቷዋል። Thomas( 1997:668-669):-

> በፋሪስ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ባለፈው አስር አመታት የተጀመረው ሳይንሳዊ ስነ-ልቦና ላይ የተመሰረተው ቴክሊክ ሳይኮናቲክ ትንተና በሁለት መንገድ ይታያል። 1ኛ በአእምሯዊ ህይዎት ውስጥ ያሉ ክስተቶች በዘፈቀደ የተደረጉ አይደሉም። ይህ የሚወሰነው ደግሞ በ2ኛ የሚያውቅ አእምሯዊ ሂደት ብዙ ጊዜ የተለመዱ እና ያልተለመዱ በአእምሮ እንቅስቃሴዎች የሚጠቃለል ነው። በሰዎች ዝግጁ ህሌና ብቻ ሳይሆን በግለሰብ ቅድመ ህይዎት ውስጥ የአእምሯዊ ህይዎት አንዱ ነው። በሰው ዝግጅቶች ውስጥ ዝርያዎች አሉ። እነዚህም ህልሞች፣ ትዕምርቶች፣ ሚት፣ አፈታሪክ፣ ተረቶች፣ ቀልዶች እና ሌሎች ዕለት ከዕለት ጠባዮች ሳንጠነቀቅ ለምናያቸው ድርጊቶች

ተተኪ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ግምት ለፍሩዲያን የስነ-አእምሮ ትንታኔዎች (ተንታኞች) የፎክሎር ትውፊት ጥራቶች በግለሰብ የህይዎት ተሞክሮ ላይ በተነሱ ግጭቶች ውስጥ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሰረት ለስነ-መለኪያው ሞዴል አለም አቀፋዊ የሰው ልጅ ሳይንሳዊ አንድነት መኖር የግለሰብ ህልሞች በፎክሎር ቡድን ውስጥ ይካተታሉ፡፡

ከላይ የተገለፀው ሀሳብ እንደሚያመለክተው ፎክሎር እያንዳንዱ ግለሰብ ያለውን ፍላጎት ሊያሚላባቸው እና ሊያሳካባቸው የሚችሉ ጉዳዮችን ጠቅለል አድርጎ የሚይዝ መሆኑን ሲሆን በሰው ልጅ አእምሮ የተሰሩ እና ተግባራዊ እንደሚሆኑ ያመለክታል፡፡ ፍላጎት ብዙ አይነት እንደመሆኑ መጠን የፍላጎት ማሳኪያ (ማሚያ) መንገዶችም ብዙ ናቸው፡፡ በተለይም ፎክሎር ከስነ-ልቦና ጥናት አንፃር በርካታ ጉዳዮችን ልናነሳ እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ፍላጎት ከውጫዊ እና ከሚታየው ነገር ተነስቶ ውስጣዊውን የሰው ልጅ ፍላጎት አስተሳሰብና አመለካከት ለማዎቅ የሚያግዝ ስለሆነ ነው፡፡ ስለሆነም ከተገለፁት የፎክሎር አይነቶች ለሰው ልጅ ፍላጎት ማሳኪያ (ማሳያ) ጉዳዮች መካከል ህልም አንዱ ነው፡፡ ይህ ጥናት በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ማህበረሰቦች የህልም እሳቤን በተመለከተ የማህበረሰቡ አመለካከቱን እና አስተሳሰቡን በህልም እንዴት እንደሚገለፅ መመርመር የሚል ነው፡፡ የህልም እሳቤ በዚህ ጥናት በማህበረሰቡ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ወግ፣ ልማድ፣ እሴት እና ሀይማኖት አንፃር የተቃኘ ነው፡፡ ጥናቱ ከይዘት አንጻር ትኩረት ያደረገው የህልም እሳቤ በምስራቅ ጎጃም ዞን በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ማህበረሰብ ላይ ነው፡፡ ማንኛውም ማህበረሰብ የራሱ የሚለው የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት እና የእምነት መግለጫ መንገድ አለው፡፡ በተለይም ማንነቱን በሚገልጽ መልኩ የሚገነባው፣ የሚተገብረው፣ የሚከተለው፣ የሚያከብረው፣ የሚጠብቀው፣ የሚጋራው፣ ዕርስ በዕርስ የሚግባባበት እና ከትውልድ ትውልድ የሚያስተላልፈው ሃብት ይኖረዋል፡፡

ስለሆነም የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብም እራሱን የቻለ እምነት፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብ እንዲሁም የህይወት ፍልስፍና ያለው ማህበረሰብ በመሆኑ በርካታ መንፈሳዊ፣ ባህላዊ እና ቁሳዊ የማንነት መገለጫዎች አሉት፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ከይዘት አንፃር ትኩረት የተደረገው በህልም እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳ ላይ ነው፡፡

ህልም በፍሮይድ እይታ የምኞት ማሳኪያ ነው፡፡ ምኞት ደግሞ ከፍላጎት የሚመነጭ ነገር ነው፡፡ ይህ ነገር ደግሞ ትውልድ እስከተተካ ድረስ( የህይወት ኡደት እስከአለ ድረስ) ያለ፣ የኖረ፣ ወደፊት የሚኖር ሲሆን በተለያዩ የግለሰቦች ማንነት ላይ በተለያየ መንገድ ቅርጹን እየለዋወጠ በየጊዜው ሊተገበር ይችላል፡፡ ሁሉም ሰው አንድ አይነት ፍላጎት እና ምኞት

እንደሌለው ሁሉ አንድ አይነት ህልምም አያልምም፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ውክልናዎችን እና ፍቺዎችን የያዘ በተለያየ ቦታ እና ማህበረሰብ የተለያየ ፍቺ እና ትርጉም ሊሰጠው የሚችል የፎክሎር አንዱ ቅንጣት ነው፡፡ የሰው ልጅ በህይዎት ሲኖር በርካታ (ዘርፈ ብዙ) የተሟሉ፤ በመሟላት ላይ ያሉ እና ያልተሟሉ ፍላጎቶች አሉ፡፡ እነዚህ ፍላጎቶች ደግሞ በሰው ላይ የደስታን፤ የሀዘን እና የጭንቀት ስሜትን ይፈጥራሉ፡፡ እነዚህ ስሜቶች ደግሞ በተለያዩ ሎሮች ጎልተው (ይፋ) ሆነው ይወጣሉ፡፡ ከሚወጣባቸው መንገዶች መካከል አንዱ ህልም ነው፡፡ ህልም በማንኛውም ማህበረሰብ ዘንድ ያለ ስለሆነ እንደየ ባህሉ ወግ፣ ልማድ፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ እሴት፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ እንደሚኖርበት መልከአምድራዊ አቀማመጥ፣ አየር ፀባይ፣ የህይዎት ፍልስፍና ወ.ዘ.ተ ከመሳሰሉት ጉዳዮች አንፃር የተለያየ (ልዩ) ነው፡፡

ይህ ጥናት በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ማህበረሰቦች የህልም እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳን በተመለከተ የማህበረሰቡ አመለካከቱን እና አስተሳሰቡን በህልም እንዴት እንደሚገለፅ መመርመር የሚል ነው፡፡ የህልም እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳ በዚህ ጥናት በማህበረሰቡ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ወግ፣ ልማድ፣ እሴት እና ሀይማኖት አንፃር የተቃኘ ነው፡፡ ጥናቱ ከይዘት አንጻር ትኩረት ያደረገው የህልም እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳ በምስራቅ ጎጃም ዞን በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ማህበረሰብ ላይ ነው፡፡ ማንኛውም ማህበረሰብ የራሱ የሚለው የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት እና የእምነት መግለጫ መንገድ አለው፡፡ በተለይም ማንነቱን በሚገልጽ መልኩ የሚገነባው፣ የሚተገብረው፣ የሚከተለው፣ የሚያከብረው፣ የሚጠብቀው፣ የሚጋራው፣ ዕርስ በዕርስ የሚግባባበት እና ከትውልድ ትውልድ የሚያስተላልፈው ሃብት ይኖረዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማጥናት ያነሳሱኝ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ❖ በህልም ዙሪያ እንዳጠና ካነሳሱኝ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የመጀመሪያ ድግሪየን በፎክሎር ትምህርት መስክ ያገኘው ሲሆን ፎክሎር ገና ያልተነካ እና ያልተጠና ብዙ ነገር ያለው ጉዳይ መሆኑን ባሳለፍኩት የትምህርት ጊዜ ቆይታ ውስጥ ተገንዝቤ አልፌያለሁ፡፡ ካልተጠኑት ልምዶቹ ውስጥ ህልም አንዱ መሆኑን በመረዳቴ ባጠናውስ የሚል ሀሳብ በአእምሮዬ ሲመላለስ ቆይቷል፡፡ ይህንን ሃሳብም ቀጣዩ ገጠመኝ እንዳጠናው አድርጎኛል፡፡ ይኸውም፡-

- ❖ በባህርዳር ዩንቨርሲቲ ለትምህርት ከተለያየ መስሪያ ቤት እና ከተለያየ ቦታ ከተሰባሰብነው ጓደኞቼ ጋር ተዋውቀን እና ተላምደን በአንድ ተሰባስበን እየተማርን ከምናደርገው የተለያዩ ውይይቶች ውስጥ አንድ ጊዜ ስለ ህልም ባደረግነው ውይይት ስለ አንድ ህልም የተለያዩ ትርጉሞች እንዳሉት ለማየት ችያለሁ፡፡ ይህም ‹‹በእኛ እንዲህ ነው›› የሚል ነበር፡፡ የተወያየንበትም የህልም አይነት ስለ ‹‹ሰገራ በህልም መንካት እና መርገጥ›› ነበር፡፡ ፍቺው ግን በአንድ በኩል የመልካም እድል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመጥፎ እድል ተምሳሌት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የሚታለመው ህልም አንድ ሆኖ የተለያየ ፍች ያለው እና የሚታለመው ህልም የተለያየ ሆኖ አንድ አይነት ፍች ያለው ሆኖ ስናገኘው ልዩነቱን በምን እንደሆነ (ከምን አንጻር ልዩነት እንዳመጣ) ከበፊቱ በበለጠ የማወቅ ፍላጎቴ በጉዳዩ እንዳስብ አደረገኝ፡፡
- ❖ በአካባቢው ይህን ርዕሰ ጉዳዩ አስመልክቶ መረጃ የሰበሰበ እና ምርምር ያደረገ ተመራማሪ (አጥኝ) አለመኖሩ ርዕሠ ጉዳዩ አለመጠናቱ እንዳጠናው አነሳስቶኛል፡፡
- ❖ ከዚህ ባሻገርም የትውልድ አካባቢዬ በሆነው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ *‹‹ህልም እንደ ፈቺው ነው››፣ ‹‹ህልም አስፈጂ ነው››፣ ‹‹ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም››* ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት የማህበረሰብ እውቀትን በሰፊው ያዘሉ አባባሎች ጸንተው የቆዩ የማህበረሰቡ ሀብቶች ሲሆኑ ስለ ህልም ምንነት እና ስለ ህልም አፈታት ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳላቸው፣ ህልም በማህበረሰቡ እንደ ፈረስ ልጓም ሆኖ ሲያገለግል በዚሁ ቦታ ሳድግ እና ስኖር በማየቴ ለምን እንደሆነ ለማወቅ ስለጓጓሁ እና ከላይ የጠቀስኳቸው አባባሎች በማህበረሰቡ ዘንድ ይታወቁ እንጅ በሳይንሳዊ መንገድ ባለመጠናታቸው ሊጠኑ ይገባቸዋል በሚል ተነሳሽነት ጥናቱን አጥንቻለሁ፡፡ ሌላው ደግሞ ከዚህ በፊት የመጀመርያ ድግሪ መመረቂያ ጹሁፍ ‹‹ባህላዊ ት/ት በደብረ ወርቅ ገዳም›› በሚል ርዕስ የሰራሁት በዚሁ አካባቢ ስለሆነ መረጃ ለመሰብሰብ አይከብደኝም ብየ ስላሰብኩኝ ቦታውን መርጨዋለሁ፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በምስራቅ ጎጃም ዞን በእናርጅ እናውጋ ወረዳ የህልም እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳን መመርመር ሲሆን ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡-

### 1.3.1 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች

- ✓ ለእናርጅ እናውጋ ማኅበረሰብ ህልም ምን እንደሆነ መግለጽ

- ✓ በእናርጅ እናውጋ ማኅበረሰብ ህልም የሚመስልባቸው ትዕምርቶችን (መተርጎም) መፈከር
- ✓ በእናርጅ እናውጋ ማኅበረሰብ ዘንድ የህልም ፈቺዎችን ማንነትና የህልም የአፈታት ልምዳቸውን መግለጽ
- ✓ በእናርጅ እናውጋ ማኅበረሰብ ዘንድ የህልምን ፋይዳ ማሳየት

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

- ✓ በዚህ ርዕስ ዙርያ በሰፊው ለሚያጠናና ለሚመራመር ተመራማሪ ግብዓት (መነሻ ሀሳብ) ሆኖ ያገለግላል፡፡
- ✓ ስለ ተጠኚው ማህበረሰብ ህልምን በመጠቀም ያለውን የህይዎት ፍልስፍና፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ የአኗኗር ዘይቤ ወ.ዘ.ተ በአጠቃላይ የማንነታቸውን መሰረት ለማወቅ ለሚፈልጉ ግለሰቦች የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡
- ✓ በተወሰነ ደረጃ ቢሆን ማህበረሰቡን ያሳውቃል
- ✓ ተጠኝው ማህበረሰብ ህልምን ለምን አገልግሎት እንደሚያውለው እና አንዱን ህልም ከሌላው በምን እንደሚለይ  ግንዛቤ (ፍንጭ) ይሰጣል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች የተወሰነ ነው፡፡ አንደኛው በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጥናቱ በሚያርፍበት ቦታ ነው፡፡ ከርዕሱ ስንነሳ ጥናቱ የተካሄደው በDorsonን አከፋፈል 4 የፎክሎር ዘውጎች ሲኖሩ ከእነዚህም ውስጥ አንደኛው ማህበረሰባዊ ልማድ ነው፡፡ ሀገረሰባዊ ልማድ የምንለው በውስጡ የተለያዩ ንዑሳን ዘውጎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡ በዚህ ጥናት የተጠናው በማህበረሰቡ ከሚከወኑ ልምዶች መካከል ህልም ላይ በማተኮር ‹‹የህልም እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳ›› በሚል ርዕስ የተጠና ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጥናት የተካሄደበትን ቦታ የሚገልጽ (የሚመለከት) ነው፡፡ ከላይ የተገለጽው ጥናት የተካሄደው በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ሲሆን ወረዳው የተዋቀረው በ27 የገጠር ቀበሌዎች እና በ3 የከተማ ቀበሌዎች የተዋቀረ ሲሆን ከእነዚህ ቀበሌዎች መካከል 4 ያህል ቀበሌዎች ለጥናት ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡት ቀበሌዎች የገጠር ቀበሌዎች  ሲሆኑ ለመረጃ ሰጭነት የተመረጡት ግለሰቦች የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮች፣ በእድሜ ታላላቆች እና ሁለቱንም  ፆታ (ሴት እና ወንድ) ያካተተ ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በስድስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናታዊ ጽሁፉን መነሻ ነጥብ ለማስተዋወቅ የቀረቡ ዳራዊ መግለጫዎች፣ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ አላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎችና የጥናቱ ወሰን የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት የአጠናን ስነ-ዘዴዎችንና የጥናቱን ትወራዊ ማዕቀፎች (ንድፈ ሃሳቦች) የያዘ ነው፡፡ ምዕራፍ ሶስት ደግሞ ክላሳ ድርሳናት የቀረቡበት ክፍል ሲሆን የተዛማድ ጥናቶች ክለሳ እና ጽንሰ ሃሳባዊ ትንታኔዎች የሚገኙበት ነው፡፡

አራተኛው ምዕራፍ ጥናቱ ያረፈበትን ቦታ /ማህበረሰብ/ ማህበረ-ባህላዊ ገለጻዎችን በሚመለከት የተደረገን ትንተና የያዘ ነው፡፡ አምስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተደራጅተው እና ተተንትነው የቀረቡበት ምዕራፍ ነው፡፡ ስድስተኛው እና የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች ጠቅለል ባለ መልኩ የቀረቡበት ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ የህልም እሳቤ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ላይ የተገኙ መረጃዎች በስነ-ልቦናዊ፣ በስነ-ፍቺ እና በተግበራዊ ቲዎሪዎች በመቀንበብ እና በጽንሰ ሃሳብ ገለጻና ትንተና የተካሄደበት ጥናት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# የጥናቱ ስነ-ዘዴ

በዚህ ክፍል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መቼት፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች እና የመረጃ መተንተኛ ቲዎሪዎች የሚቃኙበት ክፍል ነው፡፡

## 2.1 መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ በዋናነት የተጠቀምኳቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለ-መጠይቅ እና የቡድን ተኮር ውይይት ናቸው፡፡ ይህን ያልኩበት ምክንያትም የህልም መረጃን ከማህበረሰቡ ለማግኘት ከምልከታ እና ከመጠይቅ በተሻለ መንገድ በመጠቀም መረጃውን ማግኘት ስለቻልኩ ነው፡፡ ይኸውም ህልም ሲያዩ ስለማይታይ እና የሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ከክወና ይልቅ በንግግር እና በዕርስ በዕርስ ውይይት መረጃውን ማውጣት ስለሚቻል ነው፡፡ እያንዳንዳቸውን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

### 2.1.1 ቃለ-መጠይቅ (interview)

ቃለ-መጠይቅ አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን መረጃ የሚሰጠውም ሆነ የሚቀበለው በቃል ፊት ለፊት ተገናኝተው የሚተገብሩት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ያለው የሚከተለውን ብለዋል፡፡ ያለው (2004፡)፡-

> በመሰረቱ ቃለ መጠይቅ በቃል የሚቀርብ መጠይቅ ነው፡፡ ከጹሁፍ መጠይቅ የሚለየው መላሹ እና ቃለ-መጠይቁን በሚያካሂደው ሰው መካከል የፊት ለፊት የቃላት ምልልስ በመኖሩ ነው፡፡ ጠያቂው ጥያቄዎቹን ለመላሹ ያቀርባል፤ ያብራራል፤ መላሹ ጋር ፊት ለፊት ሆኖ የተቻለውን ያህል መረጃ ለማግኘት ጥረት ያደርጋል፤ መላሹ ደግሞ ለተጠየቀው ነገር መልሱን በቃል ይሰጣል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ቃለ-መጠይቅ በጥያቄ እና መልሳችን ሂደት ላይ ያልገቡንን ጥያቄዎችና መልሶች እንዲብራራልን ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቃለ-መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን በተመለከተ Goldstein (1964:104) የሚከተለውን ይገልጻል፡፡

> Interviewing is the most common field method employed by folklore collectors. Interview data may include information on what the informat n knows, believes, expects, feels, wants, does, or has done or which explainsor gives reasons for any of the preceding. It supplies the collector with an insider's view to the individual, his culture, and his folklore.

ከላይ ያለው ጹሁፍ የያዘው ሃሳብ የሚያስገነዝበው ቃለ-መጠይቅ በፎክሎር የመስክ ምርምር የታወቀ መሆኑን ሲሆን የሚሰበሰበው መረጃም መረጃ አቀባዮች ምን ሊያውቁ እንደፈለጉ እምነቶችን፣ አስተሳሰቦችን፣ ፍላጎቶችን፣ የሚደረጉ እና የማይደረጉ ነገሮችን ሆነው እነዚህ ጉዳዮች የሚሰጡን ምክንያት ለሂደቱ ወሳኝ የሆኑ ናቸው፡፡ እንዲሁም ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው ከመረጃ ሰጭዎች ጋር ቤተኛ እንዲሆኑ ያደርጋል የሚል ነው፡፡ ስለሆነም ቃለ-መጠይቅ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች በትክክል ከተሰራበት እና ከተጠቀምንበት የተሻለ መረጃ የምናገኝበት ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃ ሰጭው እና መረጃ ተቀባዩ ፊት ለፊት ተገናኝተው የሚተገብሩት ስለሆነ መረጃ አቀባዩ የመረጃ ሰጭውን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያውቅበት መንገድ ስለሚፈጠር ትክክለኛ መረጃ እየሰጠው መሆን እና አለመሆኑን ማረጋገጥ ይችላል፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ ሰፊ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ሌላው ደግሞ ስለ ቃለ-መጠይቅ ምንነት እና ጠቀሜታ አለም (2001፡61) የሚከተለውን ገልጸዋል፡፡

> ቃለ-መጠይቅ ተጠያቂው ከጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝቶ በጽሁፍ ሳይሆን በቃል መልስ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡ ቃለ-መጠይቅ በብልሀት ከተያዘና ተግባር ላይ ከዋለ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያና ማጠናቀሪያ ስልቶች በተሻለ መንገድ መረጃ ለማሰባሰብ ያስችላል፡፡ ቃለ-መጠይቅ መረጃን ከዋናው ከምንጩ የመሰብሰቢያ መንገድ አንዱ በመሆኑም ርቱዕ የመረጃ ምንጮችን በመመርኮዝ የተሻለና የበለጠ አስተማማኝነት ያለው መረጃን ሰብስቦ ለማጠናቀር ያስችላል፡፡ ከዚህም በቀር ተጠያቂው ጥያቄውን በትክክል ሳይረዳው ቢቀር ጥያቄውን በማብራራት እንደገና ማስረዳት የሚቻልበት አጋጣሚ በቃለ- መጠይቅ ሂደት ውስጥ አለ፡፡

በመስክ ስራ እና ምርምር ወቅት ቃለ-መጠይቅ አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም ፎክሎሮኛው በመስክ ጉብኝት ወቅት ያስተዋላቸውን ጉዳዮች ወይም በክዋኔው ላይ ያስተዋላቸውን ነገሮች ፍች ለማወቅ በክዋኔው ላይ የተሳተፉት እና ባህሉን በሚገባ የሚያውቁ ሰዎችን በመምረጥ (በመለየት) ቃለ-መጠይቅ ማድረግ ስለሚችል ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ጥሩ

ቃለ-መጠይቅ የሚያደርግ ተመራማሪ ቃለ-መጠይቅን ከቃለ-ምልልስ መለየት እና በድብቅ ተግባራዊ እንደማይሆን ጠንቅቆ ማወቅ   እንዳለበት Jackson (1987፡) ‹‹Field Work›› በሚለው መጽሀፉ አስፍሮታል፡፡

ቃለ-መጠይቅ ስናደርግ የምንጠቀምባቸው ቃላት ቃለ-መጠይቅ የምናደርግለት ግለሰብ ሊረዳቸው የሚችሉና ሙያዊ ቃላት ባይሆኑ ይመረጣል፡፡ ቃለ-መጠይቅ ስናደርግ መሪ እና አስገዳጅ አማራጭ ጥያቄዎች እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ አንዱ ወይም ሁለቱን የቃለ-መጠይቅ አይነቶችን  መርጦ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ቃለ-መጠይቅ ሶስት ናቸው፡፡ እነርሱም፡- ውስን ቃለ-መጠይቅ (structured interview)፣ ከፊል ነጻ ቃለ-መጠይቅ (semistructured interview) እና ነጻ ቃለ-መጠይቅ (unstructured interview) ናቸው፡፡

ውስን ቃለ-መጠይቅ የሚባለው ተመራማሪው ለመላሹ የሚያቀርበው ጥያቄ ቀድሞ የተጻፈ እና ከዚያ ውጭ የማይጨመርበት ሲሆን ለመልስ የሚሆኑ አማራጮችንም ያካትታል፡፡ ሁለተኛው አይነት ከፊል ነጻ ቃለ-መጠይቅ ሲሆን ይህ ከነጻ የጹሁፍ መጠይቅ ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ከፊል ነጻ የተባለበት ምክንያት መላሹ የራሱን ሀሳብ ለመጠየቅ ነጻ የሚያደርገው እና በተወሰኑ አማራጮች ተገድቦ የግል ሀሳቡን እንዳይገልጽ ማእቀብ የሚያደርግበት አይደለም፡፡ ሶስተኛው እና የመጨረሻው አይነት ነጻ (ልቅ) ቃለ-መጠይቅ የሚባለው ሲሆን ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ነጻነትን ለመላሹም ለተመራማሪውም ይሰጣል፡፡ ከዚህ በመነሳት የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በከፊል ነጻ እና ነጻ (ልቅ)  የቃለ-መጠይቅ አይነቶች ነው፡፡ በከፊል ነጻ ህልም ምንድን ነው? በሚል ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ እና በነጻ (ልቅ) የቃለ-መጠይቅ አይነት ደግሞ ህልሞች እና ፍቺዎቻቸው እንዲሁም እንዴት እንደደረሱ የሚያሳዩ የማህበረሰብ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

### 2.1.2 ቡድን ተኮር ውይይት (focus group discussion)

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለተመረጠው ጥናት አስፈላጊ እና ወሳኝ ዘዴ ነው፡፡ አስፈላጊነቱም በተናጥል የቀረቡትን ጥያቄዎች እና መልስ የተሰጠባቸውን መረጃዎች በቡድን (በጋራ) ሆኖ በመወያየት የተሰበሰቡትን መልሶች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተነሱትን (የተረሱትን) ጥያቄዎች በማንሳት ሰፊ እና ጥልቅ መረጃን ለማግኘት የሚያግዝ በመሆኑ ነው፡፡ ያለው (2004፡191) የሚከተለውን አስቀምጧል፡፡

> በቡድን ተኮር ውይይት የሚካሄደው  በችግሩ ዙርያ በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎችን በመውሰድ በሚነሳው ጥያቄ ዙርያ በቡድን በመሆን

እየተወያዩ መረጃ እንዲሰጡ በማድረግ ሲሆን ተሳታፊዎቹ እስከ 12 ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ይህ ዘዴ የቡድን ቃለ-መጠይቅ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ከቃለ-መጠይቅ የሚለየው ዋናው ነጥብ በርካታ ሰዎች በአንድ ጊዜ መሳተፋቸው እና ጠያቂው ግድብ የሆነ ሚና መኖሩ ነው፡፡

ከላይ ያለው ሃሳብ የሚያስረዳው ቡድን ተኮር ውይይት አንድን ሃሳብ አንስቶ በተነሳው ሃሳብ ዙርያ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ የሚለውን ጉዳይ ያመላክታል፡፡ ስለሆነም የዚህን ጥናት መረጃ ሰጭዎች በተለይም ህልም ፈቺዎችን ስለ ህልም አፈታት ልማድ፣ ልምዱን እንዴት እንደለመዱት እና እንዴት እንደሚያስተላልፉት፣ የህልም አፈታት መሰረት ምን እንደሆነ፣ ህልም መቼ ይፈታል? በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በተመረጡት ቀበሌዎች የተወሰኑትን በማቧደን አወያይቻለሁ፡፡

## 2.2 መረጃ መሰብሰቢያ መቼት

የመስክ መቼት የምንለው አንድ ፎክሎር አጥኝ ፎክሎሩን የሚሰበስብበትን አውድ የሚመለከት ነው፡፡ ይህም አጥኝው የሚሰበስበውን መረጃ መቼ እና የት መሰብሰብ እንዳለበት ግንዛቤ የሚሰጥ ነው፡፡ አንድ የፎክሎር አጥኝ ስለ አንድ የፎክሎር ቅርጽ በተመለከተ የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅሞ መረጃን ሊሰበስብ ይችላል፡፡ በፎክሎር ጥናት ሶስት መረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች አሉ፡፡ እነሱም ተፈጥሯዊ መቼት፣ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት እና አርቲፍሻል መቼት ናቸው፡፡ ከእነዚህ መቼቶች መካከል የዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰበው በተፈጥሯዊ መቼት ነው፡፡ ተፈጥሯዊ መቼት በውስጡ ሶስት አውዶችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህም ከፍተኛ መደበኛ፣ ከፊል መደበኛ እና ኢ- መደበኛ  የሚባሉ አውዶችን የሚያካትት ሲሆን ተጠኝው ማህበረሰብ ህልምን አስመልክቶ የሚነጋገርበትን ቦታ በማጤን በከፊል መደበኛ እና በኢ-መደበኛ አውዶች መረጃው ተሰብስቧል፡፡ እነዚህ ቦታዎችም የአመት በአላት በደጋሾች ቤት፣ ቤተ-ክርስቲያን (የሰንበታ ሰንበቴ፣ የስላሴ ዝክርት፣ የሙት አመታት ዝክርት፣ የሰንበት)፣ የደብረ ዘይት በአል በቁሶች ቤት የንስሃ ልጅ የሚባሉት ግለሰቦች በተሰበሰቡበት ፣ ማህበር እና በተለያዩ ማህበራዊ ውይይቶች እና ንግግሮች ላይ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

## 2.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ናሙና የምንለው አንድን ጥናት ለማጥናት ስንነሳ የጥናታችን አካላዮች ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ ያንን ብዙሃኑን ይሸፍናሉ፤ መረጃውን በትክክል እናገኝባቸዋለን የምንላቸውን መረጃ ሰጭዎች ከጥናቱ አካላዮች የምንመርጥበትን ተግባር የሚመለከት ሃሳብ ነው፡፡ ናሙና በአንድም

በሌላም ችግር ሁሉንም ተጠኚ ልንወስደው ስለማንችል አስፈላጊ ነው፡፡ ያለው (2004፡120) ስለናሙና የሚከተለውን ገልጸዋል፡፡

> ናሙና ስንል በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ የጥናቱን አካላይ አባላት በሙሉ በመውሰድበጥናታችን ተሳታፊ ለማድረግ ሳንችል ስንቀር ወይም ማሳተፍ አስፈላጊ ሳይሆን ሲቀር ነገር ግን አጠቃላዩን ብንወስድ ልናገኝ እንችላለን ብለን የምናስበውን መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ ሰዎችን (ነገሮችን) ስርዓታዊና ተጠያቂያዊ መንገዶችን መበከላከል መርጠን በጥናታችን እንዲካተቱ እና መረጃ እንዲሰጡን የምናደርጋቸው የጥናቱ አካላይ ውስጥ ክፍል ናቸው፡፡ በቁጥር ከአካላዩ አብዛኛውን ጊዜ ያንሳሉ፡፡

ከላይ ባለው ሃሳብ መሰረት ናሙና ብዙውን የጥናት አካላይ ሊሸፍኑ የሚችሉ መረጃ ሰጭዎችን የመመልመል ተግባር እንደሆነ ያሳያል፡፡ ከላይኛው ሃሳብ በተጨማሪ ያለው (2004፡132) ‹‹እነማንን ብመርጥ የሚፈለገውን መረጃ ኖኖራቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ? የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የጥናቱን አላማ ለማሳካት ሰዎቹን ወይም ሌሎች ነገሮችን ይመርጣል››፡፡ በማለት ስለ ናሙና ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ናሙና ለምርምር ስራ አስፈላጊ ነው፡፡

ናሙና ሁለት አይነት ሲሆኑ እድል ሰጭ ናሙና እና ወሳኝ ናሙና ናቸው፡፡ ሁለቱም በውስጣቸው ንዑሳን የናሙና ዘዴዎች አሏቸው፡፡ ስለዚህ እኔ ለዚህ ጥናት በቂ መረጃ ይሰጡኛል ያልኳቸውን መረጃ ሰጭዎች የመረጥኩት ከወሳኝ ናሙና አይነቶች ውስጥ በጠቋሚ እና በአላማ ተኮር የናሙና ዘዴዎች ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥናት የሚሳተፉት መረጃ ሰጭዎች ሁሉም የጥናት አካላይ ልምዱን መከወን ስለማይችል እና መረጃ ሰጭዎችን ካለኝ ጊዜ፣ ገንዘብ እና ጉልበት አንጻር ሁሉንም ማካተት ስለማልችል በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ በህልም ፈችነት የታወቁ፣ ታማኝ የሆኑ፣ ትልቅ ቦታ እና ከበሬታ ያላቸውን ግለሰቦች መረጃዬ እስኪጠግብ ድረስ ለማግኘት በማህበረሰቡ ጥቆማ መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ እና በዚህ ጥናት የሚሳተፉትን መረጃ ሰጭዎች መምረጥ ያለብኝ ከጥናቴ አላማ አንጻር ስለሆነ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

## 2.4 መረጃ መተንተኛ ዘዴ

የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን አይነታዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ የምናገኛቸውን ገላጭ (Dsicrbtive) እና የይዘት ትንተና (content analysise) የሚባሉትን የመተንተኛ ዘዴዎችን ተጠቅሚያለሁ፡፡ ይህን የመረጠኩበት ምክንያትም ያለውን ነባራዊ ሁኔታ (ሀቅ) በገለጻ

ለማቅረብ እና የተሰበሰቡትን ህልሞች ከያዙት /ከአዘሉት/ ማህበረሰባዊ መልክት ወይም ፍሬ ነገር አንጻር ለመተንተን የሚመች ዘዴ ሆኖ ስላገኘሁት ነው፡፡

## 2.5 የመረጃ መተንተኛ ቲወሪ (ንድፈ ሃሳብ) ቅኝት

ንድፈ ሀሳቦች ለፎክሎር ጥናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ምክንያቱም የምናጠናውን ነገር መስመር ስለሚያሲዙልን ነው፡፡ ይህ ደግሞ የተመረጠው የጥናት ርዕስ በምን የመተንተኛ ንድፈ ሀሳብ እንተንትነው የሚለውን መረጃ የሚይዝልን ነው፡፡ በመሆኑም ንድፈ ሀሳብ የምንለው ኢትኖግራፊ የሆነውን መረጃ የምናይበት፣ አንጻር፣ የምንተነትንበት መንገድ ነው፡፡

ንድፈ ሃሳብን በተመለከተ የሚከተለውን ሃሳብ እንመልከት ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት (1978፡267) ‹‹ የእውነታን የተለያዩ ክፍሎሮች ስርዓት ባለውና በተጠቃለለ ሁኔታ የሚገልጽ ዕውቀት ንድፈ ሃሳብ ይባላል፡፡ ስርዓቱ የሚገልጸው የንድፈ ሃሳብን ስነ-አመክንዮአዊ ባህሪይ ሲሆን የተለያዩ ነገሮችንና ክስተቶችን የሚያገናዝብ በመሆኑ ደግሞ የማጠቃለል ጠባይ አለው፡፡ ›› በሚል ሰፍሯል፡፡ ሃሳቡ የሚያስረዳው ንድፈ-ሃሰብ አንድን ርዕሰ ጉዳይ በምን አተያይ እንመልከተው የሚለውን ሃሳብ የያዘ ነው፡፡

ስለሆነም ይህን ጥናት ከግብ ለማድርስ የተጠቀምኳቸው ቲወሪዎች ስነ-ልቦናዊ (Phycoanalisis Theory)፣ ጠቀሜታዊ(Functionalism Theory) እና ሴሜዮቲክስ (Semiotics Theory) ናቸው፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት አስፈላጊ እና ወሳኝ ስለሆኑት የስነ-ልቦና፣ ሴሜዮቲክስ እና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳቦችን እያንዳንዳቸውን እንደሚከተለው እንመልከት፡-

### 2.5.1 ስነ-ልቦናዊ ንድፈ ሃሳብ

ይህ ንድፈ ሃሳብ የሰው ልጅ ውስጣዊ አስተሳሰብ እና አመለካከት ለማወቅ የምንጠቀምበት ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ የፍካሬ ልቦና ቲወሪ ስነ-ልቦናን የሚያጠና ሲሆን ፍሮይድ የታመሙ ሰዎችን የኋላ ታሪክ እንዲናገሩ በማድረግ ለህመማቸው ምክንያት ያሳለፉት የበፊት ታሪካቸው ነው ብሎ በማሰብ የማከሚያ ዘዴ አድርጎ የፈጠረው ነው፡፡ ይህ የፎክሎር ንድፈ ሀሳብ በስነ-ልቦና አስተምህሮ ውስጥ ጉልህ ስፍራ የሚሰጠው እና የፍካሬ ልቦና (phychoanalysis) መስራች የሆነው የሲግመንድ ፍሮይድን (1856-1939) አስተሳሰብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የፍካሬ ልቦና የፎክሎር ንድፈ ሀሳብን የሚያራምዱ የተለያዩ የፎክሎር ባለሙያዎች የፍሮይድን አስተሳሰብ መሰረት በማድረግ በሚቶች፣ በተረቶች፣ በእምነቶች፣ በውዝዋዜዎችና በሌሎችም ፎክሎሮች ውስጥ ያሉ ተሞክእሮዎችን አጥንተዋል፡፡ በጥናታቸው መሰረትም በፎክሎሮች

ውስጥ የሚገኙ ትምዕርቶች የወሲብነት (sexuality) ትርጓሜን ይዘው እንደሚቀርቡ ገልጸዋል፡፡

ይህ ትወራ ከመነሻው ፍሮይድ የአእምሮ ህሙማንን ያለፈ የህይዎት ታሪክ በማዳመጥ እና ህልሞቻቸውን በመፍታት ህሙማኑን ለማከም ይገለገሉበት የነበረ ቢሆንም፣ በዚህ ዘመን በተለይም በአሜሪካ፣ ፍካሬ ልቦና ለህክምና የሚውሉ መረጃዎችን ከማስገኘት ባለፈ፣ የፎክሎሩን ባለቤቶች ስጋት፣ ጭንቀት፣ እውነተኛ ፍላጎት፣ ተስፋ ወ.ዘ.ተ. ለመረዳት፤ የከሸፈ የልጅነት ዘመን ፍላጎታቸው በኋለኛው ዘመን በህይዎታቸው የሚፀባረቅባቸውን መንገዶች የሚያስከትላቸውን ውጤቶች እንዲሁም የተጣለባቸውን ማህበራዊ ማዕቀብ የሚጥሱባቸውን ስልቶችና በእነዚህ ሁሉ ውስጥ የሚገኙትን ትምዕርቶች በመተንተን የሚጥሱባቸው ስልቶች በስፋት አገልግሎት ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ ለማ (2008፣1-2) ስለ ስነ-ልቦናዊ ንድፈ-ሃሳብ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍሯል፡፡

> ፍካሬ ልቦና ሌላው መስክ ሊያደርገው የማይችለውን፣ በቴክስቶች፣ በማህበራዊ፣ በታሪካዊ ፖለቲካዊ አውዶች መካከል ያለን ግንኙነት ለመተርጎም እንደሚያስችል ያስገነዝባሉ፡፡ ይህን በተሳካ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለውም፣ የባህል ጥናት ከፍካሬ ልቦና ራሱን ከፋታበት አስታርቆ ትኩረት የተላበሰ የቅርብ መናበብ ሲፈጥር እንደሆነም ያስገነዝባል፡፡

ከላይኛው ሃሳብ በተጨማሪ Lois (2006-10) ‹‹አለምን በስነ-ልቦና መነፀር ማየት የእያንዳንዱን ግለሰብ ህይዎት ምን እንደሚመስል ጭምቅ አድርገን ማወቅ እንችላለን፡፡ የስነ-ልቦና ታሪክ ከልጅነት በቤተሰብ ውስጥ የርዕስ በዕርስ ትስስር ይጀምራል፡፡ የስነ-ልቦና ጥናት የሚያገለግለው ስነ-ልቦናዊ የሆኑ ችግሮችን ማለትም የህይዎት ምስቅልቅል መፍታት ነው፡፡››

የተጠቀሱት ሃሳቦች የሚያስረዱት የስነ-ልቦና ንድፈ-ሃሳብ የሰው ልጅ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ እምነት፣ የህይወት ፍልስፍና በቀላሉ ለመረዳት የሚያስችል መሆኑን እና ንድፈ-ሃሳቡ አስፈላጊነቱ ከፍተኛ እና ቀዳሚውን ቦታ የሚይዝ መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም Freud በስነ-ልቦና ንድፈ ሀሳብ ህልሞች በሰው ልጅ ኢ-ንቁው የአእምሮ ክፍል ውስጥ ለረዥም ጊዜ ተሸሽገውና ታምቀው የቆዩ ድብቅ ፍላጎቶችን የሚገልጹ መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ ፍሮይድ ህልምን ወደ ድብቁ የአእምሯችን ክፍል የምንሸጋገርበት ብቻ ሳይሆን በህብረተሰቡ ውስጥ በጥብቅ የተወገዙ ጥልቅ ስሜቶቻችንን የምናስተናግድበት ነው ይላል፡፡ በመሆኑም ቲወሪውን መሰረት በማድረግ የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልምን እንዴት፣ ለምን፣

በምን...መንገድ ውስጣዊ የሆነውን አመለካከቱ እና አስተሳሰቡን፤ እውቀቱን ይገልጻል የሚለውን ለማወቅ እና የህልሞችን ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ማህበራዊ በሆነ ስልት ለማጥናት የስነ-ልቦናዊ ንድፈ ሀሳብ ቀዳሚውን ቦታ ስለሚይዝ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘሁት ተጠቅሜበታለሁ።

ንድፈ-ሃሳቡ የስነ-ልቦና እሳቤን ከተለያየ አቅጣጫ የሚያይባቸው እና የሚመረምርባቸው አራት ዋና ዋና ፓራዳይሞች በውስጡ ያካተተ ነው። እነዚህም በፍሮይድ አስተሳሰብ የተከፋፈሉ ሲሆኑ አእምሮን የመገንባት ቲወሪ (Drive Theory)፣ የግንኙነታዊ ቲወሪ (object Relations Theory)፣ የኢጎ ስነ-ልቦና ቲወሪ (Ego psycology theory) እና ለራስ ትልቅ ቦታ የመስጠት ስነ-ልቦናዊ ቲወሪ (self psychology) ናቸው። ከእነዚህ መካከል ለዚህ ጥናት ግብ መሳካት ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው አእምሮን የመገንባት ቲወሪ መሆኑ ከጥናቱ የተገኘ መረጃ የሚያመላክት ሲሆን ሌላው ደግሞ ህልምን ከአስተዳደግ አንጻር ማየት ስለሚያስችል ነው። ቲወሪው እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 2.5.1.1 አእምሮን /ስነ-ልቡናን/ የመገንባት፤የማነቃቃት ቲዮሪ (Drive or structural theory)

አእምሮን የመገንባት ቲዮሪ በ Freud አስተሳሰብ ነገሮች በሰው አእምሮ ውስጥ እንዴት እንደሚታዩ የመረመረበት ነው። ለነገሮች የተለየ ትኩረት በመስጠት በርካታ የስነ-ልቦና ችግሮችን ለመከላከል የተለያዩ የመግባቢያ ነጥቦችን በማፍለቅ የሰዎችን የአእምሮ ህመም ለማከም አዲስ ጽንሰ ሀሳብ ያሳየበት ቲዮሪ ነው። Freud በዚህ ቲዮሪ በወሲብ ፍላጎት ምክንያት እርካታ ያላገኘ ወይም ተስፋ የቆረጠ ስሜት (Frustrated) የነርቭ በሽታን ሊያመጣ ስለሚችልና ህመሙን ለማስወገድ ጥናት ባደረጉ የነርቭ በሽታ ተመራማሪዎች cahrcot እና Bernheim በተባሉ ሙህራን ተነሳሽነት ጥናቱን አጥንተዋል።

ከዚህ በመነሳት በኢ-ንቁ አእምሮ የሚከሰትን ችግር በማከም አእምሮን ለመገንባት የዕለት ከዕለት ተግባራቶቻችን በህይወታችን ውስጥ ምን ማለት እንደሆኑ እና እንዴት እንደሚታዩ የመረመረበት ቲዮሪ ነው። የቲዮሪው ዋና ጭብጥ ውስጣዊ ግጭቶችን ማከም አንደኛው ምክንያት ነው። ABE (2004) Freud (1984)ን በመጥቀስ በዚህ ሞዴል አእምሮ በአምስት የስነልቦናዊ መዋቅር አስተሳሰቦች የተገነባ መሆኑን ይገልፃሉ። እነርሱም መልከአምድራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ መዋቅራዊ፣ ልውውጣዊና እና ስነ-ባህሪያዊ በማለት በአእምሮ ውስጥ ያሉ አስተሳሰቦችን ከእነዚህ እይታ አንፃር የመረመረበት ነው።

በመልከአ ምድራዊ አቀማመጥ እይታ አእምሮን በመሬት አቀማመጥ ገጽታ አምሳል በመወከል ንቁ፣ ኢ-ንቁ እና ከፊል ንቁ ገጽታዎች በማለት ገልጸዋቸዋል፡፡ በልውውጣዊ እይታ አእምሮ ከፍተኛ በሆነ የወሲብ ስሜት የሚመጣ የቁጡነት ባህሪ በመሆኑ የመነቃቃት ቲዮሪ ይለዋል፡፡ በኢኮኖሚያዊ እይታ በሀብት አለመመጣጠን የመቀነስ እና የመጨመር ምክንያት የሚመጡ ህመሞችን እና ጭንቀቶችን የማስወገጃ መንገድ በመጠቀም መከላከል የሚቻልበትን መንገድ ጠቁሟል፡፡ በመዋቅራውያን ንድፈ ሃሳብ ደግሞ የአእምሮ ወኪሎች የሆኑ አካላት ኢድ፣ ኢጎ እና ልእለኢጎ የአእምሮ ክፍሎችን በመግለጽ ኢድ የአእምሮ ክፍል መሰረታዊ እና ትእዛዝ የሚሰጥ አካል ሲሆን፣ ኢጎ እና ልእለ ኢጎ የአእምሮ ውቅሮች ደግሞ የኢድን የእድገት ደረጃ የሚጠብቁና ለአላማዎች መሳካትና ለውስጣዊ ግጭቶች መቀነስ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ናቸው ይላል፡፡

ከሀሳቡ መረዳት እንደሚቻለው በዚህ የመዋቅራውያን ስነልቦናዊ ቲዮሪ አስተሳሰብ ግለሰቦች በሚኖሩበት ማህበረሰብ የዕለት ከዕለት ህይወት ስነልቦናዊ ሁከት እንዲያደርስ የሚያደርገው በመዋቅሮቹ ውስጥ ያሉት አስተሳሰቦች ተቆጣጣሪውን አካል ሲጎዱ ወይም ሊጎዱት እንደሆነ ነው፡፡ እንዲሁም በስነ-ባህሪያዊ የእድገት አስተሳሰብ የመጀመሪያውና አሁን ላለንበት ባህሪ መሰረት የሆነ ነው፡፡ ይህም 0-18 ወር መካከል ያለ ህጻን አፋዊ ደረጃ፣ ከ18-36 ወር ከፊንጢጣ ጋር የተያያዘ ደረጃ እና ከ3-6 አመት ያለ ህጻን ደግሞ ከብልት ጋር የሚኖር የመነሳሳት ስሜት ደረጃዎች መሆናቸውን በመግለጽ የቀድሞው ባህሪ የሚጸናና የሚቀጥል ነው ይላሉ፡፡ (past persistents in to the present).

ABE (2004) በFreud (1984) አስተሳሰብ ከፍተኛ የሆነ የመነቃቃት ስሜት እና ስጋቶች እንዲሁም በስነልቦና ጥናቶች የሚታዩ በሽታዎችና መከላከያዎች በአምስቱም የአእምሮ መነሻ እይታዎች ሊታዩ ይችላሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም፣ የሰዎች አእምሮ የመነቃቃት ስሜት በሚኖራቸው የመርካት ደረጃ የሚወሰን ሲሆን እርካታን ማግኘት እና የአለመርካት ችግርን በመከላከል የመነቃቃትን ስሜት ማስረጽ ይቻላል ብለው ያምናሉ፡፡ በመሆኑም የመርካት ችግርን ለመቋቋም በህይዎት ውስጥ የተፈጥሮን ማሻሻልና ተስፋ የሚያሳጣ ሞትን እሳቤ በመቃረን ህይዎትን በማስቀጠል ነው፡፡

እንዲሁም የአእምሮን የማንቃትና የማረጋጋት መመሪያ እንደሚገልጸው ህዝቦች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ሲገኙ ሀይላቸውን በመጠበቅ ምቹ ደረጃ መፍጠር አለባቸው ይላል፡፡ እንዲሁም ለገሃዱ አለም እውነታዎች መመሪያ እንደሚገልጸው ከፍተኛ የሆነ ጭንቀትን /ስጋትን) ሊያመጡ የሚችሉና በአለም ላይ የሚተገበሩ ጉዳዮች በማስወገድ መቋቋም ይቻላል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ስለሆነም አንዱ የገሃዱ አለም እውነት እና ስጋት፣ ለከፍተኛ ጭንቀት እንዲሁም ከፍተኛ ለሆነ አእምሮ ችግር ወይም አእምሮ ፀብ እንዲያጭር የሚያደርግ የወሲብ ፍላጎትን አፍኖ መያዝ እና በወሲብ አለመርካት ምክንያት የሚፈጥር የአእምሮ ህመም ነው፡፡ ይህ የገሃድ አለም ድርጊትና ችግር ፈጣሪ ተግባር ከላይ በተገለጹት መመሪያዎች በመጠቀም የመርካት ስሜትን መቆጣጠር ይቻላል፡፡ Freud (1920) እንደሚሉት ስጋት የሚመጣበት ምክንያት በውስጡ የስነ-ልቦና ግፊት መኖር በወሲብ የመርካት እጥረትና የአእምሮ አቅም ከቁጥጥር ውጪ የመሆን ሁኔታ እንዲሁም አእምሮ ሊያገኘው በማይችለው ከፍተኛ የወሲብ ስሜት /ምኞት/ በሚኖርበት ጊዜ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በሰው ልጅ አስተሳሰብ ከፍተኛ የወሲብ ምኞት ሲኖር አእምሮ የተመኘውን ነገር እንደማያገኘው ስለሚያቅ ስጋት ይፈጥራል፡፡ ያንን ችግር ሰብሮ ለማለፍ ከመናገር ይልቅ ወደ ውስጥ አምቆ ያስቀረዋል፡፡

በመሆኑም እነዚህ ተግባራት እየተወራረሱ የመጡ የተፈጥሮ ስጦታዎች ናቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ስጋት የሚፈጠረው ከመጠን ያለፈ የወሲብ ፍላጎት እና ከመጥን ያለፈ የወሲብ ስሜት ምክንያት ወይም ከፍተኛ የሆነ የወሲብ ፍላጎት በሚኖርበት ጊዜ ከአእምሮ ጋር ጥላቻ ሲፈጠር ነው፡፡ ስለሆነም ይህንን የአእምሮ ህመም ለመከላከል ወይም ለማከም የወሲብን ፍላጎት ተመጣጣኝ ማድረግ ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ በዚህ የስጋት ምንጭ በስነ-ልቦናዊ ቲዮሪ የጥናት ዘዴ መጠናት አለበት፡፡ ምክንያቱም ከፍተኛና የታመቀ የወሲብ ፍላጎት እሳቤ በስነ-ልቦና ውስጥ የሚኖር ከሆነ ወይም ካልተሟላ ተጽእኖው ከፍተኛ ነው፡፡ በጉርምስና ወቅት አእምሮ የሚፈልገውን ነገር በማሳካት አስተሳሰብን ለመገንባት በሚደረግ እንቅስቃሴ ጤነኛ ያልሆነ ፍቅር አላማ ከተያዘለት ፍቅር ውጪ ሲሆን በስነ-ልቦና ላይ በሚኖር የሀሳብ መለዋወጥ የሚፈጠር የአላማ ቢስነት ችግር ስጋትን ይፈጥራል፡፡ ከብልት መለካካት ጋር በሚኖር የወሲብ ፍላጎት የመርካት ደረጃ (ከ3-6 አመት በሚኖር ደረጃ) በአእምሮ ውስጥ በሚኖር አላማን ያገናዘበ እርካታ የማግኛ መንገድ ፍርሀትና ስጋትን ይቀንሳል፡፡ ምክንያቱም ፍላጎቱ ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ የተሟላ ከሆነ ልእለ ኢጎ ይባላል /እደገቱን ያገኛል፡፡

በዚህ የፍሮይድ ቲዮሪ የሰው ልጅን የታመቀ ፍላጎትና በህጻንነቱ የተፈጠረ የወሲብ ፍርሀትን በትምዕርት የሚገልጹ እንዲሁም በሰው ልጅ በከፊል ንቁው የአእምሮ ክፍል (sub conscious mind) ውስጥ ያሉ አስተሳሰቦችን የሚያጸባርቁ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም የሰው ልጅ የወሲብ ፍላጎት የእድገት ደረጃውን ተከትሎ እንደሚመጣ ይገላጻሉ፡፡ ስለሆነም Freud እንደሚገልጹት የስነ-ልቦና በሽታ ጥናት በስነ-ልቦና ላይ የሚደርስን ጤነኛ ያልሆነ ምኞት በማከም ወደ ነበረበት የእድገት ደረጃ ተማርኮ በነበረ ወሲብ ችግር ከመጎዳት እንዲጠበቅና

የበሰለ አእምሮ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በመሆኑም በዚህ አእምሮን የመገንባት ቲዮሪ ወይም ችግሮችን የመከላከል ቲዮሪ የስነ-ልቦና ጥናት ጠቀሜታዎች ውስጣዊ አስተሳሰቦችን ከውጭው አለም ጋር አስታርቆ የማስቀጠል ፋይዳ አለው፡፡ ይህ ከሆነ በግለሰቡ ስነ-ልቦና ላይ የሚፈጠሩ ጭንቀቶችና ስጋቶች ጤናማ ሆኖ ህይወትን መኖርና ችግርን መቋቋም እንዲችል ያደርጋል፡፡ ስነ-ልቦናዊ ገጽታ በአእምሮ በስሜት ላይ ያርፋል፡፡ በመሆኑም፣ ይህ ገጽታ መነጠል ሂደት ውስጥ ላይ ያለውን |አእምሯዊ እና ስሜታዊ አተያይ የሚመለከት ይሆናል፡፡

በመሆኑም የሰው ልጅ ስነ-ልቦና ማድረግ የሚፈልጋቸውን ተግባራት በሚኖሩት የተለያዩ አስተሳሰቦች ግፊቶች የሚወሰን ነው፡፡ በዚህም የተነሳ Turner (1967:609) ሲገልጹ፡- አእምሯዊ አካላት (congnitive components)፡- እውቀት፣ ግምት፣ እምነትና ትውስታ በአእምሯዊ ማዋቀሪያነት የሚካተቱ ናቸው፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች አማካኝነት በውስጣዊና በውጫዊ ግፊቶች ላይ የተገደበ፣ አልያም ያልተገደበ እውቀት ይፈጠራል፡፡ ይላሉ ከዚህ የተነሳ የግለሰቦችም ሆነ የማህበራዊ ቡድኖች የለውጥ እንቅስቃሴ ሂደት በጣም አስቸጋሪ የሆነና ቀስ በቀስ የሚመጣ ሆኖ ይታያል፡፡

በመሆኑም ግለሰቦች አእምሯዊና ስሜታዊ መዋቅሮችን በመገንባት የሚዋቀሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም ውጫዊ ግፊቶች ግለሰቡ እንዲቀበላቸው እና እንዲያከብራቸው የሚያስገድዱ ማህበራዊ ስምምነቶች በመሆናቸው እነዚህን መጠበቅ እንዳለበት ያስገነዝቡታል፡፡ በዚህ የተነሳ ማህበረሰባዊነት ማፈንገጥ ስነ-ልቦናዊ ስሜት እርካታ ስለሚያስገኛቸው ደንቦችን፣ ስርዓቶችንና የተለያዩ ተቋማትን እንዲጠብቁና እንዲያከብሩ አእምሯቸው ያምናል፡፡ በዚያ ስርዓቶች ከሚተገብሩት ነገር መታገድ ለስነ-ልቦና እረፍት መንሳቱ አይቀርም፡፡

በአጠቃለይ ይህ ንድፈ-ሃሳብ የሰዎችን የታመቀ ፍላጎት ለማሳካትም ሆነ ከህመማቸው ለመፈወስ መፍትሄ የሆኑትን ጉዳዮች የሚያጠና ነው፡፡ በመሆኑም Freud በስነ-ልቦናዊ ንድፈ ሀሳብ ህልሞች እና ሌሎች ከበራች እንዲሁም ‹‹ህራም›› የሆኑ ጉዳዮዎች የሰው ልጅ ኢ-ንቁው የአእምሮው ክፍል ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተሸሽገውና ታምቀው የቆዩ ድብቅ ፍላጎቶችን የሚገልጹ መሆናቸውን አሳይተዋል፡፡ ስሆነም በዚህ ጥናት ህልም ለሰው ልጅ ያለውን ፋይዳ ከስነ-ልቦና አንጻር ለማየት ንድፈ ሃሳቡ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ተጠቀምቤታለሁ፡፡

## 2.5.2 ስነ-ፍቺ ንድፈ ሀሳብ

ስነ-ፍቺ ንድፈ ሀሳብ የማህበረሰቡ የዕርስ በዕርስ መግባቢያ የሆኑትን ትዕምርቶች በመመርመር ላይ የሚያተኩር የጥናት ዘርፍ ሲሆን የወካይ እና የተወካይን ሚና የሚለይ እንዲሁም

ተወካዮች የያዙትን ፍቺ የሚያጠና ነው፡፡ ስነ-ፍቺ ንድፈ ሀሳብን በተመለከተ Browen and Felizitas (2000፡ 1-2) የሚከተለውን ሀሳብ ገልጸዋል፡፡

> ስነ-ፍቺ የሚለው ቃል የመጣው ሲሚኦን ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ይህ ማለት ደግሞ ምልክት ማለት ነው፡፡ ጆንሎክ የተባለ ፈላስፋ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ስነ-ፍቺን ‹‹የምልክቶች ህግ›› በማለት ገልጸታል፡፡ የምልክቶችን የተፈጥሮ መገኛ ጉዳይ ስነ-ሰብ በአእምሯችን የምናገኘው ነገሮችን ለመገንዘብ ወይም ከሌሎች ጋር እውቀትን ለመለዋወጥ ነው፡፡ ስነ-ፍቺ በእውነቱ በጣም ትልቅ አላማ ያለው ሲሆን የቲወሪው ፍቺ ሀሳብ ጥናት የሚያደርገው የትውልዱን ማንኛውም ጠቀሜታ የሚሰጠውን ነው፡፡ ይህ ማለት የተጻፉትን ቃላት ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ማህበራዊ ትግበራና በቅደም ተከተል ስራ ላይ በማንኛውም መልክ ትርጉም ያላቸው ስነ-ፍቺዎች ትምዕርት የሚሸፍን እና ሁሉንም ስርዓት የሚሸፍን መሆን አለበት፡፡ የስነ-ፍቺ ጥናት ሶስት ነገሮችን ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ የሚባሉትን ጉዳዮች የሚያካትት ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ እያንዳንዳቸው ብዙ ነገሮች በውስጣቸው ይይዛሉ፡፡

የተገለጸው ሃሳብ የሚያስገነዝበው የስነ-ፍቺ ንድፈ ሀሳብ የሚያጠናው ምልክቶች አንድን ጉዳይ (ነገር) እንዴት ሊወክሉ ይችላሉ የሚለውን ነው፡፡ ስነ-ፍቺ ንድፈ ሃሳብ ማንኛውም የአንድ የማህበረሰብ አባል ሊግባባቸው እና ትርጉም ሊሰጥባቸው የሚችሉ ወካይ ነገሮችን ጠቅለል አድርገው ሊይዙ የሚችሉ ትዕምርቶችን የሚመለከት ነው፡፡

የሚከተለውን ሃሳብ እንመልከት Lois (2006: 216) ‹‹ሴሚዮቲክስ ቋንቋዊ እና ቋንቋዊ ያልሆኑ ነገሮችን እና ባህሪያትን ምሳሌያዊ መንገድ የሚያከናውኑትን ተግባር ይመረምራል፡፡›› በማለት ተንትኗል፡፡ ይህ ሃሳብ የሚያስረዳው ስነ-ፍቺ ንድፈ ሃሰብ ቋንቋዊ መገለጫ ያላቸውን እና የሌላቸውን ጉዳዮች ወካይ በሆነ መንገድ የሚታዩበት ወይም የገለጹበት ዘዴ መሆኑን ነው፡፡

ስለሆነም የስነ-ፍቺ ንድፈ ሀሳብ አንድ የጥናት ዘርፍ ሲሆን በማህበረሰቡ የተለያዩ ጉዳዮችን በመወከል ለማንነት መግለጫነት የሚውሉትን የተለያዩ ምልክቶች የሚያጠና መሆኑን ያሳያል፡፡

ስነ-ፍቺ የማህበረሰቡን ታሪክ፣ ባህል እና ሁለነገር ስለተሸከሙት ትርጉም ስላላቸው እና የጋራ ተግባቦት ስለሚፈጥሩት ትዕምርቶች የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ስለሚጠኑት በህልም ውስጥ ስለሚገኙት ትዕምርቶች ትንታኔ ለመስጠት ተመራጭ በመሆኑ ተጠቅሜበታለሁ፡፡

### 2.5.3 ተግባራዊ ንድፈ-ሃሳብ (functionalism Theory)

ይህ ቲወሪ አንድ ፎክሎር ለማህበረሰቡ ያለውን አስተዋጾ የሚመለከት ሲሆን የፎክሎርን የተለያየ አገልግሎቶች በመለየት ፎክሎርነቱን ከጠቀሜታው የሚያረጋግጥ ነው። ይህን በተመለከተ ሰሎሞን ( 2007፡75) የሚከተለውን አስፍሯል።

> *የጠቀሜታዊነት የፎክሎር ንድፍ ሀሳብ በአንድ ማህበረሰብ ወይም ፎክ ቡድን ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሎሮች ለማህበረሰቡ ወይም ለፎክ ቡዱኑ የሚሰጡትን ጠቀሜታና በቡድን ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ትርጓሜ በማሳየት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው። የዚህ ንድፈ ሀሳብ አራማጆችም ተረቶች፣ ሚቶች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ እምነቶችና ሌሎችም ማንኛውም ሎሮች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ ወይም ሌላ ጥቅም መስጠትና የማህበረሰቡን ፍላጎት ማሟላት ይኖርባቸዋል የሚል አስተሳሰብ የሚያራምዱ ሲሆን፣ ‹‹ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ ምን አይነት ተርጓሜና ጠቀሜታ አለው፡፡›› የሚለው አብይ ጥያቃያቸው ነው።*

ሌላው ስለተግባራዊ ቲወሪ ፎክሎራዊ አገልግሎት ባስኮም የተባለ የተግባራዊ ንድፈ-ሀሳብ አቀንቃኝ ምሁር የሚከተለውን ገልጧል።

> Bascom (1965) ‹‹who identified what he called the foure functions of folklore, one function he identified is ‹‹ education, particulariy, but ont exclusively in non literate societies›› (1965፡ 293), second ‹‹ to escape from limits or imposition the culture places on us ››(1965,290), threed ‹‹ maintaining conformity to the accepted partterns of behavior ›› (1965, 297), for the ‹‹ folklore validates culture ›› ( 1965,292)››

የባስኮም ሃሳብ የሚያስረዳው ፎክሎር አራት አይነት ጠቀሜታዎች እንዳሉት እና እነዚህ ጠቀሜታዎቹም የማስተማሪያነት፣ በእኛ ላይ ከተጫነብን ተፅዕኖ ለማምለጫነት፣ ተቀባይነት ያለው ባህሪ ለመቅረፅ እና ባህል ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ አስተዋፅኦ እንዳለው ነው።

ሌላው ደግሞ ስለተግባራዊ ቲወሪ ፎክሎራዊ አገልግሎት ፈቃደ (1991፡7) Jonesንን በመጥቀስ (በማካተት) የሚከተለውን ገልጧል።

> *ፎክሎርን ከጥናት እና ምርምር ጎን ለጎን ለሌላ ማህበራዊ ፍይዳ ማዋል ይገባል የሚሉ ፎክሎረኞችም አሉ። ጥንታዊውንና የዛሬውን ፎክሎር በተለያየ መንገድ መሰብሰብ፣*

መሰነድ፣ መተንተን እና መቅረፅ ላይ ያተኮሩ ሙህራን ያሉትን ያህል ፎክሎር የዛሬውን የየዕለት ህይወት ፕሮብሌሞች በመፍታት ረገድ አስተዋጾ ማድረግ እንደሚችል የሚያሳዩም ፎክሎረኞች አሉ፡፡ ይህን ሃሳባቸውን ፎክሎርን ጥቅም ላይ ማዋል (putting folklore to use,1994) በሚል መጽሀፍ ባቀረባቸው 13 መጣጥፎች አስፍረዋል፡፡ ፎክሎር የማስተማር ዘዴን በማበልጸግ፣ ማኅበራዊ ፕሮብሌሞችን ለምሳሌ፡- የጎዳና ነዋሪዎችን ፕሮብሌም፣ በመፍታት ባህላዊ ቅርስን በመጠበቅ፣ የአኗኗርን ሁኔታ በማሻሻል (ለምሳሌ፡- በጤና) እና የራስን ማንነት (identity) በማዳበርና አንድን ቀበሌ (community) እና ባለእጅሙያውን በማነቃቃትና በማበረታታት ሊጠቅም እንደሚችል በጥናታቸው አስፍረዋል፡፡

የተገለጸው ሃሳብ እንደሚያስረዳው ፎክሎር በርካታ ተግባራት እንዳሉት እና እነዚህ ተግባራቶቹም በማህበረሰቡ መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመስማማቶችን በምን መንገድ መፍታት እንደሚችሉ መፍትሄዎችን በማዘጋጀት ችግሮች እንዲፈቱ፣ የሰዎችን ታሪክ በመመዝገብ እንዲጠበቁ፣ የሰዎችን አስተሳሰብ እና አመለካከት እንዲሻሻል እና እንዲያድግ በማድረግ ለስራ እና ለእድገት ተነሳሽ እንዲሆኑ መንፈሳቸውን በማነቃቃት ማንነታቸውን እንደያዙ እንዲኖሩ የማድረግ አስተዋፅኦ እንዳለው ነው፡፡

ከላይኛው ሃሳብ በተጨማሪ Sims and Stephens (2005; 174) ‹‹ ስለ ፎክሎር ትርጉም ስንነጋገር ብዙ ጊዜ ሰዎች ፎክሎር ለቡድን አባሎች ምን ጥቅም አለው፣ እንዴት ይጋባቡበታል እና ምን ይካፈላሉ? የሚለውን ይጠይቃሉ፡፡ አንዱ የፎክሎር መነሻ ትርጉም ለማህበረሰቡ የፎክሎር የጥቅም መንገድ መመርመር ነው፡፡›› ይህ ሃሳብ የፎክሎርን ተግባራት ከማህበረሰብ አንጻር ምን እንደሚመስል የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህ ህልምም አንዱ የፎክሎር ዘርፍ ስለሆነ ለእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ምን ፋይዳ አለው የሚለውን ጉዳይ የሚመለከት ስለሆነ ተጠቅሜበታለሁ፡፡

## 2.6 የመስክ ተሞክሮ ዘገባ

ወደ መስክ ለመስራት የሚያስችለኝን ቅድመ ዝግጅት ያካሄድኩት መጀመሪያ ትልም ጥናት ከማዘጋጀቴ በፊት ሲሆን ለጥናት በተመረጠው ማህበረሰብ በእናርጅ እናውጋ አካባቢያዊ ዳራ ለማግኘት ከወረዳው ኮሚኒኬሽን ቢሮ የተለያዩ በሶፍት ኮቢ (Soft copy) እና (Hard copy) ማለትም የተወሰኑ ጋዜጦችን፣ መፅሄቶችን ማየት እና መዳሰስ የጀመርኩት በሀምሌ ወር 2010 ዓ.ም ነበር፡፡ ወደ እናርጅ እናውጋ ወረዳ ማህበረሰብ መረጃ ለመሰብሰብ ከመሄዴ በፊት

ትምህርት ላይ በነበርኩበት ወቅት የማጠቃለያ ፈተና ተፈትኘ እስከሚሄድ ድረስ በመስከረም ወር 23/01/2011 አ.ም ስለ ወረዳው አየር ፀባይ ሁኔታ፣ ስለ መልከአምድሩ አቀማመጥ፣ ስለ ወረዳው ሰብል ምርት አመራረት በአጠቃላይ ወረዳውን የተመለከተ ከወረዳው ግብርና ፅፈት ቤት በመሄድ የተለያዩ መረጃዎችን እንዲሰጡኝ አድርጌ ጥናቴን ከአየር ጸባይ አንጻር ከወይና ደጋ ሁለት፣ ከደጋ አንድ እና ከቆላ ደግሞ አንድ ቀበሌዎችን በመምረጥ እዛ ቦታ የሚገኙ እና የሚያግዙኝ ሰዎችን አፈላልጌ ሳገኝ ቦታዎች ለጥናት እንደሚሆኑ ደብረወርቅ ከተማ ሆኘ አጥንቸ ከተመረጡት ቀበሌዎች ተወካይ የሚሆኑ ሰዎችን ተዋውቄ እና ስልካቸውን ተቀብየ (ተቀያይረን) በመስከረም 28/01/2011 አ.ም ወደ ባህርዳር ተመለስኩ፡፡

ጥቅምት 1/02/2011 አ.ም ለሁለተኛ አመት ትምህርት ተመዝግቤ ትምህርት እስኪጀመር ድረስ ወደ ወረዳው ኮሚኒኬሽን ቢሮ በመሄድ ሀላፊ ከሆኑት ከወይዘሮ ጥሩሴት መንግስት ጋር በመገናኘት ለምን ከቢሮሯቸው እንደሄድኩ አላማየን በማብራራት ነገርኳቸው፡፡ እሳቸውም ከዚህ በፊት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተጠና ጥናት እንደሌለ እና ሌሎች ሊተባበሩኝ የሚችሉ ሰዎችን አስተዋውቀውኝ ወደ መረጃ ክፍል መርተውኝ ተለያየን፡፡ ከኮሚኒኬሽን የመረጃ ክፍል ሰራተኛ ጋር ስለ ህልም ምንነት፣ አላሚዎች እና ህልምን መፍታት ስለሚችሉ ሰዎች ተወያተን እና መረጃ እንደማላጣ በተስፋ ሞልተውኝ እና በሚችሉት ነገር ሁሉ ከጎኔ ሆነው እንደሚያግዙኝ እና እንደማይለዩኝ እኔም መበርታት እንዳለብኝ አይዞታቸውን ሰጥተውኝ በድጋሜ ለሁለተኛ አመት ትምህርት ዘመን ለትምህርት ወደ ባህርዳር ተመለስኩ፡፡

ከዚያም በትምህርት ገበታ ላይ እያለው ለመረጃ ስብሰባ እስክወጣ ድረስ ስልክ ከተቀያየርኳቸው ግለሰቦች ጋር ማድረግ ያለባቸውን ነገር ሳይዘነጉት እንዲተገብሩት በተደጋጋሚ እየተደዋወልን ቆይቼ ጥር 20/05/2011 አ.ም የኮርስ ማሚያ ፈተና ተፈትኘ በይካቲት 16/06/2011 አ.ም ወደ መስክ ስራየ ሄድኩኝ፡፡ በመሆኑም በ17/06/2011 አ.ም በቋሚጨርቅ ቀበሌ ደብረ በድህኔአለም ቤተ-ክርስቲያን እንደመጣው እንዲነግሩልኝ ከቄስ ግዛ ደነቀው ጋር ተገናኝተን ለህልም ፈቺነት የተመረጡትን ሰዎች ስም ዝርዝር ሰጥተውኝ መቼ መገናኘት እንዳለብን እና በምን ዙሪያ ልጠይቃቸው እንዳሰብኩኝ ቀንጨብ ቀንጨብ አድርገን አውርተን ተቀጣጥረን ተለያየን፡፡ በየካቲት 21/06/2011 አ.ም ወፊት ቀበሌ ቤተ-ክርስቲያናቸው ማርያም ስለሆነች ወራዊ በአሉን ለማክበር ሰዎች ስለሚሰበሰቡ መረጃ አቀባዮችን በዛው አግኝቸ ተዋውቄያቸው እንድመጣ ጥሩ አጋጣሚ ስለሆነ ከእህቴ ጋር የሁለት ስአት መንገድ ሂደን እንዳሰብኩት ሆኖልኝ የተወሰነ መረጃ ሰብስቤ ቀጠሮ ይዤ ተመለስኩ፡፡

የካቲት 24/06/2011 ኢ.ም ደግሞ ከጥዋቱ 12፡25 ስአት ላይ ከቋሚጨርቅ ቀበሌ ወደ ደብረወርቅ ከተማ ከ40 ደቂቃ በኋላ ደርሸ ደብረወርቅ የምትኖረውን ጓደኛየን ይዤ ወደ አራራ ቀበሌ ከደብረወርቅ ከተማ በስተምስራቅ በኩል ተገንጥላ ወደምትገኘው መጥያ አመራን ከ20 ደቂቃ በኋላ ደረስን፡፡ ከመጥያ ትንሽ ከተማ እንደደረስን አባተ የሚባል የድብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ተማሪ አግኝተን ወደ ሰፈሩ አራራ ቀበሌ ይዞን እንዲሄድ አድርገን ቁርሳችንን መጥያ በልተን በእግራችን ሁለት ሰአት ተጉዘን አራራ ቀበሌ ገባን ሊቀመንበር ለሆኑት አቶ አበባው ውድነህም አገኘናቸው፡፡

ይህን አካባቢ ለመጀመያ ጊዜ ስሄድበት የማውቀው የዛን ጊዜ ሲሆን ከእርቀቱ ጋር፣ ከፅሀዩ ግለት እና ከቦታ ውጣ ውረድ የተነሳ ጉዞው አድካሚ ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ደርሸ መረጃ መሰብሰቤን (ማግኘቴን) ስለማስብ ቆራጥ የሆነ ጉዞ አድርገን ገባን፡፡ ከዚያ ሶስት ሆነን ሊቀመንበሩን አግኝተን መረጃ ሰጭዎችን አሰባስበዋቸው ከግራር ስር አገኘናቸው፡፡ 4፡20 ስአት ላይ ቃለ-መጠይቅ ማቅረብ ጀምረን እስከ ሰባት ስሀት ቆይተን ለምሳ ተለያይተን ዘጠኝ ስአት ጀምረን እስከ 11፡00 ስአት ቆይተን መጋቢት 5 ቀን የቀበሌው አመታዊ በአል ስለሆነ በዋዜማው ሂጄ ማደር እንዳለብኝ እና እነርሱም ተዘጋጅተው እንደሚቆዩኝ ቃል ገብተውልኝ ደብረወርቅ ሂደን አደርን፡፡

በሌላ ጊዜ መጋቢት 7/07/2011 ኢ.ም አምባ አገር ከሚባለው ቀበሌ ከቋሚጨርቅ ፈለገ ብርሀን ከምትባል ከተማ ድረስ የ10ብር ትራን ስፖርት በ25 ደቂቃ ከደረስኩ በኋላ ወደ ምእራብ ከወላጅ አባቴ ከአቶ የሽዋስ ጥሩነህ ጋር ተራራማ እና ድንጋያማ ቦታውን፣ ጠመዝማዛ መንገዱን ቀዝቃዛ ንፋስ ከተቀላቀለበት የአየር ፀባይ እየተጎነጨን በእግራችን ሁለት ስአት ተኩል (2፡30) አካባቢ ደረስን፡፡ በበነጋታው 2፡30 ላይ ፋሲለደስ ቤተ-ክርሲቲያን ሂደን መረጃ አቀባዮችን አገኘዋቸው፡፡

በዚህ ቀበሌ መመለስ አዳጋች ስለሆነ ከ7-12 ተከታታይ ቀኖች ቃለ-መጠይቁን እና ቡድን ተኮር ውይይቱን ጨርሸ ተመለስኩ፡፡ ሌሎች ቀበሌዎችንም እንደዚሁ በዚህ ሁኔታ መረጃዎችን እስከ መጋቢት 23/07/2011 ኢ.ም ሰብስቤ መጋቢት 24/07/2011 ኢ.ም ወደ ባህርዳር ከተማ ተመለስኩ፡፡ በመቀጠልም መረጃየን አደራጅቼ በመልክ በመልካቸው በማስቀመጥ የድምፅ መረጃየን ወደ ፁሁፍ ትራንክራይብ አድርጌ ከጨረስኩ በኋላ እዚያው ሆኜ መረጃየን ተንትኛለሁ፡፡

## 2.7 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

1. ከጊዜው ሁኔታ ጋር ተያይዞ መረጃ አቀባዮች በእኔ ላይ አመኔታ አለመጣል እና መረጃ የመደበቅ ችግር፡፡

2. የአጋዥ መረጃ ሰብሳቢ በቀጠሮ ቀን እና ስአት ያለመገኘት ችግር፡፡

### የተወሰዱ መፍትሄዎች

1. መረጃ ሰጭዎች መረጃውን እንዲያወጡት ቦታውን የሚያውቁ እና የአካባቢው ተወላጆች ይገኙ በመሄድ፣ የቀበሌዎችን ሊቀመንበር አግኝቸ የመጣሁበትን አላማ በደንብ አስረድቸ የተመረጡት ግለሰቦች እንዲረዱኝ በማድረግ፣ በማበረታታት እና ከባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የተጻፈውን የትብብር ወረቀት በማሳየት ያላቸውን መረጃ እንዲሰጡኝ አድርጊያለሁ፡፡

2. አጋዥ መረጃ ሰብሳቢ ከስራ ስአት ውጭ ማለትም ቅዳሜ እና እሁድ እንዲያግዙኝ በማድረግ፤ አንዳንዴም እኔ ብቻ ልሰበስበው የምችለውን መረጃ ብቻ በመሰብሰብ ሌላ ጊዜ አጋዦች አብረውኝ እንዲሰበስቡ በማድረግ፣ ተመርቀው ስራ በመፈለግ ላይ ያሉትን ግለሰቦች በመፈለግ አብረው አንዲሄዱ በማድረግ እና መረጃ የሰበሰብኩበት ወቅት የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ከግቢ ለእረፍት የመጡበት ጊዜ ስለነበር መረጃ የምሰበስብበት አካባቢ ያሉትን ልጆች ለመረጃ አቀባይነት የተመረጡትን ሰዎች እንዲዘጋጁ በመቀስቀስ እንዲያግዙኝ በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ሁለት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮችን የምንመለከትበት ክፍል ነው፡፡ የመጀመርያው የጽንሰ ሀሳብ ቅኝት ሲሆን ስለ ህልም አጠቃላይ ሁኔታ ገለጻ የሚሰጠን ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ነው፡፡ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የምንለው ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች የሚቃኙበት (የሚዳሰሱበት) ክፍል ነው፡፡

## 3. የፅንሰ-ሀሳብ ቅኝት

### 3.1 ሀገረሰባዊ ልማድ

ፎክሎር በውስጡ በርካታ እና ሰፊ ጉዳዮችን ያካተተ ነው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ የሰውን ልጅ የሚመለከቱ ሰዋዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ፎክሎር ከሚያካትታቸው ጉዳዮች መካከልም ሀገረሰባዊ ልማድ አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ሀገረሰባዊ ልማድ አንዱ እና ሰፊው የፎክሎር ዘውግ ነው፡፡ ሶሎሞን (2007፡151) Doresnን ጠቅሶ ‹‹ሀገረሰባዊ ልማድ ማህበረሰቡ በተደጋጋሚ የሚከውነው ድርጊት እና ቅደም ተከተላዊ ስርአትን መሰረት በማድረግ የሚቀርቡ ጥበቦች ጥቅል መጠርያ ነው፡፡›› ይላል የተገለጸው ሀሳብ የሚያስገነዝበው ሀገረሰባዊ ልማድ በማህበረሰቡ በጥሞና፣ በተደጋጋሚ የተተገበረ እና አጀማመር እና የአጨራረስ፣ የአከዋወን ስርዓት ያለው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ልማድ ማለት ዐመል፣ የተለመደ ግብር፣ ህግ፣ ስርዓት፣ ትምህርት ማለት ነው፡፡

ልማድ የአንድ ማህበረሰብ አባላት እንደ ትክክለኛ መንገድ በማሰብ በተደጋጋሚና በተለምዶ የሚፈጽሙት ተግባር፣ የሚከተሉት ባህሪ ነው፡፡ ይህ የጋራ ማህበራዊ ተግባር እና ባህርይ ደግሞ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ተለምዶ እንዲከተሉት እና እንዲተገብሩት ማህበረሰባቸው የሚጠብቅላቸው ስርዓት ይሆናል፡፡ እነዚህ በተለምዶ ይባል በባህል የምናከናውናቸውን ተግባራት እና የምንከተላቸውን ባህርያት (አጠቃላይ አወንታዊ እና አሉታዊ ተግባሮቻችንን) የሚመሩ ያልተጻፉ ህግ እና ደንቦች በማህበረሰባችን ልማድ ይደነገጋሉ፤ ገዥም ይሆናሉ፡፡ ጥያቄም የማናቀርብባቸው፣ መልስም የማናሻባቸው ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከሰው ልጅ የህይዎት እጣ ፈንታ ጋር የተያያዙ ተምሳሌታዊ ፍችዎችና ትርጓሜዎች በዚህ ፈርጅ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

ሌላው ደግሞ ፊቃደ (1991፡13) ‹‹ሰዎች አጥብቀው የያዟቸው እምነቶች እና ልማዶች መነሻ ምንጫቸው ምንድን ነው? ትርጓሜያቸው እና ፍቻቸውስ ምንድን ነው? ሰዎች በአንድ ነገር ለምን ያምናሉ? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በተለይ ፈላስፎች፣ ደራስያን፣ ስነ-ሰቦች (Anthropologists) እና ፎክሎረኞች ጊዜ ወስደው የተመራመሩባቸው እና ዛሬም የሚመራመሩባቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡››

የላይኛው ሀሳብ የሚያስረዳው ሀገረሰባዊ ልማድ ለአንድ ማህበራዊ ልማድ ያልተጻፉ መተዳደርያ ህጎችን በማበጀት ለቡድኑ አባላት የዕርስ በዕርስ ተግባቦት በመፍጠር የሚጨበጡት እና የማይጨበቱትን የማህበረሰብ ተግባራትን እና እምነቶችን የሚያካትት መሆኑን ነው፡፡

ሌላኛው ሙሁር Thomas (1997:168) ደግሞ ስለሀገረሰባዊ ልማድ የሚከተለውን ገልጸዋል፡፡

> ልማድ በተጠበቀ መንገድ የሚደረግ ባህላዊ ነገር ነው፡፡ ልማድ የተለመዱ እና ያልተለመዱ መንገዶች ጭምር ነው፡፡ ያልተለመዱ ህጎችን የሚወስዱ እጆች ‹‹mores››ን ይፈጥራሉ፡፡ እያንዳንዱ ልምዶች እና ስልቶች የህግ ስርዓት አካል ይሆናሉ፡፡ ልማድ የባህሪ አጠቃቀምን ያካትታል፡፡ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እንደልማዳዊ ድርጊቶች አድርገው ከሚመለከቷቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ እንደልማዳዊ እምነት ወይም ተረቶች ያቀዱ ናቸው፡፡ ሰዎች ልምዳቸውን ይማራሉ በትናንሽ ጊዜያት የቡድኑ ኀበዝ አባላት  የሚጠቀሙበት ባልተለመዱ ወይም በተግባር በንቃት ሁኔታ ምን አይነት ባህሪ እንደሚገልጽ ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ የቤተሰብ ይዞታዎች አንዳንድ ባህሪያት ከተወሰኑ አውዶች መቼ እና በምን መንገድ እንደሚገልጹ በመግለጽ በተናጥል ባህላዊ ልምዶች ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

ከላይ የተገለጸው ሀሳብ የሚያስረዳው ሀገረሰባዊ ልማድ ለአንድ ማህበራዊ ልማድ የተስፋ መንደር አድርገን የምንሰራቸውን በአብዛኛው ያልተጻፉ መተዳደርያ ህጎችን እና የተወሰኑ የተጻፉ ህጎችን በማበጀት ለቡድኑ አባላት ዕርስ በዕርስ ተግባቦት በመፍጠር የሚጨበጡት እና የማይጨበጡትን የማህበረሰብ ተግባራትን እና እምነቶችን የምንገልጽበት መንገድ መሆኑን ነው፡፡

ሀገረሰባዊ ልማድ ከሌሎች የፎክሎር ዘውጎች ሰፊ እና ጥልቅ ዘውግ በመሆኑ በውስጡ የያዛቸውን ዘውጎች በጥራት ለመከፋፈል (ለመመደብ) አዳጋች ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ Sims and Stephens (2005፡16) የሚከተለውን ይገልጻሉ፡፡ ‹‹ customary lore of the three broad generes is perhaps the most difficult to characterize. A custom is

repeated habitual action, a usual way of doing something.›› በማለት ያስቀምጡታል፡፡ የተገለጸው ሃሳብ የሚያመለክተው ሀገረሰባዊ ልማድ ከፎክሎር ሰፋፊ ዘውጎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ልማድ የምንለው በተደጋጋሚ የማድረግ ተግባር እና ሁልጊዜ አንድን ነገር በተደጋጋሚ የመተግበር መንገድ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሰፊ ዘውግ በውስጡ በርካታ ንዑሳን ዘውጎችን ያካተተ ነው፡፡

### 3.1.1 የሀገረሰባዊ ልማድ ክፍሎች

በDorsonን (1972፡3) አከፋፈል ሀገረሰባዊ ልማድ በሚከተላቸው እምነቶች እና በሚፈጽሟቸው ዋና ዋና ክፍሎች በአራት እንደሚከፈል ያመለክተናል፡፡ እነዚህም ሀገረሰባዊ ሀይማኖታዊ ድርጊቶች፣ ሀገረሰባዊ መድሀኒት፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች እና ፌስቲቫሎችና ሪችዋልስ ናቸው፡፡ በሶሎሞን (2007፡153) ሀገረሰባዊ ልማድን በስድስት ተከፍለዋል፡፡ እነዚህም ህዝባዊ ሁነት፣ ሀገረሰባዊ ጨዋታ፣ ሀይማኖት፣ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ሀገረሰባዊ መድሀኒት እና የጊዜ ሰሌዳዊ ልማድ በሚል ነው፡፡ ሌሎችም ሙህራን እንዲሁ በተለያዩ አይነቶች መድበዋቸዋል፡፡ ፈቃደ እንደዚሁ ሀገረሰባዊ ልማድ በ4 እንደሚከፈሉ Dorsonንን ጠቅሶ አስቀምጧል፤ ፈቃደ (1991፡13) ላይ እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም ሀገረሰባዊ እምነት የሃገረሰባዊ ልማድ አንዱ ዘርፍ ሲሆን ለመንደርደሪያ ያህል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 3.1.1.1 ሀገረሰባዊ እምነት

ሀገረሰባዊ እምነት ማህበረሰቦች አለማቸውን ለመረዳት፣ አለምን ለመገንዘብ ትርጉም እና ቅርፅ ለመስጠት ብሎም የየእለት እንቅስቃሴያቸውን ለማስተሳሰር የሚተገብሯቸውን፣ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ባህል እና ሁሉም ቦታ ሊገኙ የሚችሉትን ጉዳዮች የሚመለከት ነው፡፡ በርካታ ባህላዊ እና ማህበራዊ ተግባሮቻችን እና እንቅስቃሴዎቻችን ብዙን ጊዜ ሀገረሰባዊ እምነትን በውስጣቸው የያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- አመጋገብ፣ የምግብ እና የቤት አሰራር፣ የበአላት አከባበር ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት በውስጣቸው የማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ እምነት ያረፈበት ነው፡፡ ሌሎችንም በርካታ ጉዳዮች እንደሰጡት ፍቺዎች፣ በግራ ጎን መነሳት…ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ሀገረሰባዊ እምነት ብዙ የሚመለከታቸው በሰው ልጅ የሚታመኑ እና የታመነባቸውን ጉዳዮች በተለይም ከመንፈስ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተግባሮች የሚወክል ነው፡፡ ሃገረሰባዊ እምነትን በተመለከተ የሚከተለውን ሃሳብ እንመልከት፡፡ Dorson (1972:225)፡- ‹‹ እምነት መንፈስን በሰው ልጅ እና በእንስሳት መንፈስ ወይም ይዞ የሚያቀይ መንፈስን የሚመለከት ሲሆን በእነዚህ ፍልስፍናዎች ላይ አርሶ አደሮች ልምድ ያላቸው ናቸው፡፡›› ሀገረሰባዊ እምነት

የማህበረሰቡን ውስጣዊ አመለካከት እና አስተሳሰብ ያረፈባቸውን በርካታ እና ሰፊ ጉዳዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ስለሆነም የማህበረሰቡን እምነት እና ትግበራ የሚጠይቅ ነው፡፡

ይህን በተመለከተ Thomas (1997:89) የሚከተለውን አስፍሯል፡፡ ‹‹ እምነት ሰፊ የፎክሎር ዘውግ ሲሆን በውስጡ የሚይዘውም ሰፋፊ ስሜቶች እና ባህሪዎች ጠቅለል ሲሉ የሚባሉትን፣ ታዋቂ እምቶችን፣ ምትሃት፣ ልዕለተፈጥሮ፣ አሮጌ የሚሰት ተረኮች፣ ሀገረሰባዊ መድሃኒት፣ ሀገር በቀል ሃይማኖት፣ የአየር ሁኔታ ምልክቶች፣ የአተካከል ምልክቶች፣ ድግምት እና ታቦዎችን ያጠቃልላል፡፡››

ከላይ የተጠቀሰው ሀሳብ የሚያስገነዝበው ሀገረሰባዊ እምነት በውስጡ የተለያዩ የእምነት አይነቶችን የሚይዝ ሰፊ የፎክሎር ዘውግ መሆኑን ሲሆን ከእነዚህም መካከል እንደ አምልኮ፣ ህዝባዊ እምነት፣ ማጅክ፣ ልዕለ ተፈጥሮ፣ ጥንቆላ፣ ዛር፣ ሀገረሰባዊ ሀይማኖት፣ የህልም ፍቺ…የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው፡፡ ከእነዚህም መካከልም አንዱ የህልም ፍቺ ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ርዕስ በመሆን ተጠንቷል፡፡ ስለህልም ምንነት በሚከተለው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከተለያዩ ቦታዎች የተገኙ መረጃዎችን በመጠቀም እንደአስፈላጊነቱ ቀርቧል፡፡

## 3.1.1.1.1 የህልም ምንነት

ህልም ሰዎች በሚተኙበት ስአት (ወቅት) የሚተገብሩት የሀገረሰባዊ እምነት አንዱ ክፍል ነው፡፡ ህልም በምንተኛበት ሰአት አእምሯችን የሚፈጥራቸው ምስሎች እና ሃሳቦች ውህድ ነው፡፡ ህልም የሚያዝናኑ፣ የሚረብሹ፣ ቀልዶች፣ የፍቅር ግንኙነቶች፣ የሚያስፈራሩ እና አንዳንድ ጊዜም ያልተለመዱ ክስተቶችን ይይዛል፡፡ ህልምን ለማለም መተኛት አስፈላጊ ነው፡፡ ህልም የተኛ ሰው የሚተገብረው መሆኑን ፍሮይድ በሚከተለው ሃሳቡ ይገልጸዋል፡፡ Freud (1856-1939፡55) ‹‹ህልም የተኛው /ያንቀላፋው/ ሰው አእምሯዊ ተግባር ሲሆን እንደሰውየው እንቅልፍ የሚወሰን ነው፡፡›› ከፍሮይድ በተጨማሪ የተለያዩ መዝገበ ቃሎች ህልም በእንቅልፍ ወቅት የሚተገበር ተግባር መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ናቸው፡፡

ኤፍሬም (1992፡11) ‹‹ህልም በእንቅልፈ ልብ የሚታይ ረቂቅ ራዕይ ነው፡፡›› በማለት ገልጾታል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማእከል (1993፡7) ደግሞ ‹‹ህልም በእንቅልፍ ልብ ወይም በእንቅልፍ ላይ እንዳሉ የሚታይ ሃሳብ፣ ድርጊት ወይም ራዕይ፡፡›› የሚል ነው፡፡ ኪዳነ ወልድ (1948:445) ‹‹ሕልም፤ (ማት፡፡ ብሕለም ፡ አሕላም፤ ማት)፤

በቁሙ፤ በእንቅልፍ: ውስጥ: የሚታይ :ነገር፤ እንደ: ትንቢት: ያለ። ህልም ፣ ፪ወገን፡ ነው÷ የነፍስ፡ የስጋ፤ የነፍስ፡ ሕልም፡ ፍሬ፡ ያለው፡ ነው፤ ትንቢት፡ ራዕይ፡ ይባላል፡ (ዘፍ ፴፯:፯::፵፩:፩። ዱን፪:፩)። የስጋ፡ ሕልም፡ ግን፡ እንደ፡ ምትሀት፡ ሁኖ፡ ቅዠት፡ ይባላል፤ ከንቱ፡ ማለት፡ ነው፤ ለሁሉም ፡ ክፉና ፡ በጎ፡ አለው፤ ሳሕስሐን፡ እይ። ወሕልምኒ ፡ ከንቱ፡ ያደነግፆ፡ ለአብድ። እስመ፡ ለብዙኃን፡ አስሐቶሙ፡ ሕልም። ሕልም፡ ዘዝሙት። አሕላም፡እኩያት። አሕላማት፡ ሕሡማት፡ (ሢ፴፩:፯። ፈ:መ:፲፬:፰። አፈ:ድ፳፬። ፊልክ:፪፰)።

ደስታ (1962፡52) ‹‹ህልም ህዋሳትን የሚቆልፍ፣ ጆሮን የሚደፍን፣ አፍንጫን የሚገጥም፣ እግር እንዳይሄድ፣ እጅ እንዳይጨብጥ የሚያደርግ በሌሊታዊ እረፍት ወቅት በአይነ ልብ ወይም በአይነ ህሌና የሚታይ፣ እውነተኛ እና ሀሰተኛ ነገር። እውነተኛው ሀላፊያትን እና መጽኢያትን የሚናገር ሲሆን ረዕይ ይባላል። ሀሰተኛው ምትሀት ወይም ቅዥት ይባላል። በማለት ገልጸውታል። ነገር ግን ይህን ጥናት ትኩረት ያደርገው እውነተኛው የህልም አይነት ላይ ነው። ከሳቴ ብርሀን ተሰማ (1941፡81) ‹‹1.ህልም በእንቅልፍ የሚታይ፣ ረቂቅ፣ ሪዕይ ነገር በእጅ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ፣ (ሐለመ፣ዐለመ፣ (ግዕ) ሕልም፣ (ዕብ) ሐለመ፣ (ዐረ)።›› ዘርገው (2001፡12) ‹‹1.ህልም በእንቅልፍ የሚታይ ሃሳብ፣ ድርጊት ወይም ረቂቅ ራዕይ፣ ቅዠት፣ በእጅ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ።›› ይላል።

የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1972፡25) ‹‹ ህልም በእንቅልፍ ጊዜ የሚታይ ነገር። ህልም አንዳንድ ጊዜ በቀን ከታየ ከታሰበ ነገር፣ በአድርጎትም የተነሳ ይታለም ይሆናል። ብዙ ጊዜ ልዩ ትርጉም አይኖረውም፤ መክ.5፡3። እግዚያብሄር ለብዙ ሰዎች በህልም በመታየት ፈቃዱን ገልጾላቸዋል፤ ዘፍ.20፡3፣28፡12፣37፡5-11። መላእክት የጌታን ፈቃድ ለሰዎች በህልም ይናገራሉ፤ ማቴ.1፡20፣ 2፡1319። ህልምን የመተርጎም ስጦታ ለዮሴፍ እና ለዳንኤል ተሰጠ፣ ዘፍ.40፡5-23፣ 41፡14-36፣ ዳን.2፡25-45፣ 4፡4-27። ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ህልምን ሊያልሙ ይችላሉ፤ ሐ.ሥ.2፡17። ህልም አንዳንድ ጊዜ ሰውን ሊያስት ይችላል፤ ዳን.13፡1-4። ‹‹ራዕይ››፤ ‹‹ትንቢት›› ይመ በሚል በጹሁፍ ሰፍሮ እናገኘዋለን። የህልም መጽሀፍ ቅዱሳዊ መዝገበ ፍቺ ብዙ እና ሰፊ መልክቶችን የያዘ ሲሆን የህልምን አጠቃላይ ገጽታ እና ትርጉም ከሀይማኖት አንጻር ለመመልከት የሚሞክር ነው። ከላይ የተጠቀሱት ምዕራፍ እና ቁጥሮች በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ ቦታ ህልም ለተለያየ አላማ አገልግሎት ላይ የዋለበትን ሁኔታ የሚገልጽ ነው። በተለይም ብሉይ እና ሀዲስ በሚባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ አይነቶች ዩሴፍ እና እና ዳንኤል ለሚባሉ ግለሰቦች የህልም መፍታት ጸጋ እንደተሰጣቸው እና የተለያዩ ህልሞችን እንደፈቱ፤ የፈቷቸው ህልሞችም እንደደረሱ በሰፊው ተተንትኖ ይገኛል።

ከላይኛው ሃሳብ በተጨማሪ ቀና (1945፡9) ‹‹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብሉይ ኪዳን አስራ ስድስት፤ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ አራት፤ ወይም አምስት ያህል ምዕራፎች ስለ ህልም ያትታሉ፡፡›› በማለት ገልጸዋል፡፡

የተገለጹት ሃሳቦች እንደሚያስረዱት ህልም ተኝተን በእንቅልፍ ሰአት የምንተገብረው ሀገረሰባዊ እምነት መሆኑን ሲሆን እንደየ ግለሰቦች የእንቅልፍ ሰአት እና እንደማንነታቸው እንደሚለያይ ያመለክታሉ፡፡ ህልም የአላሚውን ማንነት የመግለጽ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በህልም የሚገለጹት ሃሳቦች፣ ምስሎች፣ ታሪኮች፣ ፍላጎቶች፣ ምኞቶች እና ስራዎች ሲሆኑ የአላሚው ሁለገብ ተግባራት ናቸው፡፡

ህልም የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጀምሮ አብሮ የኖረ አሁንም ያለ እና ወደፊትም የሚኖር ትውፊታዊ ሎር ነው፡፡ ይህ የህዝብ ሀብት የፎክ ቡድን አባላት እንደየ አካባቢው እና እንደ ማህበረሰቡ አስተሳሰብ፣ አመለካከት እና ፍልስፍና የተለያየ ፍቺ ያለው ቢሆንም ህልም እንደ አንድ ሀገረሰባዊ እምነት የሚያምነው ሰው ብዙ ነው፡፡ የሰው ልጅ በጋራ መኖር የሚጀምረው ከቤተሰብ ስለሆነ ህፃናት የፎክ ቡድን አባላት ናቸው፡፡ ህፃናት የቤተሰባቸውን የአኗኗር ዘይቤ እና አስተሳሰብ እየተማሩ የሚያድጉት በመጀመሪያ የቤት ውስጥ እና አካባቢያቸው ላይ በሚኖሯቸው መስተጋብር ነው፡፡ ህፃናት በአንድ የፎክ ቡድን ውስጥ አባል ሆነው ሲኖሩ እና ሲያድጉ ባላቸው ጊዜ (ወቅት) ከሚያገኙት ነገር ተመስርተው በዚያ ነገር ላይ ባሉበት የህይዎት ደረጃ በአላቸው ወይም ወደፊት ሊኖራቸው በሚፈልጉት ነገር ላይ ጊዜ ወስደው ያስባሉ፡፡

ሌላው ደግሞ ባሉበት የህይዎት ደረጃ መቦረቅ፣ መደሰት፣ ማግኘት፣ መስራት፣ ማዘን በተለይም ከጓደኞቻቸው ጋር አብረው ሆነው የሚያሳልፉት የጨዋታ ጊዜ ከታላላቆቻቸው እና ከታናናሽ እህት ወንድሞቻቸው ጋር ያላቸው የጠበቀ ትስስር፣ እናት እና አባታቸው በእነርሱ ላይ ያላቸውን ጠቅለል ያለ ሀላፊነት ሚና ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣ ተግባር ብዙ ነገሮችን በማየት እውቀት ይቀስማሉ፡፡ ህጻናት ከምንም በላይ ነገ ነግቶ (ጠብቶ) ስለሚጫወቱት ጨዋታ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ተገናኝተው አብረው የሚሆኑበት ሰአት ያጓጓቸዋል፤ ያሳስባቸዋል፡፡ ህፃናት ዛሬ ላይ ሆነው ነገ ለሚኖሩት ወይም ለሚያሳልፉት ህይዎት ያስባሉ፤ ይጨነቃሉ፡፡ ህፃናት የራሳቸውን ውሳኔ በእራሳቸው የማይወስኑ ስለሆኑ እና ከማህበረሰቡ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ ስለማይወጡ የሚገኙበትን የማህበረሰብ ማንነት በመቅዳት ያድጋሉ፤ ያከብራሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚኖሩበትን አካባቢ እና ማህበረሰብ ስለሚመስሉ ስለሚጋሩ የሆነ ሎር ተከታይ፣ አክባሪ እና ባለቤት ናቸው፡፡

በመሆኑም ህፃናት የሆነን ሎር ተከታይ ከሆኑ ደግሞ ስለዚያ ሎር ከታላላቆቻቸው፣ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጎረቢቶቻቸው፣ ከአባቶች፣ ከትልልቅ ሰዎች እና ከእናቶች ወ.ዘ.ተ ከዚያም ከመሳሰሉት የማህበረሰብ አባሎች እያዩ እና እየሰሙ ይኖራሉ፣ ያድጋሉ እና ይተገብራሉ፡፡ ከእነዚህ ሎሮች መካከል አንዱ ህልም ሲሆን ህልም ደግሞ አእምሯዊ ተግባር ነው፡፡ አእምሮ ደግሞ የሰዎችን ውስጣዊ ፍላጎት፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ ምኞት፣ ደስታ እና ሃዘን የሚስተናገድበት መድረክ ነው፡፡ አእምሮ ከልጅነት እስከ እርጅና ያለውን ተግባሮቻችንን እንደ ደረጃችን እየሰራን የምናልፍበት ነው፡፡ አእምሮ በውስጡ የተለያየ ተግባር ያላቸው በርካታ ክፍሎች አሉት፡፡

ይህን በተመለከተ ፀሐይ (2008፡14-16) ፍሮይድን ጠቅሶ አእምሮ በሶስት መዋቅራዊ ሞዴል እንደሚዋቀር ማለትም ኢድ (Id)፣ ኢጎ (Ego) እና ልዕለ-ኢጎ (super Ego) እንደሆኑ እና እያንዳንዳቸው የራሳቸው ተግባር ያላቸው መሆኑን አስረድቷል፡፡ ይኸውም፡-

> ኢድ፡- ልባችንን በደስታ ሊሞሉ የሚችሉ ተፈጥሯዊ የሆኑ ሲቃዎች እና ግፊቶች አሉ፣ እነዚህን ፍላጎቶች የሚነዳው ኢድ የተባለው ክፍል ነው፡፡ ኢድ የሚመራው በ ‹ትፍስህት መርሆ› ነው የሰውየው ፍላጎቶች እና ምኞቶች በአስቸኳይ መሟላት እና ሰውየው በተድላ እንዲፈነድቅ ለማድረግ ነው፡፡ ኢድ በሰዎች የሚገኙ የባዮሎጂካዊ ደመ-ነፍሶች ግፊቶችን ይወክላል ይላል የፍሮይድ ንድፈ ሀሳብ፡፡
>
> ልዕለ-ኢጎ፡- በማህበር የሚኖር የሰው ልጅ እንደ እንስሳ ሁሉ ልቡ የአሻውን ልፈፅም ቢል፣ የዕርስ በዕርስ መጨራረስ ይከተላል፡፡ ግለሰቡ ፍላጎቶቹን ለማርካት ስርዓቶች ተበጅተዋል፤ እነዚህን ስርዓቶች ህጻኑ በወላጆቹ፣ በማህበረሰቡ፣ በመንግስት ህግ እየተኮተኮተ ያድጋል፡፡ ጥሩ፣ መጥፎ፣ አሳፋሪ፣ አኩሪ፣ አዋራጅ፣ አስመስጋኝ… ባህሪያትን ማወቅ ብቻ ሳይሆን በመንፈሱ እያሰረጸ ይጎለምሳል፡፡ እነዚህ መልካም እና መጥፎ የተባሉትን እንዲሁም ህጎች እና ደንቦች ከንቃተ-ህሌናችን እንዲሁም ከኢ-ንቃተ-ህሌናችን ውስጥ በጊዜ ሂደት ይከማቻሉ፡፡ ስለዚህ ልዕለ-ኢጎ ለበርካታ የኢድ ፍላጎቶቻችን ገርጋሪ ነው፡፡
>
> ኢጎ፡- በኢድ በሚፈልጉት አስደሳች ሲቃዎች እና በልዕለ-ኢጎ በሚደረገው በሞራላዊ፣ የህጋዊ፣ የሀይማኖታዊ፣ ወ.ዘ.ተ ተቃውሞዎች መሀከል ቆሞ እንደ አደራዳሪ እና እንደ ገላጋይ ሆኖ የሚሰራ ነው፡፡ በዚህም ሁለቱን ተቃራኒ ሀይሎች ያረጋጋቸዋል፡፡ በማለት ተንትኗል፡፡

ሃሳቡ የሚያስረዳው የሰው ልጅ በህጻንነቱ፣ በወጣትነቱ እና በእርጅናው ዘመን ምን እንደሚያደርግ ሲሆን ይህን የህይወት ኡደት ደግሞ ማንኛውም የሰውዘር ሳይዘለው የሚያሳልፈው ሂደት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሁሉም ፎክ ቡድኖች ማለትም በሃይማኖት፣ በስራ፣ በሙያ፣ በእምነት፣ በእድሜ፣ በጾታ…ወዘተ በመሳሰሉ ቡድኖች እና የማህበረሰብ ክፍሎች የህልሙ ይዘት ይለያይ እንጂ ድርጊቱ በሰው ልጅ የሚከሰት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ ታምሩ በናይል መጽሄት ላይ (2007፡9) የሚከተለውን ሃሳብ አስፍሯል፡፡

> ህፃንም ሆነ አዋቂ ሴትም ሆነች ወንድ፣ እይነስውርም ሆነ አይናማ ብቻ ማንኛውም ሰው ህልምን ያያል፡፡ ጥናቶች እንዳውም እያንዳንዱ ሰው በአንድ ሌሊት ብዙ አይነት ህልሞችን እንደሚያይ እያንዳንዱም ህልም በአማካኝ ከ5-20 ደቂቃ እንደሚረዝም አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህም በመነሳት በአለም ላይ ካለው የአንድ ሰው አማካይ እድሜ ውስጥ 6ቱ አመት የሚሆነው ህልም በማየት እንደሚጠፋ ይገመታል፡፡

ከላይ ያለው ሀሳብ የሚያስረዳው የሰው ልጅ በህይዎት ሲኖር ማሰብ፣ መስራት፣ በጋራ መኖር፣ ማዘን፣ መደሰት ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን ተግባራት እስከፊፀመ ድረስ እንደ ሁኔታው ይለያያል እንጂ ህልም ማንኛውም ጤነኛ ሰው እንደሚያይ ነው፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር ተያይዞ ቀና የሚከተለውን ሃሳብ ብሏል፡፡ ቀና (1945) A.P.N.ንን ጠቅሶ ‹ሕልም ጨርሶ አለማየት ወይም አለማዘውተር የአንጎልን መዳከምንና በአንጎላችን ውስጥ ዐብይ የሆኑ ክፍሎችን መቃወስ ያመለክታል፡፡› ይላል፡፡

ህልም በተለያየ ማህበረሰብ ልዩ ልዩ ትርጉሞች እና ፍቺዎች ሲሰጠው ይታያል፡፡ እንዳንድ የማህበረሰብ ክፍሎች ህልምን ቀን ሲታሰብ፣ ሲተገበር እና ሲታይ ከዋለ ነገር ላይ ተነስቶ ያንን ነገር በምንተኛበት ሰአት መከለስ ነው ይላሉ፡፡ ምክንያታቸውም በምናልመው ህልም ላይ ዕለት ከዕለት የምንሰራቸው እና የምናስባቸው እንዲሁም ከመተኛታችን በፊት ስናስባቸው የቆየናቸው ሃሳቦች ተጽእኖ አላቸው ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ህልም በልጅነት ጊዜያችን ሳናሳካ ያሳለፍናቸውን በኢ-ንቁ አእምሮ ውስጥ የተደበቁትን ፍላጎቶች እና ምኞቶች ማውጫ ወይም ማሳኪያ መንገድ ብለው ሲፈርጁት ሌሎች ደግሞ ህልም የወደፊት (የመጪውን ጊዜ) እጣፈንታን፣ እድልን፣ የሚገጥመንን ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር የሚያሳየን ነው በማለት ወደፊት ሊከሰት የሚችልን ነገር የሚያመለክት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ጭራሹን ህልም የለም ይላሉ፡፡ ነገርግን ህልም አይነቱ እና ፍቺው ይለያይ እንጅ ህልም እንዳለ Freud በሚከተለው ሃሳብ ይገልጻል፡፡ እናም Freud ህልምን በስነ-ልቦና እይታ በማየት ‹‹የህልም ትንታኔ›› በሚለው መጽሀፉ የሚከተለውን ገልጧል፡፡ Freud (2010:147) ‹‹ህልሞች ትርጉም

አልባ አይደሉም፤ የማይመስሉ (ዘበት) አይደሉም፤ በተቃራኒው ግን ህልሞች ተገቢነት ያላቸው የስነ-ልቦና ክስተቶች ሲሆኑ ምኞትን ማሳኪያነት፣ ጎልቶ በሚታይ የአእምሮ ስራ ውስጥ ለማስገባት የሚቀሰቅሱ እና ህልሞች የተገነቡት በከፍተኛው የተጧጧፈ የአእምሮ ተግባር ነው፡፡›› ይላል፡፡

Freud በዚሁ መጽሃፍ ህልሞች የሰው ልጅን የታመቀ ፍላጎት እና በህጻንነቱ የተፈጠረ የወሲብ ፍርሀትን በትምዕርት የሚገልጹ እንዲሁም በሰው ልጅ በከፊል ኢ- ንቁው የአእምሮው ክፍል (sub conscious mind) ውስጥ ያሉ አስተሳሰቦችን የሚያንጸባርቁ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ስለዚህ ህልም የአንድን ግለሰብ ስነ-ልቦናዊ ተግባር በተጨባጭ የሚገልጽልን ዘዴ ነው፡፡ ግለሰቡ ምን እንደሚያስብ፣ ምን እንደሚፈልግ፣ ምን እንደሚያስቆጣው፣ ምን እንደሚያስደስተው፣ ምን እንሚያስቀው፣ ምን እንደሚያስለቅሰው ….ወዘተ የመሳሰሉት ጉዳዩዎች የዛን ሰው ማንነት ባህሪያዊ በሆነ መንገድ ሊገልጹ የሚችሉ ነገሮችን የሚይዝ ነው፡፡

ከላይኛው ሃሳብ በተጨማሪ ታዬ የሚከተለውን ይገልጻል፡፡ Taye (1988:155)፡- ‹‹ህልሞች በጣም ጠቃሚ ሲሆኑ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ እነሱን ተጠቅሞ መልካም ወይም መጥፎ እድችን እንደጠቋሚ (አመላካች) ይቆጥሯቸዋል፡፡ ከእነዚህ ህልሞች መካከል ትንቢታዊ ህልሞች በመርማሪነት ውስጣዊ ተደርገው ስለሚታመኑ አብዛኛውን ጊዜ በተንቀሳቃሽ ህይወት ውስጥ በእውቀት የተሞሉ ናቸው፡፡›› በማለት አስፍሯል፡፡ ሰሎሞንም Destroን (2010፡227) ጠቅሶ የሚከተለውን ሃሳብ ጽፏል፡፡

> ህልም አንድ ሰው በሚተኛበት ወቅት ያለ የከፊል ንቃተ ህሌና (subconscious) እንቅስቃሴ ሲሆን ወደፊት የሚከሰትን ድርጊት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያመለክት፣ ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ፣ አካላዊና አእምሯዊ ሁኔታ የሚያሳይ ትርጓሜውም ከባህል ባህል የተለየ ነው፡፡ የህልም ፍቺ በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ጥበብ ሲሆን፣ ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ያለው ነው፡፡

ሃሳቦቹ የሚገልጹት ህልም የሰው ልጅን ውስጣዊ ማንነት ግልጽ አድርጎ በማሳየት በማህበረሰቡ ውስጥ ሆኖ ምን አይነት ፍላጎት ከምን አይነት ተግባር ጋር አስተሳስሮ መቀጠል እንዳለበት ያመላክታል፡፡ ህልም የግለሰቦችን ስነ-ልቦናዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ አስተሳሰባቸውን እና አመለካከታቸውን ለማወቅ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ህልም በተለያየ ማህበረሰብ የተለያየ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ ይህን በተመለከተ ለማ (2009፡60) ስለ ህልም

በ4ኛው ባህርዳር ዩንቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋና የባህል ዘርፎች አገር አቀፍ አውደ ጥናት መድብል ላይ ጠቅለል አድርጎ የሚከተለውን ብሏል፡፡

> የፍካሬ ልቦና ትወራ የሰውን ልጅ አእምሮ (ውስጣዊ ፍላጎት) ለመረዳት ከሚያተኩርባቸው ጉዳዮች አንዱ ህልም ነው፡፡ Mijilla (2005፣444) እንደሚያስረዱት ህልም ለፍሮይድ በእውኑ ህይዎት የታፈንን ፍላጎት ማሚያ ወኪል ሲሆን፣ ለያንግ አለማዊው ውስጣዊ እውነተኛ ሁኔታ ትምርታዊ ቅርፅ ይዞ በኢ-ንቁው፣ አእምሮ በግባታዊነት የሚከሰት የራስ መገለጥ ተፈጥሯዊ እና ጤነኛ ልቦናው ክስተት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ Kieffer (1996፣275)፣ ህልም ትዝታን ማስታወሻ አንዳንዴም የበሽታን ውስጣዊ ሁኔታ መግልጥ ማግኛ በመሆን እንደሚያገለግል ሲያስረዱ፣ ቪጎትስኪን ዋቢ አድርገው እንደሚገልፁት ደግሞ፣ ህልም ውስጣዊ ንግግር ወይም ውስጣዊ ሀሳብ ነው፡፡ ውስጣዊ ንግግርን፣ ውጫዊ ንግግርን መገለጫ የማይገኝለት ለራስ የሚደረግ ንግግር ነው በማለት ይገልፁታል፡፡ Freud (1955 2010፣148) ህልሞች ሁል ጊዜ ምንም አይነት ሽፋን ሳይፈልጉ በራሳቸው የምኞት ማሚያ ሆነው መገለጣቸውን ለማስረዳት እንደማይከብድ ያስገነዝባሉ፡፡ ህልም በፍካሬ ልቦና ምርምር ጉልህ ስፍራ እንዳለው የሚገልፁት Das (2014፣15) እንደሚያስረዱት ደግሞ፣ ለፍሮይድ ህልም ኢ-ንቁ ይዘቶችንና ድርጊቶችን የሚፀባረቁበትን የኢ-ንቁ አዕምሮ ሂደት ለመረዳት፣ ወደ ኢ-ንቁ አዕምሮ እውቀት የሚወስድ ጥርጊያ መንገድ ነው፡፡

ህልም በሀይማኖት እይታ፣ ከልማድ እይታ፣ ከባህል እይታ፣ ከስነ-ልቦና ባለሙያዎች እይታ፣ ከሀኪሞች እይታ፣ ከስነ-ባህሪ ተመራማሪዎች እይታዎች አንጻር በርካታ ትርጉሞች አሉት፡፡ ይህን በተመለከተ በሚከተለው ጽሁፍ የተወሰኑትን የጥናት አይነቶች በህልም ላይ ያላቸውን ሃሳብ እንመልከት፡፡ ታምሩ በናይል መጽሄት (2007:13)፡-

> ‹ሱፐር ናቹራል ንደፈ ሀሳብ›- ህልም ማለት ፈጣሪ (አማልክት) ለሰዎች ለራሳቸው ወይም ወገኖቻቸው አሊያም ስላሉበት ወይም ስለሚመጣው ዘመን እጣ ፈንታ ለማሳወቅ መልክት የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው ብሎ የሚረዳ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መረጃው ሰዎች እራሳቸውን ሊከሰት ከሚችል አደጋ እንዲጠብቁ እና በአጠቃላይ ህይወታቸውን በተስተካከለ መንገድ እንዲመሩ ይጠቅማል ብሎ ያምናል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ‹ኢጎ ድፌንስ ንድፈ ሃሳብ›- የህልም አላማ በህሊና (ፈርሃ ፈጣሪ) ማደግ እና በገሃዱ አለም ክልከላ ምክንያት ያላሳካናቸውን ምኞቶች ለማሳካት የምንጠቀምበት መንገድ ነው፡፡ ጥቅሙም እነዚህ ያልተሳኩ ምኞቶች የሚፈጥሩትን ውጥረት ለመቀነስ ነው፡፡ ሶስተኛው

ደግሞ ‹ኒውሮ ባዮሎጂካል ንድፈ ሀሳብ›- ይህን ንድፈ ሀሳብ የጻፉት ሆባሳንና ማከርሌ ሲሆኑ እንደእነሱ እምነት ህልም የሚፈጠረው ‹ ኮርቴክስ› (cortex) የተባለው የአንጎል ክፍል በእንቅልፍ ሰአት የሚደርሱትን ሞገዶች ትርጉም ለመስጠት በሚያደርገው ጥምረት የሚፈጠር ነው ይላል፡፡

ከላይ የተገለጸው ሃሳብ እንደሚያመለክተው በተለያዩ እይታዎች የህልም አይነትም ሆነ ፍቺው ልዩነት እንደሚኖረው ሲሆን ህልም ሁልጊዜ በሰው ዘር ዘንድ የሚተገበር ነገር ሲሆን ያለው ትርጉም በግምት የሚሰራ ቢሆንም የተወሰነም ቢሆን ሳይንሳዊ ንድፈ ሃሳቦችን እንደ መመሪያ በመጠቀም ጭንቀታችንን ይፈታል ማለት ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ እስካሁን ድረስ ስለህልም ቁርጥ ያለ ስምምነት ላይ እንዳይደረስ ካደረጉት ዋና ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የህልም ሃሳብ እስካሁን ድረስ አከራካሪ ነው፡፡

እንደሙዚቃ፣ ልብስ፣ ጨዋታ፣ ስዕል ሁሉ ህልም አንድን የማህበረሰብ ክፍል ሀዘን፣ ደስታ፣ ምኞት፣ ስርዓት መቅረጫ፣ መዳኛ ወ.ዘ.ተ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በተለይም በተለያዩ ቅዱሳን መጽሀፍት (ታአምረ እየሱስ፣ ታምረ ማሪያም፣ የገድላት መጽሀፍት፣ ስንክሳር፣ ድርሳናት፣ ህልመ ዮሴፍ…ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት) ተጽህፎ የምናገኘው የተለያዩ የጻድቃን፣ የሰማእታት፣ የድናግል፣ የመነኮሳት፣ የሀዋርያት፣ የመስህያውያን ለተጋድሎ (hero) ለመውጣት ትልቅ መሳርያ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ ይህም ህልም ከሚት ጋር ቅርብ ትስስር ያለው መሆኑን ያሳየናል፡፡ ይህን ሃሳብ በተመለከተ ቴወድሮስ ከግርጌ ማስታወሻው ካምቤልን (Campbell 1968:19) ጠቅሶ:-

> ‹ሚት ማህበረሰቡ የሚያየው ህልም ነው፤ ህልም ደግሞ በግለሰቡ ልቦና የሚበጅ ሚት ነው፡፡ (‹‹myth [is] adream of the masses of the people›› lotto Rank,The myth of the Birth of the hero,1913 (p.6) or ‹‹dream is the person alited myth,myth The deprsenalized dream:both myth and dream are symbolic in The same general way of the dayenamics of the psyche››

ከዚህ ጋር አያይዞ ቴወድሮስ ገብሬ በገድለ ተክለ ሀይማኖት ውስጥ የሚገኘውን ለተክለ ሀይማኖት እናት ለእግእዚያርያ ስለ እርሷ ልጅ የታያትን ህልም አስፍሮታል፡፡ ይኸውም እንደሚከተለው ነው፡፡ ቴወድሮስ (2001፡112-113)፡-

> የብርሀን ምሶሶ ከቤቷ ውስጥ ቁሞ፡፡ የምሶሶው እራስ ከሰማይ ደርሶ በአለም ያሉ ህዝብ ሁሉ ነገስታቱም በዙርያው ቁመው እኩሎችም ይሰግዱለታል፡፡ እኩሎቹም እሱን ዝቅ

አድርገው ይቀመጣሉ፡፡ በእርሱም ላይ ብዙ አእዋፍ ተቀምጠውበታል፡፡ እኩሎቹ ነጫጮች እኩሎቹም ቀያዮች፣ እኩሎቹም አመድ አመድ ይመስላሉ፡፡ ዝንጉርጉርም ናቸው (14፡6-15)፡፡ ሚካኤል መተርጉምም ነው፤ በህልም የከሰታቸውን ትምዕርታዊ ንግግሮች ደግሞ በህልም ተገልጦ ይፈክራል፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ፀጋ ዘአብን በህልሙ ታየው ተነጋገረው፡፡ ጸሀይ ከቤትህ ሲወጣ ያየኸው ከአብራክህ የተከፈለ ይህ ልጅህ ነው፡፡ በብርሀኑ ከምእመናን ላይ የሀጢያት ጨለማን የሚያርቅ፡፡ በክንፍም ላይ ታዝለው ያየሀቸው ከዋክብት በመንፈስ ቅዱስ ይወለዱ ዘንድ ያላቸው ልጆቹ ናቸው፡፡ ሚስትህም በቤታቹህ ላይ የብርሀን ምሶሶ ቁም እራሱ ከሰማይ ደርሶ ያየችው ይህ ነው፡፡ ነገስታቱ፣ ጳጳሳቱ ሲገዙለት ያየችውም በእውነት ነገስታቱ ይሰግዱለታል (16፡8፤7-21)፡፡

ከላይ ያለው ሃሳብ የሚያስረዳው ህልም የአንድን ሰው በፈጣሪ መመረጥ፣ መጽናኛ ቃል መስሚያ፣ ትእዛዝ መስጫ እና መቀበያ መንገድ፣ በህይዎት ውስጥ ግልጽ ያለሆነ ጉዳይ ግልጽ ማድረጊያና በማድረግ እረገድ አስተዋጽኦ እንዳለው ነው፡፡ ሰዎች ለተጋዳይነት እንዲወጡ አስቀድመው በህልም አማካኝነት ይነገራቸዋል፡፡ ይህም ለተመረጠው ሰው ለራሱ እና ለወዳጆቹ አስቀድሞ በመናገር ነገሩን እንደአዲስ እንዳይሆን ቀድመው እንዲዘጋጁ እና ብቸኝነትን፣ መነጠልን እንዲለማመዱ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ነው፡፡

ህልም የሰው ልጅ እስካለ ድረስ የሚኖር ሲሆን የሰው ልጅ የእራሱን እና የሌሎችን አስተሳሰብ እና አመለካከት አእምሯዊ በሆነ መንገድ የሚረዳበት እና የሚመረምርበት ነው፡፡ ህልም እራሱን የቻለ ጥሩ እና መጥፎ የሚባል ያለው ሲሆን ይህ ክፍፍል እንዲኖር ደግሞ የህልም ማያ (ማለሚያ) አመቶች፣ ወራቶች እና ቀናቶች እንደሆኑ አንዳንድ አጥኝዎች ይመሰክራሉ፡፡ ከእነዚህ አጥኝዎች መካከልም ቀና (1945፡15-16) ላይ ‹‹የህልም መፍቻ›› በሚለው መጽሀፉ በሰፊው ተንትኖ አስፍሮታል፡፡ ይኸውም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

> ጥሩና ቀና ህልም (ሠናይ) እንዲሁም ክፉና መጥፎ ህልም (እኩይ) የሚታይባቸው ቀናትና ወርኀ ከዚህ ቀጥሎ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡ ሠናይ ህልሞች መስከረም 9-12-16-18፣ ጥቅምት 5-12-27፣ ሕዳር 2-13፣ ታኅሣሥ 5-6-9-16፣ ጥር 7-12-19-23፣ የካቲት 1-11-24፣ መጋቢት 5-13-17-27፣ ሚያዝያ 19-23-24-26-28፣ ግንቦት 1-16-26፣ ሰኔ 10-12-28-30፣ ሐምሌ 7-12-19-16-29፣ ነሐሴ 7-5-8-24 እና እኩይ ህልሞች መስከረም 4/6/19/20/፣ ጥቅም 9/17/19/፣ ኅዳር 7/17፣ታኅሣሥ 4፣ጥር 5/15/25/፣ የካቲት 3/10/15/22/28/30፣ መጋቢት 8/26፣ ሚያዝያ 29/25፣ ግንቦት 4/11/፣ ሰኔ 7/12/24/30፣ሐምሌ 13/14፣ ነሐሴ 7/21/27 ነው፡፡

ከላይ የተገለጸው ሃሳብ የሚያሳየው ህልም ለማለም እና ጥሩ /መጥፎ/ ብሎ ለመመደም ጊዜ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ነው። ይኸውም በጊዜ ሂደት ሰዎች ልጅነትን፣ ወጣትነትን፣ እርጅናን ተቀዳጅተው በአሉበት የጊዜ ሁኔታ ደስታን፣ ሃዘንን፣ ማግኘትን እና ማጣትን ያዩበታል። ለመኖር፣ ለማሰብ እና ለመስራት ጊዜ ወሳኝ ነው። በጊዜ ወሳኝ ሃብትነት የሰው ልጅ በርካታ ተግባራትን ያከናውናል በእሱ ህይወት ላይም ብዙ ነገሮች ያልፉበታል። ጊዜ ህልም ለማለም ብቻ ሳይሆን ህልም ለመፍታትም አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በጊዜ ምክንያት የህልም ፍቺ የተለያየ እንዲሆን የሚያደርግ ሲሆን ይህ ደግሞ አላሚውን ብቻ ሳይሆን ህልም ፈቺው ላይም የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው። ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ መልኩ ተሾመ (2001፡2) ስለህልም ሁኔታ የሚከተለውን አስቀምጧል።

> ህልም አስደሳችም፣ አስጨናቂም፣ አመራማሪም፣ የሚረሳም ለብዙ አመታት ከአላሚው ጋር የሚኖር ሊሆን ይችላል። ህልም እንደ ሁኔታው ባለጥሩ ወይም መጥፎ ትርጉም ወይም ትርጉም አልባ ሊሆን ይችላል። ህልም ማስጠንቀቂያና ወደፊት የሚመጣውን የሚተነብይ ወይም በልቦና ውስጥ ያለውን በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያመለክትም ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል። ይህም ሆኖ በአንዱ ህልም ላይ የሌላውን ህልም ፈጽሞ መፍታት አይችልም የሚሉ አሉ።

የተገለጸው ሀሳብ የሚያመለክተው ህልም በሰው ልጅ ህይዎት ውስጥ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶት (ታምኖበት) የደስታ፣ የሀዘን፣ የምኞት እና የትንቢት ማሳያ ሆኖ ስነ-ልቦናን በመመርመር የተለያየ ህልም ፍች እንዳለ ነው። ህልም የአንድን ግለሰብ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ስራ፣ ተግባር፣ እንቅስቃሴ፣ ምኞት ወ.ዘ.ተ አጠቃላይ ግለሰቡን ከግለሰብ አድርገው ያኖሩትን መገለጫዎች መሰረት ያደረገ ጉዳይ ነው። ህልም እንዲፈጠር እንዲታለም ያደረገው የግለሰቡ አጠቃላይ የህይዎት መገለጫዎች ናቸው። በመሆኑም እነዚህ መገለጫዎች ለህልም አፈታት ልዩነት ዋና መሰረቶች ናቸው። የህልም አፈታት መሰረቱ እንደየ ማህበረሰቡ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት እና ፍልስፍና የተለያየ ነው። በተለያዩ ማህበረሰቦች ህልም የመፍታት ችሎታ መስፈርቶች ልዩ ልዩ መልክ አላቸው። ህልም ፈቺ በአብዛኛው ህብረተሰቡ የሚያምነው የሚፈታው ህልም ፍቺ እና አደራረሱ (ሲደርስ) አንድ አይነት ከሆነ ነው። አንዳንዴ ህልም አላሚዎችም ህልም ፈቺ ይሆናሉ። በአብዛኛው ከህልም ጋር በሚኖራቸው ዘወትራዊ ትውውቅ፣ ልምምድ፣ ትስስር እና ትግበራ ህልምን መፍታት ይማራሉ።

በአንዳንዱ ማህበረሰብ አባቶች፣ በማህበረሰቡ ደግ ሰው ተብለው የሚታመኑ ግለሰቦች፣ በህይማኖታቸው በቅተዋል የተባሉ ሰዎች ያሳያቸዋል በሚል እምነት፣ ደናግላን (ንፁህ ናቸው ተብለው የሚታመኑ ሰዎች) ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ሰዎች ህልም ፈቺ አድርጎ ማህበረሰቡ ይሾማቸዋል፡፡ በሌሎች ደግሞ በህይዎታቸው የተፈተኑ ሰዎችን ሀዘን እና ደስታን፣ ርሀብ እና ጥጋብን፣ ማግኘት ማጣትን፣ ጦርነት እና ሰላምን ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ሰናይ እና እኩይ ነገሮችን በህይወታቸው ያሳለፉ ሰዎችን ህልም ፈቺ ያደርጋቸዋል፡፡ ነገር ግን በአንድ የማህበረሰብ ቡድን ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ህልም ፈቺ አይሆኑም፤ አይደሉምም፡፡ ከዚያ ማህበረሰብ መካከል ነጥረው የወጡ የማህበረሰቡን ሁለገብ ጉዳይ ሊረዱ የሚችሉ ሰዎች ህልም ፈቺ ይሆናሉ፡፡ በተለይም ህልምን ከተለያዩ ሌሎች ነገሮች ለይተው የሚያውቁ ግለሰቦች ናቸው፡፡ ይኸውም ህልምን ከሚመስሉ እንደ ቅዠት፣ ራዕይ እና ትንቢት ያሉ የማህበረሰብ ሃብቶች ላይ በቂ እውቀት ያለው ሰው ህልም ፈቺ ይሆናል፡፡

ማንኛውም ጽንሰ-ሃሳብ በቁሙ ሲታይ አንዱ ከአንዱ ተመሳሳይነት ያለው ሊመስለን ይችላል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ነገር የራሱ የሆነ ትርጉም፣ ፍቺ፣ ምንነትና ፋይዳ አለው፡፡ አንዳንድ ግለሰቦች ቅዠትን፣ ህልም እና ራዕይን በተመሳሳይነት ለአንድ ጉዳይ ይጠቀማሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ለያይተው ለየብቻ ይጠቀማሉ፡፡ ያም ይሁን ይህ እንደየ ግለሰቦች አስተሳሰብ እና አመለካከት ይለያያል፡፡ እነዚህን ቃላቶች በተመለከተ የተለያዩ መዝገበ ቃል ፍቺዎች በሚከተለው ሁኔታ የእያንዳንዳቸውን ምንነት እንደሚከተለው በጥቂቱ እንመልከት፡፡

የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፡195) ቅዠት፡- የተዘበራረቀና በትክክል ለማስታወስ የማይቻል ህልም በእንቅልፍ ላይ ያለ የማላዘን፣ ጨኸት የማሰማት ወይም አንዳች ነገር የማሰማት ድርጊት የተዘበራረቀ የማይጨበጥ ወይም ሊታመን የማይቻል ወሬ፡፡ ራእይ (ገጽ101)፡- በእንቅልፍ ወይም በተመስጦ ጊዜ የሚታይ ህሌናዊ ትርኢት፤ ህልም፡፡ ትንቢት (ገፅ 260)፡- ስለ ወደፊት ይደረጋል፣ ይፈጸማል ተብሎ በቅድሚያ የተነገረ ቃል፣ ንግረት፡፡ ኤፍሬም (1993፡117) ትንቢት፡- ንግርት፣ ቅዠት (ገፅ 53)፡- የህልም ጨኸት ማለት ነው ይላል፡፡ የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (2010፡70) ራዕይ፡- ሰው ሳያንቀላፋ በተመስጦ የሚያወራውና የእግዚያብሄር ቃል የሚገልጽበት፡፡ ራዕይ ከህልም የተለየ ነው፡፡ ራእይ እግዚያብሄርን ለሚያውቁ፣ የእግዚያብሄር መንፈስ ላደረባቸው ይሰጣል፤ ዘኍ.12÷6፤ ሐ.ሥ.2÷17፡፡ በብ.ኪ.ዘመነ ራእይ የታየባቸው ነቢያት ብዙዎች ናቸው፡፡ በተለይም ህዝቅኤል እና ዳንኤል ብዙ ራዕይ አይተዋል፡፡

በአጠቃላይ ቅዠት የምንለው አንድ አስፈሪው የህልም አካል ሆኖ የሚያቃዠው ግለሰብ እንዴት እንዳቃዠው፣ ምን እንዳለ፣ እንዴት እንዳደረገ፣ ምን እንደሰራ ላያውቀው ይችላል። በሰዎች ዘንድ የመታወስ ደረጃው በጣም ዝቅተኛ ነው። ቅዠት ባባት፣ ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ጩኸት፣ መንፈራገጥ፣ እንቅስቃሴ፣ ልቅሶ፣ መቧጨር…ወ.ዘ.ተ ነገሮች ሊስተናገዱበት ይችላል። ህልም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሰዎች ተኝተው በእንቅልፍ ላይ እያሉ የሚያዩት ጥሩ እና መጥፎ  አይነት ያለው ሲሆን ስለአለፈው፣ ስለአለንበት እና ስለሚመጣው ነገር ሊያሳየን የሚችል ነው። ህልም ለማየት (ለማለም) መተኛት ወሳኝ ነው። ህልም ሰዎች በሚተኙበት ጊዜ የተለያዩ ስሜቶችን እና ሀሳቦችን የሚያስተናግዱበት ክስተት ነው።

ህልም በህጻናት፣ በወጣቶች፣ በጎልማሶች፣ በአረጋዊያን፣ በሴቶች፣ በወንዶች፣ በጥቁሮች፣ በነጮች፣ በአጭሮች፣ በረዥሞች፣ በቀጭኖች፣ በወፍራሞች…ወ.ዘ.ተ እንደየ ሁኔታው ህልሙ ይለያይ እንጂ የሚተገበር ነው። ራዕይ ሰው ሳያንቀላፋ እና ሳይተኛ ተቀምጦም ሆነ ቁሞ በተመስጦ የሚያየው አንዳች ነገር የሚገለጥበት መንገድ ነው። ራዕይ ከህልም የሚለይ እና ደረጃውም ከፍ ያለ ነው። ራዕይ ከህልም በበለጠ ታማኝነት ስላለው በመድረሱ እርግጠኛ ሆነን እንናገራለን። ራዕይ የሚያይ ሰው በአንድ ነገር ላይ አጥብቆ አማኝ መሆን አለበት (የአንድ ሀይማኖት ተከታይ)። ምክንያቱም ራዕይ የሚያይ ሰው የበቃ መሆን ስላለበት ነው። መብቃት የሚለካው ህግን የማክበር እና የሆነ ግዳጅን ከመውጣት ብቃት ጋር የሚገናኝ ነው። ትንቢት ደግሞ ከሁሉችም ከፍ ያለ እና ሰፊ ጉዳይን የያዘ የመጨረሻው ደረጃ ነው። ትንቢት ከራዕይ ጋር የሚመሳሰል እና የሚቀራረብ  ሲሆን የሆነን ጉዳይ ተከትሎ የሚመጣ እና የሚነገር ነው። ትንቢት ተናጋሪ ሰው ከሌላው ሰው በተለየ ከልዕለ ተፈጥሮ ሃይል ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው ነው። ስለዚህ ሁሉም ቃሎች ልዩነት ስላላቸው አንዱን ከአንዱ የመለየት እውቀት ወይም ብቃት ያስፈልጋል።

ይህን ሃሳብ በተመለከተ Ackroyd (2001:1) *‹‹ ማንኛውም በህልም የሚታይ (የሚመጣ) ነገር የሆነ ትርጉም አለው። ነገር ግን አንድ አይነት ስዕል በህልም ውስጥ ለተለያየ ሰው የተለያየ ትርጉም ሲኖረው ወይም ለአንድ አይነት ሰው በተለያየ ጊዜ ትርጉሙ ልዩነት ይኖረዋል።››* በማለት ይገልጻል።

የተገለጸው ሃሳብ የሚያስረዳው በህልም ውስጥ ትዕምርት ሆኖ የሚገኝ ነገር ትርጉም አልባ አለመሆኑን እና የተለያየ አስተሳሰብ እና አመለካከት ለሚከተል ህልም ፈቺ እንዲሁም በተለያየ ዘመን የሚታይ ህልም የተለያየ ትርጉም እንደሚኖረው ነው። የጊዜ መፈራረቅ ለህልም ትርጉም እና ፍቺ ልዩነት እንዲኖረው ትልቅ አስተዋጾ አለው። ስለሆነም ሁሉም ሰው አንድ

አይነት ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ እምነት፣ የህይወት ፍልስፍና ስለሌለው ህልም ማለም እና ህልም ፍቺ ላይ ልዩነት እንዲኖረው ምክንያት ሆኗል ማለት ነው፡፡

የህልም ፍቺ እና ተግባር በተለያዩ ቅድሳት መጽሃፍት እና በሳይንሳዊ መጽሃፍት በተለያየ መልክ ልዩ ልዩ ተግባሮችን ይዞ እናገኘዋለን፡፡ ከእነዚህ መካከልም በመጽሃፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁራን የህልምን ተግባር ምን እንደሚመስል በጥቂቱ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

## 1. ህልም በመጽሀፍ ቅዱስ

ህልም የሌለበት የሰው ህይወት እና ቦታ የለም፡፡ በሰው ልጅ ህይዎት ውስጥ በንግዱ፣ በትራንስፖርት፣ በግብርናው፣ በሽመናው፣ በባህለዊ መድሀኒት፣ በሰላምታ አስጣጥ፣ በደስታ፣ በሀዘን፣ በሀይማኖት፣ በእምነት ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት ጉዳዮች ውስጥ ተሰላስሎ እናገኘዋለን፡፡ ህልም የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር ያሉበትን የዘመኑን (ወቅቱን) ሁኔታ ርሀብ፣ ድርቅ፣ ቸነፈር፣ ጥጋብ፣ ብልጽግና፣ ልምላሜ፣ ሰላም፣ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሀዘን፣ ጭካኔ፣ ርህራሄ፣ መተዛዘን፣ መገዳደፍ (መተባበር) ወ.ዘ.ተ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያለውን የዘመን መንፈስ ሊያሳይ ይችላል፡፡

ይህን እንደ አጠቃላይ ስናየው ፖለቲካውን፣ ኢኮኖሚውን፣ ማህበራዊውን፣ ስነ-ልቦናውን ከማህበረሰቡ የሚነበበውን እና የሚታየውን እንቅስቃሴ ሊመረምር ይችላል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ ብዙ ዘመናትን በተለያዩ ሁኔታዎች አልፎ እደረሰበት ደርሷል፡፡ ካለንበት ዘመን እስኪደርስ ድረስ ህልም አገልገሎት ላይ እየዋለ ሲሆን አሁንም በመጠቀም ላይ ያለ ወደፊትም የሚጠቀም ይሆናል ማለት ነው፡፡ አጠቃቀሙም ህልም አላሚው እና ህልም ፈቺው በቡድኑ ውስጥ ካለው ማህበራዊ ደረጃ፣ ጾታ፣ እድሜ ከሚኖሩበት መለከአምድር እና የአየር ንብረት ባህል፣ ወግ፣ እምነት፣ ሀይማኖት አንጻር ነው፡፡ ይህ ደግሞ የህልምን ጥንታዊነት እና እድሜ ጠገብነት ያሳየናል፡፡ ይህን በተመለከተ ሶሎሞን ብርሀኑን (2001፡ 4) ጠቅሶ ‹‹በአለማችን ላይ የነበሩ ታላላቅ ሀይማኖቶች እና የፖለቲካ መሪዎች ዳዊትን፣ ሰሎሞንን፣ ፈርኦኖችን እና የሮማውያን ቄሳሮችን ጨምሮ የ21ኛው ክፍለ ዘመን መሪዎች የህልም ፍች ጥበብን ይጠቀሙበታል›› በማለት አስፍሯል፡፡

ከዚህ ሃሳብ በመነሳት ህልም በመጽሀፍ ቅዱስ በተለያዩ ቦታዎች በተለያየ መልክ በሰፊው ተገልጾ እናገኘዋለን፡፡ በተለይም የተጠቀሱት ህልሞች እና ፍቾቻቸው መንፈሳዊ መሆንን እና

መንፈሳዊ አለመሆንን የሚያመለክቱ ናቸው። ህልም በመጽሀፍ ቅዱስ በብሉይ እና በሀዲስ ኪዳን ውስጥ በተለያየ መልክ እናገኘዋለን። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰው የምናገኛቸውን ጥቂት መረጃዎች እንመልከት፡- ይኸውም ኦዘፍ.41÷1-36 ላይ የምንመለከተው በህልም አማካኝነት የርሀብ ዘመንን ቁጠባን በመጠቀም ማለፍ እንደቻሉ ነው። ይህም የሆነው በግብጽ ሀገር በፈርኦን ዘመን ለፈርኦን የታየ ህልም ሲሆን ህልሙን የፈታው ደግሞ ዮሴፍ ነው። ኦዘፍ.40÷1-22 ከዚህ መረጃ የምናገኘው በህልም አማካኝነት የወደፊት እጣ ፈንታን ማወቅ እንደሚቻል ነው።

ይኸውም በፈርኦን ንግስና ዘመን አንድ የጠጅ አሳላፊዎች ሃላፊ እና የእንጀራ ጋጋሪዎች አለቃ ፈርኦንን በድለው ዮሴፍ ከታሰረበት የግዞት ቤት (እስር ቤት) ታስረው እያሉ ህልምን አይተው ለዮሴፍ ሲነግሩት የጠጅ አሳላፊዎች ሀላፊ ህልሙ ለመልካም እንደሆነ ፍቺውን ነግሮ ሁለቱም ወደነበሩበት ስልጣን ሲመለሱ የእንጀራ ጋጋሪዎች ሃላፊዎች አለቃ ደግሞ ህልሙ መጥፎ እንደሆነ እና ፈርኦን እስከ ሶስት ቀን አንገቱን እንደሚቆርጠው፣ እንደሚሰቅለው እና የሰማይ ወፎች እንደሚበሉት ዮሴፍ ነግሮት በሶስተኛው ቀን  እንዳለው ሆነ።

ሌላኛው ደግሞ ኦዘፍ.37÷5-11 ላይ የምንመለከተው ዮሴፍ ህልም እንዳየ ያሳየናል። ዮሴፍ ህልምን አለመ፤ ለወንድሞቹም ነገራቸው። እርሱም አላቸው ‹‹እኔ ያለምኩትን ህልም ስሙ፤ እነሆ እኛ በእርሻ መካከል ነዶ ስናስር ነበርና፣ የእኔ ነዶ ቀጥ ብላ ቆመች፣ የእናንተም ነገዶች በዙርያ ከበው እነሆ፣ ለእኔ ነዶ ሰገዱ።›› ወንድሞቹም ‹‹በዕኛ ላይ ልትነግስብን ይሆን? ወይስ ገዢ ትሆነን ይሆን? ›› አሉት። እንደገናም ስለ ህልሙ እና ስለነገሩ የበለጠ ጠሉት። ደግሞ ሌላ ህልምን አየ፤ ለአባቱ እና ለወንድሞቹ ነገራቸው፤ እንዲህም አለ፤ ‹‹እነሆ፤ ሌላ ህልምን አለምሁ፤ ህልሙም እንዲህ ነው፡- ጽሀይ እና ጨረቃ አስራ አንድ ከዋክብትም ይሰግዱልኝ ነበር።›› አባቱም ገሰጸው፤ እንዲህም አለው፤ ‹‹ይህ ያለምከው ህልም ምንድን ነው? በውኑ እኔ እና እናትህ፣ ወንድሞችህም መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆን?›› ወንድሞቸም ቀኑበት፤ አባቱም ግን  ይህን ነገር በልቡ ይጠብቀው ነበር።

ከላይ ያለው (የተገለጸው) የዮሴፍ ህልም የሚያመለክተን ፈጣሪ ዮሴፍን በምድረ ግብጽ እንደሚነግስ አስቀድሞ ያሳየው መሆኑን ያመለክተናል።

አሁንም ከመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 1÷1-45 ያለውን ስንመለከት ናቡከደ ነጹር የባቢሎን ንጉስ ህልም አይቶ ህልሙ እንደጠፋው እና በምርኮ ከእየሩሳሌም ወደ ባቢሎን የሄደው ዳንኤል የንጉሱን የጠፋ ህልም ከነፍቺው እንደነገረው ያመለክታል፡፡ በዚህ ጹሁፍ ውስጥ ንጉሱን የተረሳ ህልም እና ፍችውን ይነግሩት ዘንድ ህልም ተርጓሚዎችን፣ አስማተኞችን እና መተተኞችን ከለዳውያንን ቢያስጠራም እንደማይችሉት ሲነግሩት ከባድ ቅጣት እንዲቀጡ  ሲነገራቸው ዳንኤል ሰምቶ ንጉሱን ጊዜ እንዲሰጠው እና ህልሙን እና ፍችውን እንደሚያቀርብለት ተናግሮ በጸሎት ህልሙ እና ፍቺው ተገልጦለት መናገሩን ያሳየናል፡፡ ሌላው በዚሁ በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 4÷3-36 ውስጥ ሰፍሮ የምናገኘው የናቡከደነጹር ሁለተኛው ህልም ነው፡፡ የንጉሱን ህልም ዳንኤል እንደተረጎመለት እና ህልሙም እንደደረሰ ያመለክታል፡፡ ሌላው ደግሞ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ማቴዎስ ወንጌል 2÷13-15 ላይ ተገልጾ የሚገኘውን ሃሳብ እንመልከት፡- ‹‹የጌታ መላዕክ በህልም ለዮሴፍ ታይቶ ሄሮድስ ህጻኑን ሊገድለው ይፈልገዋል፡፡ ተነሳ ህጻኑን እና እናቱን ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ፡፡ እስክነግርህ ድረስ በዚያው ተቀመጥ አለው፡፡››

ይህ ሃሳብ የያዘው መልክትም ዮሴፍ የእየሱስን እናት ማሪያምን እንዲጠብቃት የተሰጠ ሲሆን ማሪያም እየሱስን ስትወልድ ሄሮድስ በዛን ዘመን የተወለዱ ወንድ ህጻናትን ይገድል ስለነበር እየሱስ በንጉሱ  እንዳይገደል መለኮታዊ ሀይል ለዮሴፍ መልክት ያስተላለፈ መሆኑን ነው፡፡ ወንድ ህጻናት የሚገደሉበት ምክንያት በትንቢት በዘመኑ ከሚወለዱት መካከል አንዱ ንጉስ ይሆናል ስለተባለ ሄሮድስ ንጉስ የሚሆነውን በስአቱ ስለማያውቅ በጅምላ በመጨፍጨፍ ስልጣኑን እንዳይወስድበት ያደረገበት ተግባር ነው፡፡ ህልም ከመለኮታዊ ሀይል ጋር የመገናኛ እና ሃሳብ መለዋወጫ መንገድ ሆኖ እንደሚያገለግልም ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ህልምን በመጽሀፍ ቅዱስ ሲታይ የተለያዩ ነገስታት በሰፊው ይጠቀሙበት እንደ ነበር ነው፡፡ በተለይም በብሉይ ኪዳን ዘመን (በህገ ልቦና ዘመን) ትልቅ አገልግሎት እንዳለው ያሳያል፡፡ ይኸውም በዚህ ዘመን የሰው ልጅ የሚመራው በተጻፈ ህግ ሳይሆን አእምሮ ውስጥ በትእዛዝ በተቀመጠ ህግ በነበረበት ስአት ስለሆነ የአድርግ አታድርግ ለእያንዳንዱ ግለሰብ የህሊናው የውስጡ የድርሻ ውጤቶች ናቸው፡፡ ህልም በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው የአለም ነገስታት ሳይቀሩ በህልም አመኔታ ጥለው እና እውነትነቱን በማመን አገልግሎት ላይ እንደሚያውሉት ያመለክተናል፡፡

## 2. ህልም በቅዱስ ቁራን

ህልም በመጽሀፍ ቅድስ ውስጥ ሰፊ አገልግሎት እንዳለው ሁሉ በቅዱስ ቁራንም በተለያየ ቦታ ተገልጾ እናገኘዋለን፡፡ የሰው ልጅ እንደ ሀይማኖቱ እና እምነቱ የተለያየ አተያይ እና ፍቺ እየተሰጠው እና ህልም በአንድም በሌላም መንገድ ተግባራዊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም በቅዱስ ቁራን የህልምን እውነታነት በማረጋገጥ ይጠቀሙበት እንደነበር በተለያየ የቁራን ክፍል ተገልጾ እናገኘዋለን፡፡ በእስልምና እምነት ውስጥ ህልም እንደ አንድ እምነት መግለጫ መንገድ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ህልም በቅዱስ ቁራን ሰዎች በአላህ ለተለያዩ ተግባራት ተመርጠው ልዩ ልዩ የስራ ድርሻዎችን ሲቀበሉ ያሳያል፡፡ በተለይም እነዚህ ሰዎች ትንቢት ተናጋሪ፣ ህልም ፈቺ፣ ሀይማኖዊ ትምዕርት አስተማሪ…ወዘተ የመሳሰሉትን ትግባራት ይሰራሉ፡፡ ይህንንም በሚከተለው ጹሁፍ እንመልከተው፡- ቅዱስ ቁርአን ውስጥ አል-የሱፍ 12÷4-6 ላይ፡-

> የሱፍ ለአባቱ ‹ አባቴ ሆይ አስራ አንድ ከዋክብትን፣ ጽሀይን እና ጨረቃንም አየሁ፤ ለኔ ሰጋጆች ሁነው አየዋቸው› ሲል አባቱ ደግሞ ልጄ ሆይ ‹ህልምህን ለወንድሞችህ አታውራ፡፡ ለአንተ ተንኮል ይሰሩብሀልና፡፡ ሰይጣን ላዋቂው ግልጽ ጠላት ነውና፡፡ እንዲሁም ጌታህ ይመረጥሀል፡፡ ከንግግሮችም ያስተምርሀል፡፡ ጸጋውንም ከአሁን በፊት በሁለቱ አባቶች በኢብራሂም እና በይስሀቅ ላይ እንደሞላት በአንተ ላይ እና አያእቆብ ዘሮችም ላይ ይሞላታል፡፡ ጌታህ አዋቂ ጥበበኛ ነው እና› አለው፡፡ (ቅዱስ ቁራን፡ 2003)

ከላይ የተጠቀሰው ሀሳብ እንደሚያመለክተን የሱፍ በፈጣሪው ለነብይነት የተመረጠበት መንገድ በህልም እንደሆነ ያመለክታል፡፡ በቅዱስ ቁራን የምናገኘው ሌላኛው የህልም ታሪክ ደግሞ የሱፍን የህልም ፊቺ ያውቅ እንደነበር የሚያመለክተን ታሪክ በዚሁ ምዕራፍ ተገልጾ ይገኛል፡፡ ሀሳቡም የሚከተለው ነው፡፡ አል-የሱፍ 12÷36-41፡-

> ከእርሱም ጋር ሁለት ጎበዞች እስር ቤት ገቡ፡፡ አንደኛቸው ‹‹እኔ በህልሜ የወይን ጠጅን ስጠምቅ አየሁ›› አለ፡፡ ሌላኛውም፡- ‹‹እኔ በእራሴ ላይ እንጀራ ተሸክሜ ከእሱ በራሪ (አሞራ) ስትበላኝ አየሁ፡፡ ፍቹን ንገረን፡፡ ከአሳማሪዎች ሆነህ እናይሀለን እና›› አሉት፡፡ የሱፍም አለ፡- ‹‹ማንኛውም የምትሰጡት ምግብ ለእናንተ ከመምጣቱ በፊት ፍቹን የምነግራቹህ ቢሆን እንጂ አይመጣላቹህም፡፡ ይህ ጌታየ ካሳወቀኝ ነገር ነው፤ እኔ በአላህ የማያምኑን እርሱም መጨረሻይቱን አለም እነርሱ ክህዲዎች የሆኑትን ህዝቦች ሀይማኖት ትቻለሁ፡፡… ካለ በኂላ የህልሙን ፍች እንዲህ አላቸው፡፡ ‹‹የወህኒ ቤት ጓደኞቸ ሆይ! አንደኛቹህማ ጌታውን (ንጉሱን) ጠጅ ያጠጣል፡፡ ሌላኛውማ ይሰቀላል፡፡

ከራሱም በራሪ (አሞራ) ትላለች፡፡ ያፍቹን የምትጠይቁት ነገር ተፈጸመ፤›› (አላቸው)፡፡ ጠጅ ያጠጣል ብሎ ህልሙ የመሰከረለት ሳይሞት ድኖ ሳለ ንጉስ ህልም አይቶ የሚፈታ ሲፈልግ የዳነው ሰው የሱፍ አለ በማለት የንጉሱን ህልም የሱፍ እንዲፈታ ተደረገ፡፡ ከወይን ቤትም ትልቅ ባለመዋል ሆነ፡፡ የንጉሱ ህልም እና ፍቺም የሚከተለው ነው፡፡ አል-የሱፍ 12÷43-50 ንጉሱም ‹‹እኔ ሰባትን የሰቡ ላሞች ሰባት ከሲታዎች ሲበሏቸው ሰባትንም ለምለም ዘለላዎች ሌሎችንም ደረቆችን (ሲጠመጠሙባቸው በህልሜ) አያለሁ፡፡ እናንተ ታላላቅ ሰዎች ሆይ! ህልምን የምትፈቱ እንደሆናቹህ ህልሜን ፍቱልኝ›› አላቸው፡፡ ሰዎቹም ‹‹የህልሞች ቅዠቶች ናቸው፡፡ እኛም የህልሞችን ፍች አዋቂዎች አይደለምን›› አሉት፡፡ ያም ከሁለቱ የዳነው እና ከብዙ ጊዜ በኂላ (የሱፍን) ያስታወሰው ሰው ‹‹እኔ ፍቺውን እነግራቹሀለው እና ላኩኝ›› አለ፤ (ወደ የሱፍም ሔደም)፡፡ ‹‹አንተ እውነተኛ የሱፍ ሆይ! ሰባትን የሰቡ ላሞች ሰባት ከሲታዎች ላሞች ሲበሏቸው ሰባትን ለምለም ዘለላዎችም ሌሎችም ደረቆች (በእነርሱ ላይ ሲጠመጠሙባቸው ያየን ሰው ህልም ፍች) ትችልን፡፡ ያውቁ ዘንድ ወደ ሰዎቹ ልመለስ እከጅላለውሁና›› አለው››፡፡ የሱፍም ከላይ በንጉሱ የታለመን ህልም እንደሚከተለው ፈትቶ ነገረው፡፡ (እርሱም) አለ፡- ‹፣ሰባትን የተከታተሉ አመታት ትዘራላችሁ፡፡ ያጨዳችሁትንም ሁሉ ከምትበሉት ጥቂት በስተቀር በዘለላው ውስጥ ተውት፡፡ ‹‹ከዚያም ከእነዚያም በኂላ ካደለባቹሁት ጠቂት ሲቀር ለእነእርሱ ያደለባችሁትን ሁሉ የሚበሉ ሰባት የችግር አመታት ይመጣሉ፡፡ ‹‹ከዚያም እነዚያ በኂላ ሰዎቹ በእርሱ የሚዛነቡበትን በርሱም (ወይንን) የሚጨምቁበት አመት ይመጣል፡፡›› አለው፡፡ ንጉሱም ‹‹እርሱን አምጡልኝ›› አለ፡፡ መልክተኛውም (የሱፍን) ባመጣው ጊዜ ወደ ጌታህ ተመለስ አለው፡፡ ( ቅዱስ ቁራን፡ 2003)

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን በቅዱሳት መጽሃፍት ውስጥ ባይገለጥም በአገራችን ምን አይነት ንጉስ እንደሚነግስ (አንደሚነሳ) ጥፋት ሆነ ልማት ምን እንደሚመጣ የታዩ ህልምዎች በአንዳንድ የታሪክ መጽሀፍት ውስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ለማስረዳት ያክል ‹‹በናይል መጽሄት›› (2007፡ 9፣13) ያገኘውት መረጃ እንደሚከተው ነው፡፡

ፓውሎስ ኞኞ የተባለ ጽሀፊ ‹አጤ ሚኒሊክ › በሚለው መጽሀፉ አጤ ሚኒሊክ ከገረድ እንደሚወለድ በህልም አማካኝነት ተነግሮ እንደተወለዱ ያመላክተናል፡፡ በዘውዴ ረታ ‹ረዥሙ የስልጣን ጉዞ› በሚለው መጽሀፉ አጤ ሚኒሊክ ስልጣናቸውን ለልጅ ልጃቸው ለልጅ እያሱ አድጎ እንዲወርስ ቢናዘዙም በተለያዩ መነኮሳት ተፈሪ መኮነን እንደሚነግሱ

ህልም እንዳዩ እና እንደደረሰ በጽሁፉ አትቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዘውዴ ረታ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ፍፃሜያቸው እንደፍቻቸው የሆኑ ህልሞችን እናገኛለን፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ንግስተ ነገስት ዘውዲቱ ከዘመነ ማርቆስ 1922 እና ራስ መኮንንም ከ1898 በህይወት እንደማያልፉ ግለሰቦቹ በህልማቸው ማየታቸውን ተጽፎ እናገኛለን፡፡

በአጠቃላይ በቅዱስ ቁራንም ይሁን በመጽሀፍ ቅዱስ ከተለያዩ ቦታዎች የህልምን ሚና በሰፊው ሰፍሮ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ የሃይማኖት እና የአምልኮ መጽሃፍት እንዲሁም ሳይንሳዊ መጽሃፍት ህልም የተለያዩ ተግባሮች እንዳሉት ተገልጾ ይገኛል፡፡ ህልም የሰው ልጅን መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ተግባሮች እና እንቅስቃሴዎች ከሚኖሩበት ማህበረሰባዊ የልማድ እና የባህል አስተሳሰብ፣ አመለካከት እና የህይወት ፍልስፍና አንጻር መግለጽ የሚችል ነው፡፡

### 3.1.1.1.1.1 የህልም አይነቶች

ህልም እንደየ ግለሰቡ የህይዎት ፍልስፍና፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ጾታ፣ እድሜ፣ የኑሮ ደረጃ፣ አመለካከት ወ.ዘ.ተ ከመሳሰሉት አንጻር ብዙ አይነት ሊሆን ይችላል፡፡ ህልም የግለሰቡን ማንነት ሊነግረን እና ሊለካ ይችላል፡፡ በተለይም ከህልም ፊቺ አንጻር ስንመለከተው የህልምን አይነት ያበዘዋል፡፡ ይኸውም ከባህል እይታ፣ ከስነ-ልቦና እይታ፣ ከሀይማኖት እይታ፣ ከስነ-ህይወት ጥናት እይታ፣ ከስነ-ሰብ እይታ ወ.ዘ.ተ አንጻር የተለያየ ህልም እና ፍቺውም እንደሚለይ ያሳያሉ፡፡ ሌላው ደግሞ ከአላሚው ማንነት እና ከህልም ፈችው የህልም አፈታት ልማድ አንጻር ሊለያይ ይችላል፡፡ በአብዛኛው ህልም በሶስት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ቅዠት (night mare)፣ ግልጽ ህልም (lucid dream)፣ እና ነጋሪ (precognition dream) ናቸው፡፡

Lucid dream በእየለቱ የምናከናውናቸው ነገሮቾ ደግመን የምናይበት በእንቅልፍና በመንቃት መካከል ሆነን ነገሮችን የምናይበት መንገድ ነው፡፡ ይህ አይነቱ ህልም በብዙ ሰዎች የሚከሰት እና ያን ያህል ለስነ-ልቦና ጉዳት የማያደርስ የህልም አይነት ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ሰዎችን የሚያስጨንቅና ሽብር ውስጥ የሚከቱ ህልሞች አሉ፡፡ እነዚህም ቅዠት (night mare) ይባላሉ፡፡ ቅዠት በአብዛኛው እድሚያቸው ከ15 አመት በታች በሆኑ ህጻናት ላይ በተደጋጋሚ ይከሰታሉ፡፡ ነገር ግን በአዋቂዎች ላይ የለም (አይከሰትም) ማለት አይደለም፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ወደፊት የሚከሰትን ነገር ቀድመው የሚተነብዩ ህልሞች ሲሆኑ ነጋሪ (precognition) ህልሞች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ህልሞች ሲታዩ ወደፊት የሆነን ነገር እንደሚከሰት እንደማረጋገጫ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ምሳሌ፡- የአሜሪካው ፕሬዘዳንት የነበሩት አብርሀም ሊንከን ሚያዚያ 12ቀን 1865 ኢ.ም ሌሊት ላይ በህልማቸው ወደ አንድ አስከሬን እየተጓዙ ተመለከቱ፡፡ ከዚያ በቀጣዩ ቀን

በነፍስ ገዳይ ጥይት ህይዎታቸው አለፈ፡፡ አንዳንድ ህልሞች ደግሞ ለግኝት እና ለፈጠራ መነሻ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ምሳሌ፡- አርበልታን ስታይል ሪላቲቪቲ (relativity) የተሰኘውን ንድፈ ሀሳቡን ለመንደፍ ያነሳሳው በወጣትነቱ ያያቸው ህልሞች ናቸው፡፡ ሊው ፔጅ ጎግልን ለመፍጠር ህልሞቹ መነሻ ሆነውታል፡፡ አስቲፈን ኪንግ የተባለ ደራሲ ለድርሰቶቹ መነሻ ሀሳቡን ያመነጨው ከህልሞቹ እንደሆነ ይናገራል፡፡ (ምንጭ፡- American psychological Association and American sleep Assocation).

በአጠቃላይ ህልም የአንድን ማህበረሰብ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ ወግ፣ ባህል፣ ልማድ፣ እምነት፣ እሴት፣ ደንብ፣ ስልጣኔ…ወዘተ የመሳሰሉትን እና የሰው ልጅ ያለበትን የዘመን መንፈስ ቅልብጭ አድርጎ የሚሳይ የሃገረሰባዊ እምነት አንዱ ክፍል ነው፡፡ ህልም ከግለሰቦች ማንነት በተጨማሪ የማህበረሰቡን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

## 3.2 የተዛማጅ ጹሁፍ ቅኝት

በዚህ ርዕስ ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከይዘት አንጻር ተዛማጅነት ያላቸው ጹሁፎች የሚዳሰሱበት ክፍል ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ስራዎች በመጀመርያ ድግሪ በባህር ዳር ዩንቨርስቲ የተሰሩ ሶስት ስራዎችን አግኝቻለሁ፡፡ ነገር ግን እስካሁን ባለኝ መረጃ በሁለተኛ ድግሪ የተሰሩ ስራዎች በእየ ዩንቨርሰቲው ባፈላልግ ስላጣው ያገኘዋቸውን ስራዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ የመጀመርያው ማሬ እና ሌሎች ‹‹ሀገረሰባዊ የህልም አፈታት ይዘታዊ ትንተና›› በሚል ርዕስ በንፋስ መውጫ ከተማ በ2004 አ.ም በባህርዳር ዩንቨርስቲ ፎክሎር ት/ት ክፍል ለመጀመርያ ድግሪ ማሟያነት ጥናት የተደረገ ጥናታዊ ጹሁፍ ሲሆን ዋና አላማቸው ህልሞችን እና ፍችዎቻቸውን በመሰብሰብ መተንተን ነው፡፡ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ-መጠይቅ ነው፡፡ የናሙና አመራረጥ ዘዴያቸው አላማ ተኮር ነው፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ መተንተኛ አድርገው የተጠቀሙት አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ የሆኑትን ገላጭ እና ይዘታዊ የመተንተኛ ስልቶችን ነው፡፡ ትንታኔያቸው ከአላማቸው አንጻር ነው፡፡ በጥናቱ መሰረት የተገኘው ውጤትም መጨረሻ ላይ በዚህ ጥናት ሰፍሯል፡፡ ይህ ጥናት ከእነ ማሬ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር የሚያመሳስለው ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ሁለቱም ትኩረት የሚያደርጉት በፎክሎር ንዑስ ዘውግ የሚገኘውን ሀገረሰባዊ እምነት የሆነውን የህልምን አጠቃላይ ሁኔታ የሚመለከት መሆኑ ነው፡፡ ከአላማ አንጻርም በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት አለው፡፡

በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እና በናሙና አመራረጥ ዘዴ በከፊል ተመሳሳይ ነው፡፡ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ላይም ሁለቱም ጥናት አንድ አይነት የመተንተኛ ዘዴን ተጠቅመዋል፡፡ ምንም እንኳን የተወሰነ ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ሰፊ ልዩነት አላቸው፡፡ ጥናቱ ከተካሄደበት ቦታ አንጻር ስንመለከት ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በምስ/ጎጃም በእናርጅ እናውጋ ወረዳ በአራት ታላሚ ቀበሌዎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን የእነ ማሬ ጥናት ደግሞ በደቡብ ጎንደር ንፋስ መውጫ ከተማ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ከይዘት አንጻር ስንመለከተው ይህ ጥናት በይዘቱ ሰፊ ሲሆን ህልም ለተጠኘው ማህበረሰብ ምን ፋይዳ አለው? ህልም ማን ያልማል? ህልም ማን ይፈታል ? ህልም መቼ እና የት ይታለማል? በህልም ውስጥ ገጸ-ባህሪ ሆነው የሚገቡት ምን ምን ናቸው? ፍቻቸውስ ? የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡

የእነ ማሬ ደግሞ ጠቅለል ባለመልኩ በህልሞች ትርጉም እና ፍቺ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ የእነ ማሬ ጥናት የራሱ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ከጠንካራ ጎኑ ስንነሳ ትንታኔያቸው ከአላማቸው አንጻር ለመተንተን ሞክረዋል፡፡ ጥናታቸው እንደሚያመለክተው ብዙ የመረጃ ምንጮችን ለማግኘት እንደለፉ ያመለክታል፡፡ ህልሞችን በመሰብሰብ ጥሩ እና መጥፎ የሚል ምድብ በማውጣት ለአንባቢያን እንዲቀል አድርገው ተንትነዋል፡፡ በጥናታቸው ያገኙትን ግኝት በጥናታቸው መጨረሻ ላይ አስፍረዋል፡፡ እነ ማሬ መረጃ የሰበሰቡበትን ቀን እና ወር በጥናታቸው ውስጥ ማስቀመጣቸው እንደ ጠንካራ ጎን የሚወሰዱ ሲሆን ክፍተታቸውን ስንመለከት ደግሞ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ላይ ስንት አብይ እና ንዑስ የመረጃ ሰጪ እንደመረጡ በግልጽ አላስቀመጡም፡፡ የመረጃ መተንተኛ ቲወሪ አለመጠቀማቸው አንዱ ክፍተት ነው፡፡ መረጃ ትንተና ላይ አንደኛው ንዑስ አላማ ማለትም አራት ንዑሳን አላማዎች ጠቅሰው ሶስተኛው ‹‹በከተማዋ ከሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ህልምን የሚፈቱት እነማን ናቸው? እንዴትስ ይፈቱታል? ›› የሚለውን ንዑስ አላማ ትንተናው ላይ ተግባራዊ አለመሆኑ እንደ ክፍተት ታይቷል፡፡

ለተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ መተንተኛ ዘዴ፣ ለመረጧቸው መረጃ አቀባዮች ከምን አንጻር እንደመረጧቸው በትንታኔያቸው ላይ በህልም ውስጥ ትዕምርት ሆነው የገቡ እንስሳት፤ ቁሳቁሶችን ምክንያታዊ ውክልናቸውን አለማስቀመጥ ችግር በዚህ ጥናት ታይቷል፡፡ ሌሎች ክፍተቶች ደግሞ የተጠቀሟቸውን መጽሀፍት ከማውጫ ላይ አለማስፈር፡፡ ይህ ደግሞ ከሌላው ሰው መረጃ እንደ ሰረቁ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ የመተንተኛ ቲወሪ አለመኖሩ (አለመጠቀማቸው)፣ በአራተኛው ምዕራፍ ማጠቃለያው እና ይሁንታ ሀሳብ ላይ የታዩ ክፍተቶች አሉ፡፡ እነዚህም በማጠቃለያው ላይ ‹‹የጥናቱ ዋና አላማ በንፋስ መውጫ ከተማ

የተሰበሰቡ ህልሞችን እና ፍቻቸውን በመተንተን እና በማደራጀት በጹሁፍ መልክ ሰንዶ በማስቀመጥ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ነው፡፡›› የሚለው ሁለት ችግር አለበት፡፡ አንደኛ ህልም እና ፍቺው ለማህበረሰብ ማስተዋወቅን ይፈጥራል እንጂ ለዛ ማህበረሰብ ህልም ማያነትም ሆነ መፍቻነት ሊያገለግል አይችልም፡፡

ምክንያቱም ህልም ማየትም ሆነ መፍታት በጊዜው የሚለያይ ስለሆነ ነው፡፡ ይሁንታ ሀሳብ ላይ ደግሞ ከላይ በጠቀስኩት ተመሳሳይ የእነ ማሬ ስጋት ህልሞች እና ፍቺዎቻቸው በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ስለሆነ የመረሳታቸው አዝማሚያ ከፍተኛና ሚዛን የሚደፋ ስለሆነ የወረዳው የባህል እና ቱሪዝም ጽ/ቤት ህልሞችን ከነፍቺዎቻቸው ተሰብስበው በጹሁፍ መልክ እንዲቀመጡ የሚል ነው፡፡ ከዚህ አ.ነገር የሚወጣው ሀረግ ቢኖር ‹‹የመረሳታቸው አዝማሚያ ከፍተኛ እና ሚዛን የሚደፋ ስለሆነ›› የሚለው ሀረግ ላይ እንደ ትልቅ ክፍተት አይቸዋለሁ፡፡ ምክንያቱም ህልም እና ፍቺውን ከማህበረሰቡ ውጭ አውጥተው በማየታቸው እና ህልም እና አፈታቱን ከትውልድ ወደ ትውልድ አንድ አይነት (ወጥ) አድርገው በማየታቸው ነው፡፡ ስለሆነም ህልምን ሆነ ፍቺው ማህበረሰብ እስካለ ድረስ እንደማይጠፋ እና የህልም ፍቺ እንደ ዘመኑ ሁኔታ እንደሚለያይ አለማየታቸው እንደ ክፍተት ታይቷል፡፡

ሁለተኛው ጥናት ደግሞ ሽታው ተገኘ ‹‹ የህልም አፈታት ትዕምርት ይዘት ትንተና›› በሚል ርዕስ በሰሜን ሸዋ ዞን አንሳሮና ዋየ ወረዳ በ2007 አ.ም ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የመጀመርያ ድግሪ ክፍል ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጹሁፍ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ ህልሞችን እና ፍቻቸውን በመሰብሰብ ከማህበረሰቡ ልማድ አንጻር መተንተን ሲሆን መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለ-መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይትን ተጠቅሟል፡፡ ትንተናው ከአላማው አንጻር ለመተንተን ሞክሯል፡፡ ሽታው መረጃ ሰጭዎችን ሴት አስራአራት እና ወንድ አስራሁለት ወንዶች በጥቅሉ ሃያ ስድስት መረጃ ሰጭዎችን ተጠቅሟል፡፡ ይህ ጥናት ከሽታው ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የመረጃ መተንተኛ ዘዴው እና የናሙና አመራረጥ ዘዴው ተመሳሳይ ነው፡፡ የክርስትና እምነት ተከታዎችን ለመረጃ ሰጭነት መምረጡ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ የመተንተኛ ዘዴዎች ሁለቱም ጥናት ተመሳሳይ የመተንተኛ ዘዴ ተጠቅመዋል፡፡

በናሙና አመራረጥ ዘዴ በከፊል ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ልዩነታቸው ደግሞ ከጥናት ቦታ አንጻር ይለያያል፡፡ ሽታው በስድስት ቀበሌዎች ጥናት ሲያደርግ ይህ ጥናት ደግሞ በአራት ቀበሌዎች ላይ ትኩረት አድርጎ የተጠና መሆኑ ልዩነት አለው፡፡ ከይዘት አንጻር ይህ ጥናት ከሽታው ጥናት ሰፊ ነው፡፡ የሽታውን ጥናት ጠንካራ ጎኑን ስንመለከት ሽታው መረጃ

የሰበሰበትን ቀን፣ ወር እና አ.ም በግልጽ አስፍሯል። ህልሞችን በምድብ ተንትኖ አስፍሯል። ሽታው በጥናቱ ህልም እና ፍቺዎቻቸውን ከተለያየ አቅጣጫ በመረጃ አስቀምጧል፤ የህልም ፈቺዎች እነማን እንደሆኑ እና የህልም የመፍታት ልማዳቸውን ከየት እንዳገኙት፣ የህልም ገጸባህሪ ተዋናኝ የሆኑትን ነገሮች፣ የህልም አላሚዎችን አጠቃላይ ሁኔታ ከማህበረሰቡ አንጻር ለማየት ሞክሯል።

መረጃ ሰጭዎችን ቁልፍ እና ንዑሳን መረጃ አቀባዮች ብሎ ከፋፍሎ አስቀምጧል፤ ወደ ክፍተቶች ስንመጣ ደግሞ የጥናት ርዕሱ ስህተት አለበት። ምክንያቱም ‹‹በሰሜን ሸዋ ዞን አንሳሮና ዋየ ወረዳ የህልም አፈታት ትዕህርት ትንተና›› የሚለው ከጥናት አካላይ አንጻር መረጃ ለመሰብሰብ ሰፊ ነው። አንዱ ወረዳ እንኳን ከባድ ነው። ሌላኛው ደግሞ ‹‹የህልም አፈታት ትዕምርት ትንተና›› የሚለው ሀረግ ደግሞ ለህልም መፍቻነት የሚውሉ ትዕምርቶች እና ምልክቶችን ያሳየናል እንጂ በህልም ውስጥ ስለሚከሰቱ እና በህልም ውስጥ ስለምናያቸው ትምዕርቶች ስላልሆነ ስህተት ነው። ትክክል ነው ብየ እንዳልደመድም የጥናት ርዕስ መስፋት እና መጥበብ በጥናት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው። እንዳውም ከሁሉም በላይ መስተካከል ያለበት የጥናት ርዕስ ነው። ምክንያቱም ከጥናት ርዕስ በመነሳት አላማውን ልናወጣ ስለምንችል እንዳንምታታ ያግዘናል። በዚህ ጥናት የጥናት የመስክ ተሞክሮ የለውም። መረጃውን የማያ ንድፈ ሀሳብ ባለመኖሩ እንደ ድክመት ታይቷል።

ሶስተኛው ጥናት ደግሞ በዳሳሽ እንዳየሁ ‹‹ የህልም አፈታት ልማድ ›› በሚል ርዕስ በእብናት ወረዳ በ2010 አ.ም በባህርዳር ዩንቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዋና አላማ የህልምን አፈታት ልማድ መግለጽ /መተንተን/ የሚል ነው። ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመችው ቃለ-መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት ሲሆን ለመረጃ መተንተኛነት ደግሞ አይነታዊ ገላጭ እና ይዘታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን ተጠቅማለች። የናሙና አመራረጥ ዘዴው አላማ ተኮር ነው።

የመረጃ መተንተኛ ንድፈ- ሃሳብ ደግሞ የስነ-ፍቺ እና ስነ-ልቦና ንድፈ-ሃሳቦችን ተጠቅማለች። ይህ ጥናት ከዳሳሽ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ሁለቱም ህልምን መሰረት /ትኩረት/ ያደረጉ መሆናቸው ሲሆን ከአላማ አንጻር የተወሰነ ተመሳሳይነት አላቸው። በመረጃ መሰብሲያ ዘዴዎች አጠቃቀም ላይ ተመሳሳይ ሲሆኑ በናሙና አመራረጥ ዘዴ ደግሞ በከፊል ተመሳሳይ ናቸው። መረጃ መተንተኛ ዘዴ ሁለቱም ተመሳሳይ ተጠቅመዋል። የመረጃ መተንተኛ ንድፈ- ሃሳብን ስንመለከት ዳሳሽ ስነ-ፍቺ እና ስነ-ልቦናዊ ንድፈ-ሃሳቦችን

ተጠቅማለች፤ ይህ ጥናት ከተጠቀሱት በተጨማሪ ተግራዊ ንድፈ-ሃሳብን መጠቀሙ ልዩነት አለው።

ይህ ጥናት ከዚህ በላይ የተገለጹትን ጉዳዮች ከዳሳሽ ጥናት ጋር የሚጋራ ቢሆንም ልዩነት አላቸው። ከጥናት ይዘት አንጻር ይህ ጥናት ብዙ ነገሮችን ስለሚያነሳ ከዳሳሽ ጥናት አንጻር ሰፊ ነው። በተለይም ይህ ጥናት አላማ ብሎ ከተነሳበት አላማ አንጻር ስንመለከተው የእናርጅ እናውጋን ማህበረሰብ የህልም እሳቤ መመርመር ከሚለው አብይ እና መነሻ ሃሳብ አንጻር ሰፊ ነው። ጥናቱ ከተካሄደበት ቦታ አንጻር ልዩነት አላቸው። ይኸውም ይህ ጥናት በምስ/ጎጃም ዞን በእናርጅ እናውጋ ወረዳ በአራት ቀበሌዎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን የዳሳሽ የጥናት ቦታ ደግሞ በደቡብ ጎንደር ዞን በእብናት ወረዳ በአንዲት ቀበሌ ላይ ትኩረት ያደርጋል። የዳሳሽ ጥናት ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አሉት።

የጥናቱን ጠንካራ ጎን ስንመለከት ጥናቱ እጥር ምጥን ባለ መልኩ ሳይንዛዛ ተደራጅቶ የቀረበ ሲሆን ከቋንቋ አጠቃቀም እስከ መረጃ አተናተን  ያለው የሃሳብ ፍሰት ጥናቱን የተሟላ አድርጎታል። የጥናቱ አላማዎች እና መረጃ ትንተናው ተመሳሳይነት አላቸው። መረጃው የተተነተነው ከጥናቱ አላማ አንጻር /መሰረት በማድረግ/ ነው። የናሙና አመራረጥ ዘዴ ላይ ስንት አብይ እና ንዑሳን መረጃ ሰጭዎችን እንደመረጠች በግልጽ አስቀምጣለች። ከመረጃ ሰጭዎች የተገኙ ህልሞችን ምድብ ምድብ በማበጀት ከማህበረሰቡ ልማድ አንጻር ተንትናለች። ለጥናቷ መስካት ይሆኑ ዘንድ የተጠቀመቻቸውን  መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች፣ መተንተኛ ዘዴ እና መተንተኛ ቲወሪ ለምን እንደተጠቀመች ምክንያታዊ ሆና አስፍራለች። የዳሳሽ ጥናት ድክመት ደግሞ ጥናቱ የመጨረሻ ግኝት አለመኖሩ እንደ ትልቅ ክፍተት ታይቷል። ሌላው ደግሞ የስነ-ልቦናን ንድፈ-ሃሳብ የት እንደምትጠም አላማው ላይ የለም፤ ከትንተናው ላይም የሚታይ ነገር የለም፤ ነገር ግን የስነ- ልቦናዊ ንድፈ ሃሳብን እንደምትጠቀም በምዕራፍ አንድ ገልጻለች። ያልተቋጩ ሃሳቦች መኖር፤ ደካማ የመረጃ ምንጭን መጠቀም ችግር ተስተውሏል። የቡድን ተኮር ውይይትን ስንት ጊዜ  እና በምን ያህል መረጃ ሰጭዎች እንደተጠቀመች የሚያሳይ አለመኖሩ እንደ ክፍተት ታይቷል ። በአብዛኛው በትንተናው ላይ በቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው  ስለሚታዩ  በጥናቱ የታዩ ክፍተቶች ናቸው።

በአጠቃላይ ይህ ጥናት እነዚህ አጥኝዎች ያልሞሉትን ጉዳይ ለመሙላት ተጠንቷዋል። ያልሞሉት ነገርም ብዙ ነው። ይኸውም ህልም ትንተናቸው ላይ የህልምን ፍቺ ጥቅል በሆነ መንገድ (በአንድ አቅጣጫ) ከልማድ አንጻር ብቻ አስቀምጠውታል። ነገር ግን ህልምን

በተመለከተ ብዙ ጉዳዮች ማንሳት ስለሚቻል ስለዚህ እኔ የማጠናው ይህን ክፍተት ለመሙላት እና ያላዩትን ክፍል ማየት በሚል የተጠና ጥናት ለማድረግ፣ ከእነሱ ተሻለ በቲወሪ የተደገፈ ስራ ለመስራት እና በዋናነት ህልምን የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እንዴት ያዩታል? ህልም ምንን ይወክላል? በውስጡ የያዛቸው ትዕምርቶችስ? ህልም ፈቺዎች እና አላሚዎች መሰረታቸው ምንድን ነው? የህልም ማያ ወሳኝ ወቅት መቼ ነው? የሚሉትን የመሳሰሉትን ጉዳዮች በማንሳት ከማህበረሰቡ አንጻር የተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መቼት፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች፣ የናሙና ዘዴን እና መተንተኛ ቲወሪዎችን በመጠቀም በተለይም ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው አጥኝዎች በአንድ ህልም ውስጥ የታዩትን ትዕምርቶች በአንድ በኩል ያዩዋቸውን ወካይ ትዕምርቶች ከተለያየ አቅጣጫ በማየት የተወሰነ መስራት ችያለሁ፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸው ሶስት ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው እና የሚያለያያቸው ነገር አለ፡፡ የሚያመሳስላቸው ሁሉችም አንዱ የፎክሎር ዘውግ በሆነው በሀገረሰባዊ ልማድ ስር የሚገኘው በሀገረሰባዊ እምነት በህልም ላይ ትኩረት ማድረጋችን ተመሳሳይነት አለው፡፡ ይኸውም ህልምን በመጠቀም ማህበረሰቡ ያለውን አመለካከት እና አስተሳሰብ እንዴት መግለጽ እንደሚችል ለማሳየት መሞከራችን ነው፡፡ የሚያለያየን ደግሞ ሁሉም ጥናቶች ለጥናት የተመረጠው ቦታ (ማህበረሰብ) የተለያየ መሆን ነው፡፡ ከይዘት አንጻር ይህ ጥናት ከሌሎች ጥናቶች ሰፊ ነው፡፡ ጥናቶቹ ጥናት የተደረጉበት ዘመን የተለያየ ነው፡፡ የተጠቀምናቸው መጽሀፍት፣ መሳርያዎች፣ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተወሰነ መልኩ ልዩነት አላቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

በዚህ ምዕራፍ ጥናቱ ስለተጠናበት አካባቢ አየር ጸባይ ፣ ስለሚመረቱ ሰብሎች፣ ስለማህበረሰቡ ቋንቋ እና ሃይማኖት፣ ስለ ወረዳው ስያሜ እና ስለሚያዋስኑት አጎራባች ወረዳዎች እና በውስጡ ስለሚያካትታቸው ቀበሌዎች ብዛት፣ በወረዳው የሚኖረነው ህዝብ ብዛት…ወዘተ የመሳሰሉትን መረጃዎች የሚያካትት ነው፡፡ እነዚህ መረጃዎች እንዲጠቀሱ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ከተጠናው ርዕሰ-ጉዳይ ጋር የሚገናኙ በመሆናቸው ነው፡፡ በተለይም የወረዳው አየር ጸባይ፣ የሚመረቱ ሰብሎች፣ ቋንቋ እና ሀይማኖት ከማህበረሰቡ የህልም አስተሳሰብ እና አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ አፈታት እና ፋይዳ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ ይኸውም ህልም በዚህ ማህበረሰብ ከአየር ጸባይ አንጻር ስንመለከተው ወረዳው በደጋ፣ በወይና ደጋ እና በቆላ የተከፋፈለ ሲሆን በእያንዳንዱ የወረዳው አየር ጸባይ የሚኖሩት ሰዎች የሚከተሉት የአኗኗር ዘይቤ እና የሚመረቱት የሰብል አይነቶች ልዩነት ያላቸው ሲሆን በህልም ውስጥ ያላቸው ሚናም ይህን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ነው፡፡ የወረዳው ቋንቋ እና ሀይማኖትም እንደዚሁ ለማህበረሰቡ የህልም ትርጉም እና ፍቺ ከፍተኛ አገልግሎት አላቸው፡፡ ቋንቋው በህልም ዙሪያ ለሚነሱ ግለሰባዊ እና ማህበራዊ ሃሳቦች የርዕስ በርዕስ መግባባት ለመፍጠር የሚያገለግል ሲሆን ሃይማኖት ደግሞ ማህበረሰቡ በህልም ላይ ያለው እንዳንድ አስተሳሰብ ፣ አመለካከት እንዲሁም የህልም ፍቺ ሀይማኖትን መሰረት ያደረገ ሆኖ ስለተገኘ ነው፡፡

## 4.1 አካባቢያዊ ዳራ

እናርጅ እናውጋ ወረዳ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ጎጃም ዞን ከደብረ ማርቆስ በ116 ኪ.ሜ. ርቀት በሰሜን ምሥራቅ ከክልሉ ዋና ከተማ ከባህርዳር ደግሞ በ187ኪ.ሜ. በደቡብ ምሥራቅ እንዲሁም ከአዲስ አበባ በስተሰሜን በሞጣ ባህርዳር ዋና መስመር ላይ በ291 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ መናገሻ ከተማዋም ደ/ወርቅ ሲሆን የወረደዋ የህዝብ ብዛት በገጠር ወንድ 83 775 ሴት 87 402 ድምር 171 174 በከተማ ወንድ 18806 ሴት 21482 ድምር 40288 በአጠቃላይ 211 465 እንደሆነ ጥናት ያመላክታል፡፡ እናርጅ እናውጋ በ27 የገጠር እና በ4 የከተማ በአጠቃላይ በ31 ቀበሌዎች የተከፈለች ሲሆን የአየር ንብረቷ አብዛኛው ወይና ደጋ (50%)፣ በከፊል ቆላ (20%) እና ደጋ (30%) ነው፡፡ ምቹና ተስማሚ የመሬት አቀማመጥ የሚገኝባት ሲሆን በሰሜን ጎንቻ ሲሶ እነሴ ወረዳ፣ በሰሜን ምዕራብ ሁለት እጁ እነብሴ ወረዳ፣ በምዕራብ ደባይ ጥላት ግን ወረዳ በሰሜን ምስራቅ እነብሴ ሳርምድር ወረዳ በደቡብ እነማይ ወረዳ በደቡብ ምስራቅ ሸበል በረንታ፣ በምስራቅ ደቡብ ወሎ መስተዳር ዞን ያዋስኗታል፡፡የእናርጅ እናውጋ ወረዳ የኢኮኖሚው መሰረት በአብዛኛው

ግብርና ነው፡፡ እናርጅ እናውጋ በ25 የገጠር ቀበሌ በ3 የከተማ ቀበሌዎች በአጠቃላይ በ28 ቀበሌዎች የተከፋፈለች ሲሆን የቆዳ ስፋቱ 9609525 ሄ/ር የሚሸፍን ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለእርሻ የዋለው 350048 ሄ/ር ለግጦሽ የዋለው 2318 ለዳ35 በቋጥቋጦ 5698 ለቤት ግንባታ 3068 ሄ/ር ለእርሻ ጥቅም ያልዋለ 48467.25 ሄ/ር ነው፡፡ የእናርጅ እናውጋ ወረዳ ከምስ/ጎጃም ዞን ብሎም በአማራ ክልል ትርፍ አምራች ወረዳዎች መካከል አንዷ ናት፡፡ ይህች ለሰብል የተመቸ የአፈር አይነት እና የአየር ንብረት ያላት ወረዳዋ ብዙ አይነት ሰብሎችን ታበቅላለች፡፡ ከእነዚህ መካከል ጤፍ፣ ስንዴ፣ ባቄላ እና አተር ዋነኛዎቹ ሰብሎች ሲሆኑ ገበያ መር የሆነውን ቦለቄም በቆላማ ቀበሌዎቿ ታበቅላለች፡፡ ወረዳዋ ከአመት ሶስት ጊዜ ምርት የሚመረትባት ናት፡፡

ወረደዋ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ብሎም መልካም ምድራዊ አቀማመጥ የታደለች ከመሆኗም በላይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ተነስተው የሚፈሱ ወንዞች ባለቤት ናት፡፡ አያልፉሽ፣ ፈላሴና የሶማ በርሃ ታሪካዊ ሰንሰለታማ ተራራዎች፤ በ15ኛው ክ/ዘ የተገነባው የፀሐይ ነገዳ ፍርስራሽ ግንብ፤ በ17ኛው ክ/ዘ የተገነባው የደጅ አዝማች ዩሐንስ ፍርስራሽ ግንብ፤ 348.5 ሄክታር ጥብቅ የፈላሴ ደንና የከረሚት የተፈጥሮ ደን፤ ከዘጠኝ በላይ ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ዋሻዎችና ፏፏቴዎች የሚገኙ ሲሆን ከ90 በላይ አብያተ ክርስቲያናት፤ ገዳማት፤ አድባራት እንዳሏትና ከነዚህም ውስጥ በ333ዓ.ም በአብርሃ ወአፅብሃ እንደተቆረቆሩ የሚነገሩት የእነሚ ደብረ ዘይት ቅ/ሚካኤል ቤተ-ክርስቲያን እና የጎንደሩ ሊቀ ጳጳስ ክርስቶዶል ያረፉባት በአብርሃ ወአፅብሃ የተመሰረተች በቤተ መቅደስነት ታገለግል የነበረች ጸበሏ ቢቀዳ የማይጎል ቢተው ሞልቶ የማይፈስ የአብናሽ ሐና ዋሻ ገዳም፤ የቋሚ ጨርቅ መድሐኒያለም ቤ/ክ፤ የድንጃሜ ማርያም ገዳም፤ ወዘተ በታሪካዊነቷ የምትታወቀው የጥንታዊቷ የ1650 ዘመን ርዕሰ አድባር ደ/ወርቅ ማርያም ገዳም እና የታላቁ የጀር ቅ/ገብርኤል አንድነት ገዳም ቤተክርስትያን የሚገኙባት ናት፡፡ (ወንዳለ፡ 2000)

### 4.1.1 የወረዳው ስያሜ

እናርጅ እናውጋ የሚለውን ስያሜ በተመለከተ ሁለት አይነት አፈታሪኮች አሉ፡፡ በአካባቢው የእድሜ ባለጸጋ አባቶች ታሪክ እንደሚያስገነዝበው የንጉስ ሰሎሞን ልጅ ምኒሊክ እናርጅ እናውጋ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ስራት ጀመረ በኢየሩሳሌም ሥርዓት መሰረት ጃን ድንኳን አስጥሎ ሽማግሌውን ከነገዱ አስጠርቶ ምከሩ ብሎ ከሀገር መልካም መልካም ሽማግሌ የደከመ የሚያርፍባት ሥርዓት የምንሰራባት በአባቶቻችን ልማድ ሊቀ ካህናቱ መስዋዕት አቅርቦ

በኢየሩሳሌም ሥርዓት መሰረት አሁን ጎል /አጥማ/ ተብሎ በሚጠራው ተራራ ላይ መስዋዕት ሰዋባት ከዚህ በኋላ ነገደ ይሁዳ ስላረፉባት እናርጅ እናውጋ ተብላ ተሰየመች ትርጉሙም የማህበር አገር ማለት ነው፡፡ 12ቱ ነገድም መስዋዕት የሚሰውባት ሀገር ሆነች እንደ ኢየሩሳሌም ወግና ታሪክ መዝገብ የሚገኝባት የሽማግሌ ሀገር ማለት ናት የሚለው ቃል ከገዳሟ መዝገብ ተጽፎ ሲገኝ ከአበው በቃል እንደሚነገረው እነዚህ ነገዶች የቦታዋን ውበትና ማማር አይተው እንግዲህ እናርጅ እና እናውጋ ብለው እንደሰየሟት ይነገራል፡፡


ሌላኛው ደግሞ በአፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግስት የልብነ ድንግል ሁለት ሴት ልጆች ወለተ ቅድሳትና አመተ ጊዮርጊስ ወደ አካባቢው መጥተው በመቀመጣቸው የዛሬዋን እናርጅ እናውጋ ለሁለት ከፍሎ የሚያልፈውን የጠዛን ወንዝ በማካለል ከወንዙ በሰተሰሜን በኩል የሚገኘውን እናውጋ የተባለውን መቀመጫቸውን በቀድሞው ጥጥ ሐር በአሁኑ ጢጣር በተባለው ቦታ ላይ ተቀምጠው ከጠዛ ወንዝ እስከ ይዳን ብሎም እስከ አንጀብ ወንዝ ይናጭ እስከ ተባለው ቦታ ድረስ በጉልት ወ/ሮ ወለተ ቅድሳት ልብነ ድንግል ሲገዙ በስተ ደቡብ ያለውን ክፍል ከጠዛ እስከ ዝያ ወንዝ እናርጅ የሚለውን አጠቃላይ መጠሪያ እንደያዘ እናርጅ መስቀል አምባ በተባለ ቦታ ተቀምጠው ወ/ሮ ዓመተ ጊዮርጊስ ልብነ ድንግል ያስተዳድሩ እንደነበርና በእርጅና ጊዜያቸው ይህንን የሁለቱ እህትማማቾች ቆይታ ከእርጅና /ከእድሜ ጫና/ ለልጆቻቸው ለማውረስ በመመካከር ከእንግዲህ አርጅተናል ቁጭ ብለን እናውጋ ሲሉ አጠቃላይ እንርጅ እናውጋ ተብሎ እንደተሰየመ ከአባቶች ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል፡፡ (ወንዳለ፡ 2000)

### 4.1.1.1 የወረዳው ቋንቋ እና ሃይማኖት

ቋንቋና ሀይማኖት ለአንድ ማህበረሰብ የማንነት መገለጫዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ሀይማኖት በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ማህበረሰቦችን ቋንቋ እና ሃይማኖት አንድ በአንድ ለማየት ተችሏል፡፡ በወረዳው ውስጥ የሚኖሩት ህዝቦች ተመሳሳይ ባህል፣ ወግ እና ልማድ ያላቸው ሲሆን ባህላቸውን ወጋቸውን እና ልማዳቸውን መግለፅ የሚችሉበት ቋንቋ አማረኛ ነው፡፡ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝብ የለም፡፡ በእምነቱ ዙሪያ ስናይ ደግሞ በወረዳው የሚገኘው ህዝብ በእምነቱ 97% ኦርቶዶክስ ሲሆን የእስልምናና ሌሎች እምነቶች ተከታዮች ደግሞ 3% ነው፡፡




ስዕል1፡- በምስራቅ ጎጃም ዞን የእናርጅ እናውጋ ወረዳን የሚያዋስኑት ወረዳዎች




ስዕል2፡- የእናርጅ እናውጋ ወረዳ ካርታ በቀበሌ

ምንጭ፡- ከ እናርጅ እናውጋ ወረዳ ኮምንኬሽን ቢሮ

# ምዕራፍ አምስት

# 5. መረጃ ትንተና

ይህ ምዕራፍ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ የህልምን እሳቤ፣ፍቺ እና ፋይዳ በተመለከተ ከተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ የተሰበሰቡ ህልምን የተመለከቱ መረጃዎች በመልክ በመልካቸው የተተነተኑበት ነው፡፡ ስለሆነም ህልም ለተጠናው ማህበረሰብ ያለውን ፋይዳ፣ ህልም ማን እንደሚያልም፣ ህልም ማን እንደሚፈታ፣ ህልም ማያ /ማለሚያ/ ወሳኝ ጊዜያት የትኞቹ እንደሆኑ፣ በህልም ውስጥ ገጸ-ባህሪ ሆነው የገቡ የተለያዩ ትዕምርቶች ያላቸውን ውክልና እና ማህበረሰቡ የሚሰጣቸውን ፍቺ የሚሉትን ጽንሰ ሃሳቦች ያካተተ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከመስክ የተገኙት መረጃዎች ከማህበረሰቡ አመለካከት፣ አስተሳሰብና የህይወት ፍልስፍና አንጻር የተተነተኑበት ክፍል ነው፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ በሚያደርስ አካሄድ በህልም እሳቤ ዙሪያ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመልክ በመልካቸው እንደሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

## 5.1 ለእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ምንድን ነው?

የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እራሱን የቻለ የእምነት፣ የአምልኮ እና የሀይማኖት ተቋማት ያሉት፣ የራሱ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የሆኑ ጉዳዮችን የሚያስተዳድርበት የሚመለከትበት ስልት ያለው፣ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱትን አለመግባባቶች እና ግጭቶች የሚፈታበት ልምድ ያለው፣ በተለያዩ በሽታዎች እንዳይያዝ ቀድሞ የሚጠቀማቸው እና ከተያዙ በኋላ ከበሽታው ለመዳን (ለመፈወስ) የሚጠቀማቸው መድሀኒቶች ያለው፣ ለሚፈራረቁ ቀናት፣ ወራት፣ ዘመናት እንዲሁም ለሌሊት እና ቀን ትርጉም የሚሰጥበት መንገድ ያለው፣ የዘመን አቆጣጠር ያለው፣ በአንድም በሌላም ምክንያት የሚያከብራቸው በአላቶች ያለው፣ እራሱን ለማዝናናት እና ለማስደሰት የሚጫወታቸው ጨዋታዎች ያለው፣ እራሱን የሚገልፁ አልባሳት እና አለባበሶች ያለው ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ነገሮች ባለቤት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ማህበረሰቦች እንደማንኛውም የፎክሎር ቡድን የእኔ የሚሏቸው ብዙ ነገሮች ያሏቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ሎሮች የማህበረሰቡ የህይወት መሰረት ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል ህልም አንዱ ሲሆን በርካታ ትርጓሜዎች ከማህበረሰቡ ዘንድ የሚሰጠው ሀገረሰባዊ እምነት ነው፡፡

ህልም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ትልቅ እና ሰፊ ቦታ ከሚሰጠው ሀገረሰባዊ እምነት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ህልም ለዚህ ማህበረሰብ የኑሮው መሰረት የደስታ እና የሀዘኑ መግለጫ፣ የማጣት

እና የማግኘት ምልክት፣ የእውቀቱ ማሻሻያ እና የክህሎቱ ማዳበሪያ ማህደር፣ የአስተሳሰቡ፤ የአመለካከቱ እና የፍልስፍናው ማሳያ መንገድ፣ የእሴት እና ደንቦች መከሰቻ እና መተግበሪያ ስልቶች በአጠቃላይ ህይወትን የሚመለከት ነገር ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚተገብርበት አንዱ ዘዴ ነው፡፡ ይኸውም ለዚህ አካባቢ የህይወት መግለጫ የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉ የሚመለከት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ማህበረሰቡ በሰፊው የሚያምንበት ጉዳይ ስለሆነ ተግባራዊነቱም የጎላ ነው፤ በተለይም የህልም ምንነት ከማህበረሰቡ አኗኗር ዘይቤ ጋር አብሮ እንደሰም እና ክር የማይለያይ መሆኑ ከማህበረሰቡ የተገኙ የተለያዩ ህልምን የሚመለከቱ ጉዳዮች፣ ትርጉሞች እና ፍቺዎች አሉት፡፡ ከእነዚህ መካከል ከማህበረሰቡ የተገኙ የህልምን ምንነት እና ትርጉም የሚመለከቱ መረጃዎች እንደሚከተለው እንመልከት፡- *‹‹ህልም እንግዲህ በምንተኛበት ሰአት ስጋ ታርፋለች እና በዚያ ሰአት ነፍስ ደግሞ እንቅልፍ አይወስዳትም በዚያ ጊዜ ስለሚታይ አይጠፋም፡፡››* (ቃለ-መጠይቅ፡ አባ ግዛ ደነቀው፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

ሀሳቡ የሚያስረዳው ህልም ከስጋችን ጋር ሳይሆን ከነፍሳችን ወይም አካላዊ ከሆነው ማንነታችን ጋር ሳይሆን መንፈሳዊ ማንነታችን ጋር ጥብቅ ቁርኝት ኖሮት የአላሚውን ማንነት ለማስረዳት፣ ለማስገንዘብ እና ለመግለፅ የሚጥር መንፈሳዊ ተግባር ያለው እንደሆነ ያመለክታል፡፡ በተለይም የአላሚውን የመንፈስ ጥንካሬ ሊያሳይ እና ሊገመግም የሚችል መሆኑን በሰፊው ያሳያል፡፡ ህልም በዚህ ማህበረሰብ አንዳች የሆነ ነገር የሚገልጥበት ነው፡፡

ይኸውም አላሚውን ግለሰብ (ሰው) ለመግለፅ፣ ለመረዳት፣ የሆነ ምልክትን ሰጥቶ እንዲተገብር ለማድረግ፣ ጥልን በፍቅር ለመተካት፣ በሰዎች ዘንድ መግባባት፣ መረዳዳት እና መከባበር እንዲኖር ለማድረግ ይታለማል፡፡ ህልሙ የግለሰቡ ይሁን እንጂ የህልሙ ትርጉም (ፈቺ) ግን ማህበረሰቡን ሊመለከት የሚችል ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ያ ግለሰብ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡም የሚያገለግል ህልም ሊያልም የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ህልም በዚህ ማህበረሰብ እንደፍሮይድ በልጅነት የተደበቁ ፍላጎቶች እና ምኞቶች ማውጫ (የሚገለጥበት) ሳይሆን የማህበረሰቡ የዕለት ከዕለት ተግባር እና እንቅስቃሴ ምን መሆን እንዳለበት መመሪያ የሚያገኙበት ነው፡፡ የፍሮይድ አስተሳሰብ በማህበረሰቡ አይታወቅም፡፡ ህልም በዚህ ማህበረሰብ ሀይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ማህበራዊ ችግርን እና ጉዳዮችን የሚመለከት ስለሆነ አላሚዎችም ሆኑ ህልም ፈቺዎች *‹‹እህ››* ብሎ የሚሰማቸው አይጠፋም፡፡ ህልም እንደየ ደረጃው የአላሚው እና የህልም ፈቺው የደረጃ ሁኔታ ይለያይ እንጂ እምነቱ መታመኑ እንዳለ ነው፡፡ ማን ያለመው ለምን ይሆናል፣ ማን የፈታው

ትክክል ነው የሚለው በማህበረሰቡ በተደጋጋሚ የሚታዩ እና የሚመለሱ ፅንሰ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን ህልም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ከፈጣሪ ጋር የመነጋገሪያ (መገናኛ) ዘዴ እንደሆነ ይታመንበታል፡፡ ህልም ሰዎች ከፈጣሪ የጠየቁትን ጥያቄ መልስ ማግኛ፣ ከማህበረሰቡ የሚያፈነግጡ ሰዎች የሚገሰፁበት፣ ያልወጡት ደግሞ የሚበረታቱበት፣ ወቅታዊ መገለጫዎች ከፈጣሪ የሚላኩበት ማለትም ድርቅ፣ በልግ መሆኑ የሚገለጥበት መንገድ በመሆኑ ይታመንበታል፡፡ ይህን ሃሳብ በተመለከተ ወ/ሮ ዋለ ህልም ማለት ምን ማለት ነው? የሚል ጥያቄ በተጠየቁ ሰአት የመለሱት መልስ እንደሚከተለው ነው፡፡

*‹‹ ህልም እማ በአብዛሀኙ ሰው የሚያየው ስታልሚ በህልምሽ ስታለቅሽ የማይሰማ፣ ስትሮጭ እሩጫው አይጠራቀምልሽ፣ ስትስቂ አይሰማ፣ ስትወድቂ ህመሙ አይታወቅሽ ይኸነው የማትይው ውጥንቅጡ የወጣ ነገር ነው እንዳው ግን አላንዳች ነገር ስለማይታለም ጥቅም አለው፡፡››* (ወ/ሮ ዋለ ገረመው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011አ.ም)

የተገለጸው መረጃ የሚያመለክተው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ማለም የሚችለው አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል የሚያየው እና ለሆነ ግለሰባዊ እና ማህበረሰባዊ አገልግሎት የሚያገለግል መሆኑን ነው፡፡ ህልም በዚህ ማህበረሰብ በእያንዳንዱ ግለሰብ የአስተሳሰብ እና የአመለካከት መንገድ ውስጥ የሚገኝ እና የሚታወቅ እንደሆነ ከመረጃው መረዳት ይቻላል፡፡

> *ህልም በእንቅልፍ ልብ በአብዛሃኙ ሰው የሚታይ ነው፡፡ ግን ስለሰው፣ ስለአዝመራው እና ስለሀገሩ ህልም አልሞ ደረሰለት የሚባል ሰው በእግዛሄር የተመረጠ ሰው ነው፡፡ በእግዛሄር የተመረጠ ሰው ክፉንም ደጉንም ስለሚያሳየው ያልመዋል፡፡ እናም እግዛሄር እኛን ለመገሰጽ በእነዚህ ሰዎች አድሮ ይናገራል፡፡ ህልም በውነቱ ስንኸድ ጥቅሙ ብዙ ነው፡፡ ሲነጋ የሚደርስብሽ መጥፎ ነገር ታለ አሳይቶሽ እንድትጠነቀቂ ያደርግሻል፣ ወደፊት የምታይው ደስታ ታለም ያሳይሻል፡፡ ግን ያለምሽውን ማሰብ እና ማስታወስ ተቻልሽ ነው፡፡* (አቶ ልንገረው ያለው፡ ቃለ-መጠይቅ፣የካቲት 2011አ.ም)

የተጠቀሰው ሃሳብ የሚያመለክተው ህልም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በበብዛት በአይነ ስጋች 4የምናየው ሳይሆን በአይነ ህሊናችን በእንቅልፍ ጊዜ የሚታለም እንደሆነ ሲሆን ህልም በተለያየ ግለሰባዊ ምክንያት የሚታይ ይሁን እንጅ ከዚያ በበለጠ በፈጣሪ ተመርጠው ህልምን የሚያልሙ ሰዎች እንዳሉ ያመለክታል፡፡ ይኸውም የተመረጡት ሰዎች ከራሳቸውም አልፈው ስለአካባቢያቸው አዝመራ፣ከብት እና ሰው ብሎም ስለሀገራቸው ሰላም ሁኔታ እንደሚያልሙ

ያስገነዝባል፡፡ በመረጃው ለማወቅ እንደተቻለው ህልም በሰዎች ላይ የሚመጣውን የወደፊት ጥሩ እና መጥፎ ክስተት የሚያሳይ ሲሆን ይህን ክስተት እንደተፈጸመ ለማወቅ ያለመንን ህልም ተገንዝበን መጠበቅ እንዳለብን ያሳያል፡፡

> *እንግዲህ ህልም የምንለው ስታልሚ በህልምሽ ታብጃለሽ፣ በሰማይ ላይ እንደ አሞራ ክፍ አውተሽ ትበሪያለሽ፣ በሰው ለሊት ሰው ሳያይሽ አቺም የምትሆኝውን ሳታውቂው ስትትከነከኝ፣ በማታውቂው አገር ወስዶ ሲያሳድርሽ፣ አይተሽው ተማታውቂው ሰው ጋር አብሮ ሲያሳድርሽ፣ የሞተበት ዘመኑ ከማይታወቅ የሞተ ሰው ጋር ስያስወራሽ እንዳው ምን ልበልሽ የትግል አለም ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንደዚያ ስንሆኝ አድረሽ ስትነሽ ያለምሽው ህልም የሚያስፈራ ተሆነ እንኳን ህልም ሆነ ትያለሽ፤ ባይሆን ለለቱ ሁኖ አያስጨንቅሽም፡፡* (አቶ በአንተ አምላክ ታደሰ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011ኢ.ም)

ሃሳቡ የሚያስረዳው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም የማይያዝ እና የማይጨበጥ፣ ሲታለም(ሲተገበር) የማይታይ፣ በእውኑ አለም ሲሰራ እና ሲተገበር እንደሚደክም የሚደከምበት፣ ሰውን ያለግብሩ ግብር ሰጥቶ እንደፈለገ የሚያሰራ፣ በሰዎች እና በሰዎች፤ በሰዎች እና በእንስሳት፤ በሰዎች እና በሌሎች፤ በእንስሳት እና በሌሎች ነገሮች መካከል ትውውቅን ፈጥሮ የሚያግባባ፣ እንስሳትን የሚያናግር ሌሎች ማውራት የማይችሉትን እንዲሁ የሚያናግር፣ ከእንቅልፍ ሲነቃ የሚታወስ መጥፎ እና ጥሩ የሚባል ያለው ሲሆን ዘግይቶ የመደርስ እና ወዲያውኑ የሚደርስ ህልም እንዳለ ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ ለጠናው ማህበረሰብ ህልም የአስተሳሰቡ እና የአመለካከቱ መሰረት ሲሆን እንደ አላሚው ማንነት የሚወሰን ነው፡፡ ህልም በዚህ ማህበረሰብ እንደ አንድ የአኗኗር ዘይቤ በመውሰድ ማግኘት፣ ማጣት፣ መደሰት፣ መከፋት፣ ርህራሄ፣ ጭካኔ፣ መውለድ፣ መምከን፣ ማግባት፣ መፍታት፣ መኖር፣ መሞት፣ፈውስ፣ በሽታ…ወዘተ የመሳሰሉትን ጉዳዮች የሚለይበት መንገድ ነው፡፡ ህልም ለተለያዩ የማህበረሰቡ አባል የግለሰብ እንቅስቃሴዎች ምልክት ሰጭ ነው፡፡

## 5.2 በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የህልም መወከያ ትዕምርቶች ምን ምን ናቸው?

በህልም ውስጥ የሚታዩ ህይወት ያላቸው እና የሌላቸው ነገሮች እንደማህበረሰቡ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ የስልጣኔ ደረጃ የተለያየ ውክልና፣ ፍቺ እና ትርጉም አላቸው፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ውስጥ የሚገኙትን ወካይ ነገሮች እንዴት ይገልጻቸዋል እና እያንዳንዳቸው ምንን ይወክላሉ የሚለውን ጉዳይ ከዚህ በታች አንድ በአንድ ተተትነዋል፡፡ ይህ ማህበረሰብ በህልም ውስጥ የሚያያቸው ትዕምርቶች በአብዛኛው በዕለት ከዕለት ህይወቱ ላይ ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ነገሮች ናቸው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ሁለት አይነት ህልሞች አሉ፡፡ አመዳደባቸውም ከአፈታት ሁኔታዎች አንጻር ነው፡፡ እነዚህም የመጀመሪያዎቹ ቀድመው በማህበረሰቡ የተተረጎሙ (የተፈቱ) ሲሆኑ ህልሙ ውስጥ ጥቂት የማህበረሰብ ትዕምርቶችን የያዙ  ህልሞች ናቸው፡፡ እነዚህ ህልምዎች በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በተደጋጋሚ የሚታዩ ሲሆኑ ማህበረሰቡ አንድ ጊዜ በሰጣቸው ፍቺ እየተፈቱ የሚኖሩ ህልሞች ናቸው፡፡

እነዚህ ህልሞች በአንድ ሰው ላይ ከታዩ ህልም ፈቺ ቤት መሄድ አይጠበቅበትም እራሱ ፈቶ ወደፊት የሚሆነውን እና የሚከሰተውን ክስተት ይጠብቃል፡፡ የተወሰኑ ጥቂት ህልሞችን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡ በህልም ባህር መግባት ከተማ ነው፣ በህልም ቀይ ሰው ማየት ታቦት ነው፣ በህልም ገደል መግባት እድሜ ነው፣ በህልም እሳት እና ንፋስ ማየት ምላስ (ልፌት) ነው፣ በህልም ማልቀስ ደስታ ነው፣ በህልም መሞት መጥገብ ነው፣ በህልም እንጨት መልቀም ሲሳይ (ሀብት) ነው፣ በህልም ቅቤ መቀባት ጉንፋን ነው፣ በህልም እርሻ ማረስ መቃብር ነው፣ በህልም ከሚወዱት ሰው ጋር መጣላት ፍቅር ነው፣ በህልም ዛፍ መውደቅ ሞት ነው፣ በህልም ወታደር በሽታ ነው እና  በህልም ጌሾ መውቀጥ ነገር ነው የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሱት ህልሞች ደግሞ በህልም ፈቺ ግለሰብ የሚፈቱ እና የህልም ውስጥ ትዕምርቶች ብዙ ስለሚሆኑ ህልሙ ውስብስብ የሆነ ነው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም አላሚው ሊፈታቸው የማይችሉ እና ውስብስብ የሆኑትን ህልሞዎች የሚመለከት ነው፡፡ በተለይም ከአንድ እና ከሁለት ጊዜ በላይ የማናያቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ህልምዎች ህልም አላሚውን በከፍተኛ ደረጃ ህልሙን ካየ በኋላ ፍቺውን ስለማያውቀው የሚያስጨንቁ፣ ከሌላው

በተለየ ጊዜ ወስደው እንዲያስቡ እና እንዲያሰላስሉ የሚያደርጉ፣ ሰዎች አብዝተው እንዲተክዙ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ናቸው፡፡

## 5.2.1 ምግብ እና መጠጦች በህልም ውስጥ

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ምግብና መጠጦች እራሳቸውን የቻለ በህልም ውስጥ ሚና እና ተግባር አላቸው፡፡ ብዙ ምግቦችና መጠጦች በህልም ውስጥ በጥሩና በመጥፎ የሚፈረጁ (የሚታዩ) አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ከህልም ውጪ ባላቸው አገልግሎት ማለትም በእውኑ ስንበላቸው ከምናገኘው እርካታ ጋር በቀጥታ የሚዛመድ የህልም ውስጥ ተግባር አላቸው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ስንጠቀማቸው ከምናገኘው እርካታ ባነሰ በመጥፎ የሚታዩ አሉ፡፡ ምግብና መጠጦች በህልም ውስጥ ያላቸው አገልግሎት ለአላሚ እና ለህልም ፈቺው ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህ/ትዕምርቶች በአብዛኛው ማህበረሰቡ በተደጋጋሚ አዘውትሮ የሚጠቀማቸው ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ በተደጋጋሚ በህልም የሚታዩትን ምግብና መጠጦች እንደሚከተለው እንመልከት፡-

**1.እንጀራ፡-** እንጀራ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ዘወትር ከሚመገቧቸው ምግቦች ዋነኛው እና ቀዳሚ ምግብ ነው፡፡ እንጀራ በህልም ውስጥ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ አንጻር ስንመለከተው በአብዛኛው ጥሩ ሲሆን በሌላ በኩል በሚታየው መጥፎ የህልም ውስጥ ፍቺ ጉዳቱ ደግሞ ያን ያህል ለአላሚዎች ጭንቀት ላይ የሚጥል አይደለም፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ እንጀራ ለእራስ መብላት፣ መሸከም እና መጋገር መልካምነት ያላቸው ሲሆን እንጀራ በሌላ ሰው መቀማት፣ ሌላ ሰው ማብላት፣ እንጀራ እየጋገሩ ማረር፣ እንደያዙት መውደቅ እና ሌሎች መጥፎ ከሚባሉት የሚመደቡ ናቸው፡፡ ከላይ ያሉትን ሀሳቦች ለማጠናከር ከማህበረሰቡ የተገኙትን የሚከተሉትን ህልሞች እንመልከት፡- አቶ ቢያድጌ ይወጉ፣ ነጋዴ ተስፋየ ደጉ እና ተማሪ ኤርሚያስ ስበር እንጀራን በተመለከት ያለሙት ህልም እንደሚከተለው ነው፡፡

> *በህልሜ ተኝቸ ይመስለኛል እንጀራ እየተጨመረኝ ስበላ ስበላ ከዚያ አባቴ ይመስለኛል አብረን እንብላ ብሎ መጥቶ አብረን እንበላለን፡፡ ከዚያ ጥቁር ሰውየ መጥቶ አብራችሁ አትበሉም ብሎ በቦንብ ሊመታን ሲል ባለቤቴ መጥታ ከኋላችን ሲያያት አንቻ ነሽ እንዲህ የምታደርጊ ብሎ በቦንብ ሲመታት ጣጥቸ ተነሳሁ፡፡ ከዚያ ያንን ህልም እንዳየው ከሁለት ሳምንት በኋላ አባቴ ትንሽ ወረት ሰጥቶኝ ተማሪ እያለው ማውረትረት (የመነጋገድ) ስራ እሰራ ነበር፡፡ የንግዴ ወረትም ሰፍቶልኛል፡፡ ብርም ይዣለሁ፡፡ ከዚያ*

*ጠበንጃ ስገዛ አባቴም ሲገዛ ብር ጎድሎት 25ሺ ብር ስሰጠው ከባለቤቱ ጋር ተጣልተን መርዝ ጠጥታ ሞተች፡፡* (አቶ ተስፋዬ ደጉ፡- ቃለ-መጠይቅ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

የአቶ ተስፋዬ ሌላኛው ህልም ደግሞ በስራዬ በንግዴ ብዙ ጊዜ ያልመኛል በማለት የሚከተለውን ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡ *‹‹በህልሜ እንጀራ እየበላሁ ከአደርኩ፡፡ በበነጋታው አተርፋለሁ፡፡ እንጀራውን እያየሁት ዝም ካልኩኝ ትርፍ አላገኝም፡፡ ልከስርም እችላለሁ፡፡››* (አቶ ተስፋዬ ደጉ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

ሌላኛው መረጃ ሰጪ ደግሞ ህልማቸውን እና የደረሰላቸውን ነገር እንደሚከተለው ተናግረዋል፡፡

*አንድ ቀን ሌሊት በህልሜ ትልቅ ባህር ገብቼ ሰዎች ከባህሩ ውስጥ እያለው ሰዎች እንጀራ ይሰጡኛል፡፡ ተዚያ እናንተ ውሀው ያርስብኛል ስወጣ እበለዋለው እያልኩ እማጠናለው፡፡ እነሱ ግን ብላ ያንተ ነው አይበላሽም ይሉኛል፡፡ እኔም ሲያስጨንቁኝ ከውሀው እያነሳሁ ስበላው በእጀ ስይዘው ምንም ውሀ ያልነካው የነበረ እንጀራ ነው፡፡ እያነሳሁ በላው፡፡ ተዚያ ነቃው፡፡ በሶስተኛው ቀን ከአንባገር ወደ ደብረወርቅ ልጆቸን ልጠይቅ ህጂ ሉተሪ ጥዬ ለእኔ ደርሶኝ በትንሽ ብር ብዙ ብር አገኘው፡፡* (አቶ ቢያድጌ ይወጉ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ኢ.ም)

ተማሪ ኤርሚያስ ስበር ደግሞ ከዩኒቨርስቲ ተመርቆ እንደመጣ ለስራ ቢቸና ሲወዳደር ያየው ህልም እንደሚከተለው ነው፡፡

*‹‹በህልሜ አብረውኝ ከተፈተኑት ተማሪዎች ውስጥ አንዱ ብዙ እንጀራ ይዤ ሲሄድ ስል አንተ ይሄ እንጀራ ለአንተ አይገባም ብሎ አንድ እንኳን ሳይቀር ሁሉን ወሰደብኝ፡፡ ከዚያ ብዙ መልሻለሁ ብየ ተማምኜ ነበር፡፡ ከዚያ እኔ ተጠባባቂ ሆንኩ አብሮኝ የተፈተነው ልጅ ገባ፡፡››* (ተማሪ ኤርሚያስ ስበር፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ኢ.ም)

እንጀራ በህልም መጋገር እንደ ሲሳይ ሲሆን እንጀራ እየጋገሩ ሲያር ደግሞ የሀብት አለመጠራቀምን፣ አለመሟላትን የሚገልጹበት ነው፡፡ እንጀራ በህልም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ቀጥተኛ ትርጉም ያለው ነው፡፡

**2. ዳቦ፡-** ዳቦ በህልም ውስጥ ከእንጀራ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ተግባር አለው፡፡ ዳቦ እንደ እንጀራ ቀጥተኛ የሆነ ትርጉም አለው፡፡ ዳቦ መመገብ ሲሳይ ነው፡፡ ዳቦ መጋገር ስራ ከመያዝ

(ከማግኘት) ጋር ይገናኛል፡፡ ዳቦን ደግሞ ለሰው አሳልፎ መስጠት እንጀራን እንደማጣት ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ዳቦ መመገብ የምንውለውን ቀን ቅኝ አድርጎ ያውለናል፡፡ በተለይም ገቢያ ሲሄዱ፣ ስራ ሲውሉ እቅድን ያሳካል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ዳቦ ሲበላ ያደረ ሰው አስቀድሞ ስለሚያውቀው ሲነሳ ደስተኛ ነው፡፡ ዳቦን በተመለከተ አቶ ነጋ እሸቱ የሚከተለው ህልም እራሳቸው አልመው የደረሰላቸው መሆኑን በማስገንዘብ ህልሙን እንደሚከተለው ተናግረዋል፡፡

*‹‹የሆነ አመት በመንደራችን አካባቢ ዱር ስላለ ድኩላ በጫካው በዝቶ ነበር፡፡ ተዚያ አንድ ቀን ተኝቸ በህልሜ ዳቦ ስበላ አደርኩ፡፡ ተዚያ በበነጋታው ወጥመድ አጥምጄ ከጫካው ነዋሪ የሆኑትን ድኩላዎች ይዤ በላሁ፡፡ በህልሜ ዳቦ በበላሁ ቀን ምንጊዜም ይቀናኛል፡፡››* (አቶ ነጋ እሸቱ፡ *ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011ኢ.ም)

ዳቦ በህልም ውስጥ ስናየው የሚይዘው ሌላ ሚስጥራዊ ተግባር የለውም፡፡ ህልም አላሚው በህልሙ ዳቦን ሲበላም ሆነ ዳቦ ሲጠፋው ቢያይ እራሱ ህልሙን በመፍታት የሚመጣውን ነገር ያውቀዋል፡፡

**3. ገንፎ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ገንፎ ከስንዴ፣ ከገብስ፣ ከበቆሎ ወ.ዘ.ተ ከመሳሰሉት እህሎች የሚዘጋጅ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ በማህበረሰቡ ልጅ ሲወለድ እና ሰርግ ሲሰረግ የሚዘጋጅ ምግብ ሲሆን የሚዘጋጀውም ካልቦካ እህል በማህበረሰቡ አባባል *‹‹ከአዲስ እህል››* የሚዘጋጅ ነው፡፡ ገንፎ በህልም ውስጥ በዚህ ማህበረሰብ አስተሳሰብ እና አመለካከት የተለያየ ትርጉም አለው፡፡ በአንድ በኩል የጥሩ ነገር ተምሳሌት ሲሆን በሌላ በኩል የነገር መምጣትን የችግር መንስኤ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህን በተመለከተ ወ/ሮ ጥሩ ቀለም ባየ እና ርዕሰ ደብር መሪ ጌታ አባተ ንጋቴ እንደሚከተለው በህልሞች የገንፎን ህልማዊ ፍቺ ያሳያሉ፡፡

> *የዛሬ ሶስት አመት አካባቢ ይመስለኛል በህልሜ በቤታችን ውስጥ በሰፊው ገንፎ ተገንፍቶ ዘመድ አዝማድ ተሰብስቦ እየበላ አየሁ፡፡ ተዚያ ያን ህልም ባየሁ በሁለተኛው ወር በልጅነቱ ጠፍቶ የኖረው ልጃችን ሞቷል እየተባለ ሳናስበው መቶ ደስታ በደስታ አድርጎን ያለምኩት ህልም በአየነ ልቦናየ እያየሁት መሆኑን ማመን እስቲሳነኝ ድረስ አሳምኖኛል፡፡ (*ርዕሰ ደብር መሪ ጌታ አባተ ንጋቴ፡ *ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011ኢ.ም)

ገንፎ በህልም መብላት እና እያገነፉ ማየት ከአንባገር ቀበሌ ውጭ የአዲስ እንግዳ መቀበልን፤ ጋብቻን፣ የናፈቀን (ጠፍቶ የኖረን) ሰው ማግኘትን፣ ልጅ መውለድን (አዲስ ልጅ ቤተሰቡን) መቀላቀልን፣ አዲስ ዘመን ሲመጣ ያለፈውን መሸኛ እና አዲሱን መቀበያ መሆኑ ይታወቃል፤ ይታመንበታል፡፡ በአጠቃላይ አዲስን (ያልታየን) ነገር የሚወክል መሆኑን የሚያመለክት መሆኑን በሶስቶች ማለትም በቋሚጨርቅ፣ በወፊት እና በአራራ ቀበሌዎች በተገኘው መረጃ ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከገንፎ አዘገጃጀት ጋር በማገናኘት መጥፎ ጉዳይ የሚወክል እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ስለሆነም በአምባገር ቀበሌ ገንፎ በህልም ውስጥ የመጥፎ ነገር መገለጫ ሆኖ አግኝቸዋለው፡፡ የሚከተለውን ህልምና ፊቺ እንመልከት፡-

> *በህልሜ ይመስለኛል የገንፎ ውሀ በበርሜል ተጥዶ መስክ ላይ (መስቀለኛ መንገድ ላይ) ሲፈላ የተሰበሰበው ሰው ዶጨቱን አስጠግቶ ማን ያማስለው ሲባል እሷ ታማስለው ተብየ የተሰበሰበው ሁሉ ሰው ሲፈርድብኝ በግድ እብይ ስል አሰፋ የተባለው ሰው ማማሰያውን ንሺ ብሎ እሱ ዶጨት እያደረገልኝ እኔ በደንብ እያጦልኩኝ ሲበስል መብሰልና አለመብሰሉን እኔው ቀመስኩት ተዚያ በኋላ ሌላው ሰው እንደአቅሙ ተሰቶ በላ ተዚያ ብንን አልኩኝ፡፡ ተዚያ ሳምንት ባልሞላ ቅዳሜ ቀን ከመስክ ላይ አንድ ሰው ተገሎ ተጥሎ አድሮ በግና ፈረስ ከቤት አስወጥቸ ሳሰማራ አግኝቸው እዛው ሆኜ ስጮህ ሰው ተሰበሰበ ከእኛ በላይ ካለ መንደር የመጣ ስለሆነ ማወቅ አልቻልንም፡፡ ተዚያ ፎሊስ ተጠራ፡፡ ተዛ ከላይ መንደር ሰው ተላከ ቤተሰቦቹ መጡ፡፡ አጋጣሚ ሆኖ የፈታሁት ባሌ ቅርብ ዘመድ ሆኖ እኔን ሊማልደኝ ሁለት ሶስት ጊዜ ተመላልሶ እምብኝ ስለው ሰድቦኝ ሄዶ ነበር፡፡ ተዚያ ማን ነው መጀመርያ ያገኘው ተብሎ ሲጠየቅ እኔ ስሆን ባሌ እና ወገኖቹ እሷ ናት ያስገደለችው፤ እንዴት በማለዳ መታ አገኘችው ልታየው ነው የመጣች ብለው በእኔ ፈረዱ፡፡ ባላየሁት ባልሰማሁት ነገር ብዙ ሲቃይ ደርሶብኛል፡፡ ተዚያም ፎሊሶቹ ብዙ ነገር ቢያደርጉኝም አንድ ሆነ መልሴ ተዚያ መፍትሄ ሲያጡ በመንደሩ ገቡ እያንዳንዱ ሰው በየቤቱ አሰቃዩት፡፡ ሁለት ወር ሙሉ የገደለው እስቲታወቅ ድረስ መሰቃየቱን አረሳውም፡፡ ገንፎ በህልም ሲታይ የጦለ ነገር ይገጥማል፡፡ አሰፋ ማለት ደሞ ሀገር ሲሆን ያለው የመንደሩ ሰው መረበሽን ያመለክታል፡፡* (ወ/ሮ ጥሩ ቀለም ባየ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

ገንፎ በህልም ሲታይ ሁለት አይነት ፍቺ አለው፡፡ አንደኛው ከምግብነቱ ከሚዘጋጅበት ነገር የሚነሳ ፍቺ ሲኖረው ሌላኛው ደግሞ ከአሰራሩ (ከአዘገጃጀቱ) በመነሳት የሚፈረጅ የምግብ

አይነት ነው። ስለዚህ ገንፎ እንግዳ (አዲስ) እህል ስለሆነ የናፈቀን ዘመድ ልናገኝ ስንል፣ ልጅ ሊወለድ ሲል፣ አዲስ ተጋቢዎች ሊጋቡ ሲሉ የሚታይ ህልም ላይ የሚታይ ትዕምርት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ገንፎ እያጦሉ የሚሰራ ሲሆን ገንፎ በህልም ሲታይ የጦለ ነገር ይመጣል ተብሎ ይታሰባል።

**4. ማር፡-** ማር በጣም ጣፋጭ ሲሆን በመጠጥ መልክና በምግብ መልክ የምንጠቀመው ነው። ማር በመጠኑ ካልበላነው ጥሩ አይደለም። ከጣፋጭነቱ ብዛት የተነሳ የብዙ በሽታ መድሀኒት ቢሆንም በበሽታዎች ለመያዝም መንስኤ ነው። ማር ከከባድነቱ ባሻገር ሲበሉት ሆድን የሚነፋ ስለሆነ ጥቂት መጠቀም እንዳለብን ይመከራል። ማር በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ሲበላ እና ሲሸከም ሲታይ ከባድ ነገር እንደሚገጥም ይታመናል። ስለማር በህልም ውስጥ ያለውን ተግባር ወ/ሮ ሁልዬ እንዳላማው እንደሚከተለው ገልጻለች።

> *በህልሜ ይመስለኛል የሚያምር ማር በሳህን አድርጌ እኔው ደፋ ደፋ እያልኩ አምሮት ያለብኝ ይመስለኛል ደብቂ እየጨመርኩ ጥርግ አድርጌ እስቲበቃኝ ድረስ በላው። ተዚያ በሶስተኛው ቀን ችዳነ-ምረትን አከብር ነበር ተዚያ እረስቸው ውሀ ስቀዳ ተሸክሜ ወደቤት ስኼድ ያናቀፈኝን ሳላውቀው ወድቄ ገደል ተንከባልየ ግራ እጄን እንስራው ወድቆብኝ በወጌሻ ብታሽም ስላልተስተካከለ እስከ አሁን ድረስ ስራ አልሰራም። እጄም የተጧነዘ ሆነ። ህመሙም ብዙ ወራት አማቆኛልና ግን አልተስተካከለም። አሁንም እንደልቤ አልንቀሳቀስም ጤናየ ይሰማኛል።* (ወ/ሮ ሁልዬ እንዳላማው፡ *ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011ዓ.ም)

የተጠቀሰው ሃሳብ የሚስረዳው ማር በህልም ሲታይ እንደሁኔታው በአላሚው ወይም በሌላ ሰው ላይ ከባድ ነገር እንደሚመጣ ነው። ማር በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ሁለት አይነት ህልም ውስጥ ትረጉም እና ፍቺ አለው። ይኸውም ማር በህልም መብላት፣ መሸከም፣ መቀባት...ወዘተ የመሳሰሉ ድርጊቶች በህይወት ላይ ከባድ ነገር ሊመጣ እንደሆነ ይገመታል። በሌላ በኩል ደግሞ በህልም የተሸከሙትን ማር ማውረድ፣ ሳይበሉ መተው፣ ለሌላ ሰው መስጠት ማቀበል ሊደርስብን ከነበረው ከባድ ነገረ (አደጋ) ማምለጥ ተደርጎ ይቆጠራል።

**5. ስጋ፡-** ስጋ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ከእንስሳት ተዋጽኦ የሚገኝ በጥሬው (ሳይበስል) እና አብስለን የምንበላው ምግብ ነው። ስጋ ከቤት እንስሳት ከበሬ፣ ከላም፣ ከፍየል፣ ከበግ፣ ከዶሮ የሚገኝ ሲሆን ከዱር እንስሳት ደግሞ ከሰሳ፣ ከድኩላ፣ ከቆቅ ወ.ዘ.ተ. ከመሳሰሉት

የሚገኝ ነው። ስጋ በህልም ውስጥ ሲበላ፣ ሲሸከም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ *‹‹ስጋት››* ሲሆን በሆነ ነገር መስጋትን ያመጣል። መጠራጠርን በአንድ ነገር ላይ እርግጠኛ አለመሆንን የሚያመጣ ነው። ስጋ በህልም መታየት በአንድ ሰው ላይ የስጋት መንፈስን የሚያመጣ ነገር እንደሚሆን ይታወቃል። ይህን ሀሳብ በተመለከተ የአቶ ነጋ እሸቱን ህልም ፍቺ እና እንዴት እንደደረሰ የሚያይ መረጃ እንደሚከተለው ነው።

> *ተኝቼ ይመስለኛል በህልሜ ተዋርካ ዛፍ ቅርጫፍ ላይ ስጋ እየፈለፈልኩ (እየቆረጥኩ) እየበላሁ እያለ አንድ ቀይ ሰው መቶ አንተ እንግዲህ ይበቃሀል ስጋው አልቋል ጊዜውም እየመሸ ነው ሀደህ ሸፍን ብለህ ተኛ አለኝ። እኔም ኧረ ጠግቢያለሁ ብየ ተኛሁ። ተዚያ ነቃሁ። በህልሙ ፊች የደረሰልኝ አንድ ሴት ልጅ ነበረችኝ አግብታ ስትወልድ እየሞተባት እሷም እኛም እያዘን መቼም ሰው ተስፋ አይቆርጥም አረገዘች። እኔ አይ ሁልጊዜ ልጇን እያሰቀቃት ብየ እጅጉን እያሰብኩ ተስፋ የለኝም። ደሞም ምጧ ጠንካራ ነው። አሁንስ ብሎ ብሎ እሷን እንዳይወስዳት እያልን እኔም እናቷም እሷ ስታረግዝ እኛ ያረገዝን እስቲመስለን ድረስ ተጨንቀን ተጠበን ተዚያ አንድ ቀን የአስተርዮ ማርያም አመትባል ሀደን በሌለንበት ወልዳ ተገላግላ አገኘናት። ልጁም በህይዎት እስታሁን ድረስ አለ። አድጓል። ዋርካ ዛፍ እኔ ነኝ ቅርንጫፍ ደግሞ ልጄ ናት። ስጋም በልጄ ላይ ያለኝን ስጋት የሚገልጥ ነው። ቀይ ሰው ደግሞ በመላክ ይመሰላል። ስለዚህ ሁሉም ነገር ትርጉም አገኘ፤ አለው።* (አቶ ነጋ እሸቱ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኣ.ም)

ስጋ በህልማችን ተሸክመንም ሆነ እየበላን ካደርን ወደፊት ይመጣብናል ብለን የምናስበውን የስጋት ስሜት፣ ያደረብን የስጋት ሀሳብ የምናወጣበት መንገድ እንደሆነ ከመረጃ ሰጭዎች የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

6. **ጎመን፡-** ጎመን ከአትክልት እና ፍራፍሬዎች አንዱ ሲሆን ለእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ውስጥ ሚና ካላቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው። ጎመን የሲሳይ ምልክት፤ የጥሩ እድል ምልክት ነው፤ የማግኘት ምልክት ነው፤ የጤንነት ምልክት ነው፤ የደስታ ምልክት ነው። በአጠቃላይ ጎመን በህልም ሲቀረድዱ (ሲከትፉ) ሲበሉና ሲሰሩ ከታዩ ጥሩ ነገርን የምናገኝበትና የምናይበት መሆኑን ከተጠኘው ማህበረሰብ የተገኘው መረጃ ያመለክተናል። የሚከተለውን ህልም እና ፍቺ እንመልከት፡-

*በህልሜ ተቤት በታች ያለው ጓሮ በሙሉ ተዳር እስተ ዳር ጎመን ተዘርቶ ይመስለኛል የእኛ መንደር ሰው እየነቀለ ይበላል። እኛም እያመጣን የበልግ ጎመን እያልን እየበላን አየሁ። ተዚያ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መችና መንገዱ አስፋልት ሊሰራ በእኛ ላይ ተቀይሶ መጥቶ ባህር ዛፍ ያለው በባህርዛፉ፣ መሬት ያለው በመሬቱ ተቆርጦ እና ተቆርሶ ለዚያ ምትክ ብዙ ሺ ብር ተሰጠን ቤታችንን አሻሽልን ሰራን ከተማ ቦታ ገዛን።*
(አቶ ተሾመ ከበደ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

ከላይ ያለው ሃሳብ የሚያስረዳው ጎመን በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የሲሳይ፣ የሆነ ነገር (መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ደስታን የሚሰጥ) የማግኘት፣ ጸጋን መጎናጸፍ፣ ሃብት ማፍራትን፣ በህይወት ሲኖሩ ትርፋማ መሆንን ያስረዳል። ነገር ግን ጎመን ይህን ብቻ የህልም ውስጥ አገልግሎት እንደሌለውም መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ። ይኸውም ጎመን በህልም ውስጥ አሉታዊ መግለጫ ሲሆን ጎመን በህልም ተጥዶ እየበሰለ ሲያር ማየት፣ በህልም በሌላ ሰው መቀማት፣ በህልም ጎመን ብለው በእጅ ሲይዙት ወደ በርበሬ እና መሰል ነገሮች ሲቀየር ከታየ የህልሙ ፍቺ እና አደራረሱ መጥፎ እንደሆነ በማህበረሰቡ ይታመናል።

**7. ብቅል፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ብቅል በአብዛኛው ለጠላ እና ለአረቂ የሚሆን ከስንዴ እና ከገብስ የሚዘጋጅ ነው። ብቅል እነዚህን ሰብሎች በውሀ ነክሮ በማብቀል የሚዘጋጅ ነው። ብቅል በተጠኚው ማህበረሰብ እራሱን የቻለ በህልም ውስጥ ፍቺ እና ተግባር አለው። ይኸውም ብቅል ማብቀል ከማርገዝ (ፅንስ ከመፀነስ) ከመውለድ ጋር ይያያዛል። በሌላ በኩል ደግሞ ብቅል መፈርፍር ደግሞ የልጅን ሞት ያመለክታል። ምክንያቱም ብቅል ሲበቀል ስንዴው እና ገብሱ የመብቀል ምልክት ያሳያል። ስለዚህ በህይዎት መቀጠልን እና መኖርን ያመለክታል። ይኸውም ብቅል በህልም ማብቀል እንደህጻናት መወለድ ተደርጎ ይቆጠራል። በዚህ ማህበረሰብ ህጻናትን ከብቅል ጋር የማገናኘቱ ሃሳብ ያለው ህይወትን ከአጀማመር አንጻር ሲሆን ህጻናት እና ብቅል የሚያመሳስላቸው ነገር አለ። ይኸውም እንደማህበረሰቡ እምነት ብቅል የሚባለው እህሉ መብቀል ሲጀምር የሚያሳየው (የሚያውጣው) ቅጠል መሰል ነገር ለእህሉ ህይወትን እንደመጀመር የሚታይ ሲሆን ህጻናትም የሰው ልጅ የመጀመሪያ የህይወት ደረጃ ማሳያ እንደሆኑ ማመልከቻ ነው በማለት ይገልጻሉ። በተቃራኒው ደግሞ ብቅልን መፈርፈር የበቀለውን ማጨናጎል (እንዳይበቅል ማድረግ) ስለሆነ መብቀል የጀመረው (ያጨፈጨፈው) ስለሚቋረጥ ይደርቃል፣ አያድግም ማለት ነው። ይህ ደግሞ የህጻናት መሞት ተደርጎ ይቆጠራል። ይህን በተመለከተ እማሆይ ባሳዝን ሙኔ የሚከተለውን ህልም ተናግረዋል።

*አንድ ቀን በህልሜ የኖረ የራሴ ብቅል ከብቅል ቆጡ እያወረድኩ እየፈረፈርኩ ሳሰጣ ሳሰጣ አደርኩ ተዚያ በበነጋታው ጨንቆኝ እማሆይ የዝና ላይ ሄጄ ነገርኳቸው። ተዚያ እሳቸውም በተ-ስኪያን እየኸድሽ ጠልይ ክፉ ህልም ነው አሉኝ። ተዚያ የመጀመርያ ልጄ ተእኔ እህት ቤት ሰርግ ሀዶ በተባረቀ ጥይት ልጆቹን እርግፍ አድርጎ ሞተ።* (እማሆይ ባሳዝን ሙኔ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

ብቅል በተጠኘው ማህበረሰብ ሁለት አይነት ትርጉም አለው። አንደኛው ጥሩ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በመጥፎ የሚፈረጅ ነው። ጥሩው ብቅል ማብቀል ሲሆን ፅንስ ከመፀነስ፣ ከማርገዝ እና ከመውለድ ጋር ይያያዛል። ሌላኛው ደግሞ ብቅል መፈርፈር ሲሆን የልጅን ሞት እንደሚያመጣ ይታወቃል። ይኸውም ብቅል መብቀል እና ማጨፍጨፍ ላይ ያለን እህል የሚመለከት (የሚገልጽ) ስለሆነ ልጆችም ገና አድገው ያልጨረሱ፣ በማደግ ላይ ያሉ ስለሆነ በዚህ ይመሰላል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ።

**8. ጠላ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ጠላ ከጌሾ፣ ከብቅል እና ከደረቀት የሚዘጋጅ መጠጥ ነው። ጠላ እራሱን የቻለ የአዘገጃጀት ስልት ያለው ሲሆን የጊዜ ገደብና ያመጣጠን (የልኬታ ስራ) ያለበት ነው። ጠላ በዚህ ማህበረሰብ በብዛት ይደረጋል፤ ይጠጣልም። ጠላ በተጠኘው ማህበረሰብ ከሚዘጋጅበት ጥሬ እቃ እና ከሚኖረው ጣእም በመነሳት በህልም ውስጥ ያለው ተግባር አሉታዊ ነው። ይኸውም ጠላ መጠጣት እንባ ነው። ነገር ግን ጠላን በህልም ሌላ ሰው ቀድቶ መስጠት እና እራስ አለመጠጣት የሚኖረው እንባ ለሌላ ሰው ይሆናል በማለት አወንታዊ ገጽታ እንዳለውም ይገልጻሉ። ይህንን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ልንገረው ያለው የሚከተለውን በህልሙ ያየውን መረጃ ሰጥቷል።

*በህልሜ ብዙ ጠላ ደጋግሜ ከጠጣው የቅርብ ዘመድ ይሞትና ብዙ አለቅሳለሁ። ግን ትንሽ ጠላ (አንድ ብርጭቆ) ከጠጣሁ የሩቅ ዘመድ ወይም ባዳ ይሞታል። እናቴ ስትሞት በህልሜ ይመስለኛል ላም ተይዛ ተእኔ ቤት አጠገብ ተይዛ ሰው ከቦ ሌላው ሰው ብዙ ሳይጠጣ ለእኔ ብዙ ደጋግመው ሰጡኝ ለምን እናንተስ ድገሙ ያልኩኝ እንደው አንተ ላሚቱን ስለምትገፍ እንድትጠነክር ብለን ነው ይሉኛል። እና ደጋግመው ሰተውኝ እየጠጣው ብንን አልኩኝ። ተዚያም እናቴ በጠና ታማ ነበር በበነጋታው ሌሊት ላይ ሞተች። ያማወትኳትም እኔ ነኝ።* (አቶ ልንገረው ያለው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

የተገለጸው ሃሳብ የሚያመለክተው ጠላ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የሆነ ሃዘን ደርሶ ሰዎች እንባ እንደሚያነቡ ሲሆን የአለቃቀሱ እና የእንባው መጠንም በህልማችን በጠጣነው ጠላ ልክ እንደሚውሰን ነው፡፡

**9. አረቄ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ አረቄ እንደ ጠላ ሁሉ ከገብስ እና ከስንዴ ብቅል እንዲሁም ከጌሾ የሚዘጋጅ ውሀ የሚመስል ቀለም አልባ መጠጥ ነው፡፡ አረቄ በዚህ ማህበረሰብ በሰፊው ይወጣል፡፡ አረቄ ከበዛ ሰዎችን የማስከርና ከአልባሌ ቦታ ላይ እስከመጣል ሊደርስ ይችላል፡፡ ሱስ ሊሆን የሚችል ቆምጣጣ ጣዕም ያለው መጠጥ ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በመጠን (ለክትን) ከተጠቀምነው የተለያዩ የሆድ ውስጥ ጀርሞችን እና ትላትሎችን የመግደል አቅም ያለው ነው፡፡ አረቄ በማህበረሰቡ ለደስታ ማለትም ለልደት፣ ለቤት ስራ፣ ለሰርግ፣ ለምርቃት፣ ዘመድ መጠየቂያ ወ.ዘ.ተ ለመሳሰሉ ነገሮች የሚቀርብ እና የሚሆን መጠጥ ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ አረቄ በህልም መጠጣትም ሆነ ማውጣት (ማዘጋጀት) ነገር እንደሚገጥም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እንደ ጥል እና ብጥብጥ አይነት ግጭቶች ይፈጠራሉ በሚል ይፈርጁታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አረቄ በህልም አለመጠጣት፣ መድፋት፣ ለሌላ ሰው መስጠት እራስን ከክፉ ነገር እንደመዳን ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ አረቄን በህልም ማየት ምን እንደሚመስል አቶ ባወቀ ምሳሌ የሚከተለውን ብሏል፡፡

> *ባለፈው ክረምት ዘር መዝርያው ወቅት ላይ ዘር እየዘራን እያለ ሌሊት ተኝቸ ከወንድሜ ጋር አንድ ጠርሙስ አቅርበን ተእኔ ቤት አንተ እንካ አንተ እንካ እየተባባልን ስንጠጣ አየሁ ተዚያ ብንን አልኩ፡፡ በበነጋታው የእኔ ደቦ ሆኖ ጤፍ እየዘራን አጋጣሚ ከባለ ድንበርተኛችን ጋር ተጣልተን ዱላ ሁሉ ደርሰን ተካሰን እንደገና ታረቅን፡፡* (አቶ ባወቀ ምሳሌ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

አረቄ በህልም መጠጣት እና ማውጣት ከጥቃቅን ግጭቶች እስከ ትልልቅ ቅራኔዎችን የሚወክል ነው፡፡ አረቄ በጣእሙ ጣፋጭ ሳይሆን ቆምጣጣ ስለሆነ ጥሩነቱ ያን ያህል አይይለም፡፡ ከዚህም በነሳት ማህበረሰቡ በህልሙ አረቄን ሲያይ በጥሩ አይተረጉመውም፡፡

**10. ቆሎ፡-** ቆሎ በተጠናው ማህበረሰብ ከስንዴ፣ ከገብስ፣ ከጠበርባሬ፣ ከማርዴ (ከጥቁር ገብስ)፣ ከማሽላ፣ ከቦቆሎ ወ.ዘ.ተ የሚዘጋጅ ምግብ ነው፡፡ ቆሎ ከስሙ እንደምንረዳው በብረት ምጣድ ላይ በመቁላት የሚዘጋጅ ሲሆን የሚቆላው የእህል አይነት የነበረውን መልክ፣ ሽታ፣ መጠን በማጣት ወደ ሌላ ወደ አዲስ ማእዛ፣ ሽታ፣ መጠን፣ መልክ በመቀየር የምናገኘው

ምግብ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ስራ በህልም ሲሰራ ከታየ (ከታለመ) በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ራሱን የቻለ ትርጉም እና ፍቺ አለው፡፡ በተለይም በህልም ቆሎ መቁላት በሽታ ነው በማለት ይፈርጁታል፡፡ ወ/ሮ ጥሩ ቀለም ባየ ዘወትር ሊያማት ሲል የሚታያትን ህልም እንደሚከተለው ገልጻለች፡፡

> *በህልሜ ቆሎ እየበላሁ ሳድር በበነጋታው እታመማለሁ፡፡ በተለይም አንድ ጊዜ ያለምኩት የማረሳው ህልም ከባድ ነበር፡፡ በህልሜ ይመስለኛል ብዙ የገብስ ፍትግ (የተፈተገ) ለሰርግሽ እየተባልኩኝ እስኪደክመኝ ስቆላ ስቆላ አደርኩ፡፡ በሌላው ቀን ህልሙን አልሜው ሳልሰነብት ተስካር ሌማት ይዘን በሄድንበት ሀገር በሀር ሆዴን ጠልቶ ጥሎኝ ከሰዎች ቤት በወሴካ መጥቶ እየሞትኩኝ በእየጠበሉ እና በየሃኪሙ እሬሳየን ይዘው እየዞሩ ብዙ ቀን ታምሜ የዘር አቡርክ ጠበል ጠጥቼ ዳንኩኝ፡፡ ተሞት አፋፍ ተረፍኩ፡፡* (ወ/ሮ ጥሩ ቀለም ባየ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

ከላይ ያለው መረጃ የሚያሳየው ቆሎ በህልም ሲቆሉ ማየት በበሽታ ተይዘን የነበረው ማንነታችን ወፍራም ከነበርን ከስተን፣ የነበረው መልካችን ተቀይሮ፣ የነበረው አቋቋም እና አካሄዳችን ተቀይሮ፣ ጥንካሬያችን አጥተን፣ ደክመን ….ወዘተ በጤንነታችን የነበሩን ጥሩ ነገሮችን እንደምናጣ የሚያመላክት የህልም ፍቺ አለው፡፡

**11. ጥሬ (ንፍሮ)፡-** በተጠናው ማህበረሰብ ጥሬ (ንፍሮ) ከባቄላ፣ ከአተር፣ ከቦቆሎ፣ ከሽብራ፣ ከምስር ወ.ዘ.ተ ከመሳሰሉት የእህል ዝርያዎች በመቀቀል የሚዘጋጅ ነው፡፡ በአብዛኛው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በቆሎ እና ባቄላ የተለመዱ ለንፍሮ የሚዘጋጁ እህሎች ናቸው፡፡ በተለይም በህልም ውስጥ ባቄላ ሲቀቀል ከታየ ቀጥተኛ የሆነ ፍቺ በአላሚው እና በህልም ፈቺው ይሰጠዋል፡፡ በህልም ጥሬ መቀቀል ሞት እንደሆነ ከተጠኘው ማህበረሰብ የተገኘ መረጃ ያስረዳናል፡፡ ይህን በተመለከተ ቄስ ሙሉቀን ተገኝ የሚከተለውን የህልም ማስረጃነት ሰጥተዋል፡፡

> *የመንደራችን አሉ የተባሉ ሽማግሌ ሲሞቱ (ሊሞቱ ሲሉ) ታመው እያለ በህልሜ ተከብት መዋያው በትልቅ ቤርሜል ንፍሮ ተጥዶ እሳቸው ተሞሽረው አግብተው ተብለው ህዝቡ ተሰብስቦ ጥሬውን እየበላን እኩሉ ይፎክራል፣ እኩሉ ያቅራራል፣ የሚደልቅ (የሚጨፍርም) አለ፤ ሴቶች ይዘላሉ በዛ መስክ ሰው ጢቅ ብሎ ሞልቶ*

*እሳቸው ወደየት እንደተሸኙ ሳላያቸው ብንን አልኩኝ፡፡ ተዚያ በአምስተኛው ቀን ሞተው ተቀበሩ፡፡* (ቄስ ሙሉቀን ተገኘ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

ንፍሮ በተጠኘው ማህበረሰብ የህልም እሳቤ ቀጥተኛ ትርጉም አለው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ አካባቢ ባለፈ ራቅ ካለ ቦታ ሰው መሞቱን የሚያውቅት ከሞተበት አካባቢ ጭስ ቀሲጨስ ሰው ሙቶ ንፍሮ እየተቀቀለ መሆኑን ይረዳሉ፡፡ ስለሆነም ንፍሮ ከሌላው በተለየ መልኩ ያለው ተግባር ለማስተዛዘኛ (የዝን) ለመቃብርተኛ ቀብሮ ሲመለስ *‹‹ነፍስ ይማር ብሎ››* የሚበላው በመሆኑ ሌላው ተግባሩ ከዚህ በበለጠ ጎልቶ የሚታይ አይደለም፡፡

**12. ወተት፡-** ወተት ከእንስሳት ተዋጽኦ የሚገኝ ነው፡፡ ከወተት ቅቤ፣ አይብ እና እርጎ ይገኛል፡፡ ቅቤ እና አይብ ለማግኘት ወተቱ መገፋት አለበት፡፡ ወተት የሚገፋውም በእንስራ ወይም በቅል በማድረግ በመወዝወዝ (በመግፋት) ነው፡፡ ይህ ተግባር ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ተግባሩ የተለመደ ይሁን እንጂ ወተት በህልም መግፋት ነገር እንደሆነ ይታመንበታል፡፡ ይኸውም ወተት ነጭ ሲሆን ነጭ ነገር ደግሞ በጥሩ (የፀጋ) ምልክት ስለሆነ ፀጋን እንደመግፋት፣ ሲሳይን እንደማጣት ይቆጠራል፡፡ ሌላው ደግሞ ወተት ንፁህ ጥርት ያለ ነጭ ስለሆነ ንፅህናን እንደመጋፋት ተደርጎ ከመቆሸሽ ከሀጢያት ጋር ከመበደል ጋር ያያይዙታል፡፡ ወ/ሮ የሮም ደመቀ በህልማቸው የታያቸውን እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

*‹‹ተኝቼ በህልሜ በትልቅ እንስራ ወተት ስገፋ አደርኩ፡፡ ተዚያ ተጣልተን ተማናውቀው የኖርን ጎረቢታሞች በአሉሽ አሉሽ ወሬ ተጣልትን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰን እስካሁን ልብ ለልብ ሳንገኛኝ አብረን ሳንበላ እስታሁን አለን፡፡››* (ወ/ሮ የሮም ደመቀ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

የተገለጸው ሃሳብ የሚያስረዳው ወተት በህልም ሲገፋ የነበረን የፍቅር፣ የሀብት፣ የንፅህናን ፀጋ እንደማጣት በመቁጠር፣ ጥልን፣ ንትርክን፣ ብጥብጥን፣ አለመስማማትን የሚገልጽ መሆኑን ነው፡፡

**13. ውሀ፡-** ውሀ ከሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ውሀ ለብዙ አገልግሎቶች የሚውል ሲሆን ለምግብ ማብሰያነት፣ ለመጠጥ፣ ለንጽህና መጠበቂያነት፣ ለቤት መስሪያ ወ.ዘ.ተ ለመሳሰሉት አገልግሎቶች ከትንሹ በጥቂቱ የተጠቀሱትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡ውሀ ከሌለ ህይዎት አይኖርም፡፡ ውሀ ለሰው ልጅ ሆነ ለሌሎች ህይዎት ላላቸው

ነገሮች ወሳኝ ነገር ነው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ውሃ ከተለያዩ ቦታዎች ከወንዝ፣ ከምንጭ፣ ከጉድጓድ አሁን አሁን ደግሞ ከቧንቧም ይገኛል፡፡ ውሀ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ውስጥ የተለያየ ትርጉም አለው፡፡ በውሀ መታጠብ መንጻትን (ንጹህ መሆንን) ስለሚያመለክት በአሉታዊ ጎኑ ሀብት፣ ንብረት፣ ገንዘብ ማጣት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ድፍርስ ውሀ በህልም ሲታይ ደግሞ ሲሳይ መሆኑ ይታመንበታል፡፡ በህልም እራስን በውሀ መታጠብ ሀብት ይሸሻል (ያሳጣል)፣ ይሰረቃል (ይዘረፋል) የሚል አንድምታ አለው፡፡ በህልም ውሀ ጎርፍ ሲሆን፣ ሲደፈርስ በአካባቢው አዝመራ ይሆናል (እህል ይሆናል)፣ ምርት ይጨምራል በሚል ይፈረጃል፡፡ የሚከተለው አቶ የአጎልን ታምራት ህልም እንመልከት፡-

*‹‹ይዳን ወንዝ እና ጭኤ የተባሉ ትልልቅ ወንዞች በህልሜ ደፍርሰው ጎርፍ ሲኼድ ካየሁት አካባቢያችን አዝመራ መሆኑን አረጋግጫለው፡፡ ሲሆን ደግሞ ያሳየኛል፡፡››* (አቶ አጎልን *ታምራት፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 *አ.ም*)

በህልም ውሀ ሲደፈርስ እና ጎርፍ ሲሆን የሚይዘው ግብስባስ ስላለ ግብስባሱ ደግሞ እንደ ሲሳይ እንደ ተጠራቀመ ነገር ስለሚቆጠር ማግኘትን ያመለክታል፡፡ ሌላው ደግሞ እራሱን በውሀ መታጠብ መጽዳት እና መጥራትን ስለሆነ ባዶ መሆንን ስለሚያመለክት እንደማጣት ይቆጠራል፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ፈንቴ እንዳለው የሚከተለውን ህልም ተናግረዋል፡፡

*‹‹በህልሜ ተኝቼ እራሴን ውሀ አድርጉልኝ እያልኩኝ ስታጠብ አድሬ በበነጋታው በርሀ ያስወረደኳቸውን ፍየሎች ነብር የተወሰኑትን ትቶ አምልጠውት አብዛኞቹን በላብኝ፡፡››* (አቶ *ፈንቴ እንዳለው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 *አ.ም*)

ከላይ ያለው ሃሳብ የሚያስገነዝበው በህልም ውሀ መታጠብ ሲሳይ ማጣትን (መገፈፍን)፣ መራቆትን፣ ባዶ መሆን የሚገልጽ መሆኑን ነው፡፡ ይኸውም ውሃ የሰዎች ቆሻሻ ንጹህ የማድረግ እና የማጥራት አቅም ያለው ስለሆነ ማህበረሰቡ መቆሸሽን ከህልም ውጭ እንደ ሃብት ስለሚቆጥረው እና ስለሚያምንበት በህልም ይህ ቆሻሻ ሲታጠብ ካየ የንብረት መውደም አልያም የሀብት መመናመን እንደሚገጥመው ያስባል፡፡

## 5.2.2 አልባሳት በህልም ውስጥ

**1. ኩታ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ኩታ ከአልባሳት አንዱ ሲሆን በአብዛኛው ያገቡ ሴቶች (እናቶች) የሚለብሱት ነው፡፡ ኩታ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ከጫፍ እና ከጫፍ

የተለያየ ቀለም ያለው ክር በመጠቀም የሚሰራ ቀለሙ በአብዛኛው አንድ አይነት ሲሆን ሴቶች ከለበሱት ቀሚስ በላይ ከትክሻቸው ላይ ለሁለት አልያም ለአራት አጥፈው ጣል በማድረግ የሚለብሱት ነው፡፡ ኩታ ገበያ፣ ልቅሶ፣ ማህበር፣ ጥሪ (ድግስ፣ የአመት በአል)፣ ስራ ብቻ ከቤት ሲወጣ ተለብሶ የሚኬድ ነው፡፡ ኩታ ያገባችትን ሴት ከአላገባችት የምንለይበት አንዱ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ኩታ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ያገባች ሴት የምትለብሰው እንጂ እንደማናቸውም ልብስ ሁሉም ሰው የሚለብሰው አይደለም፡፡ ኩታ በማህበረሰቡ የክብር መግለጫ የማዕረግ ማሳያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይኸውም በማህበረሰቡ ማግባት ማዕረግ ሲሆን ማዕረግነቱም እራስን ከዝሙት መጠበቂያ እና እራስን ማክበሪያ (ክብር ማግኛ) ለማድረግ ስለሚያገለግል ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ያገባች ሴት በባሏ ምክንያት ትከበራለች፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በክብር ያላገባች ሴትም ሆነ ወንድ *‹‹ቁሞ ቀር››* እየተባለች /ባለ ይሰደባል፡፡ ስለዚህ በዚህ ማህበረሰብ ጋብቻ ክቡር ነው፡፡ ስለሆነም ኩታ በህልም ውስጥ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ይኸውም ኩታ በህልም መልበስ ባል ማግባት የሚል ፍች ያለው ሲሆን ኩታ በህልም ሲጠፋ የባል ሞት ነው ተብሎ ይፈረጃል፡፡ ይህን በተመለከተ ወ/ሮ ሁልዬ እንዳላማው የሚከተለውን ህልም ከእነ ፍቺው ተናግረዋል፡፡

> *የህግ ባሌን ላገባ ስል የእናቴ አክስት ትልቅ ጃኖ ኩታ አምታ ስታለብሰኝ እኔም ደስተኛ ሁኘ ስቀበላት በህልሜ አየው፡፡ ተዚያ የወርሀ ጦም የእኩል ጦም እንደዚያ ያሳየኝ በፋሲጋ በእኛ ጊዜ አንድ ሰው ሲያገባ ስለማይነገር ተአክስቴ ከባሏ ወገን ባል አምታ አገባው፡፡ ጃኖ ኩታ የሚባለው ከውቅያቢ የሚያስታርቅ ስለሆነ የግቢውን እውነተኛነቱን አሳይቶኛል፡፡ ኩታም ያው ባል ነው፡፡* (ወ/ሮ ሁልዬ እንዳላማው፡ *ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 አ.ም)

ኩታ በህልም የተጠቀሰው ሃሳብ እንደሚያሳየው አንድ ሴት ከአገባች ጀምራ የምትለብሰው (የምትደርበው) ልብስ *መሆኑን* ሲሆን በህልም ኩታ *መጥፋት* ደግሞ ክብር የሆነውን ባልን በሞት *መነጠቅ መሆኑንም* ከዚህ ጋር አያይዘው ይናገራሉ፡፡

**2. ቀሚስ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ቀሚስ የምንለው ከአልባሳት አንዱ ሲሆን ሴቶች በተለያየ ስም የሚሰይሙትን ቀሚስ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ቀሚስ ከህጻናት እስከ አዋቂ ሴቶች የሚለብሱት ነው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የህፃናት ቀሚስ ያለነጠላ ይለበሳል የእናቶች ግን ከኩታ ጋር እንጂ ብቻውን ቀሚስ አይለበስም፡፡ ስለሆነም ቀሚስ በባህል ውስጥ እራሱን

የቻለ ተግባር እና ትርጉም አለው። በተለይም እናቶች ከህጻናት በበለጠ ስለቀሚስ ህልም እንደሚያልሙ ይናገራሉ። በህልም ቀሚስ መልበስ ፀጋ እንደሆነ ይታመናል። በህልም ኩታ እና ቀሚስ ለብሶ ቤተ-ክርስቲያን መሳለም ቅዱስ መላክ መቅረብን እንደሚያመለክት መረጃ አአቀባዮች ይናገራሉ። ቀሚስ በህልም ከታየ በሌላ በኩል ሀገር እንደሆነም ይታመናል። ቀሚስ በህልም መልበስ ባል እንደ ማግባት፣ ትዳር፣ ጎጆ ከመስራት (ከመቀለስ) ጋር ያያይዙታል። ምክንያታቸውም ቀሚስ ገበናን ሸፋኝ ስለሆነ ትዳርም (ጎጆም) እንደ ቀሚስ ገበናን ሸፋኝ መሆኑን ይናገራሉ። እማሆይ የዝና ቸኮል የሚከተለውን ህልም አይተው እንደደረሰላቸው ይናገራሉ።

> *ባለቤቴ ቄስ አባ አዳሙ ሊሞት ሲል በህልሜ ቀሚሴን ሲቀደደው፤ ምጣዴን ሲሰብረው አየው። ተዚያ እንዴታ ብየ የጠየኩት እንደው አንቺ ተእንግዲህ ግብር ማድቀቅ እና መክለፍት መጋገር ስራ ነው የምትሰሪ ይለኛል። ተዚያ ትንሽ ሰነባብቶ አባ አዳሙ ሞተ። እኔም በቀጥታ የተነገረኝን ስላላደረኩ በቁርጥማት እያሰኝ ህመምተኛ ሆንኩ። የተባልኩትን ባደርግ ግን አልታመምም ነበር። ቀሚስ ባል ነው (ማረግ) ነው እሱን አጣው። ነጠላ ሆንኩኝ። ምጣድ ደግሞ ሲሳይ ነው፣ ባል ሲሳይ ነው በባል ላይ እንጀራ ይበላል፤ እንጀራ ይጋገራል፤ ከሰው ጋር በሀዘን በደስታው አብሮ መዋል ይችላል። ትዳር ባል ከሌለ ግን ማንም አይወነፍልሽም።* (እማሆይ የዝና ቸኮል፡ *ቃለ-መጠይቅ*፣ *መጋቢት* 2011 ሊ.ም)

ከተጠቀሰው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ቀሚስ በህልም ውስጥ ሀገርን፣ ባልን፣ ጸጋን ማግኘትን፣ ትዳርን የሚወክል መሆኑን ያመለክታል። ይህ ነገር ደግሞ *‹‹ቀሚስ መልበስ ሀገር ነው››* ከሚለው አባባል ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው። ምክንያቱም አባባሉ የሚያስተላልፈው መልክት ሀገር ገበና ሸፋኝ መሆኑን ሲሆን ቀሚስም የሰውን ገላ ራቁትነት የሚሸፍን መሆኑ አንድ ያደርጋቸዋል።

**3. መቀነት፡-** መቀነት እንደ ኩታ ሁሉ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ያገባች ሴት ብቻ በወገቧ የምትታጠቀው ነው። መቀነት ቁመቱ እኸርም እና ወርዱ ጠባብ ሆኖ እንደኩታ በአራት ማዕዘን የሚሰራ ሲሆን ጫፍ እና ጫፍ ላይ በሰፊው የተለያየ ቀለም በአላቸው ክሮች በመጠቀም የሚሰራ ነው። ስለሆነም በህልም ውስጥ እራሱን የቻለ ትርጉም እና ፍቺ ያለው ሲሆን ተግባሩም እንደአላሚው የህልም ሁኔታ ይወሰናል። ይኸውም መቀነት በህልም ውስጥ

አወንታዊ እና አሉታዊ ፍቺዎች ያሉት በመሆኑ ነው፡፡ አወንታዊን ስንመለከት ከምንም በላይ ጥሩ ጎኑ ጎልቶ የሚታይበት ነው፡፡ ስለዚህ በህልም መቀነት መታጠቅ ሴትነትን (ሙያን) የሚገልጽ ሲሆን ማግባትን ምልክት እና የሴትን ጠንካራነት የሚገልጹበት ነው፡፡ በህልም ውስጥ መቀነት ታጥቆ ማየት ጥሩ እንደሆነ ሁሉ በህልም ውስጥ የታጠቁትን መቀነት መፍታት ደግሞ መጥፎ ሲሆን ሴትነትን (የሙያ መጥፋትን) ማጣት እና ከባል ጋር መፋታትን ያመለክታል በማለት መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡ አቶ አስራቴ ቢተው መቀነት በህልም ሲታይ ያለውን ፍቺ እንደሚመለከተው ይገልጻሉ፡፡

*‹‹በህልሜ ስለሴት ልጆቼ እና ስለ የልጅ ልጆቼ ሲያልመኝ ሊያገቡ ሲሆን ሁል ጊዜ በህልሜ መቀነት ሲታጠቁ አያለው ሌላ ደሞ ሊፋቱ ሲሉ መቀነታቸው ሲፈታ እና ሲጠፋቸው አያለው፡፡ እሱም ይደርሳል፡፡››* በማለት ገልጸዋል፡፡ (አቶ አስራቴ ቢተው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011  አ.ም)

ከላይ ያለው ሀሳብ የሚያመለክትን በህልም ውስጥ መቀነት መታጠቅ እና መፍታት አወንታዊ እና አሉታዊ የህልም ፍቺ እንዳለው ነው፡፡ ይህም በህልም መቀነት መታጠቅ በማህበረሰቡ እምነት ሴት ልጅ ጥሩ ነገር ወደፊት እንደሚገጥማት ይታመናል፡፡ ከዚህ በተቃራኒው በህልም መቀነት መፍታትም ሆነ መጥፋት ሴት ልጅ የሚገጥማት መጥፎ ነገር ወደፊት እንዳለ ይታመናል፡፡

**4. አውሳ (ብርድ ልብስ)፡-** ብርድ ልብስ በመኝታ ጊዜ የሚለበስ ልብስ ነው፡፡ አውሳ ከሌለው ልብስ በተለየ ለብርድ የሚሆን ሲሆን ወፍራም ነው፡፡ ብርድ ልብስ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እራሱን የቻለ የህልም ትርጉም አለው፡፡ ትዕምርትነቱም ከፍ ያለ ነው፡፡ ብርድ ልብስ በህልም መልበስ የጋብቻን መጽናት (ተጋቢዎች መለመዳቸውን) ያመለክተናል፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ አስራቴ ቢተው የሚከተለውን ህልም ከእነ ፍቺው እንደደረሰላቸው ገልጸዋል፡፡

> *ትንሽ ወንድም አለኝ እና ሚስት እያገባ አይለምዱለትም፤ እናመጣለታለን ይኼዳሉ፤ እስትንሰለች ድረስ ከ10 በላይ ሚስቶች አግብቶ እነሱም ሳይወልዱ ይኼዳሉ፡፡ ተዚያ ብዙ ጊዜ አላገባም እያለ ተቀመጠ ተዚያ አንድ ሁለት አመት ተቀምጦ አንድ ሴት ተገኘች ተብላ አምተን አጋባነው፡፡ ተዚያ አንድ ቀን ሌሊት በህልሜ ተኝቼ ሙሽሮቹ በአንድ አልጋ ተኝተው አውሳ ለብሰው አየዋቸው፡፡ ህልም ፈቺ እማሆይ የዝና ቸኮል ላይ ሀጄ የሆንኩትን ስነግራቸው ሙሽሮቹ መላመዳቸው ነው ብለው ነገሩኝ፤*

*እንዳሉትም ተላምደው ልጅ እስተመውለድ ደረሱ፡፡* (አቶ አስራቴ ቢተው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ *መጋቢት* 2011 ዓ.ም)

የተገለጸው ሃሳብ የሚያስረዳው ብርድ ልብስ በህልም ውስጥ ሁለት አይነት ፍቺ ያለው ሲሆን እንደህልሙ ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡ ነገር ግን ብርድ ልብስ ያለበት ህልም ከጋብቻ ጋር የሚገናኝ ትርጉም እንደሚኖረው ከተጠኘው ማህበረሰብ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

**5. ደበሎ፡-** ደበሎ የምንለው በአብዛኛው ደጋማ አየር ንብረት በአላቸው አካባቢዎች ለብርድ መከላከያነት የሚለበስ ልብስ ሲሆን ከበግ ቆዳ በማልፋት የሚዘጋጅ ነው፡፡ ደበሎ ለቀን ልብስ እና ለሌሊት ልብስነት እንዲያገለግል ተደርጎ በሁለት መልክ ይዘጋጃል፡፡ በተለይም ሌሊት የሚለበሰው የብዙ በጎች ቆዳ በአንድ ተሰፍቶ በማልፋት ቤተሰቡን እንዲያለብስ ተደርጎ የሚሰራ ነው፡፡ በዛ ማህበረሰብ ደበሎ ከምንም በላይ ወሳኝ እና አስፈላጊ (ተፈላጊ) ልብስ ነው፡፡ ደበሎ በግ እና ሌላ ሃብት ያላቸው ሰዎች በብዛት የሚጠቀሙት ነው፡፡ ሁሉም ሰው ሳይሆን አንዳንድ ሰዎች ለእያንዳንዳቸው ቢኖራቸውም ብርድ ልብስ ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም በግ የሌለው ሰው በግ ገዝቶ፣ ሲዘጋጅ ደግሞ በብዛት ቅቤ ስለሚያስፈልገው ብዙ ቅቤ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ማድረግ የሚችል ሰው ብቻ የሚጠቀመው ስለሆነ ሁሉም ሰው ደግሞ ይህን አይችልም፡፡ አዘገጃጀቱም አድካሚ ስለሆነ ጉልበት እና ሰው እንደሚያስፈልግ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ደበሎ በህልም ውስጥ ያለውን ሚና አቶ ንጉሴ አንዱለም ይናገራሉ፡፡ ደበሎ በህልም ውስጥ ተለብሶ ሲታይ ስልጣን ማግኘትን መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ምክንያታቸውም ደበሎ በአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ልብስ ስለሆነ ሹመትም ከፍተኛ ነገርን መቀዳጀት ስለሆነ ነው ይላሉ፡፡ ስለደበሎ የአቶ አስራቴ ቢተው ለሌላ ሰው የፈቱለት ህልም እንደሚከተለው እንመልከት፡-

> *አንድ ድሃ በእየ ቤቱ ሎሌ እየገባ የሚኖር ነበር አንድ ቀን ህልም አለመኝ ብሎ ተእኔ መቶ ህልሙን ነገረኝ፡፡ ህልሙም ተገበያ መሃል ቆሜ ይመስለኛል የሆኑ ቀይ ሰውዬ ደበሎ ሲያለብሱኝ ይተው ይኸ ነገር ለብሸ ስለማላውቅ አይገባኝም ብዬ ስላቸው ቆጣ ብለው እስከመቼ በዚህ ብርድ ብለው አለበሱኝ፡፡ ተዚያ እኔም ተቀብያቸው ተሰወሩኝ ብሎ ህልሙን ነገረኝ፡፡ ተዚያ የሚመጣልህ ሹመት አለ ጠብቅ አልኩት፡፡ ደስ ያለው እሱም ኼደ፡፡ በወሩ ደኑ ይጠበቅ ተብሎ ተወረዳ ትዛዝ መቶ ማን ጠንካራ ዘበኛ አለ*

*ሲባል ሁሉም እኔ እኔ ሲል ቀበሌው ሳይታሰብ እሱን አንድ ሰው ጠቁሞ አስቀጠረው። (* አቶ አስራቴ ቢተው :*ቃለ-መጠይቅ፣መጋቢት* 2011 ኣ.ም)

ሃሳቡ የሚያስረዳው ደበሎ በተጠናው ማህበረሰብ በህልም መልበስ ማዕረግ እና ሹመት ማግኘትን ሲሆን ደበሎ የሚባል ልብስ በማህበረሰቡ በቀላሉ እና በማንኛውም ቤት የሚገኝ ስላልሆነ ስልጣን እና ሹመትም እንዲሁ የሚገኝ እና የሚመጣ እንዳልሆነ በመገንዘብ ሁለቱን አስተሳሰቦች በማገናኘት በህልም ያስተሳስሯቸዋል።

**6. ሱሪ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ሱሪ ከአልባሳት አንዱ ሲሆን ወንዶች ከወገባቸው በታች የሚታጠቁት ልብስ ነው። ሱሪ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የጀግንነት መግለጫ ሆኖ ያገለግላል። ወንድ ልጅ ሲወለድ *‹‹ሱሪ ያለው፣ ጀግና››* ሆኖ እንዲያድግ ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን የአካባቢው ነዋሪም የበኩሉን ሚና ይጫወታል። የተወለደው ልጅ ምን ሆኖ ማደግ እንዳለበት ገና ከተወለደ ጀምሮ ትግበራው ይካሄዳል። ሲያድግም ወንድ ልጅ ምን መሆን እንዳለበት ይመከራል። ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ከዱር አውሬ አድኖ ከገደለ፣ ጠላት ካሸነፈ (ድል ካደረገ) *‹‹እገሌ እማ ሱሬ የታጠቀ ወንድ ነው››* ይባላል። ስለዚህ ለሱሪ የሚሰጠው ክብር ከፍ ያለ ነው። ሱሪ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት ሰርፆ የገባ ጠንካራ አቋምን የሚገልጽ ነገር ነው። ስለሆነም ሱሪ በህልም ውስጥ መታጠቅ እና መውለቅ እራሱን የቻለ ትርጉም እና ፍቺ አለው። ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ አለባቸው ከበበው ህልሙን እና የህልሙን ውጤት እንደሚከተለው ተናግረዋል።

> *በህልሜ ይመስለኛል ጎዬ የሚባል ሰውየ የታጠኩትን አዲስ ሱሪ አውልቆ ለሌላ ሰው ሲያስታጥቀው ለምን እንደዚህ ታደርጋለህ ብየ ስለው ለአንተ አይገባህም ለአንተ የሚሆን ብሎ ትንሽ የፋንት መሳይ አስታጥቆኝ ኼደ፤ እኔም ነቃው። ተዚያም ሀሙስ ቀን ያለመኝ እሁድ ስብሰባ ተደርጎ ከወረዳ የመጡ ሰዎች ሊቀመንበር ነበርኩ በዚሁ ሀሳብ ሹመቴን አውርደው የቀበሌ የጎጥ ፈጅ ሆኜ ተሾምኩ። ለልማት የጎጥ ቀስቃሽ ሆንኩኝ።* (አቶ አለባቸው ከበበው፡- ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011ኣ.ም)

ሱሪ በህልም ውስጥ ሚስት ማግባት ጋር፣ ሰርቶ ባለጸጋ ከመሆን ጋር፣ ከሰው ጋር ገጥሞ ማሸነፍን ሌት ከቀን የሚሰራን ለፊ ሰው፣ መምራት እና ማስተዳደር የሚችልን፣ ተናግሮ በንግግሩ ማሳመን የሚችል ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ጉዳዮ የሚወክል መሆኑን ያመለክታል። በተቃራኒው ደግሞ ሱሪ በህልም መቃጠል፣ መውለቅ እና መጥፋት ከላይ ከተገለጹት ሀሳቦች

በተቃራኒ የሚቆም ሀሳብ እንዳላቸው መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ፡፡ ሌላኛው ሱሪን በተመለከተ የጨሰ ገበዝ ደረሰን ያለሙትን እና የደረሰላቸውን ህልም እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

*‹‹ተኝቼ በህልሜ አዲስ ሱሪ የለበስኩ ይመስለኛል ተዚያ ጎበስ ብዬ ያየውት እንደሆን የአንደኛው እግሬ ሱሪ ልብስ አልቋል፡፡ ተዚያ በውኔ እንደምጨነቀው እየተገረምኩ ሳለሁ ብንን አልኩ፡፡ ህልሙን እንዳለምኩት ብዙ ሳይሰነብት ሚስቴ ሞተች፡፡››* (ጨሰ ገበዝ ደረሰ ገላኤ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሱሪ በተጠናው ማህበረሰብ ወንድን ልጅ የሚመለከት ሲሆን በህልምም ይህ አተሳሰብ እንደሚንጸባረቅ ያሳየናል፡፡ ይኸውም ወንድ ልጅ በህልም ሱሪው ሲቃጠል፣ ሲያልቅ፣ ሲቆሽሽ፣ ሲቀደድ፣ ሲለብሰው ልኩ አልሆን ሲል( አላምርለት ሲል)፣ ሌላ ሰው ሲወስድበት ሲታይ የህልሙ ፍቺ እና አደራረሱ መጥፎ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከተጠቀሱት በተቃራኒ በህልም ውስጥ ሲታይ ደግሞ የህልሙ ፍቺ እና አደራረሱ በማህበረሰቡ በጥሩ ይታመናል፡፡

**7. ቆብ፡-** ቆብ በተጠናው ማህበረሰብ በሰዎች እራስ ላይ የሚደረግ ሲሆን ወንዶች ከልጅነት ጀምረው ያደርጋሉ፡፡ ሴት ግን ስታገባ የሰርጓ ዕለት እና ስትመለኩስ ቆብ ታደርጋለች፡፡ ቆብ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ማድረግ ሹመት መሾምን፣ ማእረግ ማግኘትን እና ከአንዱ የህይዎት ምዕራፍ ወደ አንዱ ምዕራፍ መሸጋገርን፣ ለሆነ ጉዳይ መመረጥን ያመለክታል በሚል ይገልጹታል፡፡ ቆብን በተመለከተ መላከ ሰላም ዳምጤ አርገህ የሚከተለውን ህልም ከነፍቺው አብራርተው ተናግረዋል፡፡

> *ገበያ እየኸድኩ ይመስለኛል ሸሃይ ልገዛ አንድ ጎልማሳ ሰውየ የት ልትኸድ ነው ብሎ ይጠይቀኝ ይመስለኛል ተዚያ ገበያ ስለው ምን ልታደርግ ሲለኝ ሸሀይ ልገዛ ስለው አንተስ ጣፋጩን ይዘሀል ይለኛል፡፡ ተዚያ ያ ገበያ መሬት ያልነካ፣ በአራት ጎጥ ሁሉ ቦገግ ቦገግ የሚል ይመስለኛል ተዚያ እዚህ ልግባ ስል ቆቤን ብድግ ሊያደርገው ሲል ጎንበስ ብየ አስቀረዋለሁ፡፡ እየው ይች እኮ ቦታ አዘውትሮ ቅዳሴ የሚገባባት ቦታ አደለችም፤ ዝም ብሎ ይቺ ሰው የሚገባባት አደለችም፤ ተመልከታት እንግዲህ መሰል የሌላት ናት ሲለኝ ሳያት አይኔን ወደየት ልጣለው ስለሚያብረቀርቅ የሚያብረቀርቅም መሬት ሳይነካ ነው፡፡ እሱን እንዳየሁ ተብዙ ጊዜ በኋላ ከእኔ በፊት የደብራችን አስተዳዳሪ የሆኑት አባ ዝሀኑ ሰው ተጣላቸው፡፡ ተዚያ ማንን እንሹም ሲባል አባ*

*ዳምጤን ብሎ ሰው ተናግሯል፡፡ ተዚያ ሲነገረኝ ህፃን ስለሆንኩ አልፈልግም ስል አባ ጀትነት የሚባሉ ቄስ ይሄ ሰውየ ይልቀቀን እንጂ እኔ እመረሃለሁ (አግዝሀለው) ብለው ተሾምኩኝ፡፡ ተዚያ አባ ዝሀኑ በወረዳ ከሰውኝ ወረዳ ህፃን ነህ ሹመቱ ምን ያደርግልሀል ተብየ ተጠየኩ ኧረ እኔም የስራ ሰው ስለሆንኩ አልሾምም ብል የወረዳው ቤተ-ክህነት ሓላፊ አጽድቀው ሳኩኝ፡፡* (መላከ ሰላም ዳምጤ አርገህ፡ *ቃለ-መጠይቅ*፣ የካቲት 2011 አ.ም)

ከማህበረሰቡ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ቆብ በህልም ማድረግ መሾምን የሚያመለክት ሲሆን ቆብን በህልም ከእራስ ላይ ማውለቅ ደግሞ ከሹመት መሻር (ከስልጣን መውረድ) እንደሆነ በማህበረሰቡ የሚታመንበት ሀሳብ ነው፡፡

**8. ካባ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ካባ በሰርግ ጊዜ ሙሽሮች ከልብሳቸው በላይ የሚደርቡት (የሚያደርጉት)፣ የሚቆርቡ ሰዎች ሲቆርቡ የሚደርጉት በአብዛኛው ጥቁር ቀለም ያለው እና ቪ ቅርጽ ያለው ዙሪያውን በወርቃማ ክር የሚሰፋ (የሚጠለፍ) የማእረግ ልብስ ነው፡፡ ካባ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ሀላፊነትን የሚሸከም (መሸከም የሚችል) ግለሰብ የሚለብሰው ልብስ እንደሆነ ይታመንበታል፡፡ በማህበረሰቡ ካባ ማንኛውም ሰው እንደማይለብሰው ይናገራሉ፡፡ በመሆኑም በህልም ካባ መልበስ ስልጣንን እንደሚመለከት መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ፡፡ የሚከተለውን መሪ ጌታ ስማቸው አሞኘ ህልም እና ፍቺውን እንዴት እንደደረሰ ይገልጻሉ፡፡

> *በህልሜ ይመስለኛል የሆነ ጨስ ካባ ለብሶ ተትክሻው ላይ የሴቶች የወርአባ ነክቶት ይመስለኛል፡፡ ተዚያ ካባውን እንደለበሰ በብርሌ ውሀ ይዞ ባለቤቱ ውሀውን በአፍንጫው ደፍታው ተዚያ ተሰማይ እሳት መቶ ውሀውን እንደ ናፍታ አድርጎ ይበለዋል፡፡ ተዚያ በህልሜ እንደዚያ እንዳደረገኝ በሁለት ሰንበት ውስጥ ጨሱ ሚስቱ እምብኝ ብላው ተፋቱ፡፡ ህልሙ ሲፈታም ካባ እና ብርሌ ስልጣኑ ሲሆን ውሀው ቅባ ቅድስ ነው፤ እሳቱ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን የሰውየውን ስልጣን (ክህነት) መቀማቱን ያመለክታል ማለት ነው፡፡* (መሪጌታ ስማቸው አሞኘ፡ *ቃለ-መጠይቅ*፣ የካቲት 2011 አ.ም)

ካባ በህልም ውስጥ እንዳየነው እራሱን የቻለ የህልም ውስጥ ተግባር እንዳለው እና በማህበረሰቡ ውስጥ የተለየ ቦታ እንደሚሰጠው ነው፡፡ ካባ በዚህ ማህበረሰብ በአብዛኛው ከሴት ይልቅ ወንድ ልጅ ለተለያዩ ሹመቶች ስለሚመረጥ ይለብሰዋል፡፡ ሴት ልጅ ግን ያገባች ዕለት፣ ስትቆርብ እና

ስትመለኩስ ትለብሰዋለች፡፡ ይህ ወቅት ደግሞ ለሴት እንደሹመት ማግኛ ጊዜ ይቆጠራል፡፡ ሴት ባአገባች ጊዜ በቤቷ ንግስት ትሆናለች፤ ስትቆርብ እና ስትመለኩስ ደግሞ ክብርን ከፈጣሪ እንደምታገኝ ስለሚታመን ሰው ያከብራታል፡፡ ስለዚህ ካባ በህልም ውስጥ ከፍተኛ ሚና ከአላቸው አልባሳቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

**9. ኮት እና ጋቢ፡-** ኮት እና ጋቢ አልባሳቶች በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በአብዛኛው ወንዶች የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡ ኮት እና ጋቢ በይበልጥ ያገቡ ወንዶች ወይም ትልልቅ የሆኑ ወንዶች እንደሚለብሷቸው ከእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ እነዚህ አልባሳት የአንድን ግለሰብ ማንነት ከፍ በማድረግ ክብር እንዲኖረው በማድረግ እና ከበሬታውን በመጨመር በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሰው እንዲሆን ያደርጉታል፡፡ በተለይ ጋቢ የሰውየውን ሁለ ነገር በማህበረሰቡ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡ ሁለቶችም ለግለሰቡ ግርማ ሞገስ የሚሰጡ ስለሆኑ ተመራጭ ናቸው፡፡ ስለዚህ ኮት እና ጋቢ በህልም ሲታይ በማህበረሰቡ ፀጋ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ኮት እና ጋቢ በህልም መልበስ ፀጋን ማግኘት ሲሆን ጸጋ ደግሞ ሃብት ማግኘትን ይመከታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ኮት እና ጋቢ በህልም መውለቅ እና መገፈፍ ፀጋ ማጣት (ድሃ መሆንን) እንደሆነ በማህበረሰቡ ይታመንበታል፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ንጉሴ አንዷለም የሚከተለውን ይናገራሉ፡፡ *‹‹በህልሜ ኮት ወይም ጋቢ ከለበስኩኝ ከብቶቼ ወይም በጎቼ ይወልዳሉ፤ በህልሜ ኮት ከወለቀብኝ ወይም ጋቢየን ከተገፈፍኩ ገንዘብ (ጥሬ ብር) ይጠፋብኛል››* በማለት ይገልጻሉ፡፡ ( አቶ ንጉሴ አንዷለም፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011ዓ.ም)

ሃሳቡ የሚያስረዳው ኮት እና ጋቢ በህልም ውስጥ ሲታዩ ሁለት አይነት ፍቺ እንዳላቸው ሲሆን በአንድ በኩል ኮት እና ጋቢ በህልም መልበስ ሃብት ማግኘትን እንደሚመለከት እና ሌላው ደግሞ በህልም ኮት እና ጋቢ ሲወልቅ (ሲገፈፉ) ማየት ሃብት ማጣት እንደሆነ ከማህበረሰቡ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

**10. ሸት፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ አስተሳሰብእና አመለካከት መሰረት ሸት ማለት ቤተ-ክርስቲያን የሳንቲም ሆነ የብር፣የስለት እና የማሪያም ባርኪ የእህል ማጠራቀሚያ አቡጀዲ የሚመስል በተለያየ ቀለም የሚሰራ በአብዛኛው ዝጉርጉር መልክ ያለው አልባሳት ነው፡፡ ሸት የስለት መጣያ ይሆን ዘንድ በቤተ- ክርስቲያን እጥር ግቢ አካባቢ የሚዘረጋ ልብስ ነው፡፡ ሸት ሌላው አገልግሎቱ ለቅዱሳን መፅሀፍት መሸፈኛ እና ካህን ሲቀድስ ለሚለብሰው ልብስም

ይሆናል። ስለዚህ ይህ ልብስ በህልም ሲታይ እራሱን የቻለ ትርጉም እና ፍቺ ያለው ነው። በህልም ሽት መቀበል ማርገዝ እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ። ወ/ሮ ጥሩ ቀለም ባየ የሚከተለውን ህልም በራሷ የደረሰውን ተናግራለች።

> *የመጀመርያ ልጄን ሳረግዝ ማርገዜን ሳላውቀው ሌሊት በህልሜ ፋሲለደስ በተ-ስኪያን ሀጀ ቅዳሴ አልቆ ይመስለኛል ጠበል ልቀበል ጠበል መጠጫ እቃችንን ይዘን እየጠበቅን ካህኑ ለሌሎች ጠበል እየቀዳ ሲሰጥ ቆይቶ ለእኔ ግን በሽት የሚያምር ልጅ ሰጠኝ ተዚያ ብንን አልኩኝ። ተዚያ እናቴ ነበረች በማለዳ ተነስቼ የሆንኩትን ነገርኳት ተዚያ እናቴ አደራ ልጄ በሆድሽ ፅንስ ይዘሻልና ምች እንዳይመታሽ ተጠንቀቂ አለችኝ። እንዳለችውም ወንድ ልጅ ወለድሁ።* (ወ/ሮ ጥሩቀለም ባየ፡ *ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 ኢ.ም)

የላይኛው ሃሳብ የሚያሳየው ሽት የተቀደሰ ነገር የሚቀመጥበት ስለሆነ በህልም ሲታይ ጥሩ ነገር እንደሚገጥም ይታመናል። ነገር ግን ይህን የተቀደሰ ነገር በህልም ሌላ ሰው ሲወስደው እና ሲቀማን ከአየን ህልሙ መጥፎ እንደሆነ ይታመናል።

**11. ጫማ፡-** ጫማ በተጠናው ማህበረሰብ ከህፃናት እስከ አዋቂዎች በእግር የሚደረግ ሲሆን የተለያየ አገልግሎት አለው። ጫማ እግርን ከተለያዩ ስለት ነገሮች ይጠብቃል፤ ከብርድ ይከላከላል፤ ከእሾህ እና ከእንቅፋት ይከላከላል፤ የእግርን ንፅህና ይጠብቃል። ጫማ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ሲታይ እንደ ሁኔታው እንደሚፈታ ይናገራሉ። በተለይም በህልም ጫማ ማድረግ ከማግባት ጋር ያያይዙታል። ጫማ ማድረግ ጋብቻ ነው በማለት ይናገራሉ። በተለይም የጋብቻን ክብርነት በመግለፅ ጫማም የሚደረገው የሚገጠምን፣ ልክ የሆነን፣ የምንወደውን ስለሆነ የምናደርገው ጋብቻም እንደዚሁ ተመሳሳይነት ያለው ነው በማለት ይገልፃሉ። ጫማ በህልም ያለውን ተግባር እና ማህበራዊ ፍቺ በተመለከተ የሚከተለውን መረጃ እንመልከት፡-

> *በህልሜ ጫማ ተራ ሁኝ ይመስለኛል አብሮኝ ያለውን ሰው ሳላውቀውም እና ጫማ ልክሽ የሆነውን ምረጭ እያለ እኔ ልብስ ይሻለኛል እያልኩ እብይ እላለሁ ተዚያ እየተከራከርን ብዙ ቆይቼ የሚያምር ጫማ ሲያሳዩኝ እሽ ብየ ተገዛልኝ። ተዚያ 4ኛ ክፍል እያለው አጎቴ ባል አምቶ አላገባም ብየ እምብይ ስል ይኽን ባል መቼም አታገኘውም ለአሁን ጊዜ ትምህርት ብሎ ለፊ እና ኀበዝ እንደሆነ ሰዎቹን አሳምኖ እቢይ ሲሉኝ እሺ ብየ አገባው።*

*እይው እንደምታይው አሁን ወልጄ ከብጀ ተቀምጫለው፡፡* (ወ/ሮ ጥሩ ቀለም ባዬ፡ *ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011ዓ.ም)

*ሃሳቡ የሚያስረዳው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ጫማ በህልም መግዛት እና ማድረግ ባል ወይም ሚስት ማግባት እንደሆነ እንደሚታመን ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ በህልም ጫማ ሲታይ ሁለት አይነት ፍቺ አለው፡፡ ይኸውም አወንታዊ እና አሉታዊ ሲሆን አወንታዊ ፍቺው በህልም ጫማ መግዛት፣ማድረግ፣ ከሌላ ሰው መቀበል (መያዝ) ባል ወይም ሚስት ማግባት ሲሆን አሉታዊው ደግሞ በህልም ጫማ መጥፋት፣ መውደቅ እና በሌላ ሰው መቀማት የባል ወይም የሚስት መሞት እና መጋባቱ መቅረት እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡*

## 5.2.3 ቁሳቁሶች በህልም ውስጥ

**1. እንዝርት፡-** *እንዝርት ለጥጥ መፍተያ ሚያገለግል መሳርያ ሲሆን በውስጡ በርካታ ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነዚህ ክፍሎችም የየራሳቸው አገልግሎት አላቸው፡፡ እንዝርት የሴት ልጅ መገልገያ ቁስ እንደሆነ የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰቦች ይገልጻሉ፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እንዝርት በህልም ውስጥ ሚና እንዳለው በማብራራት ይገልፃሉ፡፡ እንዝርት በህልም ውስጥ ሁለት አይነት ፍቺ አለው፡፡ ይኸውም በህልም እንዝርት መያዝ ሴት ልጅ ማርገዝ ሲሆን በህልም የእንዝርት ቁርሽ መስበር የሴት ልጅ መሞት እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች በአለማቸው ህልም እና ከደረሰላቸው አንፃር መረጃ ሰጭዎች ገልፀዋል፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች መካከልም በእራሳቸው ላይ የደረሰውን እንደሚከተለው እማሆይ የዝና ቸኮል ይገልፃሉ፡፡*

*‹‹ሴቶች ልጆቼ ሁለቱ ሲሞቱ በህልሜ ሽጋ እንዝርት አበጅቸ ይመስለኛል ልሰራበት ስል ቁርሿ እየተሰበረች እምብይ ትለኛለች፡፡ ተዚያ ሁለቱ ሴት ልጆቼ ሞቱ፡፡››* በማለት ተናግረዋል፡፡ (*እማሆይ የዝና ቸኮል፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 ዓ.ም)

*ከላይ የተጠቀሰው ሀሳብ የሚጠቁመው በእናርጅ እናውጃ ማህበረሰብ እንዝርት ሴት ልጅ የምትገለገልበት መሳሪያ እንደሆነ የሚያመለክት ሲሆን በማህበረሰቡ እንዝርትን ትዕምትር ያደረጉ ህልሞች ይታለማሉ፡፡ ይህ ደግሞ አወንታዊ እና አሉታዊ ፍቺ እንደ ህልሙ ይዘት ሊኖረው ይችላል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ፍቺዎች ሴትን ልጅ እንደሚመለከቱ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡*

**2. ብርሌ፣ ዋንጫ እና መለኪያ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እነዚህ ነገሮች በቤት ውስጥ የሚገለገሉባቸው ቁሳቁሶች ሲሆኑ ወንድም ሴትም የሚጠቀምባቸው መሳርያዎች ናቸው። እነዚህ መገልገያ መሳርያዎች በህልም ውስጥ የራሳቸው አገልግሎት እናትርጉም አላቸው። መረጃ አቀባዮች እንዳሉት የተጠቀሱት ነገሮች በአጠቃላይ በህልም ውስጥ የሚወክሉት (የሚገልፁት) ልጅ ነው። እነዚህን እቃዎች መያዝ ልጅ ማርገዝን እና መውለድን ያመለክታል። በሌላ በኩል ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት ቁሳቁሶች በህልም መሰበር እና መጥፋት የልጅን መሞት እንደሚያመጣ ያመለክታል። መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት እነዚህ ነገሮች ከልጅ ጋር የሚገናኝ አስተሳሰብ በማህበረሰቡ ስላለ ሲሆን አስተሳሰቡም ብርሌ፣ ዋንጫ እና መለኪያ ሲጠጡባቸው የሚያስደስቱ፣ ሲያጥቧቸው በአንድ ጊዜ ጽድት የሚሉ፣ ሲመለከቷቸው የሚያምሩ፣ውበት ያላቸው፣ የሚያስደስቱ…ወዘተ የመሳሰሉትን በርካታ ጥሩ ጎኖች ያሏቸው ቁሳቁሶች በመሆናቸው ማህበረሰቡ እነዚህን መሳሪያዎች ከህጻናት ጋር ንጽህናን መሰረት ያደረገ ግንኙነት በመፍጠር እንደሚያያቸው መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ። ይኸውም በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት ህጻናት ቢመቷቸው፣ ቢጣሏቸው፣ ቢሰድቧቸው ቂም የማይዙ ስለሆኑ ንጹህ እንደሆኑ ስለሚታመን ነው።

**3. ጓንዴ፣ ረዥም ሚኒሽር፤ ክላሽ እና አጭር ሚኒሽር፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እነዚህ የጦር መሳርያዎች በህልም ውስጥ የሚታዩ ሲሆን የራሳቸው ትርጉምና ፍች ያላቸው ሲሆን በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት መሰረትነት ህልም ላይ ትርጉማቸው እና ፍቻቸው ከአላቸው ማህበራዊ ትርጉም አንጻር ታይቶ ይፈታል። እነዚህ መሳርያዎች በህልም ውስጥ በማህበረሰቡ በተደጋጋሚ የሚታዩ ናቸው። ስለሆነም ጓንዴ እና እረዥም ሚኒሽር ሲያዝ ወንድ ልጅ መውለድ (ማስረገዝ) ሲሆን ክላሽ እና አጭር ሚኒሽር መያዝ ሴት ልጅ መያዝ ወይም ማርገዝ፤ ማስረገዝ ነው። መረጃ አቀባዮች እንደገለጡት ጓንዴ እና እረዥም ሚኒሽር ከክብደታቸው አንፃር፣ ከሚይዘው የሰው አይነት ሴት ወይም ወንድ ያታ አንፃር የወንድ ልጅ ፀባይ፣ እርጋታ፣ ሲናገር አስደንጋጭነቱን በማገናኘት ወንድን ልጅ መያዝ ወይም መወከል እንደሚችሉ በማመን ነው። ክላሽ እና አጭር ሚኒሽር ሴት ልጅ መያዝ ትችላለች። ሴት ልጅ ከፍጥነቷ አንፃር፣ ነገሮችን ከተለያየ ከመመልከት አንፃር ሴት ቀዳሚውን ቦታ የምትይዝ እንደሆነ መረጃ አቀባዮች ይገልፃሉ። የሚከተለውን የአቶ ምንይችል አባተን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹ተኝቼ በህልሜ ይመስለኛል አበረ ማዘንጊያ ክላሽ፤ ሙንየ የትነበርክ አገልግል ክላሽ ይዘው አየሁ፡፡ ተዚያ ሁሎችም ሴት ልጆች ወለዱ፡፡››* (አቶ ምንይችል አባተ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 20011 አ.ም)

ከላይ የተጠቀሱት የጦር መሳርያዎች በህልም ውስጥ በአላሚዎች እና በፈቺዎች አስተሳሰብ እና አመለካከት ፍልስፍና ወንድ ልጅ ያለው አጠቃላይ ማንነት ሊወክል ይችላል የሚለውን እና ሴትን ልጅ ያላትን ማንነት ምን እና ማን ሊወክላት ይችላል የሚለውን በማጥናት የሚተገብሩበት እንደሆነ ያመለክታል፡፡

**4. ካራ (ቢለዋ)፡-** ካራ ወይም ቢለዋ በተጠናው ማህበረሰብ ከብረት የሚሰራ ስለታማ ነገር ሲሆን ለሽንኩርት መክተፊያነት፣ ለስጋ መቆራረጫነት የሚውል መሳርያ ነው፡፡ ካራ በተጠናው ማህበረሰብ የወንድ ልጅ መሳርያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ካራ ይቆርጣል እንጂ አይቆረጥም በሚለው አስተሳሰብ ወንድ ልጅም በዚሁ አስተሳሰብ ውስጥ ይገባል (ይሳላል)፡፡ ካራ አሸናፊ ስለሆነ በህልም ውስጥ ሲታይ የወንድ ልጅ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በህልም ካራ መያዝ ወንድ ልጅ ማርገዝ ሲሆን በህልም ካራ መጥፋት የወንድ ልጅ ሞት ነው፡፡ ካራ ወንድ ልጅ የሚጠቀምበት (የሚገለገልበት) ቁሳቁስ በመሆኑ ስለካራ ጉዳይ ወይም ካራን የሚመለከት ህልም ሲታለም ፍቺውም ሆነ አደራረሱ ትኩረት የሚያደርገው ወንድ ልጅ ላይ ነው፡፡ መረጃ አቀባዮች እንዳሉት ካራ በጥሩም ሆነ በመጥፎ በህልም ውስጥ ይታያል፡፡ ዞሮ ዞሮ ደጉም ሆነ መጥፎውም ህልም ሲደርስ ወንድ ልጅ ላይ ያርፋል በማለት ይገልፃሉ፡፡ ስለካራ የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

> *በህልሜ ባሌ ይመስለኛል ካራውን እንቺ አስቀምጭው ብሎ ሊሰጠኝ ሲል እዛው ያዘው እስቲ ስለው አንቺ ያዥው ባንቺ ያምራል እኔማ እዴት ብየ ይለኛል ካራ መያዝ ክብዶህ ነው ብየ እቀበለዋለው፡፡ ተዚያ ተቀብየ ትንሽ እንደያዝኩት ይጠፋብኛል ተዚያ ስፈልገው አጠዋለው ተስፋ ስቆርጥ ተውኩት፡፡ እንደዚያ እንዳለመኝ አጋጣሚ እርጉዝ ነበርኩ እዳሪ ወጥ ስሰራ ምች መቶኝ ወንድ ልጅ ጠፋብኝ፡፡* (ወ/ሮ ታንጉት የወግነህ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011አ.ም)

ከላይ የተገለጸው ሃሳብ የሚያስረዳው ካራ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት በህልም ውስጥ አወንታዊ እና አሉታዊ ፍቺ እንዲሁም አደራረሱ በወንድ ልጅ እንደሚሆን ያስረዳል፡፡

**5. ጥላ፡-** በአናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ጥላ ከዝናብ እና ከፅሀይ እራስን ለመከላከል የሚጠቀሙበት መሳርያ ነው፡፡ ጥላ ለሚደርስብን ችግር ለመከላከል የሚረዳ ስለሆነ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ ጥላ በህልም ውስጥ እራሱን የቻለ ትርጉም እንዳለው መረጃ ሰጭዎች ይገልፃሉ፡፡ ስለሆነም ጥላ በህልም መያዝ ባል ማግባት ሲሆን  በህልም ጥላ መስበር ደግሞ የባል ሞት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ ሲያብራሩትም ጥላ ከችግር የምንከላከልበት ስለሆነ ባልም ከተለያዩ ችግሮች ሊያድነን የሚችል ነው፡፡ ይኸውም ከዝሙት፣ ከዘለፋ እራስን ለማሰጠበቅ እና ዘርን ለመተካት ባል አስፈላጊ ነው ይላሉ፡፡ ጥላ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት ከለላ ማለት ሲሆን ከተለያዩ ነገሮች የሚጠብቅ እና የሚከላከል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ነገር በህልም ውስጥ ለአላሚው ግለሰብ የቅርብ ወዳጅ ሆኖ የሚኖረውን ሰው የሚያመለካት እንደሆነ ያሳያል፡፡

**6. አልጋ፡-** አልጋ በተጠናው ማህበረሰብ ከተለያየ ጥሬ እቃ ማለትም ከእንጨት፣ ከጠፍር (ቆዳ)፣ ከብረት፣ ከሸቦ ወ.ዘ.ተ ከመሳሰሉት ነገሮች የሚሰራ ነው፡፡ አገልግሎቱም ለመኝታ ወይም ለመተኛነት ያገለግላል (ይውላል)፡፡ አልጋ በቅድሚያ ለባልና ለሚስት መለያየት ስለሌለባቸው ቅድሚያ የሚሰጥ ነው፡፡ አልጋን በተመለከተ መረጃ አቀባዮች በህልም አልጋ ሲሰበር ማየት የባልና የሚስት ፍቺ እና አንደኛው ሞትን ያመለክታል፡፡ በህልም አልጋ ላይ ባልና ሚስት አንድ ላይ ማደር የጋብቻውን መፅናት እና ዘለቄታ ያመለክታል፡፡ አልጋን በህልም ውስጥ ያለውን ተግባር እና ፍቺ በተመለከተ አቶ በአንተ አምላክ ታደሠ  የሚከተለውን ህልም ተናግረዋል፡፡

> *በህልሜ ተኝቼ ይመስለኛል ተሚስቴ ጋር ተኝተን የተኛንበት አልጋ በእሷ በኩል ያለው ተሰብሮ አብረን ወደቅን፡፡ ተዚያ እኔ የመጀመርያ ሚስት በህጣንነቴ ነው ያገባሁ አላውቃትም፡፡ ሁለተኛ ሚስቴን ነፍስ ታወኩ፤ ታደኩ ከአገበዋት ሚስቴ ጋር ምንም በማያጣለው ተጣልተን ይቅርታ ጠይቄ ባስማልዳትም እምብኝ አለች ተፋታን፡፡* (አቶ በአንተ አምላክ ታደሠ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

ከላይ ያለው ህልም የሚያስረዳው አልጋ በባል እና በሚስት የሚተኙበት ቁስ ሲሆን በባል እና በሚስት  የሚመጡትን አወንታዊ እና አሉታዊ ነገሮች የሚመለከት ነው፡፡

**7. ጀንዲ፡-** ጀንዲ በአናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ከቆዳ ተለስልሶ የሚሰራ መተኛ ሲሆን በአቅሙም ትልቅ እና ሰፊ ነው፡፡ እያንዳንዱ ጀንዲ  ከአንድ ከብት ቆዳ እንድ ለአንድ የሚዘጋጅ

ነው፡፡ ጀንዲ የከብት ቆዳ በደንብ ተፍቆ፣ ተለስልሶ የሚሰራ ነው፡፡ ከመረጃ አቀባዮች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ጀንዲ በህልም መዘርጋት ሀገር ነው ይላሉ፡፡ ይህ ማለትም በህልም ጀንዲ ከተዘረጋ በሀገር የሚመጣን ሀዘን፣ ደስታ፣ ድርቅ፣ ርሀብ፣ ጥጋብ ወ.ዘ.ተ የሚመለከት ነው፡፡ ጀንዲ በህልም ውስጥ ከታየ ሰፊ ስለሆነ ሀገርን የሚወክል መሆኑን አቶ ፀጋ ይመር በቃለ-መጠይቅ አማካኝነት ተናግረዋል፡፡

**8. ሽመል (ዱላ)፡-** ሽመል በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ለምርኩዝነት (ለመደገፊያ) የሚውል ከመያዣው ላይ ቅልስ እና ቀጥ ያለ ቅርፅ ያለው መደገፊያ ሲሆን በአብዛኛው ወንድ ልጅ ከልጅነት እስከ እርጅና ዘመን የሚጠቀምበት ሲሆን ሴቶች ደግሞ ጉልበታቸው ሲደክም ለመደገፊያነት ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህ በአለፈ ሽመል ጉልበት፣ ጥንካሬ፣ ብርታት ስለሚሆን የህልም ውስጥ ውክልናው ወንድ ልጅን የሚመለከት ነው፡፡ ሽመል ከህልም ውጭ በአለው የማህበረሰብ አስተሳሰብ እና አመለካከት ንብረትነቱ ለወንድ ልጅ፤ ወንድ ልጅ የሚጠቀምበት መሳሪያ ነው፤ የወንድ ልጅ መገለጫ ነው፡፡ ሽመል በህልም ውስጥ ያለውን ሚና በሙሉ የሚፈፀመው በወንድ ልጅ ላይ ነው፡፡ ሽመልን በተመለከተ አቶ ሚኒችል አባተ የሚከተለውን ህልም ከነ ፍቺው ተናግረዋል፡፡

*‹‹ሀብታሙ ካሳ የሚባል ሰው ልጅ ሲወልድ ይሞትበት ነበር፡፡ አንድ ቀን ሚስቱ እርጉዝ እንደሆነች በህልሜ ተኛቸ ለሃብታሙ ካሳ ረዥም ሽመል ቆርጨ ሰጠውት፡፡ ተዚያ ሚስቱ ወልዳ ይሞት የነበረው አደገለት፡፡ ረጅም የሚገልጠው እድሜውን ሲሆን ሽመል ደግሞ ወንድ ልጅ መውለዱን ነው፡፡ ››* (አቶ ምንይችል አባተ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ኢ.ም)

የተጠቀሰው ሃሳብ የሚያስረዳው ሽመል በህልም ውስጥ ሲታይ ጥሩም ይሁን መጥፎ እንደሁኔታው ወንድን ልጅ እንደሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ሽመል የማይዝ ወንድ ልጅ እንደ‹‹ፈሪ ሰው፤ ሴት›› ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ወንድ ነኝ የሚል ግለሰብ በሄደበት ሁሉ ሽመል መያዝ አለበት፡፡ አልያ ግን ይዋረዳል፡፡ የሚዋረደውም ድንገት ጸብ ቢነሳ ሽመል በያዙት ሰዎች ስለሚመታ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለብዙ ጊዜ ያሰድበዋል፤ ያሳፍረዋል፡፡ ይህ የማህበረሰብ አስተሳሰብ በህልም ውስጥ ተግባራዊ ሲሆን ይስተዋላል፡፡

**9. ብር መስቀል፡-** በተጠናው ማህበረሰብ ብር መስቀል አንዱ የመስቀል አይነት ሲሆን ሰዎችን ከተለያየ ጥሩ ካልሆነ መንፈስ እንዲጠብቅ የሚደረግ መሆኑ ቀዳሚው አገልግሎቱ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ቀጣይ አገልግሎቱ ደግሞ ለሃይማኖት መግለጫነት እና ለጌጥ በአንገት

ላይ ይደረጋል። ብር መስቀል በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ መገልገያነቱ በቀዳሚነት የሚሰጠው ለሴት ልጅ ነው። ሴት ልጅ እርኩስ መንፈስ እንዳይጠናወታት ስታገባ፣ ስተወልድ፣ ብቸዋን ስትተኛ እና ስትሄድ እንዲጠብቃት ይደረግላታል። ስለሆነም ብር መስቀል አብዛኛውን ለሴት ልጅ ጠባቂዋም ጌጧም ስለሆነ ከእርሷ ጋር ይያያዛል። ብር መስቀል አብዛኛውን ጊዜ ለሴት ልጅ ስታገባ  ያንገቷ የላይ፣ የታች መስቀል፣ አንባር፣ አልቦ፣ ፈርጥ (ቀለበት)፣ የጌሮ ጌጥ ወ.ዘ.ተ በመሆን ያስውባታል። ስትወልድ ደግሞ ከእርኩስ መንፈስ እንዲጠብቃት ታርሳ እስክትነሳ ድረስ ባንገቷ አልያም በመኝተዋ ይደረግላታል። ይህ ማለት ግን ወንድ አይጠቀምም ማለት አይደለም። ለብር መስቀል ያለው የማህበረሰብ  አስተሳሰብ ከወንድ በበለጠ ለሴት ትኩረት ስለሚሰጥ እንጂ። ብር መስቀል በህልም ሲደረግ እና ሲያዝ ሴት ልጅ ማርገዝ እንደሆነ መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ። የብር መስቀልን በህልም ውስጥ ሚና እንደሚከተለው እማሆይ ዋለ ገረመው ይገልጻሉ።

> *በህልሜ ይመስለኛል የልጅ ልጄ ብር መስቀል በደረቷ በሲር ተተብትቦ በአንገቷ አድርገው ሙኔ ቢዘንጋው አንዷቱን ውል ይነካት ይመስለኛል ተዚያ ሲነካት ከማሰሪያው ላይ ተፈትታ መስቀሉ ገደም ሲል እኔ ኸረ አንተ አጥብቀህ እንደገና የተፈታችትን መልሰህ እሰራት ስለው ይቺ አትሆንሽም ተያት ትፈታ ብሎ ሌሎች እንደነበሩ አንዷት ውል ተፈትታ እየተንዘላዘለች ብትት አልኩ። ተዚያ የልጅ ልጄ የመጀመሪዋን አርግዛ ከሆዷ ውስጥ ልጅት ሙታ ወጣች እሷም ተሞት አፋፍ ተረፈች። ብር መስቀል ማሰሯ ሴት ልጅ መጠነሏ ነው። ማህተቡም የተጠነሰችው ልጅ ናት። ሰውየውም ሀዘንን የሚያዘናጋ መልአክ ነው።* (እማሆይ ዋለ ገረመው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 አ.ም)

ሃሳቡ የሚያስገነዝበው ብር መስቀል በማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ ከሚሰጡት የመስቀል አይነቶች የመጀመሪያው እንደሆነ ሲሆን ትልቅ ቦታ እንዲሰጥ ያደረገውም በማህበረሰቡ ከእርኩስ (መጥፎ) መንፈስ፣ ከበሽታ እና ለከተያዩ መጥፎ ነገሮች ይጠብቃል ተብሎ በመታመኑ ነው። በመሆኑም ማህበረሰቡ በብር መስቀል ላይ ያለውን ልዩ ፍላጎት በተለያዩ ነገሮች ሲገልጽ ይስተዋላል። ከእነዚህ መካከልም ከላይ እንዳየነው በህልም ውስጥ ይገልጹታል።

**10. ጠርሙስ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ጠርሙስ ፈሳሽ ነገሮችን መያዣ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን በቤት ውስጥ ሴቶች ለአረቂ መያዣነት በአብዛኛው ይጠቀሙበታል።

ጠርሙስ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ሲታይ ጥሩም ይሁን መጥፎ ልጆችን ይወክላል። ምክንያቱም ጠርሙስ፣ ብርጭቆ፣ ብርሌ፣ መለኪያ ወዘተ የመሳሰሉት ነገሮች በዚህ ማህበረሰብ ንጽህናን፣ ጥራትን፣ ጽዳትን፣ አለመቆሸሽን ስለሚወክሉባቸው ህጻናትንም በዚሁ መንገድ ይፈርጇቸዋል። ምክንያቱም ህጻናት ቂም በቀል ስለማያውቁ ንጹህነታቸውን ከዚህ ስለሚያዩት ነው። ስለሆነም ወ/ሮ ቀኑብሽ አለሜ የሚከተለውን ህልም ጠርሙስን በተመለከተ ተናግረዋል።

*‹‹ በህልሜ የቤተ-ስኪያኑ የሰንበት ቂጣ መቁረሻ ጥዱ ተገንድሶ ጠርሙሶችን ሊሰብራቸው ሲል እናንሰው ሲሉ የማላውቃቸው ሰዎች ተውት አትንኳቸው ብየ እኔ ሰበሰብኳቸው። ተዚያ በሶስተኛው ቀን ተዚያ ትልቅ ሰው ሙቶ ከጥዱ ስር ተቀበረ። ጠርሙሶችም ልጆቼ ናቸው። ››* (ወ/ሮ ቀኑብሽ አለሜ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ኢ.ም)

ከላይ የተገለጸው መረጃ የሚያመለክተው ጠርሙስ ንጹህ ስለሆነ ከዚህ ንጹህ ቁሳቁስ ጋር በህልም የሚወከለው የህጻናት አካላዊ እና አእምሯዊ ባህሪያቸው እና ተግባራቸው እንደሆነ ነው።

**11. ቦንብ፡-** ቦንብ ፈንድቶ ሰውን የሚገል መሳርያ ነው። ቦንብ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎችን የመግደል እና የመጉዳት ችሎታ ያለው የጦር መሳሪያ ነው። ቦንብ ከሚያስከትለው ጉዳት የተነሳ አስፈሪ ስለሆነ በማንኛውም ሰው ላይ ጥሩ አመለካከት እና አስተሳሰብ የለውም። በተጠናው ማህበረሰብ ቦንብ በህልም ሲታይ ያው ቦንብ ነው። ነገር ግን በህልም ውስጥ በሚኖረው ሚና ሁለት አይነት ፍቺ ይሰጠዋል። ይኸውም በህልም በቦንብ መመታት፣ቦንብ መያዝ፣ ቦንብ መሸከም  ውክልናው የሰውን መሞት፣ በከባድ በሽታ መያዝ እና በሆነ ነገር ምክንያት መሰቃየት እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ። በአብዛኛው ሞትን ይወክላል። በሌላ በኩል ደግሞ በህልም በቦንብ ከመመታታ መዳን (ማምለጥ)፣ቦንብ ይዞ ሳይወረውሩ መቅረት የመሳሰሉትን ማድረግ ከላይኛው በተቃራኒ የሚቆም ፍቺ አለው። ቦንብን በተመለከተ ያለሙትን ህልም ቄስ ጌታቸው በላይ እንደሚከተለው ተናግረዋል።

*በህልሜ ባይነሳኝ የሚባል የአክስቴ ልጅ ይመስለኛል ቦንብ ይሰጠኝ እና እጀ ላይ ይንጫጫል ተዚያ አንተ ብዬ ቦንቡ እየትጫጫ ለምን ነው የሚንጫጫ ስለው መልሶ አንተ አታውቅበትም  ብሎ ቀምቶ በላየ ላይ ይወረውረዋል ተዚያ ዞር ስል በእኔ ላይ አልፎ ተመሬት ላይ ተእኔ ፈቀቅ ብሎ ፉም እሳት መስሎ ሲነድ አየዋለው ወዲያው ብትት*

*አልኩ። ተዚያ በጣም ቀይ የሆነ ትልቅ በሬ ነበረኝ ተዚያ እሱ ታሞ አገኘውት። ተዚያ የባህል ህክምና የሚያውቅ ላይ በበነጋታው ይዠው ሀጀ አይተረትፍም እያልኩ ነገርኳቸው ይበጣ ብለው አስበጣሁት ግን አልተረፈም ሞተ።* (ቄስ ጌታቸው በላይ፡ *ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 አ.ም)

የተገለጸው *መረጃ የሚስረዳው* በተጠናው *ማህበረሰብ* ቦንብ በህልም ውስጥ *ሲፈነዳ ማየት* በአላሚው ዘንድ ጥሩ *ያልሆነ መጥፎ* ክስተት እንደሚደርስበት *ይታመናል*። ቦንብ በዚህ *ማህበረሰብ* ከህልም ውጭ እንደሚታሰበው ሁሉ በህልም ውስጥ ተግባር *መኖሩን ነው*።

## 5.2.4 እንስሳት በህልም ውስጥ

**1. በሬ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በሬ ከቤት እንስሳት ውስጥ አንዱ ሲሆን ከቤቱ እንስሳት ዋነኛ እና እንደ ቤት ውስጥ የቤተሰብ አባወራ የሚቆጠር ነው። በሬ ከሌሎች እንስሳቶች የመጀመሪያው እና ወሳኝ ነው። በሬ እና የአንድ ቤተሰብ አባወራ አንድ ናቸው። ምክንያቱም በሬ ከአንድ ቤተሰብ አልፎ ሀገርን እያረሰ የሚመግብ ነው። በሬ እና ገበሬ የተለየ ነገር የላቸውም። አንድ አይነት ክብር እና ስራ አላቸው። በሬ አርሶ ልጆችን ያሳድጋል፣ ገበያ ያስገበያል፣ አንድ ሀገር ምርት አምርታ የውጭ ምንዛሬን እንድታገኝ እና ከሌሎች ሀገሮች ጋር ተወዳዳሪ እንድትሆን ያደርጋል። ገበሬም ከበሬው ባልተናነሰ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው። ስለሆነም በሬ በህልም ውስጥ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ እና አመለካከት ይዞ እናገኘዋለን። ይኸውም በህልም በሬ ማየት ሰው ማየት ነው። በሬ በህልም ውስጥ የሰው ልጅን ይወክላል። በሬ በህልም ውስጥ ገደል መግባት የሰው ሞት ነው። በሬ በህልም ሲያባርር ከታየ ሰው ሊመታህ ወይም ሊገድልህ እንደሆነ ይታወቃል። በሬ በህልም ገደል ሲገባ የበሬው ባለቤት ከሰው ይጋጫል ወይም ሞት ይመጣበታል። የሚከተለውን የእማሆይ ይረብ አወቀ ህልም እንመልከት።

*‹‹ በህልሜ ይመስለኛል ከመሀል ደጃፍ ቀይ በሬ ጎረቤቴ አርዶ መንደረኛውን ኑ ተካፈሉ ብሎ ሲጠራ እኔ እምብይ አልኩት። ሌላው አራጅ ብዙ ወሰደ። ተዚያ ሰውየው ልጅ ሞተበት። ››* (እማሆይ ይረብ አወቀ፡ *ቃለ-መጠይቅ*፣ የካቲት 2011  አ.ም)

ሌላኛ  ህልም ደግሞ እንደሚከተለው እንመልከት።

*በህልሜ የአክሌ ከብቶች እየተፈናጠዙ አለሙ የሚባለውን ሌላ ጠባቂ ሰውዬ ሊወጉት ሲሉ አባሯቸው ሳይወጉት ሲቀሩ አየው። ህልሙን እንዳየው ወደ ሰውየው ሀጀ አለሙ ክፉ ህልም ቀጥቅጦኛል ሰው ጠበንጃውን ብሎ ሰው እንዳይገል ብዬ ነገርኩት እሱም እሽ አለ። ተዚያ በሳምንቱ ሌላ ከሚጠብቅበት አጠገብ ሻይ ቤት የሚጠጡ ሰዎች ተሳክረው ጠበጃውን ቀምተው ሊጋደሉ ሲሉ እሱ እሩጦ አመለጣቸው። ህልሙ ሲፈታ አክሌ የሚለው የሰው ስም እክል (ችግር) መግጠመን የሚወክል ሲሆን ከብቶችም የሰከሩት ሰዎች ናቸው።* (ወ/ሮ ቀነብሽ አለሜ፡ *ቃለ-መጠይቅ*፣ የካቲት 2011 አ.ም)

ከላይ የተገለጹት ሃሳቦች የሚያመለክቱት በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በሬ በህልም ውስጥ ሲታይ ህልሙ ጥሩም ይሁን መጥፎ ሰውን እንደሚወክል ያመለክታሉ።

**2. ላም፡-** ላም እንደ በሬ ሁሉ በዚህ ማህበረሰብ ከቤት እንስሳት ውስጥ አንዷ ስትሆን ለቤቱ እንስሳት መሰረት ተደርጋ ትወሰዳለች። ላም እንደቤቱ እማወራ ትቆጠራለች። ላም በሬን መውለድ እርሻ ታርሶ ሰብል እንዲመረት የመጀመሪያውን ድርሻ ትወስዳለች። በመሆኑም ላም በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ክብር እና እንክብካቤ የሚደረግላት ናት። ላም ሴት እና ወንድ ጥጆችን በመውለድ በሬ እና መልሳ ላም የምትሆንን ሴት ጥጃ የምትወልድ (በመውለድ) ዘርን ትተካለች። በማህበረሰቡ ዘንድም ትልቅ ከበሬታ ካደረጓት  ስራዎች ውስጥ ዋነኛው ይሄ ነው። አንዳንዴም ላም እንደ በሬ ሆና ታርሳለች። ላም በዚህ እና በሌሎች ምክንያቶች በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት ውስጥ ሰርፃ የገባች በመሆኑ በህልምም ውስጥ የራሷን ድርሻ ይዛ እናገኛታለን። ስለዚህ መረጃ አቀባዮች እንዳሉት በህልም ላም መታረድ የቤት እመቤት መሞት ነው። (የሴት፣ የእናት)፤ በህልም ላም ገደል መግባት የሴት ልጅ ሞት ነው። በህልም ላም በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ካገኘነው ፍቺው ሴትን የሚመለከት እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ። የሚከተለውን የእማሆይ ዋለ ህልም እንመልከት።

*በህልሜ ላም እና በሬ ቀርበው ይመስለኛል ላሚት ላይ ተቀንዷ ላይ ቀፈት የተደረገባት ይመስለኛል ብዙ አራጅ ተሰብስቦ ላሚት ልትታረድ ስትል መንትጋቸው ትሮጣለች። በሬው ተይዞ ምንም ሳይል ታረደ። ስፈታው ላሚት እኔ ነኝ በሬው ባለቤቴ ሲሆን እሱ ሞተ እኔ ቀረው። ቀፈቱ ወይም ገመዱ የእኔ እድሜ ነው።* (እማሆይ ዋለ ገረመው፡ *ቃለ-መጠይቅ*፣ *መጋቢት* 2011 አ.ም)

የተጠቀሰው ህልም እንደሚያስረዳው ላም ሴት ልጅን በተለይም እማወራን ወይም እናትን የምትወክል ስትሆን በሬ ደግሞ የወንድን ልጅ አባትን ወይም አባወራን እንደሚወክሉ ነው፡፡ ይኸውም ላም እና በሬ እንደ እናት እና አባት የጥጆች፣ የወይፈኖች እና የጊደሮች እናት እና አባት ናቸው፡፡ እናት እና አባትም በቤቱ እንደዋና አስተዳዳሪ የሚቆጠሩ ሲሆን ከህፃናት እስከ ትልልቅ ልጆች የሴቶች እና የወንዶች እናት እና አባት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የላም እና የበሬ ወይም የእናት እና ያባት ያላቸው ሚና በአብዛኛው አንድ አይነት ስለሆነ በህልምም ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

3. **ፍየል፡-** ፍየል በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ከቤት እንስሳ ውስጥ አንዷ ናት፡፡ ፍየል በአብዛኛው በቆላማው እና በደጋማው ቦታ የምትገኝ መሆኗን ከመረጃ ሰጭዎች ሃሳብ ማግኘት ተችሏል፡፡ ይኸውም ፍየል ቅጠላቅጠል የምትበላ ስለሆነች በቆላው እና በደጋው አየር ንብረት ብዙ ተራራማ ቦታ ስላለ ዛፍ በብዛት በዛ ይገኛል፡፡ ነገር ግን በወይና ደጋው ፍየል የለም ማለት አይደለም፡፡ ወይና ደጋው አካባቢ ሜዳ ስለሆነ በአብዛኛው ለሰብል ምርት ስለሚያገለግል ብዙም ዛፍ ስለሌለበት ነው፡፡ እንስሳዋ በአንድ ጊዜ ሁለት እና ከዚያ በላይ የምትወልድ እንስሳት ናት፡፡ ብትሆንም ግን በማህበረሰቡ እርኩስ እንደሆነች ይታመናል፡፡ ፍየል እንደ ሰይጣን ትቆጠራለች፡፡ በማህበረሰቡ ፍየል እና ክፉ የሚሰራ(ሃጢያተኛ)ሰው አንድ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ይኸውም ፍየል ሀፍረተ ስገዋን የማትሸፍን እና ገልጣ ምትሄድ ስትሆን ሃጢጣተኛ ሰውም እንደዚሁ ክፉን ስራ በአደባባይ የሚሰራ፣ የሰዎችን መጥፎነት ብቻ የሚመለከት  የምትቆጠርበትም ምክንያትም በመፅሀፍ ቅዱስ ፈጣሪ ሰይጣንን በፍየል ስለሚመስለው እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ስለሆነም ፍየል በህልም ውስጥ ያላት ተግባር እኩይ የሆነ ሲሆን እኩይነቷ ከማኅበረሰቡ የሃይማኖታዊ አስተሳሰብ እና አመለካከት አንጻር እንደታየ ያስገነዝባል፡፡

4. **በግ፡-** በግ ከቤት እንስሳት አንዷ ነች፡፡ በግ ስጋው ለምግብነት እና ቆዳው ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል፡፡ በግ በተጠናው ማህበረሰቡ ውስጥ በጥሩ ነገር ትመሰላለች፡፡ ስለሆነም በግ በህልም ውስጥ ሲታይ እንደ መልአክ እና እንደ ሰው ይቆጠራል፡፡ በግ በህልም ስትሄድ ከተከተለህ ወንድም ወይም እህት እናትህ ልትወልድልህ ነው፡፡ በህልም ከበግ ጋር ካደርግ መንፈስ ቅዱስ እንደ ቀረበህ ይቆጠራል፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት በግ በህልም መታረድ የሰው ሞት ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚያብሄር (ፈጣሪ) ሰውን በበግ ይመስለዋል ተብሎ በዚህ ማህበረሰብ ስለሚታመን ነው፡፡ ስለዚህ የሚከተለውን መረጃ የወ/ሮ የንጉሴ በላይን ህልም እና ፍቺ እንዴት እንደደረሰ እንመልከት፡-

*ይመስለኛል በህልሜ ተኝቼ ተእህቴ ልጅ ቤት ጋጥ ቀይ በግ ሰው ተሰብስቦ ልትታረድ ስትል ተንፈራግጣ ስትነሳ እኔም ብትት አልኩ። ተዚያ በበነጋታው ቤተ- ክስያን ህፎ የህቴን ልጅ አጠኋት። ጎረቢቶቿን አግኝቼ ስጠይቅ በጣም ከባድ ህመም አሟት እንደተኛች ነገሩኝ፡፡ ተዚያ በኋላ ቀን ታማ ልትሞት ነው ሲባል በአልጋ ላይ ምቅቅ ብላ ተምንጣፍ ጠፍታ ዳነች።* (ወ/ሮ የንጉሴ በላይ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኣ.ም)

በግ በህልም ውስጥ አወንታዊ እና አሉታዊ ፍቺ አለው። በግ በሰው ልጅ ላይ የሚደርሰውን ሁሉ ነገር በህልም ውስጥ ትምዕምርት ሆኖ አጣርቶ እንደምልክት ሆኖ አቅጣጫ በማመልከት ማንነትን ይነግራል።

**5. ፈረስ፡-** ፈረስ የጋማ የቤት ውስጥ እንስሳ ነው። ፈረስ ለትራን ስፖርት አገልግሎት የሚውል ነው። በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ፈረስ ማየት መልአክ ነው ይባላል። ፈረስ በውክልናው በህልም ውስጥ በጥሩነት ነው። ምክንያቱም ፈረስን የሚሰቀሉት መልአክ ስለሆኑ መንፈስ ቅዱስ የቀረበው ነው፤ ሰይጣን አይሰቀለውም የሚል በማህበረሰቡ እምነት አለ። መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት የቅዱስ ጊወርጊስን ፈረስ እንደምሳሌ ይሰጣሉ። ፈረስ በህልም ውስጥ ሲታይ የህልሙን ጥሩነት አስቀድሞ በነበራቸው እውቀት ፈተው ይጠቀሙታል። የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

> *በህልሜ ብዙ ፈረስ ያለኝ ይመስለኛል እና እንዴት እረቡልኝ እያልኩ እየተደሰትኩ እንዳው ቢሄዱት ቢሄዱት እልቆ የሌለው እና የሳሩ ልምላሌው፣ አስተዳደጉ የሚያሳሳ መስክ ወስጃ ሳበላቸው አየው። ተዚያ የአቦ ማበር የለኝም ነበር እና አቦ ገብቼ ዝግርቱ የኔ ሁኖ ዝክርት ዘከርኩ። እነዚያ ፈረሶች በመልአክ ተመስለው ነው፣ እነሱን ማብላቴም በእነሱ ስም ዝክርት መዘከሬን ነው።* (ወ/ሮ አበቡ ተገኘ፡ ቃለ-መጠይቅ፣የካቲት 2011ኣ.ም)

*ሃሳቡ የሚያመለክተው በተጠናው ማህበረሰብ ፈረስ ቅድሳን መላይክት የሚገለገሉበት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ እና ስለሚታመን በህልም ውስጥም ይህ እውቀት ተግባራዊ እንደሚሆን ነው።*

**6. በቅሎ፡-** በቅሎ ከጋማ ከብቶች አንዷት ስትሆን ለትራንስፖርት እና ለጭነት አገልግሎት ትውላለች። በቅሎ የማትወልድ መካን ፍጡር ናት። በቅሎ በማህበረሰቡ እንደሰይጣን

ትቆጠራለች፡፡ ምክንያቱም መካን የሆነችበትን ምክንያት እግሯን በማንሳት አባቷን እረግጣው አባቷን ባለማክበሯ አባቷ ስለረገማት መካን ሆናለች ስለዚህ ጥሩ ያልሆነች እንስሳት ናት በሚል አስተሳሰብ ነው፡፡ አንዳንዶች አባቷን በእርግጫ ስለመታችው ነው ይላሉ፡፡ ሌሎች ሰዎች ደግሞ በጣም ጠግባ ስለነበር ሰማዩን ሽቅባ በእርግጫ ስለመታችው ሴት ልጅ እግሯን ስለማታነሳ እርሷ አንስታ ተራግጣ ስለሆነ ተረግማ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ አንፃር በቅሎ እንደ ጥሩ አትታይም፡፡ በህልም ውስጥም ስትታይም ህልም ያየው አካል ከህልሙ በስተጀርባ ጥሩ ያልሆነ ክስተት እነደሚገጥመው ያስባል፡፡ መረጃ አቀባዮች እንዳሉት በህልም በቅሎ ማየት ከእርኩስ መንፈስ ወይም ከሰይጣን ጋር ማደር ነው፡፡ በተለይም በህልም በቅሎ መሰቀልን፣ በቅሎ ጭኖ መሄድን፣ በቅሎ መሳብን ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ስናይ ጥሩ እንዳልሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቅሎን በህልም መምታት፣ ማባረር፣ ጉድጓድ ውስጥ መክተት፣ ጥሎ መሄድ፣ መግደል ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ማየት ደግሞ ሰይጣንን ማራቅ ወይም ማሸሽ እንዳይቀርብ ማድርግ ነው፡፡

**7. ድመት፡-** ድመት የቤት ውስጥ እንስሳት ስትሆን ቤትን ከአይጥ ለመከላከል ትጠቅማለች፡፡ ድመት በአብዛኛው የምትመገበው ስጋ ሲሆን የምትጠጣው ደግሞ ወተት ነው፡፡ ድመት ከሰው ጋር አብራ ተላምዳ የምትኖር ስለሆነች ማህበረሰቡ እንደመንፈ ስቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ይቆጥራታል፡፡ በህልም ውስጥ ድመት ሲታይ ጥሩ ነገር ይገጥማል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያትም ድመት ከሌሎች እንስሳት ተለይታ ቤተ መቅደስ መግባት የምትችል ስለሆነች ቅዱስ ናት የሚል አመለካከት እና አስተሳሰብ በማህበረሰቡ ዘንድ ስላለ ነው፡፡ ስለድመት በህልም ያላትን ተግባር እና የህልም ፍቺ ከማህበረሰቡ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ነው፡-

> *በህልሜ መንታ መንገድ ላይ ቆሜ የምኼድበት መንገድ ጠፍቶኝ ይመስለኛል በዚህ ልሀድ በዚያ ልሀድ እያልኩ ግራ ስጋባ ሻሽ የመሰለይ ድመት መታ ነይ በዚህ እያለች እየመራች ስትወስደኝ እኔም ጣል ጣል ያልኩ እየተከተልኳት ተአንድ መልኩ ተሚያብረቀርቅ፣ ሽታው ተሚያውድ ቤት ይዛኝ ትገባለች ኧረ የት ይዘሽኝ መጣሽ ስላት አንቺ ከእንግዲህ ግራ መጋባት የለብሽም ከዚህ መንገድ አትውጪ ብላ አስገብታኝ የኼደችበት ጠፋኝ እኔም ብትት አለኩ፡፡ ተዚያ በጥቅምስ ያየሁት ህልም የትሳስ ባታ እንዳው ሳላስበው በእድሜያቸው የገፉ ያሉ ጎረቢቶቼ ላሊበላ እንሂድ ብለው አደፋፍረው ኧረ ምንነቱን ሳላውቀው ተውኝ ስላቸው አንቺ ተእንግዲህ ምን ልትባይ ነው ብለው*

*እነሸኝ ባታን ታሳስ 3 ቀን ተሳልመን ህደን ሲገርመኝ ሲደንቀኝ ሰንብቸ መጣው እኔም እየው ተዚያ ወዲህ በእያመቱ ቀርቸ አላውቅም፡፡ (እማሆይ ባሳዝን ሙኔ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 አ.ም)*

የተገለጸው ሃሳብ የሚያስረዳው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እያንዳንዱ ግለሰብ አስተሳሰብ እና አመለካከት ውስጥ የድመት ንጽና ሰርጾ የገባ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ድመት በተገለጸው ህልም የጽድቅን መንገድ እንዳሳየች ያመለክተናል፡፡

**8. ውሻ፡-** ውሻ እንደ ድመት ወተት እና ስጋ በአብዛኛው የሚጠቀም ወይም የሚበላ እና የሚጠጣ የቤት እንስሳ ሲሆን ቤትን ከአዳጋ ለመከላከል፣ ለመጠበቅ የሚጠቅም እንስሳ ነው፡፡ ውሻ በማህበረሰቡ ታማኝ ጠባቂ እንደሆነ ይታመንበታል፡፡ ውሻ ልክፋት የሚባል መጥፎ በሽታ ያለው ሲሆን ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለሰውም የሚተርፍ ከባድ በሽታ የሚይዘው ነው፡፡ ከዚህ ጋር በሚያያዝ የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ውሻ በህልም ሲነክስ ውሬዛ የሚባል መንፈስ ይይዛል በማለት ይናገራሉ፡፡ ውሻ በህልም ውስጥ ጥሩ ያልሆነ ትምዕርት ተደርጎ ይወሰዳ፡፡ የሚከተለውን ከማህበረሰቡ የተገኘውን ህልም እንመልከት፡-

*በህልሜ የእኔ ውሻ ይመስለኛል ጥቁር፣ ወፍር ነው እና ሳደልበው የኖርኩ እና አንድ ቀን እርቦት ሳልሰጠው ቀርቼ ሲያባርረኝ ሲያባርረኝ እግር ባቴን ቡጭቅ ሲያደርገኝ ብትት አልኩ፡፡ ተዚያ የእናት የአባቴ አምላክ እያልኩ የማመልከው የጥር ደም፣ የሰኔ ደም፣ የህዳር ሚካኤል ደም እያልኩ ዳንግሌ በግ እና ሰሎላ ደሮ እና በሶው፣ ቆሎው፣ ዳቦው፣ ቡቅሩ ሳይቀር እኛ ሳንቀምሰው ጅኑ ይቅመሰው እያልን እህሉን እየወረወርን ነበር፡፡ ተዚያ አንድ አመት የህዳር ሚኪያል ገንዘብ አጥቼ አንድየበት ተዚያ ተብዙ ጊዜ በኋላ ጥብቅ እመም አመመኝ እና ጀር ቅዱስ ገብርኤል ጠበል ገብቼ ስለፈልፍ እኔ ውሬዛ ነኝ ብሎ እንዳንደልኩ በትተናገረ፡፡* (ወ/ሮ ታንጉት የወግነህ፡ ቃለ-መጠይቅ፣መጋቢት 2011አ.ም )

**9. እባብ፡-** እባብ በደረቱ የሚሳብ ገመድ መሰል ተናዳፊ ፍጡር ነው፡፡ እባብ ሲናደፍ መርዝ ስላለው እስከ ሞት ድረስ ያደርሳል፡፡ ስለሆነም በተጠናው ማህበረሰብ በህልም እባብ ሲያባርር፣ ሲነክስ እና በሰውነት ላይ ሲጠመጠም ሲታይ ብዙ አይነት የህልም ፍቺ እንዳለው መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ይኸውም እባብ በህልም ሲያባርር ምቀኛን፣ ምላስን እና ውሬዛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት በህልም እባብ ሊናደፍ ወይም ሊበላ

ሲያባርር ለቤተ-ክርስቲያን ይህን ታደረክልኝ፣ ከደረሰልኝ ተብሎ ለፈጣሪ የሚሰጥን ብር ሆነ እህል በማህበረሰቡ አባባል ‹ስለት›› ይባላል እናም በሰአቱ ሳይሰጥ ሲቀር የሚታለም እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ የሚከተለውን የአባ ብሬ ተካን ህልም እንደሚከተለው እንመልከት፡-

*ብዙ ጊዜ ተጎረቢቶቼ ጋር መውጫ መንገድ በእያመቱ እያጠበቡ እየዘጉብን፣ልጆችን እና ከብቶችን እየደበደቡ እየተጣላን ሲያስቸግረኝ በወረዳ ከስሸው መከሰሱን ሲሰማ ለእየባለስልጣኑ ያላደረገው ነገር የለም፡፡ እኔም ሁሉን እየሰማው ዝም ብየ ተቀመጥኩ ብዙ ቀን እንደተመላለስን አንድ ቀን በህልሜ አንድ ወፍራም ጥቁር እረዥም እባብ ሊበላኝ ተወዲያ ተወርውሮ ሊበላኝ ሲል አናት አናቱን ቅጥቅጥ አደርጌ እገድለው ይመስለኛል፡፡ ተዚያ ብንን ብዬ ለባለቤቱ አንቻ ይህን ሰውዬ ልረታው ነው መሰለኝ እንዲህ ብሎ አለመኝ አልኳት፡፡ ተዚያ በሌላው ቀን ለእኔ ተፈርዶልኝ እሱም ቅስሙ እንክት ብሎ መንገዱ እንደልብ ተከፈተልኝ፡፡* (አባ ብሬ ተካ፡ቃለ-መጠይቅ፣መጋቢት 2011ዓ.ም)

**10. አይጥ፡-** አይጥ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ አስተሳሰብ እና አመለካከት ጥሩ ያልሆነች ፍጡር ስትሆን እንደ ሰይጣን መልእክተኛ ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ አይጥ በህልም ስንመለከታት በአብዛኛው መጥፎ የህልም ገፀ ባህሪ ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ አይጥ በህልም ከታየ በአላሚው ላይ መጥፎ ነገር እንደሚመጣበት ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ስለሆነም አይጥ በህልም ከቦሀቀው ወይም ቡኮ ከሚቦካበት ስትገባ ከታየ ምቀኛን ይገልፃል፡፡ አይጥ በህልም ሲታይ የእርኩሰት (ቅዱስ አለመሆንን) መግለጫ መሆኗ ይታመንበታል፡፡ ስለ አይጥ የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

*በህልሜ አንድ ቀን ከእንጀራው ሙኸዶ ውስጥ ገብታ እንጀራውን ቡጭቅጭቅ አድርጋ መሀል መሃሉን በልታው ይመስለኛል እራሴን ይዤ አዝን እያልኩ ከእንግዲህ ምን ያደርጋል አፈር ትብላና የእሷን ትርፍ ማን ይበላል እያልኩ አንድ ሳላስቀር የሞኸዶውን እንጀራ አውጥቸ እደፈዋለው፡፡ ተዚያ ጎረቢቶቼን እኔማ እንዲህ ስሆን አደርኩ ብየ ነገርኳቸው አይጥ በህልም ስትታይ መጥፎ ናት ደሞ እንጀራሽን በላችው፣ አንቺም እንጀራውን አውተሽ መጣልሽ ጥሩ አደለም ብለው አይ አሉ፡፡ ተዚያ እንዳሉትም ቀስ በቀስ ሀብቴ ወደመ ምኑን ተምን ላድርገው ግራ ተጋብቼ የምጨብጠው ሳጣ አሁን የየድስ (የቁጠባ) ብር ተበድሬ እዳውን መክፈል እና ተእዳው መላቀቅ አቅቶኝ*

*እሰቃይልሻለው እና አይጥ መጥፎ ናት፡፡* (ወ/ሮ ታንጉት የወግነህ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት2011አ.ም)

**11. አህያ፡-** አህያ በተጠናው ማህበረሰብ ለጭነት አገልግሎት የምትውል የቤት እንስሳት ናት፡፡ በአህያ ላይ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ሁለት አይነት አመለካከት አለው፡፡ አንደኛው አህያ ማለት በአወንታዊ መንገድ ቻይ ወይም የመቻልን ተግባር የምታከናውን ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቻይነቷን ወደ አሉታዊ በመውሰድ ከባድ ችግር፣ የማይቻል ነገርን የምታመለክት ናት፡፡ አህያ አለማወቅን፣ ከነገሮች ሁሉ ነፃ መሆንን የምትወክል ናት፡፡ ስለሆነም አህያ በህልም ውስጥ ሁለት አይነት ነገርን ትወክላለች፡፡ መረጃ አቀባዮች እንዳሉት በህልም አህያ ጤፍ ጭኖ ይዞ መሄድ የገንዘብ መጥፋት ያጋጥማል ይላሉ፡፡ ይኸውም አህያ በህልም ከባድ ነገርን የምትወክል ስትሆን ጤፍም እንደዚሁ ከባድ አደጋን የሚወክል ነው በማለት መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡ የሚከተለውን የአቶ ቢያድጌ ይወጉን ህልም እንመልከት፡-

> *በእውኔ ማሪያም ቤተ-ስኪያን እየተመላለስኩ እጠልያለው፤ ምነው የማትሰሚኝ እያልኩም እጠይቃለሁ፡፡ ተዚያ አንድ ቀን በህልሜ እንደ እውኔ ህጄ የምጠልይ ይመስለኛ፡፡ ተዚያ እየጠለይሁ አንድ ሀለሌ አህያ ሲመጣ ልመታው ስል ዘሎ ቤተ-መቅደስ ይገባል፡፡ ተዚያ ብንን አልኩኝ በበነጋው ህልሙን ስፈታው ሃለሌ አህያው ያፈረሰ ጨስ ነው፡፡ ዘሎ ቤተ-መቅደስ የገባው ተቄስ ውጭ ቤተ-መቅደስ የሚገባ ስለሌለ እሱ ነው፡፡ በእውኔ የማትሰሚኝ ያልኳት በህልም ያፈረሰጨስ ስለቀድ ስለረከሰች እንደሆነ ማሳያ ነው፡፡* (አቶ ቢያድጌ ይወጉ፡ ቃለ-መጠይቅ፣መጋቢት 2011አ.ም)

**12. ዝንጀሮ፡-** ዝንጀሮ በአብዛኛው በቆላማ አካባቢዎች ጥራጥሬ በመመገብ የሚኖር የዱር እንስሳ ነው፡፡ ዝንጀሮ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰብሎችን መብላት (ማውደም) የሚችል እንስሳ በመሆኑ በቆላማ አካባቢ የሚገኙ ማህበረሰቦች ሰብላቸው ተዘርቶ እስኪመረት፣ ከቤት እስኪደርስ ድረስ እየጠበቁ ይጠቀማሉ፡፡ አልያ ግን ዝንጆሮ ስለሚበላው ረሀብ ሊከሰት ይችላል፡፡ ዝንጆሮ በህልም የተለያየ ትርጉም አለው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በቆላው አካባቢ በተገኘው መረጃ መሰረት ዝንጆሮ በህልም ሲታይ ርሀብ ይሆናል፡፡ ሌላው ደግሞ ዝንጆሮ ከቆላው ወደ ደጋው ሲወጣ በህልም ከታየ በቆላው ድርቅ እንደሚይሆን ይታወቃል፤ በህልም ከደጋው ወደ ቆላው ዝንጀሮ ሲገባ ከታየ አዝመራ ይሆናል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ምክንያታቸውም ዝንጀሮዎች የሚወጡት የሚበላ የተዘራ አዝመራ (ሰብል) ሲያጡ ነው፡፡ ዝንጀሮዎች የሚገቡት

ደግሞ የሚበሉት አዝመራ ወይም ሰብል ስለሚያገኙ ነው በማለት አቶ ቢተው ሰው አገኝ በማብራራት ገልፀውታል።

**13. ጅብ፡-** ትልቅ የዱር እንስሳ ሲሆን በተጠናው ማህበረሰብ በህልም ውስጥ የተለያየ ፍቺ እና ትርጉም አለው። በህልም ጅብ ሲበላ ቡዳ ነው ተብሎ ይታመናል። በህልም ጅብ ማባረር እና መግደል ርሀብን ማሸነፍ ነው። ጅብ በህልም ውስጥ ርሃብን እና ቡዳን ይወክላል። የሚከተለውን ከማህበረሰቡ የተገኘውን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹በህልሜ ደምሴ የሚባል የመንደራችን ሰው በድምድም ጓንዴ ጅቡን ሲገለው አየው። ተዚያ ያሰው በዚያኑ አመት ሁለት ሶስት ጉተራ ማሽላ አገኘ። ጅብ እርሀብን ይወክላል ደምሴም ረሀብን የሚደመስስ ማለት ሲሆን ድምድም ጓንዴም ወንድ ልጅን የሚመለከት ሀሳብ ነው። ›› በማለት ገልጸዋል።* (አቶ ምንይችል አባተ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

የተጠቀሰው ሃሳብ የሚያመለክተው ጅብ ከሌላው እንስሳት በተለየ ሆዳም ነው ተብሎ በማህበረሰቡ ስለሚታመን ሆድን ድገሞ ከርሃብ እና ከጥጋብ ጋር በማገናኘት አስተሳሰባቸው እና አመለካከታቸውን በህልም አማካኝነት እንደሚገልጹ ያሳያል።

## 5.2.5 እፅዋት በህልም ውስጥ

**1. ጌሾ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ጌሾ በአብዛኛው ለአረቂ እና ለጠላ ማዘጋጃነት የሚውል እፅዋት ሲሆን አንድ አንድ ወፍራም እግሮች በ ትንንሹ ከተከተከቱ በኂላ አድርቆ በመውቀጥ የሚዘጋጅ ነው። ጌሾ በሁሉም የአየር ፀባይ የሚበቅል እፅዋት ነው። ጌሾ ጣዕሙ መራራ ነው። ጌሾ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ውስጥ የሚታይ ትዕምርት ሲሆን ፍቺ እና ትርጉሙ ከሁለት አቅጣጫ አንፃር የሚታይ ነው። አንደኛው አሉታዊ ሲሆን በህልም ጌሾ መሸከም፣ ማንፈስ፣ መትከል እና መውቀጥ የዘመድ ሞት ነው። ጌሾ መራራ ስለሆነ መራር ሀዘን ውስጥ መግባትን ያመለክታል። ሁለተኛው ደግሞ አወንታዊ ሲሆን ጌሾን በህልም ከገደል መጣል፣ መቁረጥ እና በሳት ማቃጠል ሞትን ማሸነፍ እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ። የሚከተለውን የእማሆይ ባሳዝን ሙኔ የህልም መረጃ እንመልከት።

> *አንድ ጊዜ በህልሜ መልኩ እሚያስደንቅ፣ ከቅጠሉ ቅባት የሚቀዳ የሚመስል ወዝ ያለው ጀሾ ደጅ ሁኘ ተዛፍ ስር በደስታ እየተፍለቀለኩ እወቀጥ ይመስለኛል። ተዚያ እየወቀጥኩ እያለ ተላይ ተዛፉ ላይ አንዷት ቅርንጫፍ ተዘንጥላ ወድቃ እራሴን ክው*

*አርጋ ስትጥለኝ አይቸ ብንን አልኩኝ፡፡ ተዚያ ብዙ ቀን ተቀምጠን የእኔ ሶስተኛ ልጅ ምንም የማያውቀው መጋዘን ሰረክ ተብሎ በወታደር ተይዞ እየተቀጠቀጠ ሲኼድ እኔንም አብራቹህ በሉኝ እያልኩ እየተከተልኩ ስጮህ ብዙ እንግልት ደርሶብኛል፡፡ ጀሽ መውቀጤ ያላሰብኩት ይኼ መራር ነገር ሊመጣብኝ ነው፤ ደስታየም ሃዘኔ ነው፣ የዛፉ እና ቅርንጫፍም ዛፊቱ እኔ ነኝ ቅርንጫፉ ልጀ ነው፣ በቅርንጫፉ መመታቴ በልጄ ምክንያት የደረሰብኝ ሃሰብ እምስልስል ነው፡፡* (እማሆይ ባሳዝን ሙኔ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011  አ.ም)

**2. በርበሬ፡-** በርበሬ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ በቆላማ አካባቢዎች የሚመረት ሰብል ነው፡፡ በርበሬ በህልም ውስጥ ትልቅ ሚና አለው፡፡ በዛ ማህበረሰብ በርበሬ ብዙሀኑ ምርታቸው ስለሆነ ስለ በርበሬ አጠቃላይ ሁኔታ እውቀቱ እና ፍልስፍናው አላቸው፡፡ ስለሆነም በርበሬን በህልም ውስጥ በተለያየ አቅጣጫ ማየት የተለመደ ነው፡፡ በህልም በርበሬ ማገላበጥ፣ በርበሬ መትከል እንደ ሞት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ማህበረሰቡ በበርበሬ ያለው አስተሳሰብ እና አመለካከት በጣዕሙ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በመሆኑም እንደ ህልማቸው ሁኔታ አሉታዊ እና አወንታዊ ትርጉም እንዳለው ይገልጻሉ፡፡

**3. ዥንፎቅ፣ ለንቋጣ፣ ገበያ፣ ዋጫ እና አጧር፡-** እነዚህ እፀዋቶች በአብዛኛው በእናርጅ እናውጋ ወረዳ በቆላማው አካባቢ የሚበቅሉ ሲሆን የህልም መረጃውም ከዚያው የተገኘ ነው፡፡ ነገር ግን ሌላ አየር ንብረት በአላቸው ቦታዎች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህ እነዚህ እፀዋቶች ለሚገኙበት ማህበረሰብ እንደ አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች ሆነው ሲያገለግሉ በህልም ውስጥ እናገኛቸዋለን፡፡ በተለይም አዝመራ ከመዘራቱ በፊት በእነዚህ እፅዋቶች አማካኝነት ምን መዘራት እንዳለበት በህልም እንደሚነገራቸው መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ በህልም ውስጥ እፅዋት ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ እነዚህን እፅዋት በህልም ሲታዩ በአካባቢው ምን አይነት አዝርት መዘራት እንዳለበት ስለሚታወቅ ለማህበረሰቡ ተጠቃሚነት የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት በህልም ዥንፎቅ አፍርቶ ማየት ማሽላ እና ጤፍ ሲዘራ ያምራል ማለት ነው፡፡ ዋጫ ሲያብብ ደግሞ ጤፍ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ለንቋጣ ሲያፈራ ዘንጋዳ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በህልም እነዚህን ዛፎች መጠጋት ጥሩ ሲሆን በህልም መቁረጥ ግን ጥሩ እንዳልሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ እነዚህ ዛፎች በአብዛኛው በህልም ሲታዩ የዘመኑን አካባቢያዊ የሆነ የአዝመራ ሁኔታን የመተንበይ ስራን የሚያሰሩ የህልም ውስጥ ትዕምርቶች ናቸው፡፡ ሰለእነዚህ እጽዋቶች ህልማዊ ተግባር የተናገሩት አቶ ቢተው ሰውአገኘው በአራራ

ቀበሌ በህልም ፈቺነት የሚታወቁ እና በማህበረሰቡ የሚታመኑ ሰው ሲሆኑ ከህልም ፈቺነት ስራቸው በአሻገር ህልም በማለም በቀቤሊያቸው የሚሆነውን እና ሊደረግ የሚገባውን ነገር የሚናገሩ ሽማግሌ ሰው ናቸው፡፡ ሰውየው እንዳሉት ከእሳቸው በአለፈ ስለሌሎች ሰዎች፣ ስለሃገር እና ስለአካባቢያቸው እንደሚያልማቸው እና ለማህበረሰቡ በቤተ-ክርስቲያን፣ በአደባባይ እና በተለያዩ ድግሶች ተገኝተው በመናገር ማህበረሰቡ የሚያደርገውን ነገር በጥንቃቄ እንዲያደርግ እንደሚነገሩ ገልጸዋል፡፡ የሰውየውን ሃሳብ በመመርኮዝ የተለያዩ ሰዎችን አናግሬ ምላሻቸው ሰውየው የተናገረውን ደግመውልኛል፡፡

**4.ጥንጁት፡-** ጥንጁት በተራ ቁጥር 3 እንደተገለፁት እፅዋቶች በአብዛኛው በቆላ አካባቢ የሚበቅል ነው፡፡ ይህ ማለት በደጋ እና በወይና ደጋ የለም ማለት እንዳልሆነ ሌብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን በብዛት የምናገኘው በቆላው አካባቢ ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ይብቀል እንጂ በህልም ውስጥ አገልግሎቱ ለሁሉም ማህበረሰብ እንደሆነ ከተጠኝዎች የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በህልም ጥንጁት ሲታጠን ማደር፣ መሽከም፣ ከሌላ ሰው መቀበል ደህንነትን ወይም ፈውስ ማግኘትን እንደሚመለከት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ጥንጁት ከእርኩስ መንፈስ እንዲከላከል አራስ እንድትታጠነው እና ጠበል እስክትረጭ ድረስ እየያዘች እንድትቀሳቀስ የእርሷ ልብስ እና የልጁ ልብስ ታጥቦ ሲሰጣ እርኩስ መንፈስ እንዳይጠናወተው ከላዩ ላይ ጥንጁት እየተደረገ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም ብቅል ሲሰጣ ከላዩ ላይ ጥንጁት ይደረግበታል፡፡ ሰው ሲሞት እሬሳው በጥንጁት ይታጠናል፡፡ የጠላ መጥመቂያ እቃው በጥንጁት ይታጠናል፡፡ ቡዳ የያዘው ሰው ጥንጁት ሲታጠን ይለፈልፋል፣ ይፈወሳል፡፡ ስለዚህ ከዚህ አንጻር በጥንጁት ላይ ያለው የማህበረሰብ አስተሳሰብ እርኩስ መንፈስን ማስወገጃ የሚለው ሚዛን የሚደፋ ስለሆነ በህልም ጥንጁት ማየት ፈውስን እንደሚመለከት መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡ የሚከተለውን የአቶ ዳኘ ሰሬን ህልም እንመልከት፡-

> *አሞኝ እንደተኛው በህልሜ አንድ ቀይ ሰውየ ግብስብስ እያለ መቶ ጉፍጥፍጥ እያደረገ ጥጁት ያጥነኝ ይመስለኛል፡፡ ተዚያ ይህን ህልም እንዳለምኩ ውሎ አድሮ ህመሜ ሲጠናብኝ የንስሀ አባቴ መተው ለባለቤቴ እና ለልጆቼ ቤተ-ስኪያን አምጡት እና ውሀ እየቀዳችሁልኝ እየደገምኩ ሁለት ሰባት ይጠመቅ ብለው አስወስደውኝ እድናለሁ ሳላል አባ ያሉት ቀን ሳይደርስ ተጠምቄ ዳንኩኝ፡፡ (አቶ ዳኘ ሰሬ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት2011አ.ም)*

**5. ወይራ፡-** ወይራ ጠንካራ እና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል እፅዋት ነው፡፡ ወይራ ጠንካራ ስለሆነ ቤት ሲሰራ ከተገኘ አልፎ አልፎ ቤቱ ቶሎ እንዳይወድቅ ሲባል ይደረግበታል፡፡ የማይ ወይም የቅዳሴ ፀበል መቅጃ እንስራ ወይም ማድጋ ይታጠንበታል፡፡ የወተት እና ሌሎች የፈሳሽ ነገሮች ማስቀመጫ እቃዎች ይታጠኑበታል፡፡ ሌላው ደግሞ የቤተ-ክርስቲያን ዘይት ከወይራ ዛፍ ይዘጋጃል፡፡ ወይራ በማህበረሰቡ ውስጥ ከቤት ውስጥ አገልግሎት ባለፈ ገበያ አውጥቶ በመሸጥ ገቢ ማስገኛ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ወይራ በተጠናው ማህበረሰብ የህልም አስተሳሰብ እና አመለካከት ፍልስፍና በርካታ አገልግሎቶች ቢኖሩትም በህልም ውስጥ ግን ያን ያህል ጥሩ የሚባል አይደለም፡፡ ይኸውም የህልም ውስጥ ተግባሩ ከጣዕሙ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መረጃ አቀባዮች እንዳሉት ወይራ በህልም ማየት ጥሩ አይደልም ይላሉ፡፡ ወይራ በህልም ማየት መራራ ነገር እንደሚገጥመን (ሊገጥምን) እንደሆነ ምልክት ነው ይላሉ፡፡ ምክንያቱም ወይራ ከቅጠሉ እስከ ግንዱ ድረስ መራራ ስለሆነ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ስለወይራ የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

> *በህልሜ ወይራ ቅጠልም ሆነ ግንዱን ተሸክሜ ካየው በበነጋታው ሳይውል ሳያድር የሆነ መጥፎ ነገር ይገጥኝመኛል፡፡ አንድ ቀን ሚስቴ ትመስለኛለች ወይራ ቅጠሉን ቆርጣ ቆርጣ እንካ ተብዙ ነገር ይጠብቅሃል ብላ ትሰጠኝ ይመስለኛል፡፡ ተዚያ ህልሙን እንዳየሁት በሳልስቱ የእሷ ዘመዶች በጣም ውራጆ፣ ቂማርተኛ፣ ሰካራም ናቸው እና አንድ ቀን ገበያ ውየ ስመለስ ብቻየን ነበርኩ ቅጥቅጥ አድርገው፣ ታለታዛቢ ጥለውኝ ህደው አንድ ሰው ስንጉር፣ ስጮህ ድንገት ሰምቶ ደንግጦ ተሩቅ ሁኖ ጩሆ ነፍሴ ሳትወጣ ሰው ተሰብስቦ ሀኪም ቤት ወስደው ታሽጌ በግድ አይድኗት ዳንኩ ግን ወገቤ አሁንም ይሰማኛል፡፡ ተባለቤቴ ጋርም ልጆች ወልደን በእነሱ የተነሳ ተፋታን፡፡ (አቶ ተሾመ ከበደ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011ዓ.ም)*

**6. ቁልቋል፡-** ቁልቋል በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በአብዛኛው ለአጥር አገልግሎት የሚውል እፅዋት ሲሆን ነጭ ደም ያለው በመሆኑ በቀላሉ ሲነኩት ይደማል፡፡ ቁልቋል በቀላሉ መብቀል የሚችል ሲሆን ከበቀለ በኋላ ድርቅ የማይበግረው እፅዋት ነው፡፡ በአብዛኛው ድርቅን መቋቋም የሚችል ስለሆነ በቆላማ አካባቢዎች ይበቅላል፡፡ በቆላው እና በወይና ደጋው አይበቅልም ማለት ግን አይደለም፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ቁልቋል እራሱን የቻለ የህልም ውስጥ ተግባር እና ፍቺ አለው፡፡ ስለሆነም በህልም ቁልቋል ማየት የማይደርቅ ነገር ወይም ከባድ ህመም ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለይም በህልም የቁልቋል ደም ሲቀቡ ማደር ከባድ ህመም እንደሆነ አቶ

ብዙነህ ታምራት እና አቶ አቻም የለው ፈንታሁን በቀለ በቃለ-መጠይቅ ገልፀዋል፡፡ ቁልቋል የእርኩስ መንፈስ መኖርያ ተደርጎ ይወሳዳል፡፡ የሚከተለውን የወ/ሮ የንጉሴ በላይን ህልም እንመልከት፡-

> *ይመስለኛል በህልሜ ቁልቋል ቤቴን መውጫ እስክናጣ ድረስ ጥጉን ዙርያውን ከቦ ሰው እንዳጠረው ታጥሮ ይመስለኛል፡፡ ተዚያ እራሴን ይዤ እዝግዞ እያልኩ ሳዝን ቆይቶ ያ ቁልቋል ሰው እንደገፈፈው ዙሪያውን ያለው ሳይነጣጠል ተቤቱ ፈቀቅ ብሎ ሲቆም አየዋለው፡፡ እንግዲያ ፈቀቅ እያለ እንጂ ጨርሶ ሲከሳ አላየውትም፡፡ ተዚያ ባለቤቱ እና እኔ መርር ያለጥል ተጣልትን እኔም ውሀ ልግባ ብየ ጠፍቼ ብዙ ደረጃ ደርሰን እንደገና ታረቅን፡፡ ግን እኔ ብዙም ደስ አላለኝም ወቀሳ ስለበዛብኝ እንጂ፡፡* (ወ/ሮ የንጉሴ በላይ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ዓ.ም)

ሃሳቡ የሚያስረዳው ቁልቋል በህልም ውስጥ እንደ መጥፎ ነገር ይቆጠራል፡፡ ይኸውም በህልም ቁልቋል ማየት ነገር የጥል፣ ብጥብጥ ይሆናል፡፡ የቁልቋል ደም በህልም ከነካ ደግሞ ህመም ይመጣል የሚል ነው፡፡

**7. ዋርካ፡-** ዋርካ በጣም ትልቅ እና ሰፊ ቦታ መሸፈን የሚችል እፅዋት ነው፡፡ ዋርካ በጣም ሰፊ ቦታን መሸፈን የሚችል ዛፍ ነው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ሰው በልጅ ሲመረቅ *‹‹እንደ ዋርካ ያድርገው ዘርህን››* ተብሎ ይመረቃል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ዘርህ ይብዛ እና ይስፋ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዋርካ በህልም ውስጥ ከዚህ ጋር ተያያዥ ወይም ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም አለው፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት ዋርካ በህልም ውስጥ ሁለት አይነት ትርጉም እና ፍቺ አለው፡፡ አንደኛው አወንታዊ ሲሆን አንድ ሰው ከዋርካ ላይ ሲሸና እና ሲፀለል ሲያይ ዘሩ ወደፊት እንደሚበዛ እና በብዙ ዘመድ መሀል እንደሚኖር የሚያሳይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በህልም ዋርካ ሲወድቅ ማየት አይነት ወይም ትልቅ የሚባል ሰው እንደሚሞት አመልካች ነው ሌላው ደግሞ ዋርካ ከአንዱ ቦታ ወደሌላ ቦታ በህልም መንቀሳቀስ የትልቅ ሰው ቅያሜ ሆኖ ቦታ መቀየራቸውን፣ ሀሳብ መቀየራቸውን ያመለክታል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ሌሎች ነገሮች በህልም ውስጥ በሚለው ርዕስ ተራ ቁጥር 11 ‹‹ ሽንት›› ላይ የተጠቀሰውን ህልም መመልከት ይቻላል፡፡

**8. ደድሆ፡-** ደድሆ ዛፍ በአብዛኛው በቆላማው አካባቢ የሚበቅል ሲሆን ከአመት እስከ አመት ሁሌም አርንጓዴ ሆኖ የሚታይ ዛፍ ነው፡፡ ድርቅ እንኳን ቢሆን ደድሆ ቅጠሉም ግንዱም እንደ

ነበረ እርጥብ ሆኖ አመት እስከ አመት የሚቀጥል ዛፍ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ምን እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ አንድ አፈ-ታሪክ እንዳለ ገልፀው የማይደርቅበትን አፈ-ታሪክ እንደሚከተለው ተናግረዋል፡፡ ይኸውም ‹‹ደድሆ የማይደርቀው ማርያም ልጇን ይዛ ስትሰደድ ደክሟት ያረፈችበት ዛፍ ስለሆነ አይደርቅም፡፡›› የሚል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ደድሆ በህልም ማየት መቀደስ፣ መንጻት እና መንፈስ ቅዱስ መቅረብን እንደሚያመለክት ተናግረዋል፡፡ ደድሆ በህልም ሲታይ ለሆነ ትሩፋት በረከት እንደመመረጥ እና ወደፊት መመረጥን እንደሚያመላክት እና እምደሚቆጠር መረጃ ሰጭዎች ይገለፃሉ፡፡

## 5.2.6 ሰብሎች በህልም ውስጥ

**1. ጤፍ፡-** ጤፍ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ውስጥ በብዛት የሚመረት ዋና ምርት ነው፡፡ ጤፍ በወረዳው ከምግብ ፍጆታነት አልፎ ለገብያነት ይውላል፡፡ የእያንዳንዱ የጤፍ ፍሬ መጠን ትንሽ ይሁን እንጂ ጤፍ በአጠቃላይ ከባድ ነው፡፡ ስለሆነም በህልም ውስጥ የጤፍ ሚና አሉታዊ እና አወንታዊ ጉዳዮችን አካቶ ይይዛል፡፡ በአብዛኛው ጤፍ በህልም ማየት አሉታዊ ጉዳዮች ይበዛሉ፡፡ በህልም ጤፍ መሸከም፣ ማበራየት፣ ወደቤት ተሸክሞ መግባት፣ በአህያ ጭኖ መሄድ ከባድ ነገርን ያመጣል ተብሎ በማህበረሰቡ ይታመናል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በህልም የጤፍ ክምር ሲቃጠል፣ በህልም ጤፍ አውጥቶ መጣል እና ከቤት ውጭ ሲደፋ ማየት የከበደን ነገር እንደወገደልን እና እንዳመለጥን ያመለክታል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ምክንያታቸው ጤፍ ከባድ ስለሆነ በህልም ሲታይ መዘረፍ፣ ግጭት፣ ሞት እና መውደቅ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ችግሮች ከበድ ባለ ሁኔታ እንደሚመጡ (እንደሚደርሱ) ይታመናል፡፡ የሚከተለውን የወ/ሮ የተመኝ አለሙን ህልም እና ህልሙ እንዴት እንደደደረሰላት እንመልከት፡-

> *በህልሜ ተኝቼ ይመስለኛል ባሌ ጤፍ እየጫነ ተቤት እያስገባ ሳየው በቃ ይበቃናል ብየ ስለው ተይው ለብዙ ቀን እንዲሆነን ብየ ነው እያለ ቤቱ ሁሉ ጤፍ ሆነ፡፡ አንተ እንግዲህ ለእኛ ይበቃናል ለሌሎች ስጣቸው ያልኩት እንደሆነ አንች ሌሎች ገብስ እና በቆሎ ይብሉ የታዘዘላቸው እሱ ነው ለእኛ ደሞ ይኸ ነው ብሎ እምብይ ይለኛል ተዚያ ብትት አልኩኝ፡፡ ተዚያ በበነጋታው በማለዳ ከንስሃ አባቴ መልአከ ሰላም ዳምጤ ህጂ የሆነውን ነገር ስነግራቸው በጣም አዝነው ጤፍ ደግሞ በብዛት ገብቷል፡፡ ብለው አይዞሽ ጠልይ እኔም እጠልያለው ብለው የህልሙን ከባድነት ነግረው ተለያየን፡፡ ወራቱን*

*አሳወኩትም እንጂ በ16 ቀን ያለምኩት በዛው ወር በ27 ቀን ባሌ ተሰው ጋር ገጥሞ ሰው ተማቶ ያሰው ሞተ። እሱም ባለደሞች ሳይውል ሳያድር ገደሉት።* (ወ/ሮ የተመኘ አለሙ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ኢ.ም)

ጤፍ በህልም ውስጥ ማምረት ከባድ ነገር እንደሚደርስ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ፍቺ ውስጥ እናገኘዋልን። ይህ የሚሆንበት ምክንያትም ጤፍ ከባድ ስለሆነ በህልም ሲታይ የማይቻል (ከባድ) ነገር በህይወታችን እንደሚከሰት አስቀድሞ ይታመናል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ።

**2. ገብስ፡-** ገብስ ከሰብሎች ሁሉ ቀላል እና ለተለያዩ ምግቦች ዝግጅት የሚውል ነው። ገብስ ሲሸከሙት ቀላል እና ሲመገቡት ለሆድ ጤንነት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው። ገብስ ለተለያዩ አሻሮው ሳይፈተግ የተቆላ አሻሮው ለጨንጓራ፣የተፈጨ በሶ ዱቄት ለልብ፣ ለደም ማነስ ገብሱን አሳርሮ በመቁላት ያንን ወቅጦ በማፍላት መጠጣት የሚሉት ወ.ዘ.ተ ለመሳሰሉት በሽታዎች መድሀኒት መሆኑ በማህበረሰቡ እንደሚታወቅ መረጃ ሰጭዎች ተናግረዋል። ስለሆነም በማህበረሰቡ ከተዘረዘሩት አገልግሎቶቹ ጋር የተያያዘ የህልም ውስጥ ተግባር እና ፍቺ አለው። በመሆኑም ገብስ በህልም መሸከም፣ መውቀጥ፣ መመገብ ጥሩ ነው። ይኸውም የነገሮችን ቅለት ያመለክታል። በህልም ገብስ መቁላት ቀላል ችግር እንደመነሰሚያ (ማስጠንቀቂያ) ያለ ህልም ነው በማለት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ።

**3. ኑግ፡-** ከቅባት እህሎች መካከል አንዱ ነው። በእናርጅ እናውጋ ወረዳ በብዛት ይመረታል። ኑግ ሰውነትን ለመጠገን ዋነኛ መሳርያ ነው። ኑግ መልኩ ጥቁር ነው። ከዚህም በመነሳት ከተጠኘው ማህበረሰብ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በህልም ኑግ ማየት ደስ የማያሰኝ ጉዳይ ወደፊት እንደሚገጥም ይታመናል። ምክንያቱም ኑግ ብዙ ጥቅም ቢኖረውም በመልኩ ግን ጥሩ እንዳልሆነ ይታመናል። ስለዚህ ኑግ ከመልኩ አንፃር በህልም ስለሚታይ ፈቺውም ከመልኩ ጋር ተያያዥነት ያለው እንደሆነ መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ። ጨሰ ገበዝ ደረሰ ሁለት በሌላ ሰው ላይ ያለሟቸው ህልሞች እንደሚከተለው ናቸው።

*በአብቴ አብይ ሲያልመኝ አንድ ቀን በህልሜ ተኝቼ አብቴ አንድ መዳበሪያ ኑግ ጭኖ ወደ ገበያ ሲኼድ አየውት። ተዚያ አብቴን አስጠርቼ ጥሩ ያልሆ ህልም አይቻለው እና ተጠንቀቅ ብየው ተለያየን። ተዚያ የቤተ-ስኪያኑ ንብረት ያዥ እሱ ነበር ሌቦች በተኛበት ማታ መተው ዘረፉት። በሌላ ጊዜ ደሞ በታመነ ፈንታ ሲያልመኝ ተኝቼ በህልሜ ታመነ*

*ጠጉሬ አላደገም እያለ አልላጭም ሲል እራስህ አድንል ብለው የሽብ የሽብ ይዘው እራሱን ሲላጩት አየው፡፡ ተዚያ ምን ሊደርስበት ይሆን እያልኩ ሳስብ አንድ ቀን ተስካር አግኝቸው ስነግረው የደስ ደስ ያመጣችሁበት በቅሎ የሆነውን ሳላውቅ ከጋጥ ሙቶ አገኝውት ሲለኝ ክው ብዬ ቀረው፡፡* (ጨሰ ገበዝ ደረሰ ገላኤ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

**4. በቆሎ እና ማሽላ፡-** እነዚህ ሰብሎች በአብዛኛው በቆላማው አካባቢ የሚበቅሉ ሲሆኑ ማህበረሰቡ በአብዛኛው ለጠላ እና ለእንጀራ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ በቆሎ እና ማሽላ እንደ ገብስ ሁሉ ቀላል እና በመልካቸው ነጭ እና ቡናማ አይነት ቀለም ያላቸው ናቸው፡፡ በህልም በቆሎ እና ማሽላ ተመሳሳይ ፍቺ አላቸው፡፡ በህልም ማሽላ ወይም በቆሎ ማምረት፣ መብላት፣ መሸከም ሲሳይ ነው፡፡ በህልሙ አንድ ሰው በቆሎ እና ማሽላ ሲሸከም ካየ ያሰው ወደፊት የሚያገኘው ገንዘብ እንዳለ ይጠቁማሉ፤ አልያ ደግሞ የዘራው አዝመራ ፍሬአማ እና ምርታማ ይሆንለታል በማለት ይናገራሉ፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት በቆሎ እና ማሽላ በህልም ሲታዩ የመጪውን ጊዜ አዝመራ መሆን በማህበረሰቡ አባባል ‹‹መብለጉን›› ለማመልከት እንደ ምልክት ሆኖ እንደሚያገለግል ተናግረዋል፡፡

**5. ባቄላ እና ቦለቄ፡-** እነዚህ ሰብሎች ከጥራጥሬ ሰብሎች ውስጥ የሚመደቡ ሲሆን ለምግብነት በተለያየ መልክ ይቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በጥሬ (ንፍሮ) መልክ፣ በክብ መልክ፣ በሽሮ መልክ ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉ የምግብ አይነቶች ይዘጋጃሉ፡፡ ቦለቄ በቆላው አካባቢ በአብዛኛው የሚዘራ ሲሆን ባቄላ ደግሞ በወይና ደጋው እና በደጋው በአብዛኛው ይበቅላል፡፡ ስለሆነም በቆላው አካባቢ እና በወይና ደጋው እና በደጋው አካባቢ ስለሁለቱም ሰብሎች ተመሳሳይ የህልም አንድምታ አለ፡፡ በቆላው አካባቢ አራራ ቀበሌ በህልም ቦለቄ በህልም መዝራት ልጅ መውለድ መክበድ ሲሆን በደጋው እና በወይና ዳጋው ደግሞ ባቄላ በህልም መዝራት ልጅ መውለድ መክበድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም በቀበሌዎቹ ላይ በአብዛኛው የሚበቅሉትን ሰብሎች መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የሚከተሉትን ሁለት የተለያዩ በሁለቱ ሰብሎች የታለሙ ህልሞችን እንመልከት፡-

በወይና ደጋ የታለመ ህልም የአቶ ሙንየ ጌትነትን ህልም እንውሰድ፡-

*አሁን ያለችው ሚስቴ ታጭታ አራት አምስት ጊዜ እናት አባቷ እምብኝ ሲሉ አንድ ቀን በህልሜ አንድ ቀይ ሰው እንዳትሰለች ሰው ላክ ብሎ ስድስት ፍሬ ባጨላ ይሰጠኝ እና*

*አንደኛይቱን መልሶ ወሰደብኝ ለምን ትወስዳታለህ ብዬ የጠየኩት እንደው አትሆንህም ብዬ ነው ብሎ ወሰደብኝ። በበነጋታው ህልም ፈቺ ከሆኑት መላክ ሰላም ዳምጤ ላይ ሂጀ ሳስፈታው ህልሙ ጥሩ እንደሆነ ነግረው ቀይ ሰው መላክ ነው፣ ባጨላም ልጅ ስለሆነ ከአጨሃት ሴት ስድስት ልጅ ወልደህ አንደኛዋ ትሞትብሃለች፣ ሚስትህም ትማለዳለች ብለው በደስታ እንደሸኙኝ በሳምንቱ አጥናፉ ዳምጤን ይዤ ሀጂ እሽ ተብየ ስድስት ልጅ ወልድን አንደደኝዋ በትንሽነቷ ሞተች የተቀሩት አሉ።* (አቶ ሙንዬ ጌትነት፡ *ቃለ-መጠይቅ*፣ *መጋቢት* 2011አ.ም)

ሁለተኛው ደግሞ ከአራራ ቀበሌ የተገኘ የወ/ሮ ጀንበር ቢዘነጋው የህልም መረጃ እንደሚከተለው እንመልከት።

*ብዙ ቀን ባል አግብቼ ስኖር መውለድ እንቢ ሲለኝ ያላደረኩት ነገር የለም። ዘራብሩክ ጠበል ሁለት ሰባት ተጠመኩ፣ በማህበር ስለት ተሳልኩ፣ የሚቀመጥ ልብስ አሰሪ ብለውኝ አሰራው ብቻ ለፋው ቁርጥ አውቄ እንደተቀመጥኩ አንድ ቀን ሌሊት ተኝቼ አንድ ቀይ ሴት ትክዝ ፍዝዝ ብየ ተተቀመጥኩበት ቦታ ተአጠገቤ መታ ትክሻዬን እየነካካች አንቺ አንቺ ተነሽ እና ተከተይኝ ብላ እጄን ይዛኝ ተሆነ ተሚያብረቀርቅ ስፍራ ይዛኝ ገባች እና በመዳበሪያ የሞላ ቦለቄ ይመስለኛል ተእሱ ደስ ያለሽን ውሰጅ ብላ ታዝዘኛለች። ተዚያ በእውኔ እንደምሳቀቀው ብዙ የወሰድኩ መስሎኝ በእጄ የቆነጠርኩ መስሎኝ ሳየው አምስት ፍሬ ይዤ እተቆረቆርኩ ወጥቻ ስኸድ ያችው ሴት ተጣርታ በንሮሽ ዝሪያቸው ብላ እሽ ብየ ብትት አልኩ። ደስታዬ አላሳድረኝ ብሎኝ ባለቤቴን ቀስቅሽ ነገርኩት። ተዚያ በበነጋታው ለእማሆይ ስነግራቸው ተነስተው ሳሙኝና ልጆች እንደምወልድ  አበስረውኝ ወደቤቴ  ተመለስኩ። ተዚያ ተአንድ ወር በኂላ አርግዤ ወለድኩ ተዚያ በተከታታይ ሶስት ሴቶችን እና ሁለት ወንዶችን ወለድኩ።* (ወ/ሮ ጀንበር ቢዘነጋው፡ *ቃለ-መጠይቅ* ፣*መጋቢት* 2011 አ.ም)

ከላይ የተጠቀሱት ሃሳቦች የሚያስረዱት ባቄላ እና ቦለቄ በህልም ሲታይ እንደማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብ እና የህይወት ፍልስፍና የተለያየ ትርጉም ይሰጡታል። በተለይም ባቄላ እና ቦለቄ ከሌላው የሰብል አይነት በሁለቱም ቀቤዎች የተመረጡበት ማህበረሰባዊ ምክንያት አላቸው። ይኸውም ባቄላ እና ቦሌቄ ከሌሎች ሰብሎች ቶሎ የሚደርሱ እና አስተዳደጋቸው ወደ ላይ የሆነ ሲሆን በአንድ ጊዜ ብዙ ፍሬ መያዝ

መቻላቸው ከህጻናት ጋር የሚመሳሰል ነገር ከሌላው ሰብል በተሻለ ስላላቸው ነው በማለት መረጃ ሰጭዎች ተናግረዋል፡፡

## 5.2.7 የሰዎች ቀለም፣ ግብር፣ እድሜ እና ፆታ በህልም ውስጥ

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሱት ርዕሰ ጉዳዮች በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ አስተሳሰብ እና አመለካከት በደረጃ ትርጉም የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ለዚህ ማህበረሰብ ቀለም አንዱ የአስተሳሰብ እና የአመለካከቱ መታያ (ማረፊያ) ነው፡፡ በተለይም ጥቁር፣ ነጭ እና ቀይ ወሳኝ መግለጫዎች ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ ለእነዚህ ቀለማት ለእያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ከህልም ውጭ በአለው የህይወት አስተሳሰብ ትርጉም ሰጧቸዋል፡፡ ይኸውም ነጭ ቀለም በማህበረሰቡ የደስታ መግለጫ ነው፡፡ ጥቁር ደግሞ የሀዘን መግለጫ ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ቀይ ቀለም ከሌላው ቀለም በበለጠ በጋቢ፣ በኩታ እና በቀሚስ የክር ምርጫ ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ ቀይ በማህበረሰቡ ከአምላክ ጋር የሚያስታርቅ፣ የዛር መንፈስ መለመኛ እንደሆነ ይታመንበታል፡፡ የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ለቀለሞች በህልም ውስጥ ያላቸውን ትርጉም እና ፍቺ ደግሞ ለእያንዳንዳቸው አመለካከቱ፣ ከአስተሳሰቡ እና ከእምነቱ አንጻር ያስቀምጣል፡፡ ነገር ግን በህልም ውስጥ ያለው ትርጉም ከዚህ ብዙም የተለየ አይደለም፡፡ ስለሆነም ነጭ ቀለም የንጽህና እና ጽድቅን (መልካም ስራን) መገለጫ ሲሆን ጥቁር ደግሞ የእርኩስ መንፈስ መግለጫ ሲሆን እርኩሰትን (ንጹህ አለመሆንን፣ሃጢያትን) እና የአጋንት መቅረብን ይመለከታል፡፡ ሶስተኛው ቀለም ቀይ ደግሞ ቅዱስ መላክን፣ መንፈስ ቅዱስን መቅረብን የሚመለከት ነው፡፡

**1. ቀይ ሰው፡-** ቀይ ሰው በህልም ውስጥ በእናርጅ እናውጋ ማህብረሰብ ብርሀንን ይወክላል፡፡ ቀይ ሰው በህልም በሴት እና በወንድ ይመሰላል፡፡ ቀይ ሴት በሴት ታቦት ስትመሰል ቀይ ወንድ ደግሞ በወንድ ታቦት ይመሰላል፡፡ ቀይ ሰው በህልም ውስጥ ጥሩ ነገርን ይወክላል፡፡ ቀይ ሰው ቅዱስ መንፈስን፣ መላይክትን፣ የተቀደሰ ወይም ጥሩ ሀሳብን፣ ጥሩ ክስተትን፣ ምርትን፣ ብልጽግናን፣ በልግን፣ እርቅን፣ ሰላምን ወይም መፈወስን መዳንን፣ ፍቅርን፣ ጤናን፣ መተባበርን እና መረዳዳትን ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይወክላል፡፡ ቀይ ሰው በአጠቃላይ በህልም ሲታይ መልካም ክስተት እንደሆነ ያመለክታል፡፡ በተለይም የመዳን ወይም የፈውስን መንስኤ የማግኘት መነሻ፣ የእድገት መሰረት በመሆን አቅጣጫ በህልም በመስጠት ያገለግላሉ፡፡ የሚከተለውን የአቶ ሙንየ ጌትነት የእርቅ ምክንያት ህልም እንመልከት፡፡

**2. ጥቁር ሰው፡-** ጥቁር ሰው በህልም ውስጥ በተጠናው ማህበረሰብ ከቀይ ሰው በተቃራኒ የሰይጣን ተምሳሌት ነው፡፡ ጥቁር ሰው ሰይጣንን ይወክላል፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ጥቁር ሰው በህልም ሲታይ ህመም፣ ሞት፣ ብጥብጥ (ግጭት)፣ መደህየት (ማጣት)፣ ከስልጣን መውረድ (መሻር)፣ ገንዘብ መጥፋት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮች በአላሚው ላይ እንደሚከሰቱ ይታመናል፡፡ ጥቁር ሰው ጨለማን ይወክላል፡፡ በህልም ጥቁር ሰው ከታየ ገና ህልሙ መድረሱ ሳይታወቅ ወይም የሚሆነው ሳይታወቅ ስጋትና ጭንቀት ይፈጥራል፡፡ ይህን በተመለከተ የሚከተለውን የእማሆይ ይረብ አወቀን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹በህልሜ ተደነቀው አይቻህ ቤት ይዞ በመንደሩ በርበሬ ይሰጣል ይመስለኛል፡፡ ተዚያ ጥቁር ሰውየ እንጨት ተሸክሞ አምጥቶ ተደነቀው አይቼህ ቤት ደጃፍ ይጥለዋል፡፡ ህልሙን ባየሁት በሳምንቱ ሰውየው መኪና ገድሎት ሞተ ሴትዮዋ በአዷጋው የካሳ ብር ተሰጥታ ሀብታም ሆነች፡፡›› በማለት ተናግረዋል፡፡* (እማሆይ ይረብ አወቀ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኣ.ም)

**3. ፆታ፡-** የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ከሌሎች ነገሮች ይልቅ በፆታ ላይ ትልቅ እና ሰፊ ትኩረት አለው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ሴትም የራሷ ወንድም የራሱ የሆነ ማህበራዊ ድርሻ አላቸው፡፡ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት ወንድ ልጅ ወንድ በመሆኑ ብቻ የሚሰራቸው፣ የሚያደርጋቸው እና የሚያከብራቸው እሴቶች እና ደንቦች ከሴት ልጅ በበለጠ (ይልቅ) በርካታ ናቸው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ልጅ ሲወለድ የተወለደችው ሴት ስትሆን እና እና የተወለደው ወንድ ሲሆን እኩል አይታይም፡፡ ወንድ ሲወለድ ደስታው እና የወላድዋ ክብር ከፍ ይላል፡፡ በማህበረሰቡ ሴት ወላድ ናት የሚባለው ወንድ አብዝታ ስትወልድ ነው፡፡

ሴት አብዝታ ከወለደች ግን ከባለቤቷ ጀምሮ ‹‹ በየጊዜው ታራለች›› ተብላ ክብሯን በማሳነስ እንደሚገልጹት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ወንድ ልጅ ሲወለድ የአባቱ ደም መላሽ የሚሆን ነው በሚል አስተሳሰብ ስሙም ደም መላሽ ተብሎ ይወጣለታል፡፡ ከዚሁ ተመሳሳይ የወንድ ልጅ ስም የሚወጣው ከጥንካሬ፣ ከማሸነፍ፣ ከመማረክ፣ ከመግደል፣ ከመሸፈት....ወዘተ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በላቸው፣ ያዛቸው፣ በላይ፣ ተምትም፣ ሚኒሽር፣ ስበር፣ ከባዱ፣ ግዛቸው፣ ጌታቸው፣ ጋሻው፣ ደባልቅ፣አንድአርጋቸው...ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ ዘወትር በፉከራ፣ በሽለላ እና በቅራርቶ የሚባል ግጥም አለ፡፡ ይህ ግጥምም ‹‹ ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደ አባቱ ቀሚስ ይልበስ እና ይሁን እንደ እናቱ›› የሚል ነው፡፡ ይህ ግጥም ወንድን ልጅ የአባቱን ጀግንነት መውረስ እና መቀበል

እንደማህበራዊ ግዴታም ይቆጠራል፡፡ ያለዚያ ግን ‹‹የእሳት ልግ አመድ›› ተብሎ ይጠራል ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ በከፍተኛ ደረጃ ለወደቀ ሰው የሚሰጥ ቅጽል ስም ስለሆነ ወንድ ልጅ ይህ ስም እንዳይሰጠው ከእሱ የሚጠበቀውን ማህበራዊ ግዴታ ይወጣል፡፡ በአጠቃላይ የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በወንድ ልጅ ላይ ያለው አስተሳሰብ እና አመለካከት ከሴት ልጅ በበለጠ ከፍ ያለ ነው፡፡

ስለሆነም የማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት በህልም ውስጥ ሲገለጽ ይስተዋላል፡፡ በዚህ ማህበረሰብ በህልም ውስጥ ወንድ ልጅ እና ሴት ልጅ መታየት አለ፡፡ ቢኖርም ግን የሁለቱ ፆታ ወሳኝ ነገር ከህልም ውጭ በአለው የማህበረሰቡ በወንድ እና በሴት ያለው አስተሳሰብ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፤ ይህም የተለያየ እንደሆነ ያሳያል፡፡ እንደአጠቃላይ ግን ጾታን ሳይለይ በህልም ልጅ መታቀፍ ብር ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እያንዳንዳቸውን ደግሞ እንደሚከተለው እንመልከት፡-

**3.1. ወንድ ልጅ፡-** ወንድ ልጅ በህልም ውስጥ ሲታይ በተጠናው ማህበረሰብ ጥሩ የህልም ፍቺ አለው፡፡ ወንድ ልጅ በህልም መታቀፍ ጥሩ ነው መላእክ መቅረብ ነው፡፡ በህልም ወንድ ልጅ ማዘል በላይህ ላይ መንፈስ ቅዱስ ማደሩን ያመለክታል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ወንድ ልጅ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ቤተ-መቅደስ ገብቶ የሚቀድስ፣ ፍታት የሚፈታ፣ የሚባርክ፣ የሚያስታርቅ፣ ትዕግስት ያለው…ወዘተ የመሳሰሉት ማህበረሰቡ የሚፈልጋቸው እና ጥሩነታቸውን አምኖ የሚቀበላቸውን ስራዎች በአብዛኛው ወንድ ልጅ ስለሚሰራ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ይህ አስተሳሰብ በህልም ውስጥም ተግባራዊ እንደሚሆን ያሳየናል፡፡

**3.2. ሴት ልጅ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ሴት ልጅ በህልም ሰይጣንን እንደምትወክል ይገልፃሉ፡፡ በህልም ሴት ልጅ መታቀፍ እና ማዘል ነገር ነው፡፡ በአላሚው ላይ ከሰው ጋር ጥል ወይም ግጭት ሊመጣበት ይችላል፡፡ በተለይም የሴት ልጅ በህልም ውስጥ መጥፎነት ከማህበረሰቡ የሴት ልጅ የተሳሳተ አሉታዊ አስተሳሰብ እና አመለካከት የመነጨ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ሴትን ልጅ ነገር አቀጣጣይ እንጂ ነገር አብራጅ እንዳልሆነች ይታመናል፡፡ በተለይም *‹‹ሴት የላከው ጅብ አይፈራም››* ከሚለው አባባል ጀምሮ ለሴት ልጅ የሚሰጠው ግምት አሉታዊ ነው፡፡ በመሆኑም ሴት ልጅ በህልም ስትታይ የሚመጣው ነገር በጎ እንደማይሆን በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ይታወቃል፡፡

4. **መነኩሴ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የምንኩስና ህይወት እንደትልቅ ነገር የሚቆጠር፣ የሚከበር እና የሚፈራ ነው፡፡ ምንኩስና በዚህ ማህበረሰብ የቅድስና መገለጫ ሲሆን አለም በቃኝ በማለት ሁሉንም ነገር ሃብት ንብረት፣ ቤት እና ልጅ የሚባሉትን ትቶ ንጽህናን በመጎናጸፍ የሚኖርበት ሃይማኖታዊ ትውፊት ተደርጎ ይታመናል፡፡ ይህ ተግባር በማህበረሰቡ አስተሳሰብ አና አመለካከት ሰርጾ የሚኖር ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በህልም ልማድ ላይ ተግባራዊ እንደሚያደርጉት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ይኸውም በህልም መነኩሴ ሰላም ካለ፣ ከአናገረ እና መልክት ካስተላለፈ ህልም ያለመው አካል መንፈስ ቅዱስ እንደቀረበው ይቆጠራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በህልም መነኩሴ ሰላም ሳይል ጥሎ ከሄደ፣ አላሚው መነኩሴውን በህልሙ እየተጠገው ሲሄድ መነኩሴው ከሸሸው መንፈስ ቅዱስ እንደራቀው ተደርጎ ይወሰዳል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ፡፡

### 5.2.8 የሰው ስሞች በህልም ውስጥ

በህልም ውስጥ እንደ ማህበረሰቡ አመለካከት እና አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና የሚታዩ ማህበረሰብ ብዙ ናቸው፡፡ ህልም የሚያካትተው ጉዳይ በርካታ ከመሆኑ የተነሳ ፍቺውም ብዙ አይነት ነው፡፡ በህልም ውስጥ እንደ ገፀ-ባህሪ ትዕምህርት ሆነው የሚገቡት እንደ እፀዋት፣ ሰብሎች፣ እንስሳት፣ ሰዎች፣ ቁሳቁሶች እና አልባሳት እንዲሁም ሌሎች ነገሮች ከዚህ በፊት ያየናቸው ሲሆኑ በዚህ ደግሞ የሰው ልጅ ስሞች በህልም ውስጥ ያላቸውን ሚና ይታያል፡፡ የሰው ስሞች በህልም ውስጥ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ከፍተኛ ነው፡፡ ከስሙ እንደምንረዳው የስሙን ባለቤት ሰውን ሳይሆን ያስም ያለውን ሰው የሚወክል ነው፡፡ የስሙን ባለቤት ሳይሆን ወካዩን (ስሙን) ጉዳይ የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ማለትም ተወካዩን ሳይሆን ወካዩን ስሙን በህልም ውስጥ ያለውን ሚና ለማብራራት ነው፡፡ የሰው ስሞች በህልም ውስጥ ሁለት አይነት መንገድ ይገልፃሉ፡፡ በአንድ በኩል አወንታዊ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አሉታዊ መንገድ ነው፡፡ እያንዳንዳቸውን እንደሚከተለው እንመልከት፡- በእውኑ አለም ጥሩ ስም ያላቸው ሰዎች መጥፎ ነገር ሲያደርጉ ከታየም በማህበረሰቡ የህልም አፈታት መንገድ ህልሙ ቀጥታ እንደሚተረጎን መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡

1. **በህልም ውስጥ ጥሩ የሰው ስሞች፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ውስጥ አወንታዊ ነገር ያላቸው በርካታ ስሞች አሉ፡፡ በአብዛኛው የሰው ስሞች በህልም ውስጥ ታይተው ሲተረጎሙ እና ሲፈቱ ቀጥተኛ ፍቻቸው እንደሆነ ከመረጃ አቀባዮች ሀሳብ ለመረዳት

ተችሏል፡፡ ከእነዚህ የሰው ስሞች መካከልም መልካም፣ ተመስጌን፣ ሙሉቀን፣ ድልነሳ፣ ዘውዲቱ፣ ብዙነህ፣ ግዛቸው፣ ጌታቸው፣ ጌታሰው፣ ጌታአለም፣ ጋሻው፣ አሰፋ፣ ቢያድግልኝ፣ ሀብታም፣ ዳኘ፣ በላይነህ፣ ደምመላሽ፣ ሰናይት፣ ጸጋ፣ሃብታም፣ሃረግነሽ፣ አወቀ፣ ሽጋሰው፣ ደስታ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ስሞች ህልም ሲታዩ የጥሩ ነገር መወከያዎች ናቸው፡፡ በህልም እነዚህ ስሞች ያሏቸው ሰዎች አብረውን ካደሩ ጥቁርም ይሁኑ ቀይ አጭር ይሁኑ እረዥም፣ ወፍራም ይሁኑ ቀጭን ህልም አላሚውም ሆነ ህልም ፈቺው ጥሩ ነገር ወደፊት እንደሚገጥም ይገምታሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ጥቂቶችን የሰው ስሞች በህልም ውስጥ ያላቸውን ሚና እንመልከት፡-

> *በህልሜ ቤተ-ስኪያን ዙሪያውን እሾህ ብቻ ይሆናል ይመስለኛል፡፡ ተዚያ ጌታቸው ተስፋ እና ጋሻው ተስፋ ወንድማማቾች እሾሁን ይከተክቱታል፡፡ እኔ እመርቃቸዋለሁ ተዚያ አንድ ውሻ ይመጣል የሁለቶቹ ውሾች ያንን ውሻ ቅጥቅጥ አድርገው ይመቱታል፡፡ ተዚያ ስፈታው በእኛ ቀበሌ ሁለት ቤተ- ስኪያን አለ፡፡ ሁለቱም እየተሰራ የሁለቱ ደብር ሰው ባለመግባባት ተጣልቶ ነበር ታረቀ፡፡ ውሻ ምላስ ነው፡፡ እሾህም ምላስ ነው፡፡* (ቄስ *መንበሩ ጌትነት፡ ቃለ-መጠይቅ ፣መጋቢት* 2011 *ኢ.ም*)

በህልም ጌታቸው እና ጋሻው የሚባሉ ስሞች ጌታቸው እንደ ፈጣሪ የሚቆጠር ሲሆን ጋሻው ደግሞ የፈጣሪ መልእክተኛ ተደርጎ በማህበረሰቡ ይወሰዳል፡፡ ጌታቸው በህልም ምን ጊዜም ፈጣሪን፣ አለቃን፣ መሪን የሚወክል ሲሆን ጋሻው ደግሞ መከታ መሆንን እንደሚያመለክት መረጃ ሰጭዎች ተናግረዋል፡፡ ሌላኛውን ህልም ደግሞ እንደሚከተለው እንመልከት፡-

> *ቄስ ዳኘ በህልሜ ተሌሎች ካባ ተለበሱ ቄሶች ጋር ካባ ለብሰው ወደ እኔ ቀርበው መ/ረ ቤተ-እዚያሃር እንዳይፈርስ ተተሰራም ታለበት ቦታ ተቀይሮ ነው ብለው ቦታውን ወስደው ያሳዩኝ ይመስለኛል፡፡ ተዚያ በሌላው ቀን ቤተ-እዚያሃር የመስራት ሀሳብ ማህበረሰቡ ተገዝቶ ተስማምቶ እዛው አለበት ላይ ፈርሶ እዛው እየተሰራ ማህበረሰቡ ዕርስ በዕርሱ ትርምስ ገጥመው ቤተ-እዚያሃሩም መሰራቱ ተቋረጠ፡፡* (ርዕሰ ደብር *መሪጌታ* አባተ *ንጋቴ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 *ኢ.ም*)

በህልም ዳኘ የሚባል ስም ከታየ አስታራቂ፣ መመሪያ የሚሰጥ፣ የሚዳኝ፣ ትእዛዝ የሚያስተላልፍ ወ.ዘ.ተ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በህልም ዳኘ የሚባል ስም ያለው ሰው ከደበደበ የፈጣሪ ቁጣ እንደሚመጣ ተደርጎ ይታመናል፡፡ ቀጣዩን ህልም እና ፍቺ እንመልከት፡-

*በህልሜ ጌታለም እና ጫኔ የሚባሉ ሰዎች ጎዳና እየሄድኩ ይመስለኛል መንገድ ላይ አገኛቸዋለሁ ከዚያ ጎረቦቶች ናችሁ ብየ ሰላም ስላቸው ጌታለም ጥምጥም ብሎ ሰላም ሲለኝ ጫኔ ደግሞ ሰላም ልለው ስል አኩርፎ ተጣልቸሻለሁ ብሎ ጥሎኝ ይሄዳል። ከዚያ 10ኛ ክፍል ተፈትኘ ብር ብየ ያየሁትን ህልም ለማሆይ ዋለ ስነግራት አይዞሽ ልታልፊ ነው። ጫኔ ሰላም ቢልሽ ኖሮ ትወድቂ ነበር ብላ ላከችኝ። ከዚያ የ10ኛ ክፍል ውጤቴ ሲታይ በማለፊያው (አናቷ ላይ) አምጥቸ አለፍኩ።* (ተማሪ ብርቲካን ተመስጌን፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

በህልም ጌታለም የሚባል ሰው ሲታይ ወይም ሲያገኝ፣ሰላም ሲል፣ ሲይዝ፣ ሲቀርብ (ሲጠጋ)፣ ሲያባርር እና ሲመታ ጥሩ ነገር ነው። ምክንያቱም ጌታ አለም የሚለው ከፈጣሪ ጋር የሚገናኝ በመሆኑ ከፈጣሪ የሚመጣን ጥሩ ነገር ያዘለ ነው ተብሎ ስለሚገመት ነው።

**2. በህልም ውስጥ መጥፎ የሰው ስሞች፡-** በተጠናው ማህበረሰብ በህልም ውስጥ ጥሩ የሰው ስሞች እንዳሉ ሁሉ መጥፎ መገለጫ ያላቸውም ጥሩ ያልሆኑ የሰው ስሞችም አሉ። እነዚህ ስሞች በማህበረሰቡ የህልም እሳቤ ውስጥ የራሳቸውን ድርሻ ይዘው የምናገኛቸው እና ዕለት ከዕለት የሚፈፀሙ የሚታመኑባቸው ናቸው። ከእነዚህ መካከልም፡- እምብይአለ፣ ሽብሩ፣ ከበደ፣ ጫኔ፣ ቢያድጎ፣ ጎዴ፣ ያሳብ፣ አሸብር፣ ትእዛዙ፣ ጠቦ፣ እራቤ፣ በአንችአይሞሉ፣ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ስሞች በህልም ውስጥ በታዩ ጊዜ በአሉታዊ ገፅታቸው የሚተረጎሙ ናቸው። ከላይ የተዘረዘሩ በአብዛኛው ሰዎች የሚያልሙባቸው እና የሚደርሱ ናቸው። የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

*በህልሜ ቢያድጎ የሚባል ሰው ደጁን ሙልጭ አድርጎ ሲያርሰው ለእኔ አስቻለ ታሪኩ የሚባሉት የሰፈራችን ሰውየ ሁለት አልጋ ያመጡልኛል። ለምን እኔ ነኝ አለኝ ያልኩ እንደሆነ ይኸ ላንቸ ታዝዟል ይሉኛል። በቤተ-ክስያን ገብስ የያዙ አቆማዳዎች ገልብጠው ይዘው ይኸዳሉ። ተዚያ ገብሱን ቆንጥረው ይኸው ነጭ ነው ብለው ያሳየኛል። ተዚያ ሁለቱ ወንድ ልጆቼ አንዱ ጦር ሜዳ ሀዶ ሞተ። አንዱ ደሞ ተዚሁ ታሞ ሞተ። ነጭ ነው ብሎ ማሳየቱ አገሩ ለእሱ ማዝመሩን (መስራቱን) ነው። ቢያድጎ የሚባለው ስምም የማይቀየር ድርጊት ማድረግን ያመለክታል። አስቻለ ታሪኩም ታሪኩ በሰው ላይ የሚደረግ (የሚከሰት) ስለሆነ ማስቻሉን ለማመልከት ነው። ‹‹ፈጣሪ ላያስችል*

*አይሰጥም›› የሚውለውን አባባል ተስሙ እናገኘዋለን።* (እማሆይ የዝና ቸኮል፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

አንዳንድ የሰው ስሞች ከሌሎች በህልም ውስጥ ከሚታዩ ነገሮች ጋርም ተቀላቅለው በመታየት ዋጋቸውን ከፍ ያደርጋሉ። በአንዳንድ ህልሞች ካልሆነ በስተቀር በአብዛኛው ከሌሎች ነገሮች ጋር ተቀላቅለው እናገኛለን።

*‹‹በህልሜ ትዕዛዙ ከሚባል ሰው ጋር ሳድር በበነጋታው ሳይውል ሳያድር ሁል ጊዜ ጥል እጣላለሁ››* (አቶ ባወቀ ምሳሌ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 አ.ም)

በህልም ውስጥ ትዕዛዙ የሚባል ስም ያለው ሰው ጋር ማደር ጥል፣ ብጥብጥ እና ግጭት ይሆናል። ትእዛዙ ማለት ትእዛዝ የታዘዘ ነገር ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች አዘዙብኝ እንዲህ አደርኩ፣ የማይታለፉ ትዕዛዜ ነው››። በማለት የመጣላቸውን መከራ ይገልፃሉ። ስለዚህ ትዕዛዙ የመጥፎ ነገር ተምሳሌት ነው።

ጫኔ የሚባል ስም በህልም ውስጥ ሲታይ ጫን ያለ ነገር፣ ከባድ ነገር በአላሚ ወይም በማህበረሰቡ እንደሁኔታው እንደሚመጣ ይታመናል። ያሳብም ለሀሳብ የሚሰጥ ነገር እንደሚመጣ ያመለክታል። ከበደ በስሙ እንደምንረዳው ከባድ ነገር በህይዎታችን ወደፊት እንደሚሆን የሚያሳይ መሆኑን መረጃ ሰጭዎች ተናግረዋል። ሌሎች ከዚህ ያልተጠቀሱት የሰው ስሞች የራሳቸው የህልም ውስጥ ተግባር እና ሚና እንዲሁም ፍቺ አላቸው መሆኑን ሊወቅ የሚገባው ርዕሰ-ጉዳይ እንደሆነ መዘንጋት እንደሌለብን ከማህበረሰቡ የተገኘው መረጃ ያስገነዝባል።

## 5.2.9 ሌሎች ነገሮች በህልም ውስጥ

**1. እሳት እና ንፋስ፡-** ማንኛውም ነገር በማህበረሰቡ እስከተፈጠር እና ማህበረሰቡ እስከተጠቀመበት እና እስከጠበቀው ድረስ በህልም ውስጥ የሚወክለው ነገር ይኖራል። እንደየ ማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት ነገሮችን የሚያይበት መንገድ ብዙ ይሁን እንጂ አንድን ነገር ለሆነ ጉዳይ ወኪል መሆኑ አይቀርም። ማንኛውም ነገር ተምሳሌት አለው። አንዱ ነገር በህልም ሲታይ የህልሙ ፍቺ ቀጥታ የሚተረጎም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ህልሙ በታየበት በተቃራኒ የህልም ፍቺ ኖሮት እናገኘዋለን። ስለሆነም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እሳት እና ንፋስም እንደሌላው ነገር በህልም ውስጥ የራሳቸው ሚና አላቸው። በእናርጅ እናውጋ

ማህበረሰብ እሳት እና ንፋስ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ የህልም ውስጥ ተግባር እና ፍቺ አላቸው፡፡ ይኸውም በህልም እሳት እና ንፋስ ማየት ነገርን ወይም ጥልን፣ ልፌትን (ምላስን) ይወክላሉ፡፡ እሳት እና ንፋስ በህልም ውስጥ ከታዩ ከባድ ነገር መጥቶ ግጭት እንደሚነሳ እና በሌሎች ሰዎች መለፈፍ (ልፌት)፣ ወቀሴታ እና ለራስህ ይበልጥ እንዳዳላህ የምትነገርበት ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው፡፡ የሚከተለውን የአባ ግዛ ደነቀውን ጥል እና ነገር ሊመጣባቸው ሲል የሚያሳያቸውን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹ እኔ ነገር በእራሴ እና በሌሎች ላይ ሊመጣብን ሲል በህልሜ እሳት እና ንፋስ ያሳየኛል፡፡ ተዚያ በበነጋታው ሰው ተጣልቶ በምስክርነት እጠራለሁ ወይም ደግሞ ልፌት ይመጣብኛል፡፡ ››* (አባ ግዛ ደነቀው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

እሳት እና ንፋስ ብዙ ጊዜ የሚጋረፍ ነገር ያላቸው ሲሆኑ ከባድ ቀላል ሊባሉ ይችላሉ፡፡ እሳት ከበድ ያለውን የግጭት ክፍል (ጥል) የሚመለከት ነው፡፡ ንፋስ ደግሞ የረባውን ያረባውን ምክንያት በመደርደር የጥል ምክንያት በመፍጠር የመጣላትን ሁኔታ ይመለከታል፡፡

**2. ዝናብ፡-** ዝናብ ህይዎት ላለው ፍጡር ሁሉ አስፈላጊ ነው፡፡ ዝናብ ለገበሬው ወይም ለገጠሬው ብቻ አይደለም የሚያስፈልገው ለከተሜውም ያስፈልገዋል፡፡ ዝናብ ከሌለ ህይዎት መኖሯን ታቆማለች፡፡ ዝናብ ከሌለ ህይዎትን ማስቀጠልም ሆነ ማቆየት ከባድ ነው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ዝናብ አዝርትን ለማብቀል፣ እፅዋትን ለማሳደግ፣ የሰውን ልጅ ህይዎት ለመምራት እና ለማቆየት በጣም አስፈላጊ ነው ተብሎ ስለሚታመን በወቅቱ እንዲዘንብ በጉጉት ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ ዝናብ በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ዝናብ በህልም ውስጥ የሚታይ ሲሆን እራሱን የቻለ ፍቺ አለው፡፡ በተለይ በዚህ ማህበረሰብ ዝናብን የሚመለከቱ ህልሞች በአብዛኛው ቀጥተኛ ትርጉም እና ፍቺ አላቸው፡፡ ዝናብ በህልም ማየት ሲሳይ ነው ይላሉ መረጃ ሰጭዎች፡፡ ከዝናብ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንደሚሉት ዝናብ በህልም መታየት እርቅ መፍጠር ወይም መውረድ፣ የፍቅር እና የሰላም ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ፀጋ ይመር አብራርተው ይገልፃሉ፡፡ *‹‹ዝናብ የተቃጠለን ማብረጃ ወይም ማቀዝቀዣ ነው፣ የእርቅ ምልክት፣ የማግኘት ምልክት እና የመባረክ ምልክት ስለሆነ ሲሳይ ነው››* በማለት ገልፀዋል፡፡

**3. የሞተ ሰው (ሙት መንፈስ)፡-** የሞተ ሰው ወይም የሙት መንፈስ ፋይዳ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ውስጥ እራሱን የቻለ ትርጉም እና አገልግሎት አለው፡፡ እናም ከተጠናው ማህበረሰብ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የሞተ ሰው በህልም መጥቶ እቃ ይዞ ከሄደ እቃ ይዞ ከሄደበት ቤት ሰው ይሞታል፡፡ ነገር ግን ከሞተው ሰው ወይም ከሙታኑ ሰው ጋር አብሮ ማደር እድሜ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ ሙታኑን ሰላም ማለት እና ማውራትም እድሜ ነው፡፡ ነገር ግን ከሙታኑ ጋር መሄድ ግን ሞትን ያመጣል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ይህን በተመለከተ እማሆይ ይረብ አወቀ ህልም በራሷ ላይ የደረሰባትን ህልም እንደሚከተለው ተናግራለች፡፡

> *እኔ በቅርብ ጊዜ አይነ ስውር ስለሆንኩ አብራኝ የምትኖር አንድ እህቴ ነበረች ልጆቼ፣ እህት እና ወንድሞቼ ለልቀው አንዲት ቀርታ አብራኝ እየመራችኝ አብረን ስንኖር አንድ ቀን በህልሜ የሞተችበት ዘመኗ የማይታወቀው እናታችን መታ ይመስለኛል አብረን ስናወራ ስንጫዎት ቆይተን በይ ፊት ፊት ተነሽ ይዠሽ ልኺድ ነው የመጣሁ ትናትእና ከተቀመጠችበት አስነስታ እጇን ይዛት ትኺድ ይመስለኛል፡፡ ለምን ነው ይዘሻት የምትኺጅ ቶሎ መልሻት እያየሽኝ እኔን ወይ እኔም አብሬ ልምጣ ብየ የጠየኳት እንደው አይ እሷ አትመለስም አንቺም እዛው ጠንክሪ እራስሽን አውጭ አትመጣም እንዳትጠብቂያት ብላ እናታችን ተፊት እህቴ በኋላ ተከትላት ሲኺዱ አይኔን ጥድብ አድርጌ እያየዋቸው ሲጠልሙ ብትት አልኩ፡፡ ተነስቼ አለቀስኩ በበነጋታው ቤተ- ክስያን ኺጀ ተሳልሜ፣ ጠልየ መጣሁ፡፡ ተዚያ ቀን ጀምሮ አለቀስኩ፡፡ ህልሙን ታለምኩት በኋላ ጭንቀት እና ሀሳብ ስለያዘኝ እራሴ ሰላም አጣሁ፡፡ ተዚያ ህልሙን ታየውት ሁለት ወር ሆኖት እህቴ እንጨት ተበርሀ ልታመጣ ሀዳ ናዳ መቷት ሞተች፡፡* (እማሆይ ይረብ አወቀ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

የሙት መንፈስ በህይዎት ላሉት ሰዎች በህልም አማካኝነት ምን ማድረግ እንዳለባቸው፣ ምን መሆን እንደሚፈልጉ ማስጠንቀቂያ መስጠት ከገቡበት መጥፎ ነገር እንዲላቀቁ ወደፊት ሊገጥማቸው የሚችለውን ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር ይናገራሉ፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት እናት እና አባት ከልጆች ቀድመው ከሞቱ እና በህይዎት እያሉ የሚያምኑት እንደ ዛር፣ አተቴ አይነት እምነቶች ካሉ የሚያወርሱት ልጅ ስለሚኖር ባይኖርም መንፈሱ ደስ አለው ልጅ ላይ ይሰፍራል የሚል እምነት በማህበረሰቡ ስላለ እነዚህ መንፈሶች በሙታኖች አማካኝነት የጎደለውን እንዲያሟሉላቸው ያደርጋሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡

**4. ጨረቃ እና ጀንበር፡-** ብርሀንን ለሰው ልጅ ከሚሰጡት ነገሮች መካከል ጨረቃ እና ጀንበር ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ አስተሳሰብ እና አመለካከት ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ጀንበር ስተወጣ፣ ስትጠልቅ፣ ጨረቃ ስትወጣ፣ ስትጠልቅ፣ ስትሄድ እራሱን የቻለ ማህበረሰባዊ አተያይ አለው፡፡ ከዚህ አተያይ መካከልም ህልምን በመጠቀም የሚበይኑት ጉዳይ አንዱ ነው፡፡ ጨረቃ እና ጀንበር በህልም ውስጥ የሚሰጣቸው ቦታ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ለሆነ ተግባር ይውላሉ፡፡ በመሆኑም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የጨረቃ እና የጀንበር ተግባር በህልም ውስጥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*‹‹ ይመስለኛል በህልሜ ደርግ ሊጠፋ ሲል ጨረቃ እና ጀንበር አንድ ላይ ይወጣሉ ይመስለኛል ተዚያ ጨረቃይቱ እየደመቀች ስትሄድ ጀንበር ትጠፋለች፡፡ ተዚያ ደርግ ወደቀ ይሀዲግ ገባ፡፡ ››* (አቶ ፀጋ ይመር፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

የተጠቀሰው ሃሳብ የሚያሳየው ጨረቃ እና ጀንበር በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የመንግስት ሹማምንት ለውጥን እንደያመለክት ሲሆን የህልሙ ፍቺም ጀንበር ከጨረቃ ቀድማ እንደምትውጣ ጨረቃ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ስለምትወጣ ጀንበር የነበረውን መሪ የሚያመላክት ሲሆን ጨረቃ ደግሞ የሚሾመውን መሪ እንደሚያመላክት ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ጨረቃ እና ጀንበር በህልም ውስጥ የመንግስት ለውጥ፣ በሀገር ላይ የሚመጣን ርሀብ፣ ቸነፈር (በሽታ)፣ ድርቅ፣ ሰላም፣ ልምላሜ፣ የተሾመውን ሰው እድለኛነት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ሀገራዊ ጉዳዮች ማወቂያ እንደሆኑ በማህበረሰቡ እንደሚታመን ያሳየናል፡፡

**5. አፈር**፡- አፈር በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እንደማንኛውም ነገር በህልም ውስጥ የራሱ የሆነ ተግባር አለው፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት አፈር መሸከም ወይም መግፋት፣ መመለስ ሞት ነው፡፡ አፈር የሚወክለው ሰውን ነው፡፡ ሰው ከአፈር እንደሚሰራ በማህበረሰቡ አስቀድሞ የታወቀ እውቀት ነው፡፡ በመሆኑም ከአፈር ጋር የተያያዙ ህልሞች የሰውን ልጅ እንደሚገልፁ እና ሲደርሱም በሰው ልጅ ላይ እንደሆነ ህልሞች ያስገነዝባሉ፡፡ የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹በህልሜ ተደጋጋሚ ልጆቼ ጉድጓድ ሲገቡ እኔም ደግሞ አፈር ስሸከም አድሬ ተብዙ ወራት በኋላ ሁሉን ልጆቼን አጣሁኝ፡፡››* በማለት ተናግረዋል፡፡ (እማሆይ ይረብ አወቀ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

የተጠቀሰው መረጃ የሚያመለክተው በህልም አፈር መሸከም ሰው እንደሚሞት ተደርጎ ስለሚታመን ፍቺውም ከሞት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡

**6. መንጋጋ እና ጥርስ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ውስጥ ተግባር እና ፍቺ ያለው መንጋጋ እና ጥርስ የምንለው የሰውን ልጅ ጥረስ እና መንጋጋ ነው፡፡ መንጋጋ የምንለው የድዳችን የኋላኛው ጥርስ ሲሆን የምግብ ማኘኪያ ሲሆን ጥርስ የምንለው ደግሞ በከንፈራችን ፊት ለፊት ያለውን ለውበት የምንጠቀምበት ነው፡፡ መንጋጋ እና ጥርስ በህልም ውስጥ ትልቅ ትዕምርት አለው፡፡ በህልም መንጋጋ እና ጥርስ መውለቅ ከመረጃ አቀባዮች የተገኘው አንደኛው መረጃ እንደሚያመለክተው በህልም መንጋጋ ሲወልቅ እና በህልም ጥርስ ሲወልቅ መንጋጋ የሩቅ ዘመድ ሞት ሲሆን የፊት ጥርስ መውለቅ ደግሞ የእህት እና የወንድም መሞት ነው የሚል ሲሆን ትርጉሙም እህት እና ወንድም በጣም ቅርርብነት ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ የፊት ጥርስም በህልም እንደምንረዳው ከቅርበት አንፃር ከፊት ወይም ቀድሞ የሚገኝ ስለሆነ እህት እና ወንድምም ከሌላው ዘመድ አዝማድ በተሻለ በደስታ እና በሀዘን ቀድመው መገኘታቸውን የሚያመለክት መሆኑን ከአራራ ቀበሌ የተገኘው መረጃ ያስገነዝባል፡፡ ሁለተኛው እና ሌላኛው ከ3ቱ ቀበሌዎች የተገኘው መረጃ ደግሞ በህልም መንጋጋ መውለቅ የወንድም ሞት ሲሆን የፊት ጥርስ በህልም መውለቅ ደግሞ የእህት መሞት ነው በማለት መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ የሚያቀርቡት ማስረጃም መንጋጋን ከጥንካሬ ጋር ወይም አንፃር በማየት ወንድም ትክሻ እና ጉልበት፣ አለኝታ ስለሆነ መንጋጋም ጠንካራ ነው ብሎ በወንድ ልጅ መመሰሉ ሲሆን የፊት ጥርስ ከእህት ጋር የታየበት መንገድ ደግሞ የፊት ጥርስ ለውበት የምንጠቀምበት እንጂ ምግብ የምንበላበት ስላልሆነ ከእህት ጋር ይመሰላል፡፡ ይኸውም እህት ድምቀት እና ውበት ስለሆነች በፊት ጥርስ ትመሰላለች በማለት መረጃ ሰጥተዋል፡፡ የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹በህልሜ የፊት ጥርሶቼ ወልቀው አየው፡፡ ተዚያም በተከታታይ ሁለት እህቶቼ ሞቱ፡፡››* (አቶ ባየ መኮነን፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

ሌላው ከአራራ ቀበሌ የተገኘው ሁለት የህልም መረጃ ደግሞ ሰዎቹ ሲሞቱ ጥቂት ህልም አሳይቶኛል፡፡

> *በህልሜ ይመስለኛል አባታችን ከበደ ይመስለኛል ሰውን ሁሉ እየተማታ ይገላል፤ ያደማል፤ ያቆስላቸዋል ተዚያ ማን ነው ብየ ያየሁት እንደው አባቴ ተዚያ እየሮጠ*

*ይመጣ እና ኧረ ልጄ ይመታሻል አትጠጊው ይለኛል እኔንስ አይመታኝም ብየ የተጠጋሁት እንደሆነ እኔንም እንደሌላው ሰው ተምድር ወደ ሰማይ አንሳፎ እንደገና ያወርድ እና ሲመታኝ አንዷት የፊት ጥርሴ ተነቃነቀች አንደኝዋ ወለቀች፡፡ ተዚያ በአራተኛው ቀን እህቴ እና ወንድሜ ደብረወርቅ ገብያ ህደው ተገብያ ሲመለሱ መችና ተገልብጦ ወንድሜ ከባድ ጉዳት ተጎድቶ ሀኪም ቢኸድም አልዳነም ሞተ፡፡ እህቴ እግሯ ተሰብሮ ነበር ታሽጋ አሁን እንደድሮው ባይሻላትም አለች፡፡* (ወ/ሮ ጀንበር ቢዘንጋው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ኢ.ም)

ሌላኛው መረጃ ሰጭ ደግሞ የሚከተለውን ህልም በሚከተለው መልኩ ተናግረዋል፡፡

*በህልሜ ይመስለኛል ወደገብያ እየኸድኩ ድንገት የእሳት ፉም ተየት መጣ ሳልለው ጉንጨን የመታኝ ይመስለኛል ሰዎች ገደለህ ገደለህ እያሉ ሲያዩኝ አንዱ መንጋጋየ ሲወልቅ አየዋለው፡፡ ተዚያ አጎቴ ልቅሶ ቤት በተተኮሰ ጠይት ተመቶ ሞተ፡፡ ስፈታውም ገብያ ማለት ህዝብ ነው፡፡ እሳትም ጥይቱ ነው፡፡ የመንጋጋየ መውለቅም ያጎቴ መሞት ነው፡፡* (አቶ ፈንቴ እንዳለው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

ከላይ የተጠቀሱ ህልሞች መንጋጋ እና ጥርስ ሲወልቅ ማየት እንደየ ማህበረሰቡ አመለካከት እና አስተሳሰብ የተለያየ ፍቺ እና ትርጉም እንዳለው ነው፡፡ ህልም አላሚውም ሆነ ህልም ፈቺውም ከማህበረሰቡ የወጡ የማህበረሰቡ አባል መሆናቸው ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

**7. ጠጠር እና ድንጋይ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ጠጠር እና ድንጋይ በህልም ውስጥ የራሳቸው ፍቺ እና ትርጉም አላቸው፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት ጠጠር እና ድንጋይ ነገር እና ሞት ነው፡፡ ትልልቅ ጠጠር በህልም ማየት ከባድ ነገር ሲሆን ትንሽ ጠጠር በህልም ማየት መጠነኛ ነገር ነው፡፡ በተለይም በህልም ጠጠር መልቀም ነገር መሰብሰብ እና መምጣት የሚመለከት ነው፡፡ ድንጋይ በህልም ከሰማይ መውረድ፣ ከድንጋይ ጋር በህልም መጋጨት፣ በድንጋይ መመታት ሞት ነው፡፡ መሪጌታ ስማቸው አሞኘ ድንጋይ በህልማቸው ሲያዩ ምን እንደሚገጥማቸው በሚመለከተው የህልም መረጃ እንመልከት፡-

‹‹ *አንዳንድ ጊዜ በሀገር ላይ ያልመኛል፡፡ በሀገር የሚሆነውን በህልም ያሳየኛል፡፡ እናም በህልሜ ተላይ ተሰማይ ድንጋይ ተጠቅልሎ ሲወርድ ሳይ በሀገሩ ላይ የሰው ሞት፣ የከብት ሞት እና ድርቅ ይከሰታል፡፡* ›› (መሪጌታ ስማቸው አሞኘ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

ሃሳቡ የሚያስረዳው ድንጋይ እና ጠጠር  እንደክብደታቸው መጠን በማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት ውስጥ የሚታይ ነገር እንደሆነ ነው፡፡ ድንጋይ በመጠኑ ከጠጠር ጋር የማይገናኝ ስለሆነ በማህበረሰቡም በዚሁ እይታ በህልም ሲታዩ የሚፈታ መሆኑ ከመረጃ ሰጭዎች የተገኘው ሀሳብ ያመለክታል፡፡

**8. ፀበል፡-** ፀበል በክርስቲያን ማህበረሰቦች ላይ የሚተገበር ሲሆን የዚህ ጥናት መረጃ ሰጭዎች ክርስቲያኖች ስለሆኑ በህልም ውስጥ ፀበል እንደ አንድ ገፀ-ባህሪ ሆኖ ማህበረሰቡ ይገለገልበታል፡፡ በተለይም ህሙማን በበሽታቸው ጊዜ ስለ ፀበል እንደሚያልሙ ይናገራሉ፡፡ እዚህ ላይ ህልም የጭንቀት መፍትሄ መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡ ስለጸበል ህልም የሚያዩ ህሙማን ብቻ ሳይሆኑ አስታማሚዎችም ስለታማሚው ጤንነት ስለሚጨነቁ ያልማሉ፡፡ ሌሎች ሰዎችም አግባብነት ያለው ስራ አልሰራንም ብለው የሚጨነቁ ሰዎችም ያያሉ፡፡ ስለሆነም ጸበል በህልም መጠመቅ ምህረትን ያመለክታል፡፡ ጸበል በህልም መጠመቅ ንፅህናን ያመለክታል፡፡ የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹በእውኔ ተሚስቴ ጋር የተቀባበልኩበት በሬ አይኑን አሞት ስጨነቅ ተኝቼ በህልሜ ቀይ ሰውዬ መጥቶ የቅዱስ ጨርቆስን ጠበል አምጥተህ እርጨው ብሎ አይኑንም ቅባው አለኝ፡፡ ተዚያ ዝም ብዬ በህልሜ ያየውትን ጠበል አምጥቸ ስቀባው ዳነልኝ፡፡››* በማለት ተናግሯል፡፡ (አቶ ዳኘ ሰሬ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

ሌላኛዋ ሴት ደግሞ ስለጸበል ያለማትን ህልም እንደሚከተለው አጫውታኛለች፡፡

> *የሆነ አመት በእየቦታው በሽታ ገብቶ ሰውን እየፈጀው በእኛ አካባቢ ገብቶ ፈርተን ስንኖር አንድ ቀን ባለቤቴ ታመምኩ ብሎ ተኛ እኔም ልጆቸም በሽታ ገባ ብለን ወገባችን ተይዞ እምንሄኽበት ቅጡ ሲጠፋን አንድ ቀን ተኝቼ በህልሜ  አንቺ ባለቤትሽን ልብሱ የሚያብረቀርቅ ሰውዬ ተገደል ወንዝ ውሃ አምጥተሽ ጥመቂው ብሎ ሲለኝ ዞር ብዬ ሳየው የሌለ ይመስለኛል፡፡ ተዚያ በበነጋታው አብራኝ ለምትኖረው ተጧሪ እናቴ ስነግራት ሰውየው በሽታ እንዳልታመመ በሽታው መንፈስ እደሆነ እንድናስጠምቀው ነገረችኝ ተዚያ ገደል ወይን አካባቢ ከሚገኘው ጊወርጊስ ሻንዳ ጠበል ተጠምቆ ዳነ፡፡* (እማሆይ አበቡ ተገኘ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011አ.ም)

ከላይ የተጠቀሱት የህልም ሃሳቦች የሚያስገነዝቡት ጸበል በማህበረሰቡ ትልቅ የፈውስ ማግኛ ዘዴ እንደሆነ በሰፊው ስለሚታመን ሰው ሲታመም ስለእሱ ማሰቡ ስለማይቀር በህልም አማካኝነት ሃሳባቸው እንደሚውጣ እና ከጭንቀታቸው በላቀቅ እንደቻሉ ነው፡፡

**9. እሾህ፡-** እሾህ በሰውነት አካል ላይ ጉዳት የሚያደርስ ሹል ነገር ሲሆን የተለያዩ የእሾህ አይነቶች አሉ፡፡ እነዚህም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የሚታወቁ እና ለአጥር የሚጠቀሟቸው የአጣጥ እሾህ፣ የአጋም እሾህ፣ የግራር እሾህ፣ የአደር እሾህ ጥቂት እና ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡ እሾህ ሲወጋን ትክክለኛውን አረማመዳችንን በማጥፋት ያሽበከብከናል፤ ሽባ ያደርገናል ወይም ላያስራምደን ሁሉ ይችላል፡፡ እሾህ ሲወጋን ለሞት ሊያደርሰን ይችላል፡፡ ስለሆነም በተጠናው ማህበረሰብ እሾህ በህልም ሲወጋ ምቀኛ ነው ይባላል፡፡ ምቀኛ ደግሞ ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች ሊወክል የሚችል ነው፡፡ ምቀኛ የቻለውን ሁሉ በማድረግ የሚመቅንበትን ሰው ለማጥፋት የሚሞክር ነው፡፡ ስለዚህ በህልም እሾህ መሸከም እና መውጋት የምቀኛ መኖርን እና ምቀኛ ማፍራትን የሚወክል ሲሆን በህልም እሾህ ማቃጠል ምቀኛን ማስወገድ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

**10. እርሻ፡-** እርሻ የምንለው ገበሬው በሬዎቹን ጠምዶ የሚያርሰውን እርሻ ነው፡፡ ነገር ግን በህልም ማረስ እራሱን የቻለ ፍቺ እና ትርጉም አለው እርሻ የማገላበጥ ስራ ነው፡፡ ስለሆነም አፈር ደግሞ የሰውን ልጅ ይወክላል፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንዳሉት እርሻ በህልም ማረስ የሰው ሞት ነው፡፡ ምክንያቱም ሲሞት የሚቀበረው የሰው ልጅ ብቻ ስለሆነ በህልም እርሻ የመቃብር ዝግጅትን የሚያመለክት ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ እርሻ በህልም ማረስ በሁለት መንገድ ይታያል፡፡ በህልም በብዙ ማረስ እና በህልም በትንሹ ማረስ ናቸው፡፡ መረጃ ሰጭዎች እንደገለፁት በህልም ብዙ ማረስ የዘመድ ሞት ነው ብዙ ያስለቅሳል፣ ያሳዝናል፡፡ በህልም ትንሽ ማረስ ደግሞ የሩቅ ወይም ዘመድ ያልሆነ የባዳ ሞት ነው ትንሽ እንባን ያመለክታል በማለት ይገልፁታል፡፡ አንዳንዶቹ መረጃ ሰጭዎች ደግሞ እርሻ በህልማቸው ሲያርሱ ካደሩ በዚሁ ቀን በበነጋታው የባድም ይሁን የዘመድ ቀብር እንደሚውሉ ይናገራሉ፡፡

**11. ሽንት፡-** በህልም ሽንት መሽናት በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በሁለት መንገድ ይታያል፡፡ አንደኛው በብዛት በህፃናት ላይ የሚታይ ነገር ሲሆን መናፈቃቸውን የሚያመላክት በህልማቸው ሲሸኑ እያዩ እዛው እንደተኙ በእንቅልፋቸው ሽንታቸውን ይሸናሉ፡፡ ይኸውም የሆነን ሰው እንደናፈቁ የሚገልጽ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የትልልቅ ሰዎች ህልም ነው፡፡ ይኸውም በህልም

ሽንት መሽናት የዘር መተካትን፣ መውለድን፣ ዘርን ማብዛትን ወይም መዋለድን ያሳየናል። ሽንት በህልም መሽናት ደጋግሞ ልጅን መውለድ፣ የልጅ ልጅ ማየትን ይወክላል በማለት መረጃ ሰጭዎች ያናገራሉ። የሚከተለውን ህልም እንመልክት፡-

‹‹ *ቆይቷል በህልሜ ተደብረወርቅ ትልቅ የገበያ ዋርካ ላይ ቆሜ ስሸና በህልሜ አየው። ተዚያ አንዲት ልጄ ደብረወርቅ አግብታ ህዳ ብዙ ልጆች ወለደች። የልጅ ልጅ ሁሉ አድርሳ እንግዲህ እኔ ቅማንት ሁሉ ደርሻለሁ።›› *(አቶ ባየ መኮነን፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ዓ.ም)

ሃሳቡ የሚያሳየው ሽንት በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በአስተሳሰብ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው መሆኑን ሲሆን የዘርን መተካት እና የመውለድ እና መዋለድን ትርጉም የያዘ መሆኑን ነው።

**12. ጨለማ፡-** አንድ አንድ የህልም ትምዕርቶች ቀጥታ ታልመው ቀጥታ የሚተረጎሙ ሲሆኑ አደራረሳቸውም ቀጥታ ነው። ከእነዚህ ማህበረሰባዊ ትዕምርቶች መካከል አንዱ ጨለማ ነው። ጨለማ በህልም ማየት ያው ጨለማ ነው። ጨለማ በህልም ውስጥ ጥሩ ያልሆነን ነገር የሚወክል ነገር ነው። በህልም ጨለማው ሲጋፋን ማየት ደግሞ በህይወታችን ውስጥ የተጋረጠብንን ድህነት፣ ጤና ማጣት፣ ሰላም ማጣት፣ ፍቅር ማጣት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት አሉታዊ ነገሮች መወገዳቸውን የሚያሳይበት መንገድ ነው። የሚከተለውን የእማሆይ ይረብ አወቀን ህልም እንመልከት፡-

‹‹ *በህልሜ ስኽድ ስኽድ ብርሀኑ እየሸሸኝ፣ ቀኑ ተሎ እየመሸብኝ እና ጨለማው እየተሻማኝ አየሁ። ተዚያ አሁን አይኔ ጠፍቶ ተቤት ዋልኩ።››* (እማሆይ ይረብ አወቀ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ዓ.ም)

በህልም ጨለማን ተራምዶ መሄድ፣ በህልም ጨለማ እንዳይደርስብን ማምለጥ (መሸሽ) ከሆነ ከችግር የመራቅ፣ የመሸሽ እና የመላቀቅ ምሳሌዎች ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ በህልም ወደ ጨለማ መግባት፣ ጨለማ ማየት እና መንካት፣ በጨለማ ውስጥ መኖር በአሉታዊ ጎኑ ጥሩ ያልሆነ ክስተት በህይዎታችን እንደሚመጣብን እና የሆነ ነገር እንደሚገጥመን ያሳየናል በማለት መረጃ ሰጭዎች ይገልጻሉ።

**13. እሬሳ፡-** እሬሳ የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ ያለውን በድን የሚመለከት ነው። አንድ ሰው በቁመናው እያለ ሳይሞት እና ሙቶ ያለው ክብደት በእጅጉ የማይገናኝ ነው። ስለሆነም

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እሬሳ በህልም ውስጥ እራሱን የቻለ ሚና አለው። በተለይም የሴት ልጅ እሬሳ በህልም ውስጥ ከፍተኛ ትርጉም ይሰጠዋል። መረጃ አቀባዮች እንደገለፁት በህልም የሴት እሬሳ ማየት አገሩ አዝመራ እንሚሆን ይናገራሉ። ይኸውም ሴት የምትወልድ የምትከብድ፣ የምትራራ የምትበዛ ፍጡር ስትሆን እሬሳ ደግሞ የሚከብድ ነገር ስለሆነ ቢዛቅ የማያልቅ ምርትን ይወክላል ብለዋል። የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹በህልሜ ተጓሮ ገደል ወደ ዲንቺ የሴት እሬሳ ሲገባ አየው። ተዚያ ጥሩ ህልም ሆነ››* (አቶ ፈንቴ እንዳለው፡ *ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 ኢ.ም)

ከላይ ያለው ህልም ከአራራ ቀበሌ የተገኘ መረጃ ሲሆን ጓሮ ገደል እና ዲንቺ የአራራ ጎጦች ናቸው። በህልም እሬሳ (የሴት እሬሳ) ምርትን ያመለክታል። እንደመረጃ አቀባዮች አባባል እሬሳ የማይቻል እና በጣም ከባድ ነው፤ ሴት ደግሞ ዘርን መተካት እና ማብዛት የምትችል ስለሆነች በምርት ማምረት ትመስላለች ብለዋል።

**14. ምሰሶ፡-** ምሰሶ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ቤት ሲሰራ ቤቱ እንዳይወድቅ በሚል ቤቱን ግራ እና ቀኝ ደግፎ እንዲይዝ የሚደረግ ጠንካራ፣ቀጥ ያለ እና ወፍራም እንጨት ነው። ምሰሶ አንድ ቤት ደግፎ በመያዝ ቤቱ እንዲቆይ ማድረግብዙ ዘመን (ጊዜ) እንዲያገለግል ለማድረግ ጥቅም አለው። ምሰሶ የቤት ዋና አካል ነው። ስለዚህ በተጠናው ማህበረሰብ ምሰሶ በህልም ውስጥ እራሱን የቻለ ትርጉም፣ፍቺ እና አገልግሎት አለው። በህልም ውስጥ ፍቺው እና ተግባሩ አወንታዊ እና አሉታዊ ነው። አወንታዊ ምሰሶ በህልም ማቆም ባል ማግባት ሲሆን ምሰሶ በህልም መውደቅ የባል ሞት ነው። የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹በህልሜ ጋሻው ልጄ የእኛን ቤት ምሰሶ ቆርጦ ሳንቃውን ሊያወጣው ቢል አንብድዶ እምቢይ ብሎት ሲቀር አየውት። ተዚያ ባለቤቴ አዲስ አበባ ጠፍቶ ኸደ ዱርዬ ሰርቆት መቶ ታሞ ሞተ። ምሰሶው እሱ ነው። ሳንቃው እኔ ነኝ። እኔ በህይወት እስታውን አለው። እሱ ግን ሞተ።››* (እማሆይ ዋለ ገረመው፡ *ቃለ-መጠይቅ፣መጋቢት* 2010ኢ.ም)

የተገለጸው ህልም የሚያስረዳው ምሰሶ በቤት ውስጥ መሪ፣ አስተዳዳሪ እና ዋና ሃላፊነት ያለውን ሰው የሚመለከት ሲሆን ሳንቃ ደግሞ የቤትን ገበና የሚሸፍን ስለሆነ ሴትም የቤትን ሁሉ ነገር ከወንዱ በተሻለ ውስጥ ሚስጢር የምታውቅ እና የምትሸፍን መሆኗን ያመላክታል። በአጠቃላይ የእናርጅ እናውጋ የህልም ውስጥ ትዕምርቶች የማህበረሰቡን አስተሳሰብ፣

አመለካከት እና እውቀት በመሸከም ማህበረሰቡ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በባህላዊ፣ በስነ-ልቦናዊ እና በፖለቲካዊ ጉዳይ ያለውን ግንዛቤ ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ትዕምርቶች መንፈሳዊ እና ቁሳዊ የሆኑ የማህበረሰብ ማንነቶችን ጠቅለል አድርጎ በመያዝ በአንድ ጊዜ ብዙ መልክት መያዝ የሚችሉ ናቸው፡፡ ትዕምርቶች ማህበረሰቡ የፈጠራቸው እና የሚገለገልባቸው የሃሳብ እና የእውቀት ወኪሎች ናቸው፡፡

**15. ፉከራ እና ቀራርቶ፡-** በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ፉከራ እና ቅራርቶ በሰርግ፣ በቤት ስራ፣ በጥምቀት በአል፣ በመስቀል በአል፣ በክርስትና፣ በምርቃን፣ በእርገት በአል፣ በደቦ፣ በተለያዩ ድግሶች…ወዘተ በመሳሰሉት ሁኔታዎች የሚከወን ከሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ ነው፡፡ ፉከራ እና ቅራርቶ በዚህ ማህበረሰብ በወንዶች የሚከውን ሲሆን በአብዛኛው ጀግንነትን፣ ወኔን፣ አሸናፊነትን፣ ጠንካራነትን፣ አይበገሬነትን በግጥም እያነሳሱ የሚሸልሉበትን የደስታ መግለጫ ነው፡፡ ፉከራ እና ቀራርቶ በአብዛኛው በቡድን የሚተገበር ተግባር ነው፡፡ ፉከራ እና ቀረርቶ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አቅራሪታ እና ፎካሪ እንዲሁም አድማጭ በመሆን የሚተገብሩት ነው፡፡ ይህን ክዋኔ ከማህበረሰቡ መካከል በጣም ይችላሉ የሚባሉ ሰዎች ያሉ ሲሆን በተቃሪኒው ደግሞ አይችሉም ተብለው የሚፈረጁ ሰዎችም ከእነዚያ ሰዎች አይጠፉም፡፡ በፉከራ እና በቀራርቶ ባህላዊ ክዋኔዎች ላይ የማህበረሰቡ አስተሳሰቡ እና አመለካከቱ ያረፈባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ነገሮች በማህበረሰቡ የህልም እሳቤ ውስጥ ሲንጸባረቁ (ተግባራዊ ሲሆኑ) ይታያል፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ፉከራ እና ቀራርቶ በህልም ውስጥ የእራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ ይኸውም በህልም ማቅራራት እና መፎከር ማልቅስ የሚል ፍቺ ያለው መሆኑን መረጃ ሰጭዎች ይናገራሉ፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች የተገኘውን ህልም እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

> *ተኝቼ በህልሜ ብቻዬን አቅራራለው እፎክራለው ይመስለኛል፡፡ ተዚያ የሚቀበለኝ ሰው የለም ዞር ዞር ብዬ ሳይ ትንሽ ወንድሜ አለ ግን ዝም ብሎ እያየ አይቀበለኝም፡፡ ተዚያ በእውኔ እንደምሆነው ይገርመኛል፡፡ ተዚያ ህልሙን አይቼ በበነጋው የእህቴ ልጅ ልጆቹን አፍስሶ ሙቶ እኔ ሳልሰማ ተቀብሯል፤ በሳልስቱ ተጠርቼ ዘመዱ ሁሉ ቀብሮት እኔ ብቻዬን ህጂ ከመቃብሩ ቁሜ አለቀስኩኝ፡፡* (አቶ አያሌው ወንዴ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ *መጋቢት* 2011ዓ.ም)

ሃሳቡ የሚያስረዳው የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በህልም ቀረርቶ እና ፋከራ ሲቅራራ እና ሲፎከር ከታደረ በእውን የሚሆነው ሰው ሙቶ በቀብሩ ማልቀስ እንደሆነ የሚያምን መሆኑን ነው፡፡ ይህ ማህበረሰብ ቀራርቶ እና ፋከራ እና ልቅሶን በክዋኔያቸው በማገናኘት እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች የተመለከተ ህልም ሲታለም እንደሚፈታ ያሳያል፡፡ በማህበረሰቡ ቀራርቶ እና ፋከራ በአንድ እና በሁለት ሰዎች የማይካሄድ ሲሆን የቀብር ክዋኔም እንደዚሁ በአንድ በሁለት ሰው የሚደረግ ስላልሆነ ተመሳሳይነት ስላላቸው በሚል አስተሳሰብ ነው፡፡

## 5.2.10 ህልም ምን ገጽታ አለው?

ህልም ብዙ አይነት ገጽታዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡ በመሆኑም ከእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ህልም ሁለት አይነት ገፅታዎች አሉት፡፡ እነርሱም፡- አወንታዊ እና አሉታዊ ገፅታዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የህልም ገጽታዎች ከማህበረሰቡ የህልም አፈታት ሁኔታዎች አንጻር የተገኙ ናቸው፡፡ ገፅታዎቹ ከምንም በላይ መጀመሪያ የአላማውን ማንነት የሚገልጹ ናቸው፡፡ የህልምን ገጽታ አወንታዊነት እና አሉታዊነት ለማወቅ የህልምን ፍቺ ማወቅ እና አደራረስ (ተግባራዊ ሲሆን ማየት) ተገቢ ነው፡፡ የህልም ገጽታ የማህበረሰቡ ሁለገብ ጉዳይ የሚገለጽበት መንገድ ነው፡፡ የህልም ገጽታ የትዕምርቶችን ውክልና ከማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት አገላለፅ መሰረት በማድረግ የሚመጣ ገጽታ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለስነ-ልቦና ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ይኸውም በህልሞች አወንታዊ እና አሉታዊ ገጽታ ምክንያት ሰዎች በርካታ ስሜቶችን ያስተናግዳሉ፡፡ እነዚህ ስሜቶችም ደስታ እና ሃዘን የሚታይባቸው ሲሆን የማህበረሰቡን ስነ-ልቦና የሚመረምሩ ናቸው፡፡

የማህበረሰቡ ስነ-ልቦናዊ ማንነት ደግሞ በውስጡ በርካታ ነገሮችን በማካተት የአላሚውን ሁለንተናዊ ህይዎት መግለፅ ይችላል፡፡ የህልም ገፅታ ከሰው ልጅ ስነ-ልቦና ጋር በእጁ የሚቀራረብ ነው፤ የሰው ስነ-ልቦና ምን እንደሚመስል የሚገልጽ ነው፡፡ ስነ-ልቦና ደግሞ የሰው ልጅ ውስጣዊ ማንነት ከመግለፅም በላይ ያለውን ጠቅለል ያለ በህይዎት ላይ ያለውን አስተሳሰብ፣ አመለካከት እና ፍልስፍና የሚመረምር ነው፡፡ ስነ-ልቦና የአስተሳሰብ መንገድ፣ የማወቅ ችሎታን፣ የመስራት ተነሳሽነትን፣ ምኞትን የማዎቅ፣ ክህሎትን፣ በሚታዩት እና በማይታዩት አለም ላይ ባሉት ነገሮች ያለውን የግንዛቤ መጠን፣ ያለውን ፈጠራ የመፍጠር አቅም፣ የማፍቀር፣ የመደሰት እና የማዘን ሁኔታ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ነገሮች የሚመለከት ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡

ህልም የሀሳቦች፣ የአመለካከቶች የአስተሳሰቦች፣ የፍላቶች እና ምኞቶች፣ የጭንቀት፣ የስዕሎች፣ የደስታዎች እና የሀዘኖች ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ የተለያዩ ነገሮች  ማያ እና ማጉያ መነፀር ነው፡፡ ስለሆነም የሰውን ስነ-ልቦና ለማዎቅ ከሚያግዙን መንገዶች አንዱ ህልም ነው፡፡ ህልም ደግሞ የሰዎች ፍላጎት፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ ወግ፣ ልማድ እና ባህል የተከለከሉ እና የሚደረጉ ነገሮች በአላሚው አማካኝነት ጎልተው የሚወጡበት መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም ህልም በርካታ ጉዳዮች መግለጫ መንገድ በመሆኑ ሰዎችን በቀላሉ ለመረዳት እና ለመገንዘብ፣ ለማገዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ህልም አወንታዊም ይሁን አሉታዊ ገፅታ በስነ-ልቦና ሊታይ የሚችል ነው፡፡ ሰዎች እንዲኖራቸው እንዳይኖራቸው የሚፈልጉትን ነገር ለማወቅ እና ለመረዳት ስነ-ልቦናዊ ጥናት መካሄድ የመጀመሪያው ስራ ነው፡፡

ጠቅለል ሲል የህልም ገጽታ የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ጉዳይ የሚይዝ ሲሆን በተለያዩ ዘርፎች ሊገለፅ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ  ፖለቲካዊ፣ በባህላዊ፣ በስነ-ልቦናዊ መንገዶች ሊገለፅ ይችላል፡፡ ስነ-ልቦና ደግሞ ሌሎች ጉዳዮችን ሊጠቀልል የሚችል ሲሆን የሰዎችን ኢኮኖሚያዊ  ሁኔታ፣ ያላቸውን ማህበራዊ መስተጋብር፣ በፖለቲካው ዘርፍ ምን ያህል ተሳታፊ እንደሆኑ ልናውቅ እና ልንረዳበት የሚችልበት መንገድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በጥሩ እና በመጥፎ ጎኖች የሚፈረጅ ነው፡፡

## 5.3 በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ማን ያያል?

ህልም የእናርጅ እናውጋ ማኅበረሰብ የፎክሎር ቡድን የሚተገብረው፣ የሚያስተላልፈው፣ የሚያምነው፣ የሚያከብረው፣ የቡድኑ አባላት ዕርስ በዕርሳቸው የሚግባቡበት ዘመን ተሻጋሪ ትውፊት ነው፡፡ ይህ ማህበረሰብ በህጻንነቱ፣ በወጣትነቱ እና በእርጅናው ዘመን ምን ሰርቶ እንደሚያልፍ፣ እንደሚያደርግ የራሱን የዘመን ቀመር በመጠቀም በጊዜው የሚሰራቸው ስራዎች አሉት፡፡ ስለሆነም ይህን የህይወት ኡደት ደግሞ ማንኛውም ህይወት ያለው ሰው ሳይዘለው የሚያሳልፈው ሂደት ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ህልም የሚያልም ሁሉም ሰው እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ይኸውም ከህፃናት እስከ አሮጌዎች የእድሜ ደረጃ ቀለም፣ ስራ እና ጾታ ሳይለይ እንደሚታለም አሳይቷል፡፡ ይህ የማህበረሰብ ክፍል በህይወት ሲኖር ማሰብ፣ መስራት፣ በጋራ መኖር፣ ማዘን፣ መደሰት ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን ተግባራት እስከፈፀመ ድረስ እንደ ሁኔታው የእያንዳንዱ ግለሰብ የህልሙ ይዘት ይለያያል እንጂ ህልም ማንኛውም ሰው እንደሚያይ ነው፡፡ ከተጠኚው ማህበረሰብ የተገኘውን መረጃ  እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

*ህልም ሰው ሁሉ ያያል። ግን አንዱ ሌላ ሌላው ደሞ ሌላ ነው የሚያየው። ተማሪው በትምርቱ፣ ገበሬው በግብርናው፣ ቄሱ በቅስናው፣ ነጋዴው በንግዱ ብቻ ማሰብ የጀመረ ሰው ሁሉ ህልም የማያልም የለም። አንዳንድ ሰው በተለይ በመንፈሳዊ የበቁ ሰዎች ተአምላክ ጋር ለመገናኘት ‹‹ህልመ ዮሴፍ›› የሚባል ድጋም አለ እሱን ድጋም በመድገም ቁልጭ ያለ ህልም ያልማሉ። የሚያልሙ ሰዎችንም አውቃለው።* (መ/ሪ ስማቸው አሞኘ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

የተገለጸው ሃሳብ የሚያስገነዝበው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ሁሉም ትንሽ ትልቁ፣ ህጻን አዋቂው፣ ሴት ወንዱ፣ ቀዩ ጥቁሩ ሰው፣ ወፍራሙ ቀጭኑ፣ ረዥም አጭሩ...ወዘተ ሁሉም የማህበረሰቡ አባል እንደሚያልም ነው። ሁል ጊዜ ባይሆንም በዚህ ማህበረሰብ በተለይም በአንድ አመት ውስጥ ብዙ (በርካታ) ህልሞችን አንድ ሰው ያያል የሚል እምነት አለ። ሁሉም ሰው በአለበት ደረጃ ያልማል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በዚህ ማህበረሰብ ‹‹ዛሬስ ሲያቀባዥረኝ አደረ›› የሚባል አባባል ከእያንዳንዱ ግለሰብ ንግግር ውስጥ አይጠፋም። ይህ አባባል በማህበረሰቡ ዘንድ ሰፊ ይዘት ያለው ጽንሰ ሃሳብ እንደሆነ መረዳት አያዳግትም። የአባባሉ ይዘትም በዚህ ማህበረሰብ አንድ ሰው በአንድ ሌሊት የመኝታ ጊዜ ውስጥ ብዙ ህልሞችን እንደሚያልም ያመለክታል። ‹‹ሲያቀባዥረኝ›› ማለት በማህበረሰቡ አስተሳሰብ ከአንዱ ህልም ወደ አንዱ ህልም መወሰድ እና አንዱን ህልም መነሻችን እስኪጠፋን ድረስ ለብዙ ደቂቃ ማለም ነው። ስለሆነም እያንድንዱ የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ለህልም ትኩረት እንደሚሰጠው ያስገነዝባል። ህፃናት ጓደኞቻቸው ጋር ስላላቸው አጠቃላይ ግንኙነት ሊያልሙ ይችላሉ። አዋቂዎችም ስራቸው ከፍ ያለ እና የሰፋ ውጥረት ያለበት ሲሆን ማለትም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ስለሆኑ ነገሮች ስለሚያስብ በብዛት ሊያልም ይችላል። ነገር ግን ይድረስ አይድረስ ላይታዎቅ ይችላል። ይህን ሃሳብ ታምሩም በሚከተለው ሃሳቡ ይደግፈዋል። ስለሆነም ከተጠቀሰው ሃሳብ ጋር በተያያዘ ታምሩ በናይል መጽሄት ላይ (2007፡9) የሚከተለውን ሃሳብ አስፍሯል።

> ህፃንም ሆነ አዋቂ ሴትም ሆነች ወንድ፣ እይነስውርም ሆነ አይናማ ብቻ ማንኛውም ሰው ህልምን ያያል። ጥናቶች እንዳውም እያንዳንዱ ሰው በአንድ ሌሊት ብዙ አይነት ህልሞችን እንደሚያይ እያንዳንዱም ህልም በአማካኝ ከ5-20 ደቂቃ እንደሚረዝም አረጋገግጠዋል። ከዚህም በመነሳት በአለም ላይ ካለው የአንድ ሰው አማካይ እድሜ

ውስጥ 6ቱ አመት የሚሆነው ህልም በማየት እንደሚጠፋ ይገመታል፡፡ በማለት አስፍሯል፡፡

ሌላው ደግሞ በዚህ ማህበረሰብ ከብዙሃኑ የማህበረሰቡ አባል ለየት ብለው ‹‹ህልመ ዮሴፍ›› ድግምትን ተጠቅመው ህልምን የሚያልሙ ሰዎች አሉ፡፡ ‹‹ህልመ ዮሴፍ›› ድጋም በዕራዩ ማሪያም፣ በታምረ ማሪያም፣ በድርሳነ ሰሎሞን፣ በመፍትሔ ሥራይ መጽሀፍቶች ውስጥ 1-7 ገጽ የሚሆን በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈ ጽሁፍ ሲሆን እራሱን የቻለ መጽሀፍ እንደሌለው ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ እራስን ከተለያዩ ነገሮች ንጹህ በማድረግ የሚደገም ሲሆን አደጋገሙ እራሱን የቻለ ሂደት ያለው መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ከማህበረሰቡ የተገኘው ሌላኛው መረጃ ደግሞ እንደሚከተለው ነው፡፡

> *ህልም የማያልም የለም፡፡ ግን ህልሙ ሁሉ አንድ አደለም፡፡ በጣም ጠጋው የበዛለት ጠጠር ጠጠር ያለ ህልም ያልማል፡፡ ማለቴ እንደ አያ ቢተው ሰው አገኝ ያለ ሰው በመንደራችን የሚመጡ ጥሩ እና መጥፎ ክሳቴዎች ሲኖሩ ህልሞችን እያየ ይናገራል፡፡ እንዳውም አያ ቢተው ብርቱ ሰው ነው ድርቅ ሲሆን ሲበልግ ሲሆን ያሳየዋል፡፡ ሌላውም እንደ ሰውነቱ ያያል፡፡* (አቶ አቻምየለው ፈንታውን፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011ዓ.ም)

የተገለጸው ሃሳብ የሚያስረዳው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልምን ሁሉም ሰው እንደሚያልም ሲሆን የህልሙ ይዘት ግን ልዩነት እንዳለው ነው፡፡ እንዳንዱ ስለራሱ እራሱ ያለበትን ሁኔታ የሚገልጽ ህልም የሚያልም ሲሆን አንዳንዱ ደግሞ ከራሱ ባለፈ ስለሌላው ሰው አልፎም ስለሃገሩ ሁኔታ የሚያትቱ እና የሚመለከቱ ህልሞች እንደሚያልሙ መረጃው ያሳያል፡፡ እነዚህ ሰፊ ይዘት ያለው ህልም እንዲያልሙ የሆኑት ሰዎች ደግሞ በልዕለ ተፈጥሮ ሃይል በመመረጥ እንደሚያልሙ ማህበረሰቡ ይታመናል፡፡ አመራረጣቸውም ጥሩ ጎናቸው በዝቶ በመታየታቸው እንደሆነ በማህበረሰቡ ይገመታል፡፡

ከዚህ አንጻር ህልም ለዚህ ማህበረሰብ የግለሰቦችን ምኞት፣ ፍላጎት፣ የወደፊት እቅድ እና የአኗኗር ዘይቤ ሲያስቡ፣ ሲያሰላስሉ፣ ሲጨነቁ በአጠቃላይ ምን መሆን እንደሚፈልጉ በውስጣቸው ያለውን ሃሳብ የሚያውጡበት መንገድ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች በማህበረሰቡ ጥሩ እና በጥፎ ተብለው የተመደቡ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህን ነገሮች እያንዳንዱ የማህበረሰብ አባል የሚመራባቸው፣ የሚያምናቸው እና ስምምነት ፈጥሮ የሚያከብራቸው

ናቸው። ስለሆነም አንዱ የማህበረሰብ አባል እነዚህን ነገሮች ሳያከብራቸው ሲጥሳቸው በአብዛኛው እምነትን የሚመለከቱ ስለሆኑ በሰውየው ላይ የተግሳጽ ተግባር በህልም አማካኝነት ይደርሰዋል።

በአጠቃላይ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እምነት ሰዎች ባሉበት የእድሜ ክልል (ደረጃ)፣ ያሉበት ዘመን እንደሚያሳያቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ህልምን እንደሚያልሙ ነው። ህልም ለዚህ ማህበረሰብ የፍላጎቱ፣ የሃሳቡ፣ የአስተሳሰቡ፣ አመለካከቱ፣ የእምነቱ፣ የምኞቱ፣ የፈጠራው…ወዘተ የመሳሰሉት ነገሮቹ ነጸብራቅ ነው።

## 5.3.1 የህልም ማያ ወሳኝ ጊዜ መቼ ነው?

በተጠናው ማህበረሰብ ህልም ማህበረሰቡ ከሚያስበው፣ ከሚተገብረው፣ በህይወቱ እንዲሆንለት ከሚመኘው ነገር፣ አጥብቆ ከሚያመልከው እና ከሚያምነው፣ የሆነ ምላሽ ከሚያገኝበት፣ ከሚሳካለት ጉዳይ፣ በሰፊው ከሚያውቀው እና ወደፊት እንዲያውቀው ከሚጓጓለት ነገር፣ አንድን ነገር አድርጎት፤ተግባር ላይ አውሎት ጠቅሞት ወይም ጎድቶት የጠቀመው እንዲደግመው እና የጎዳው ነገር ተመልሶ እንዳይመጣበት ከሚያስበው ሃሳብ፣ ከሚደሰትበት፣ ከሚያዝንበት ነገር አንስቶ የሚያልመው መሆኑ ከማህበረሰቡ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

በመሆኑም የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ደግሞ እራሱን የቻለ ጋብቻ የሚፈጽምበት፣ የሚሰራበት፣ ምርት የሚያመርትበት፣ የሚዘራበት፣ የሚያጭድበት፣ በአላትን የሚያከብርበት፣ የሚጫወትበት፣ የሚዝናናበት፣ እርቅ የሚፈጽምበት፣ ማህበራዊ ህይወት የሚኖርበት፣ ልጅ የሚወልድበት፣ የተለያዩ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ትሩፋቶችን የሚፈጽምበት ጊዜ አለው። ስለዚህ እነዚህ ደግሞ የተለያዩ ጉዳዮች እንዲፈጸሙ ምክንያት ናቸው። እንደ ደስታ፣ ሃዘን፣ ሃሳብ፣ ምኞት፣ ፍላጎት እና በተለያዩ ነገሮች የተሞሉ ስሜቶች ከጊዜ ጋር ወቅታቸውን ጠብቀው የሚመጡ ናቸው። እነዚህ ደግሞ በሰዎች ህይወት ውስጥ ልዩ ድርሻ አላቸው። በህይወት ሂደት ውስጥ አንዳች ነገር በመፍጠር ሰዎችን ለሆነ ስራ ያነሳሳሉ፣ እንዲፈጽም ይገፋፋሉ። ይህ ደግሞ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ስነ-ልቦናዊ ተግባር አለው። ስነ-ልቦናዊ የሆነው ጉዳይ በተለያዩ መንገዶች ወደ ውጭ ይወጣል። ከእነዚህ የሰው ውስጣዊ ስሜት መውጫ መንገዶች መካከል ህልም አንዱ ነው። ህልም የሰዎችን የደስታ፣ የሃዘን፣ የስራ፣ የማግኘት፣ የማጣት፣ የማግባት፣ የመውለድ፣ የመዳን (የመፈወስ እና የማገገም)፣ የመሞት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን

ጉዳዮችን መሰረት የሚያደርግ ስለሆነ እነዚህ ነገሮች ደግሞ ጊዜን መሰረት አድርገው የሚፈጸሙ ስለሆኑ ጊዜ ትልቁን ሚና ይጫወታል፡፡ ስለሆነም የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰቦች ህልምን የሚያዩት በዘፈቀደ አይደለም፡፡ ህልም የሚታለመው ታስቦ እና ታቅዶ ባይሆንም ለአላሚው ግን ህልም የሆነ ግብ እና አላማ አለው፡፡ በአንድ በኩል የሰውየውን (የአላሚውን) ድብቅ ፍላጎት በማውጣት እርካታ እና እፎይታን ሲፈጥር በሌላ በኩል ደግሞ የአላሚውን የወደፊት የህይወት እጣፈንታ ማሳያ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ህልም ክፉንም ጥሩውንም የሚያሳይ ስለሆነ ጊዜ (ወቅት) ወሳኝ ነገር ነው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ለማለም በእንቅልፍ ወቅት የሚታለፍባቸው ሂደቶች አሉ፡፡ ስለሆነም ከማህበረሰቡ የተገኘውን መረጃ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

> *ህልም እንደተኛን ሳይቆይ የሚታይ አደለም መጋደም እና ጧ ያለ እንቅልፍ መውሰድ የተለያየ ነው፡፡ ህልም የሚታየው እንቅልፍ በወሰደን በማንለማ በማንሰማበት ጊዜ ሲሆን እንዳው በግምት በብዛት ከ8-11 ሰአት ባለው ይታያል፡፡ ተስምንት በፊትም በስራ እና በጨዋታ ስለሚቆይ፣ ቢተኛም እንቅልፍ ውሰደኝ አትውሰደኝ የሚታገልበት ጊዜ ነው፤ ተአስራ አንድ ሰአት በኋላም በመንቃት እና ባለመንቃት መካከል ስለምንሆን የማይጠፋ ህልም አይታለምም፡፡ ተዚያስ ቅዠት ይታያል፡፡ ቅዠት ደግሞ ቅጥ የለውም፡፡ ወራቶችን ስናይ ደግሞ ሀምሌ እና ነሃሴ ዳፍንት ነው ተብሎ ስለሚታመን አይደለም ህልም ጠበል እንኳን የሚጠመቅ ስለማይኖር ህልም አይታይም ቢታይም አይደርስም ስለሚባል ትኩረት የሚሰጠው ሰው የለም፡፡ ተእነዚህ ወራቶች ውጭ ግን ህልም ይታለማል፤ በተለይ የካቲትን ግማሽ ይዞ መጋቢት፣ ሚያዚያ እና ግንቦት ወራቶች አባሽ ናቸው፡፡ ምክንያቱም እርሻ እና ዘር የሚታሰብባቸው ስለሆኑ ምን አይነት አዝርት እደሚዘራ ማወቂያ ጊዜ ስለሆነ ነው፡፡ ጥሩ እና መጥፎ ህልም የሚታለመው ደሞ በሙሉ ቀን እና በጎደሎ ቀን ሲሆን ነው፡፡ ሙሉ ቀን የሚባለው አመታዊ በአል የሆነ እና የቀኑ ቁጥር ሙሉ ቁጥር ተሆነ ሲሆን ጎደሎ የሚባለው ደሞ ቅድም ተነገርኩሽ በተቃራኒ የሆነውን ነው፡፡ ምሳሌ፡- በ29 ቀን የታየ ህልም ምንጊዜም መጥፎ ነው፡፡ 29 ቀን መጥፎነቱ ቀኑን ሳይሆን ሌሊቱን በመቁጠር የህልሙ መጥፎነት ይታወቃል፡፡ ሌሊቱ ጨለማ ስለሆ ነው፤ ቀኑ ደግሞ ብርሃን ነው፡፡* (ከቡድን ውይይት የተገኘ፡ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

ከላይ ያለው ሃሳብ የሚያስረዳው ህልም ማየት ዘፈቀዳዊ ሳይሆን ምክንያታዊ የሆነ ማያ ሰአት፣ ቀን እና ወር እንዳለው ነው፡፡ ማንኛውም ሰው የእኔ የሚለው እና ከሱ ውጭ የሆኑትን ጉዳዮች የሚለይበት የአኗኗር ዘይቤ እና የህይወት ግንዛቤ አለው፡፡ አንድን ነገር እንዲከተለው እና እንዲያምንበት የሚያደርገው የራሱ ምክንያት አለው፡፡ ይህ ደግሞ በጊዜ መሰረትነት ይተገበራል፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብም እራሱን የቻለ የህልም ማለሚያ ወቅት እንዳላቸው ከተሰበሰበው መረጃ ማወቅ ተችሏል፡፡ መረጃው እንደሚያሳየው ህልም የምናይባቸው ወራቶች እና ቀናቶች ወሳኝ እንደሆኑ እና ህልም ማለምም ሆነ መፍታት የራሳቸው ሚና እንዳላቸው ነው፡፡

## 5.4 በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ፈቺ ማን ነው? መቼ ይፈታል?

የህልምን ትክክኛነት ለማወቅ የህልምን ትርጉም እና ፍቺ ማህበረሰባዊ እውቀት፣ የዘመን ሁኔታ፣ የአላሚዎችን ማንነት በሚገባ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ ለአንዱ ሰው የሚታየው ህልም ለሌላኛው ሰው ላይታይ ይችላል፡፡ አንዳንዴ መመሳሰል ቢኖርም ሁልጊዜ መመሳሰል አይኖርም፡፡ አንዱ ህልም በተፈታበት መንገድ ሌላ ህልም መፍታት አይቻልም፡፡ የህልም ፍቺውም እንደዚሁ ለሁሉም ሰው አንድ አይነት አይደለም፡፡ ህልም ፈቺዎችም ከሚከተሉት የህይወት ፍልስፍን አንጻር አንድ አይነት የአፈታት መንገድ አይከተሉም፡፡ ስለሆነም ይህን የማህበረሰብ እውቀት በሚገባ ማውቅ እና መረዳት የሁነቶችን መፈጠር እና አለመፈጠረ ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ህልም ፈቺ ሰው በህብረተሰቡ ዘንድ የፈታው ህልም በተደጋጋሚ ትክክል እና እውነተኛ መሆን አለበት፡፡ በተለይም በዚህ ማህበረሰብ *‹‹እገሌ ያየው ህልም አንድም ሳይዛነፍ ይደርሳል እንደሚባለው ሁሉ እገሌ የሚፈታው ህልም ከመሬት ጠብ አይልም››* የሚባል ሰው አይጠፋም፡፡ ህልም ፈቺውም የተነገረው ህልም እና ፍቺው አንድ አይነት መሆን አለበት፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ህልም ፈቺ ሰው የሚፀልይ፣ የሚያስታርቅ፣ የሰዎች መጎዳት የሚሰማው፣ የሰዎች ማግኘት የሚያስደስተው በአጠቃላይ የሰዎችን ሀዘን እንደራሱ ሀዘን የሚያይ እና የሰዎችን ደስታ እንደራሱ ደስታ የሚመለከት፣ ሁሉንም ሰው እኩል የሚመለከት ሰው ህልም ፈቺ እንደሚሆን መረጃው ይገልፃል፡፡ ህልም ፈቺ በሁሉም ነገሩ አርያ እና አስተማሪ መሆን አለበት ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህ ደግሞ የሚመጣው ከመልካም አስተሳሰቡ ጀምሮ እስከ አተገባበሩ ያለው ጠቅላላ ሁኔታ ታይቶ እንደሆነ አያጠራጥርም፡፡ ህልም ፈቺ በአንድም በሌላም ማህበረሰቡ የጣለበትን ሀላፊነት መወጣት የሚችል ሰው እንደሆነ ይታመናል፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ፈቺ የሚሆን ሰው በሀይማኖቱ የተሻለ

ግንዛቤ ያለው (ፈርሀ እግዛብሄር) የሚያድርበት ሰው፣ በህይዎቱ ሲኖር የተለያዩ ፈተናዎችን ያለፈ ሰው፣ በእድሜ ታላላቅ የሆኑ ሰዎች ህልም እንደሚፈቱ መረጃው ያስገነዝባል፡፡ ህልም ፈቺ በዚህ ማህበረሰብ ፆታን ሳይለይ እድሜን፣ እውቀትን፣ አስተሳሰብን እና አመለካከትን መሰረት አድርጎ በመለየት ለህልም ፈቺዎች መደብ ይሰጣል፡፡

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም የሚያየው ሰው (የሚያልመው) ሁሉም ሰው ይሁን እንጂ ህልም የሚፈታ ግን ሁሉም ሰው እንዳልሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ህልም የሚፈቱ ሰዎች ከማህበረሰቡ አባላት መካከል ጥቂት ሰዎች ናቸው፡፡ ይኸውም በእድሜ ገፋ ያሉት (ታላላቆች)፣ የሀይማኖት አባቶች፣ በህይዎት ዘመናቸው የተፈተኑ፣ የህይዎትን ውጣ ውረድ አይተው ያለፉ፣ የኑሮን የተለያየ አቅጣጫ የመረመሩ ሰዎች፣ አግኝተው ያጡ ሰዎች፣ ሀዘን እና ደስታ የተፈራረቁባቸው ሰዎች በሀይማኖታቸው የበቁ ሰዎች ህልም እንደሚፈቱ ይናገራሉ፡፡

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ከሚያየው ሰው ይልቅ ህልም የሚፈታው ሰው ትኩረት እንደሚደርግበት መረጃው ያሳያል፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ህልም ፈቺዎች ህልምን የሚፈቱት በግዴለሽነት ከራሳቸው የህይዎት ልምድ አንፃር ስለሚሆን እነዚያን ሰዎች ለይቶ ማወቅ ጥንቃቄ ስለሚጠይቅ ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ ህልም ፈቺ ደግሞ በማህበረሰቡ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ ህልም ፈቺ የሚባሉት ከማህበረሰቡ በተለያየ ምክንያት ማለትም በመንፈሳዊ እና በቁሳዊ ምክንያቶች ከሌላው የማህበረሰብ አባል ነጥረው የወጡ ግለሰቦች ህልም ፈቺ ይሆናሉ፡፡ ህልም ፈቺ ሰው የማህበረሰቡን አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ ምኞት፣ የኑሮ ሁኔታ፣ የእውቀት ደራጃ፣ የአላሚውን የእድሜ ክልል፣ ስራ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ መሰረታዊ ነገሮችን ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ እና የሚያውቅ (የተረዳ) ሰው  መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ህልም ፈቺ ሰው እንዳው ዝም ብሎ ከመሬት ተነስቶ ህልም መፍታት አይችልም፡፡ ህልም ፈቺ ከሌላው በተለየ ትግዕስትኛ እና አስተዋይ የሰዎችን አጠቃላይ ሁኔታ በቀላሉ መረዳት የሚችል መሆን እንዳለበት ይናገራሉ፡፡ ህልም ፈቺ በዚህ ማህበረሰብ እራሱን ዝቅ በማድርግ ትህትና ያለው መሆኑን ማሳየት አለበት፡፡ ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ እምነት አንድ ህልም ፈቺ ህልም የመፍታት ስጦታ ከፈጣሪው የሚሰጠው ፀጋ ስለሚሆን ይህን ፀጋ ለማግኘት የህልም ፈቺው መልካምነት የጎላ ድርሻ እንዳለው ይታመናል፡፡

ከዚህ አንጻር በእናርጅ እናውጋ የማህበረሰብ ቡድን ውስጥ የሚኖር ሁሉም ሰው ህልም ፈቺ አይደለም፡፡ ከዚህ ማህበረሰብ መካከል እንደ ባቄላ ቅርጣን ነጥረው የወጡ የማህበረሰቡን ሁለገብ

ጉዳይ ሊረዱ የሚችሉ ሰዎች ህልም ፈቺ ናቸው፡፡ የዚህ ማህበረሰብ ህልም ፈቺ በአብዛኛው ህብረተሰቡ የሚያምነው፣ የሚፈታው ህልም ፍቺ በትክክል( ሳይዛነፍ) እውነትነቱ የሚያሳምን እና አደራረሱ (ሲደርስ) አንድ አይነት የሆነ ነው፡፡ በተጠናው ማህበረሰብ ህልም አላሚዎችም ህልም ፈቺ ይሆናሉ፡፡ ይኸውም እነዚህ ሰዎች በአብዛኛው ከህልም ጋር በሚኖራቸው ዘወትራዊ ትውውቅ ፣ልምምድ፣ ትስስር እና ትግበራ ህልምን መፍታት ይማራሉ፡፡

ስለሆነም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልምን የሚፈታ ሰው በተለያዩ ጉዳዮች የተሻለ ነገር ያለው ሰው ነው፡፡ ይኸውም ህልም የሚፈታ ሰው ከሌሎች ግለሰቦች በተሻለ በህይማኖቱ ጠንካራ አቋም እና እውቀት ያለው፤ የሚፀልይ፣ የሚያስታርቅ፣ እድሜ ጠገብ፣ መልካም አስተሳሰብ እና አመለካከት ያለው፣ በህይዎት መኖሩ እና መቆየቱ የሚያስደስተው፣ ሰዎችን ተናግሮ ማሳመን የሚችል፣ በተለይም በፈጣሪ የተመረጠ ሰው ህልም ፈቺ ይሆናል፡፡ መላከ ሰላም ዳምጤ 2011 ኢ.ም *‹‹ህልም የሚፈታ ሰው በፈጣሪ የተቸረው (ፀጋ የተሰጠው) ሰው እንጂ ማንኛውም ሰው ህልም አይፈታም አሊያም የራስን እና የሌላን ሰው ህልም የመፍታት ፍላጎት ሲኖር መጠለይ፣ መማጠን እና ፈጣሪን መለመን ያስፈልጋል፡፡›› በማለት* ተናግረዋል፡፡ (መላከ ሰላም ዳምጤ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም )

ይህ ሀሳብ የሚያስረዳው የህልም መፍታት ችሎታ የሚኖረን በፈጣሪ ስንመረጥ (የመፍታት ፀጋውን) ስናገኝ እንደሆነ ነው፡፡ ህልም መፍታት የሚችል ሰው ከፈጣሪ ፀጋውን ያገኘ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ነገሮች፣ ክስተቶች እና ጉዳዮች ላይ መመርመር፣ መሞከር እና መፈላሰፍ የሚችል ሰው ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በተደጋጋሚ ህልም የሚያዩ እና ከህልማቸው የሚደርስላቸው ሰዎች ከአላቸው ከህልም ጋር የዘወትር ትውውቅ ህልም መፍታት ይችላሉ፡፡ ከእድሜ አንፃር ስንመለከተው በአብዛኛው ህልም የሚፈቱት በእድሜ ገፋ ያሉት ሲሆኑ በአማካኝ ከ40 አመት በላይ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ከፆታ አንፃር ስናየው ደግሞ ሴትም ወንድም እንደሚፈታ ከእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ህልም መፍታት ተግባር የሚጀመረው ዝም ብሎ ከመሬት ተነስቶ አይደለም፡፡ መረጃው እንደሚያሳየው ህልም አስፈቺ ሲመጣ ህልምህን በቀጥታ ንገረኝ ሳይሆን ህልም ፈቺው የሚያደርጋቸው ዝግጅቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ያስገነዝባል፡፡ ይህን ሃሳብ በተመለከተ የሚከተለውን መረጃ እንመልከት፡፡

> *ህልም መፍታትም ሆነ ማስፈታት ወትሮ ያስጨንቅ ነበር ህልም አስፈቺው ተህልም ፈቺው ቤት ሲኸድ ህልም ፈቺዎች እንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ላለማስጨነቅ ህልም*

*አልፈታም እንዳይሉ ህልም ፈቺው ጨዋ እና ሴት ተሆነ አረቄ፣ ቡና እና የቡና ቁርስ ተይዞ ይኸዳል፤ ጨስ ተሆነ ደግሞ ውዳሴ ማሪያምን በመድገም ህልም ፍቺው እንዳይሰሳት ለማድረግ ይጥራሉ፤ የህልም አላሚውን የክርስትና ስም በመንገር ጠሎት እንዲያደርጉላቸው በማድረግ ጥሩው የህልም ፍች እንዲደርስላቸው መጥፎው የህልም ፍች እንዳይደርስ ይለፉ ነበር አሁን እንዳው ጨሶች ታልሆኑ ያ ሁሉ ነገር አሁን የለም እንደውም ወትሮ ህልም በባዶ ሆድ በጠዋት ይፈታ ነበር አሁን ተብልቶም ይፈታል ጊዜውም ህልም አላሚው ባስታወሰው ሰአት ሲናገር ይፈታል፡፡* ( ርዕስ ደብር መሪጌታ አባተ ንጋቱ፡ ከቡድን ውይይት፣ መጋቢት 2011አ.ም)

የተገለጸው ሃሳብ የሚያስገነዝበው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ማስፈታት እና ህልም መፍታት ለውጥ እንዳለው ሲሆን መፍታት እና ማስፈታት ተግባር በፊት ይደረግ የነበረው ነገር ሁሉ እየቀረ መምጣቱን ያስገነዝባል፡፡ ይህ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ማህበረሰቡ በህልም ላይ ያለው አስተሳሰብ እና አመለካከት እንዲሁም እምነት መቀነስ ያመጣው ክስተት እንደሆነ ያሳያል፡፡

## 5.4.1 የህልም ፈቺዎች ማህበራዊ ደረጃ

የሰው ልጅ ክብር ከሚገባው ፍጡሮች መካከል የመጀመሪያውን ድርሻ የሚይዝ ነው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በሁሉም የእድሜ ክልል ያለ ሰው የራሱ ማህበራዊ ተግባር እና ሚና አለው፡፡ ስለሆነም ሚናውን (ተግባሩን) የስራ ድርሻውን የሚወጣ የማህበረሰቡ አባል ወይም አንድ ግለሰብ የራሱ ማህበራዊ ደረጃ አለው፡፡ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ፈቺዎች የተለየ ክብር ከሚሰጣቸው እና ከሚከበሩ ሰዎች መካከል የሚመደቡ ናቸው፡፡ ይህ ሃሳብ ሌላው የማህበረሰብ አባል ክብር አይሰጠውም ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ህልም ፈቺዎች እንደ አስታራቂ የሀገር ሽማግሌዎች፣ እንደ ሀይማኖት አባቶች፣ እንደ እድሜ ባለፀጋዎች፣ በማህበረሰቡ አንድ አንድ ሀላፊነት ላይ እንደተቀመጡ (እንደተሾሙ) ሰዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ምክንያቱም ህልም የመፍታት ሚና እንደትልቅ ስራ የሚቆጠር በመሆኑ ነው፡፡

በተለይም ብዙ ጊዜ በማህበረሰቡ ውስጥ ህልም በመፍታት የሚታወቁ እና የፈቱት ህልም አንድም ሳይቀር የሚደርስ ከሆነ ለሚናገሯቸው ንግግሮች ሁሉ ሰዎች ትኩረት ሰጥተው

ያዳምጧቸዋል። ይኸው በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት፣ ታማኝነት እና ተቀባይነት እንዳላቸው ያመለክታል። ህልም ፈቺዎች በዚህ ማህበረሰብ የህልም ፈቺነት ሚና ብቻ ሳይሆን ያላቸው ሌሎች ተግባሮችንም ስለሚያደርጉ ሁለገብነታቸው ከምን ጊዜውም በላይ በማህበረሰቡ ላይ ተቀባይነትን እንዲያገኙ አድርጓቸዋል። በዚህ ማህበረሰብ ላይ ህልም ፈቺ የሆነው ሰው (ግለሰብ) በማህበረሰቡ እና በግለሰቦች በሚደረጉ ድግሶች፣ ከበራዎች፣ ሰርጎች፣ ተስካር ላይ እንዲገኙ በክብር ይጠራሉ ተጠርተው በልተው እና ተጫውተው መርቀው እንዲሄዱ ያደርጋል። አንዳንድ ጊዜ ከህልም ፈቺው የህልም አፈታት እውቀት ክህሎት የተነሳ ከሌላ (እራቅ) ካለ ቦታ መጥተው ህልም የሚያስፈቱ ሰዎች አሉ።

ህልም ፈቺ ማንኛውም ሰው ስለማይሆን እነዚህን ሰዎች ደግሞ ተንከባክቦ መያዝ የሁሉም ማህበረሰብ ግዴታ ነው። ይህ ካልሆነ ግን ያልተለመዱ እና ውስብስብ የሆኑ ህልሞች ሲኖሩ ሰዎች ጥሩ ህልም ፈቺ ከሌለ የስነ-ልቦና ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል። በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ፈቺዎች ህልም የመፍታት ችሎታ ብቻ ሳይሆን ሌሎች የተለያዩ ችሎታዎች እንዳሏቸው መረጃ ሰጭዎች ተናግረዋል። ይኸውም በማህበረሰቡ ዘንድ መንፈሳዊነታቸው እየጎላ ስለሚሄድ የንፋሱን አነፋፈስ አይተው ዝናባማ፣ ፅሀያማ፣ ድርቅ፣ በልግ የሚባለውን የአየር ሁኔታ የሚተነቢዩ፣ የሰላም ዘመን የትኛው እንደሆነ የሚናገሩ፣ የጥፋት እና የልማት ዘመን የትኛው እንደሆነ የሚገልፁ ስለሆኑ ያላቸውን ማህበራዊ ክብር ክፍ እንደሚያደርገው ይገልፃሉ። የሚከተለው ሃሳብ ማህበረሰቡ ክብር ይሰጣቸዋል? የሚል ጥያቄ ለህልም ፈቺዎች ጥያቄ በቅርብ ጊዜ የተገኘ መረጃ ነው። ይኸውም፡-

> *አዋቂ በጠፋበት ዘመን ሰውስ ክብር ይሰጠናል። ክብሩም ተአለን የህልም መፍታት ተግባር ጋር በተገናኘ መልኩ ነው። ማለቴ ህልም መፍታት ከባድ ነው። ህልም ያዩ ሰዎች ህልሙን በጥሩ እና በመጥፎ ስትፈቺው የሚደሰተው እና በዚያው ልክ ደሞ የሚያዝነው ብዙ ነው። እንዲውም አንዳንዱ ህልሙ ሲከብደው በውስጡ አፍኖ ይዞ የሚብሰለሰል አለ። ክፉ ፍቺ ያለውን ህልም ተፈታሽ በኋላ ዝም አትይም እንዲህ ብታደርግ እንዲያ ብታደርግ የሚል መፍትሄ ጭምር ተናግረሽ ታጥናኛቸዋለሽ። ይኸን የሚያደርግም ተሰጦው ያለው ሰው ስለሆነ ሌሎች ሰዎች እንደሚበልጥ ስለሚያውቁ ያከብሩታል።* (ከቡድን ውይይት፡ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

የተገለጸው ሀሳብ የሚያስገነዝበው ህልም ፈቺዎች ከአላቸው ማህበራዊ ተግባር እና ከሚያበረክቱት ማህበራዊ አስተዋፅኦ የተነሳ ማህበራዊ ደረጃዎች ከፍ ያለ መሆኑን ነው።

ህልም አላሚዎች ህልማቸው በትክክለኛው መንገድ ሲፈቱላቸው፤ የተጣሉ ሰዎች ለእርቅ ሲበቁ፣ በህልም አማካኝነት ያለውን የዘመን ሁኔታ ተናግረው ሰዎች የራሳቸውን እርምጃ በመውሰድ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በማድረግ፣ ከማህበረሰቡ የወጡ (ያፈነገጡ ሰዎች) ከማህበረሰቡ ተስማምተው  ተናበው (ተግባብተው) እንዲኖሩ በማድርግ እረገድ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወቱ ማህበራዊ ደረጃቸውም ከፍ ያለ ነው፡፡ ህልም ፈቺዎች በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ነገሮችን በምክንያት እና በውጤት የሚረዱ የማህበረሰብ አባል ስለሆኑ ማህበረሰቡ የሚቀበላቸው ናቸው ፡፡ በዚህ ማህበረሰብ አንድ አንድ ሀገረሰባዊ እምነት የሚቆጠር እና የሚታመን በመሆኑ ህልም የሚፈታ አካል እንደሚያስፈልግ ይታወቃል፡፡ ይህ አስፈላጊ ነገር ደግሞ በማህበረሰቡ ሀብት እንደመሆኑ መጠን እንክብካቤ እና ጥበቃ የሚፈልግ በመሆኑ ክብር መስጠት ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

## 5.4.2 የህልም ፈቺዎች የለመዳ ሁኔታ

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም የመፍታት ተግባር በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል፡፡ የህልም ፈቺዎች ችሎታ እንደማናቸውም ግላዊ ፍላጎት እና እንቅስቃሴ ተለምዶ ተግባር ላይ የሚውል አይደለም፡፡ የህልም አፈታት የለመዳ ሁኔታዎች በአብዛኛው ሌሎች ልምዶች እንደሚተላለፉት ከአባት ወደ ልጅ በምልከታ እና በተለያዩ አጋጣሚዎች በተገኘ የተግባር ሙከራ የሚለመድ ነው፡፡ ህልም የመፍታት ልምድ እንደ ህልም ማለም በፈጣሪ የሚሰጥ ፀጋ አልያም  ከህልም ጋር በሚኖረን የረዥም ጊዜ ህልም ማየት ተግባር ከህልም ጋር ካለን የረዥም ጊዜ ትውውቅ የተነሳ ህልም መፍታት እንደሚቻል በማህበረሰቡ ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው በህይዎቱ በተለያዩ አቅጣጫዎች በተለያየ ነገር ሲፈተን ህልም መፍታት እንደሚችል ይናገራሉ፡፡ በተለይም ህልም መፍታት በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚለመድ እንዳልሆነ ይገልፃሉ፡፡ ህልም መፍታት ህልም ከማየት የማይተናነስ ሲበዛም ሊበልጥ የሚችል እንደሆነ የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ያምናል፡፡ ሌላው ደግሞ ህልም መፍታት በራስ ሙከራ ያገኙት እንደሆነ ህልም ፈችዎች ይገልፃሉ፡፡ የህልም መፍታት ለመዳን በተመለከተ አቶ ቢተው ሰውአገኘ ህልም መፍታት እንዴት  እንደለመዱ እንደሚከተለው ገልፅዋል፡፡

> *ህልም መፍታት የሚችል ሰው በጣም ፈላስማን የሆነ ሰው ነው እኔ ህልም መፍታት የለመድኩት እኔም ነገረኛ ነኝ ነገርም ይመጣብኛል በእነዚህ ላይ ብዙ ጊዜ አምሰለስላለው ስኖር ያልሰራውት ስራ የለኝም እብደቱንም ሌብነቱንም አሳልፌዋለው ትንሽት የቆሎ*

*ትምህርትም ተምሬያለው እና ተዚያ አንጣር ብዙ አይቻለው ብዙም አውቃለው ማለት ነው።* (አቶ ቢተው ሰውአገኝ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

ሌላኛዋ ህልም ፈቺ ደግሞ ህልም መፍታት እንዴት እንደለመደች በሚመለከተው በልኩ ተናግራለች። ‹‹ *ህልም መፍታት የለመድኩት በራሴ ላይ ሲደርስ የማየውን ህልም መከታ አድርጌ ዝም ብየ በመለማመድ እንጂ ከላይ ተሰቶኝ ነው* አልልም።›› (እማሆይ ይረብ አወቀ፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 ኢ.ም)

ከላይ የተገለጹት ሃሳቦች የሚያስረዱት በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ፈቺ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች ህልም ፈቺ እንደሆኑ ሲሆን አንዳንዶቹ በአሳለፉት የህይወት ተሞክሮ ያገኙት እንደሆነ ያመለክታሉ። ሌሎች ደግሞ ከልምዱ ጋር በአላቸው ጥብቅ ግንኙነት እንደሆነ ያስረዳሉ።

## 5.5 የህልም ፋይዳ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ

ህልም በርካታ ማህበረሰባዊ እና ግለሰባዊ ፋይዳዎች አሉት። ህልም ለአላሚውም ሆነ ለህልም ፈቺው የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው። ህልም ከአላሚው አንፃር ስንመለከተው የአላሚውን ማንነት ለመረዳት እና ለማወቅ ያግዛል። ህልም ኢ-ንቁው አእምሮ ውስጥ የተደበቁ አወንታዊ እና አሉታዊ ፍላጎቶችን እና ስሜቶችን መግለጫ ነው። መጭው ዘመን ምን እንደሚመስል የሚተነብይልን ህልም ነው። ህልም የሰዎችን የወደፊት እጣ ፈንታ የሚነግር ነው። ህልም በተለያዩ ጉዳዮች እና መንገዶች እራሳችንን እንድንጠብቅ ያደርገናል። የተለያዩ ሰዎች ምኞቶች፣ ስነ-ልቦናዊ ክስተቶች፣ መገልገያ ቁሶች እና ቅራኔዎች (ተቃውሞዎች) በህልም ይከሰታሉ። ህልም ዕርስ በዕርሳቸው ሊነጣጠሉ ወይም ተነጣጥለው ሊታዩ የማይችሉ ልዩ ልዩ ጠቀሜታዎችን ያካተተ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ስለሆነም ህልሞች በሚኖራቸው ቁሳዊ እና መንፈሳዊ አገልግሎት ወይም ተግባር አንፃር እያንዳንዱን ተግባራቸውን ከእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ አንፃር እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

### 5.5.1 የህልም ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ

ስነ-ልቦና የሰዎችን ውስጣዊ ጉዳይ መመርመር የሚቻልበት መንገድ ነው። ስነ-ልቦና ሰዎች ምን እንደሚያስቡ፣ ወደፊት ሊሰሩት ያቀዱት እቅድ ምን ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ፣ ምኞታቸው ምን እንደሆነ፣ከዚህ በፊት የሰሩት ስራ የትኛው አእምሯዊ ጠባሳ እና ጸጸት

እንደሆናቸው፣ የደስታቸው እና የሃዘናቸው ምንጭ ምን እንደሆነ፣ የስኬታቸው መሰረት ምን እንደሆነ…ወዘተ የመሳሰሉት ጉዳዮች ለኖሩበት፣ለሚኖሩበት እና ሊኖሩበት በአሰቡት ላይ ያለውን አወንታዊ እና አሉታዊ ገጽታ በሰፊው የሚመለከት ነው፡፡

ስነ-ልቦናዊ የሆኑ ጉዳዮች ከሚታዩባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ህልም ነው፡፡ ህልሞች ሰዎች በእንቅልፍ ውስጥ እያሉ የሚከሰቱ አእምሯዊ ክዋኔዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን አላሚው በሚያይበት ሰአት ያለመውን ህልም ይዞት አስታውሶ ካወቀ በኂላ የህልሙን አስደሳችነት እና አስጨናቂነት በውስጡ ከሚያስበው እና ከሚፈጠረው አካባቢው ከአሉ ሁኔታዎች ጋር በማያያዝ ይገልጸዋል፡፡ ስለሆነም ህልም አእምሮን የመጠገን እና አእምሮን የመጉዳት ተግባር እንዳለው ያሳያል፡፡ ህልም ከተጠናው ማህበረሰብ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው አንዳንዴ የደስታ ምንጭ፣ ከህሳብ መገላገያ ወይም ማረፊያ ሲሆን በአብዛኛው በጭንቀት የተሞላ ነው፡፡ ህልም ስናይ ጥሩ ቢሆንም ወደፊት የሚሆነውን ስለማናውቅ የሆነ ነገር እስክናይ (እስኪከሰትብን) ድረስ እንጨነቃለን፡፡ ህልም የሰዎችን ሀሳብ፣ ፍላጎት፣ ስሜት፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት፣ ፍልስፍና ተከትሎ የመጣ መሰረታዊ የእንቅልፍ ደረጃ ስለሆነ ሰዎችን በህልማቸው አማካኝነት ያላቸውን ስነ-ልቦናዊ ጉዳይ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ህልም በአንድ በኩል ስነ-ልቦናን ሊጎዳና ሊያስጨንቀን የሚችል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ደስታን ሊፈጥር፤ እፎይታ ሊያመጣ ይችላል፡፡

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም አስደሳች (የልጅ መውለድ) ብስራትን የሚሰራበት የሀብት ማግኘት መንገድ የሚታይበት፣ የመዳን (የፈውስ) መንስኤ፣ አንድ ሰው ከማህበረሰቡ እንዳይወጣ ህግ ማስጠበቂያ፤ እንዳያፈነግጥ ያደርጋል፣ እውቀት ማግኘትን ፈር የሚቀደድበት፣ እርቅ እና ግንኙነት የሚፈጠርበት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ነገሮች የህልምን መልካምነት የሚፈረጅባቸው ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህልም የሞት ምልክት፣ በበሽታ መያዝ ምልክት፣ የማጣት (ድሃ የመሆን) ምልክት፣ የግጭት ምልክት ስለሚሆን በአላሚዎች ዘንድ ያለመረጋጋት፣ የመደንገጥ፣ የመጨነቅ፣ የመተከዝ፣ እረፍት ማጣት፣ መረበሽ፣ ሰላም ማጣት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ነገሮች በግለሰቡ ስነ-ልቦና ላይ ይከሰታል፡፡ ይህን ክስተት ለማከም ደግሞ ሰዎችን በስነ-ልቦና እይታ ማየት እና መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ስነ-ልቦናዊ የህልም ጠቀሜታን በተመለከተ ከእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የተገኘ የህልም መረጃ እንደሚከተለው ነው፡፡

*እኔ በቅርብ ጊዜ አይነ ስውር ስለሆንኩ አብራኝ የምትኖር አንዲት እህቴ ነበረች ልጆቼ፣ እህት እና ወንድሞቼ አልቀው አንዲት ቀርታ አብራኝ እየመራችኝ አብረን ስንኖር አንድ ቀን በህልሜ የሞተችበት ዘመኗ የማይታወቀው እናታችን መታ ይመስለኛል አብረን ስናወራ ስንጫዎት ቆይተን በይ ፊት ፊት ተነሽ ይዝሽ ልሂድ ነው የመጣሁ ትላት እና ተተቀመጠችበት አስነስታ እጇን ይዛት ትሄድ ይመስለኛል። ለምን ነው ይዘሻት የምትሄጅ ተሎ መልሻት እያየሽኝ እኔን ወይ እኔም አብሬ ልምጣ ብዮ የጠየኳት እንደው አይ እሷ አትመለስም አንቺም እዛው ጠንክሪ እራስሽን አውጭ አትመጣም እንዳትጠብቂያት ብላ እናታችን ተፊት እህቴ በኋላ ተከትላት ሲሄዱ አይኔን ጥድብ አድርጌ እያየዋቸው ሲጠልሙ ብትት አልኩ። ተነስቼ አለቀስኩ በበነጋታው ቤተ- ክስያን ሄጀ ተሳልሜ፣ ጠልየ መጣሁ። ተዚያ ቀን ጀምሮ አለቀስኩ። ህልሙን ታለምኩት በኋላ ጭንቀት እና ሀሳብ ስለያዘኝ እራሴ ሰላም አጣሁ። ተዚያ ህልሙን ታየሁት ሁለት ወር ሆኖት እህቴ እንጨት ተበርሀ ልታመጣ ህዳ ናዳ መቷት ሞተች።* (እማሆይ ይረብ አወቀ፡ *ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 ዓ.ም)

ከላይኛው ሃሳብ ጋር በተያየዘ Lois (2006፣10) *‹‹ አለምን በስነ-ልቦና መነፀር ማየት የእያንዳንዱን ግለሰብ ህይዎት ምን እንደሚመስል ጭምቅ አድርገን ማወቅ እንችላለን። የስነ-ልቦና ጥናት የሚያገለግለው ስነ-ልቦናዊ የሆኑ ችግሮችን ማለትም የህይዎት ምስቅልቅል መፍታት ነው። የስነ-ልቦና ታሪክ ከልጅነት በቤተሰብ ውስጥ የርዕስ በዕርስ ትስስር ይጀምራል።››* በማለት አትቷል።

ስለዚህ ሃሳቡ የሚያስረዳው የሰው ልጅ ስነ-ልቦናዊ ችግሮች ከተፈቱ ደግሞ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ማሟላት እና ማሳካት ቀላል ነገር እንደሆነ ያስረዳል። የሰው ልጅ ስነ-ልቦና ከተጎዳ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ የሆኑ ተግባሮችን ማከናወን ያዳግተዋል። ስለሆነም የመጀመሪያው መስተካከል ያለበት ሰዋዊ ጉዳይ ስነ-ልቦናን ማከም ነው። እናም የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልምን በመጠቀም ለተጫነው ስነ-ልቦናዊ ችግር የተለያዩ መፍትሄዎችን በማምጣት ችግሩን እየፈታ ይኖራል። ይህን ለማድረግ ደግሞ በስነ-ልቦና ጥናት ላይ በቂ እውቀት እና ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ የህልም ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ከሁሉም የህልም ግለሰባዊም ሆነ ማህበራዊ ፋይዳዎች እንደሚበልጥ ከተጠናው ማህበረሰብ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በመሆኑም ሌሎች የህልም ፋይዳዎች በህልም ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ድልድይ አልፈው የምናገኛቸው ናቸው።

## 5.5.2 የህልም ማህበራዊ ፋይዳ

ህልም በማህበረሰቡ የተለያዩ ማህበራዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡ የህልም ማህበረሰባዊ ፋይዳ በተለያየ መንገድ ሊገለፅ የሚችል ነው፡፡ ህልም በህልም አላሚው እና በህልም ፈቺው ዘንድ ትውውቅን በመፍጠር ከማስፈታት እና ከመፍታት በአለፈ እስከ መጋባት፣ ጸበል በአንድ መጠጣት፣ ክርስትና መናሳት፣ በስራ መወናፈል፣ በአንድ አንድ በአል ላይ የመጠራራት፣ በሽምግልና እና በእርቅ መተባበር በሀዘን፣ በደስታ መተባበርን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ህልም ሰዎች ከአሉበት ከሚኖሩበት፣ ከአሳደጋቸው የማህበረሰብ የፎክሎር ቡድን እሴት፣ ደንብ፣ ወግ፣ ልማድ፣ አመለካከት፣ አስተሳሰብ እና እምነት አፈንግጠው እንዳይወጡ ይጠብቃቸዋል፡፡ ይኸውም ከማህበረሰቡ ሊወጡ የሚፈልጉ ግለሰቦችን በህልም አማካኝነት ይገሰፃሉ፡፡ የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡-

*‹‹በህልሜ ስለሴት ልጆቼ እና ስለ የልጅ ልጆቼ ሲያልመኝ ሊያገቡ ሲሆን ሁል ጊዜ በህልሜ መቀነት ሲታጠቁ አያለው ሌላ ደም ሊፋቱ ሲሉ መቀነታቸው ሲፈታ እና ሲጠፋቸው አያለው፡፡ እሱም ይደርሳል፡፡››* በማለት ገልጸዋል፡፡ (አቶ አስራቴ ቢተው፡ ቃለ-መጠይቅ፣ የካቲት 2011 ኣ.ም)

ከላይ የተገለጸው ህልም የሚያሳየው የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ጋብቻን በተመለከተ ህልምን በማለም እና በመፍታት እንደሚጠቀም ያሳያል፡፡ አንድ አንድ ሰዎች በተለያየ ምክንያት ሲጣሉ እንዲታረቁ እና አብሮነትን እንዲያጠናክሩ በህልም አማካኝነት ይነገራቸዋል፡፡ ሰዎች ትዳራቸውን ሲፈቱ በተለያዩ የህልም አይነቶች በተለያየ መንገድ እና መልክ ወደ ትዳራቸው እንዲመለሱ እና ትዳራቸው ተመልሶ የሚገነባ መሆኑን እና ተስፋ እንዲኖራቸው ህልም ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ህልም ፍቅርን፣ ትብብርን፣ አብሮነትን፣ መተሳሰብን፣ መረዳዳት እና በጤናማ ግንኙነትን በማህበረሰቦች ዘንድ እንዲኖር ከሚያደርጉ መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ እነዚህ ነገሮች በህልም ከሚተገብሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ አንዱ መሆኑን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

## 5.5.3 የህልም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ

ህልም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አለው፡፡ በህልም አማካኝነት የአንድን ዘመን አካባቢያዊ እና ሀገራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታን ማወቅ ይቻላል፡፡ ይኸውም ወቅትን ጠብቀው የሚዘሩ አዝርቶችን እና ሰብሎችን የወቅቱን (የአየር ፀባዩን) የዝናቡን የአዘናነብ

ሁኔታ በማየት መዘራት ያለባቸው ሰብሎችን በህልም ማየት እንደሚቻል የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰቦች ይገልፃሉ፡፡ *‹‹ህልም መቼ ይታለማል››* በሚለው ርዕስ ለመግለፅ እንደተሞከረው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በአብዛኛው መጋቢት እና ማዚያን የሚታለሙት ህልሞች የማህበረሰቡን የግብርና ሁኔታ የሚያወሱ መሆናቸውን በተገኘው መረጃ ተረጋግጧል፡፡ በእነዚህ ወራቶች የሚታለሙት ህልሞች ወደፊት ለመዘራት በተዘጋጀው እርሻ ላይ ምን አይነት ሰብል ቢዘራ ምርታማ እንደሚሆን ይተነብያሉ ወይም ይናገራሉ፡፡ ሌላው ደግሞ የዘመኑን እርሀብነት እና ድርቅ በመግለፅ ሰዎችን እንዲጠነቀቁ ይናገራሉ፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር የተያያዘ ሃሳብም በቁራን እና በመፅሀፍ ቅዱስ መጽሃፍቶች ላይ በሰፊው ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የትኛው ዘመን እንስሳት የሚራባበት፣ የእንስሳት ሞት የሚበረክትበት፣ እፅዋት የሚበረክቱበት (የሚፀድቁበት)፣ የሚደርቁበት፤ በአጠቃላይ የእንስሳት እና የእፀዋት ዘመን የሚሆነውን እና የማይሆነውን በህልም ማወቅ ይቻላል፡፡ የሚከተለውን ህልም እንደምሳሌ እንመልከት፡-

*‹‹ይዳን ወንዝ እና ጭኤ የተባሉ ትልልቅ ወንዞች በህልሜ ደፍርሰው ጎርፍ ሲኸድ ታየሁት አካባቢያችን አዝመራ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡ ሲሆን ደግሞ ያሳየኛል፡፡››* (አቶ አጎልን *ታምራት፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት* 2011 *አ.ም*)

የህልም ፋይዳ ከኢኮኖሚ አንጻር በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ  ከግብርና ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን በንግድ፣ ከሽመና፣ የተቀበረ ብር ከማግኘት እና ከመጥፋት ጋር፣ ስራ ከማግኘት እና ደመወዝ ጭማሬ ከማግኘት ጋር፣ እቁብ ከመድረስ እና ሎተሪ ከመድረስ ጋር፣ ሽልማት ከማግኘት ጋር ወ.ዘ.ተ ከመሳሰሉት ኢኮኖሚን የሚመለከቱ ጉዳዮች ድህ እና ባለፀጋ መሆንን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ኢኮኖሚን በተመለከተ በሚኖራቸው አስተሳሰብ እና አመለካከት ህልም እንደ አንድ ማሳያ መንገድ አድርገው ይገለገሉበታል፡፡

## 5.4.4 የህልም ፖለቲካዊ ፋይዳ

ህልም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ እና አመለካከት ላይ የራሱ ድርሻ እንዳለው ከተሰበሰበው መረጃ ማወቅ ተችሏል፡፡ ህልም በዚህ ማህበረሰብ በአካባቢያቸው እና በሀገራቸው ላይ አስተዳዳሪ እና መሪ ሆነው የሚሾሙትን እና የሚሻሩትን ግለሰቦች የሚያውቁበት መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም  የንጉሱን ወይም የገዢውን፣ የተሾመውን ግለሰብ እድለኝነት እና እድለኛ አለመሆን፣ አንዱ ንጉስ ወድቆ ሌላኛው ሲተካ ስለሚያሳይ ህልም ትልቅ ተግባር አለው፡፡ በአንድ ሀገር ላይ ያለውን ፖለቲካዊ ለውጥ፣ ያለውን ሀገራዊ ሰላም፣

የገዢውን አካል (አስተዳዳሪውን) ጨቋኝነት፣ በዳይነት፣ ጨፍጫፊነት፣ ሰላም የሚያሰፍን መሆን አለመሆኑን በህልም ለተለያዩ ግለሰቦች ይገልጡላቸዋል፡፡ የትኛው እንደሚነግስ (እንደሚሾም) እና ከስልጣን እንደሚወርድ ወይም እንደሚሻር ህልሞች ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ ህልሞች ፖለቲካዊ የሆነውን የማህበረሰብ ህይዎት በአወንታዊ እና በአሉታዊ መንገድ ማሳየት እና መግለፅ ይችላሉ፡፡ ባለስልጣኖቹ ስልጣናቸውን ተመክተው ሰው እንዳይበድሉ፣ በስልጣናቸው ጥሩ ያልሆነ ነገር እንዳይሰሩ እና ህዝቡ ከመሪው ጋር ተዋዶ እና ተስማምቶ እንዲኖር ለማድረግ ህልሞች የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ፡፡ ከመረጃ ሰጭዎች የተገኘውን የሚከተለውን ህልም እንመልከት፡- *‹‹ ይመስለኛል በህልሜ ደርግ ሊጠፋ ሲል ጨረቃ እና ጀንበር አንድ ላይ ይወጣሉ ይመስለኛል ተዚያ ጨረቃይቱ እየደመቀች ስትኼድ ጀንበር ትጠፋለች፡፡ ተዚያ ደርግ ወደቀ ይሀዲግ ገባ፡፡ ››* (አቶ ፀጋ ይመር፡ ቃለ-መጠይቅ፣ መጋቢት 2011 አ.ም)

ከላይ የተገለጸው ሃሳብ የሚያሳየው ህልም የተጠኘውን ማህበረሰብ ያለውን ፖለቲካዊ አስተሳሰብ እና አመለካከት የሚያሳይ ሲሆን ማህበረሰቡ በአገሩ ላይ ያለውን የአገዛዝ ሁኔታ በተመለከተ እንደሚያስብ እና እንደሚጨነቅ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ፖለቲካዊ የሆኑ ጉዳዮችን እና ክስተቶችን በህልም አማካኝነት ያለፈውን፣ የሚመጣውን እና ያለውን የአስተዳደር ሁኔታ በሰፊው እንደሚገልፅ ነው፡፡

በአጠቃላይ ህልም በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ዘንድ ያለው ፋይዳ ዘርፈ ብዙ ሲሆን እንደየ ህልሙ ሁኔታ እና  እንደ አላሚው ማንነት ሁኔታ ልዩ ልዩ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የማያሻማ የማህበረሰቡ ሃቅ ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ህልም መንፈሳዊ እና ቁሳዊ የሆኑ ፍላጎቶችን የሚያንጸባርቁ ጠቅለል ያሉ እና አንዱ ለአንዱ ዋስትና የሆኑ ፋይዳዎች አሉት፡፡ እነዚህም ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዳዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ፋይዳዎች የማህበረሰቡን ባህላዊ እና ልማዳዊ አስተሳሰቦች እና አመለካከቶች አካተው የሚይዙ ቡድናዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ህልም በማህበረሰቡ የመጣውን፣ እንዲመጣ የታሰበውን እና የሚመጣውን ክስተት የሚያሳይ ነው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# 6. ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳብ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች እና ጠቃሚ ሀሳቦች ከተጠናው ማህበረሰብ የህልም እሳቤ አንፃር እንዲሁም የጥናቱ መረጃ ትንተና አጠቃላይ ሂደት ምን እንደሚመስል እና የይሁንታ ሀሳቦች ተጠቃለው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡

## 6.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት መነሻ ዋና ጉዳይ የህልም እሳቤ በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ምን እንደሚመስል ከማህበረሰቡ ልማድ አንፃር የተመረመረበት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ *‹‹በእናርጅ እናውጋ ወረዳ የህልም እሳቤን መመርመር››* ሲሆን ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ በተጠናው ማህበረሰብ ህልም ምንድን ነው? ህልም የሚመሰልባቸውን ትምዕርቶች መፈከር፤ ህልም የሚያልም እና የሚፈታ ማን እንደሆነ፤ ህልም መቼ እንደሚታይ እና መቼ እንደሚፈታ፤ የህልም ፈቺዎች የለመዳ ሂደት ምን ይመስላል፤ የህልም ፈቺዎች ያላቸው ማህበራዊ ደረጃ እንዴት ነው እና ህልም ለእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ምን ፋይዳ እንዳለው የተመረመረበት ጥናት ነው፡፡

ይህ ጥናት በምስራቅ ጎጃም ዞን ከእናርጅ እናውጋ ወረዳ ለጥናቱ መረጃውን ለመሰብሰብ እና መረጃውን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማግኘት አመቺነት ያላቸውን 4 የገጠር ቀበሌዎችን ከአየር ንብረት ፀባይ አንፃር በመምረጥ ጥናቱ ተጠንቷል፡፡ ቀበሌዎችም ከደጋ አምባ አገር፣ ከቆላ አራራ እና ከወይና ደጋ ቋሚጨርቅ እና ወፊት ላይ ጥናቱ ተወስኗል፡፡ ጥናቱ ማጠቃለያውን ጨምሮ በአጠቃላይ በስድስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፡፡ ምዕራፍ አንድ ለጥናቱ መግቢያ (መንደርደሪያ) የሆኑ ፅንሰ ሀሳባዊ የሆኑ ዳራዎችን፣ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ አላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት የጥናቱ ስነ-ዘዴዎች፣ የመስክ ተሞክሮ ዘገባ እና በጥናቱ ሂደት ላይ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ቀርበውበታል፡፡ ምዕራፍ ሶስት ክለሳ ድርሳናት ማለትም ፅንሰ ሀሳባዊ ዳራዎች እና የተዛማጅ ጥናቶች ክለሳ ተካተውበታል፡፡ ምዕራፍ አራት የተጠናውን ማህበረሰብ የሚመለከቱ አካባቢያዊ ዳራ መገለጫዎች የቀረቡበት ነው፡፡

ምዕራፍ አምስት ደግሞ ከመስክ የተሰበሰቡ የእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የህልም እሳቤን የሚመለከቱ መረጃዎች የተተነተኑበት ነው፡፡ የመጨረሻው ምዕራፍ (ምዕራፍ ስድስት) ደግሞ ስለጥናቱ አጠቃላይ የሆነ ማጠቃለያ ሀሳብ የተሰጠበት ክፍል ነው፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይ እና ከአካላይ መረጃ ምንጮች የሰንበታ ሰንበቴ ድግስ፣ ማህበር፣ የአመት በአል ዝክርት፣ የሙት አመታት ዝክርት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን በመጠቀም ቃለ-መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት በ16 ሰዎች ተሳታፊነት የተሰበሰበ ነው፡፡ በመሆኑም የመስክ መረጃው አዕምሮን የመገንባት (የማዋቀር) ስነ-ልቦናዊ ቲወሪን፣ የስነ-ፍቺ ቲወሪን እና ተግባራዊ ቲዎሪን በመጠቀም ገለፃ እና ትንተና ተደርጓል፡፡

በመረጃ ትንተናው በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ የህልም እሳቤን መሰረት በማድረግ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ እና አመለካከት ከህልም ምንነት እስከ ህልም ማህበራዊ ፋይዳ ያሉ መረጃዎች በህልም እሳቤ ፅንሰ ሀሳብ ሞዴል የሰው ልጅ ሲኖር የሚገጥሙትን አዕምሯዊ ብሎም አካላዊ ክስተቶች እና ችግሮች መፍትሄ ለማበጀት የሚያደርገው ጥረት ከስነ-ልቦና እድገት ደረጃ ጋር በማያያዝ ችግሮችን ከመጋፋጥ አንስቶ ለችግሮች መፍትሄ እስከመስጠት (እስከመውሰድ) ድረስ ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ በመሆኑም በትንታኔው የተገለፁት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በህይዎት እስከአለን ህይዎትን ለማቆየት እና ማህበራዊ የሆነ ግንኙነት መኖሩ አይቀሬ ስለሆነ እነዚህ ነገሮች እንዲሳኩ ግለሰቦች ያላቸውን ሃይል ሁሉ በሚሚጠጥ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፡፡

ስለሆነም በተለያዩ ነገሮች ምክንያት እና በተለያዩ ጊዜያት ፍላጎታችን ወደኋላ ሊጎተት አልያም ባላሰብነው ጊዜ ሊሳካ ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ ደስታን እና ጭንቀትን በውስጣችን ይፈጥራል፡፡ እነዚህ ደግሞ የግለሰቡን ማንነት መግለጫዎች ናቸው፡፡ ማንነትን መልሶ ለራስ የማሳየት ትልቅ ተግባር ከአላቸው መንገዶች አንዱ ህልም ነው፡፡ በተጠናው ማህበረሰብ በህልም ማህበረሰባዊ አስተሳሰብ አንፃር የህልም ማለሚያ ተግባር፣ የህልም አፈታት ስርአት፣ የህልም ማያ ወሳኝ ጊዚያት፣ የህልም አፈታት ልማድ እና የአላሚዎች ማህበራዊ ደረጃ እና የህልም ሚና ከምን አንፃር ነው የሚባሉት በዚህ መሰረትነት የተቃኙ ናቸው፡፡

እሳቤ በህልም ትርጉም እና ምንነት ከማህበረሰቡ ስነ-ልቦናዊ ተግባር ከሚፈጥረው አወንታዊ እና አሉታዊ ስሜት አንፃር፣ ህልምን በማየት እና በአለማየት የአለውን ጭንቀት እና ውዝግብ፣ የህልም ፈቺዎች የለመዳ ሂደት እና የሚከተሉት የአፈታት ስርአት፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የህልም አላሚዎች እና የህልም ፈቺዎች የተቀባይነት ሁኔታ ምን ያህል እንደሆነ በማህበረሰቡ

እስካሁን ድረስ የሚተገበር እንደሆነ በጥናቱ መረጃ ተገኝቷል፡፡ በትንተናው ህልም በአላሚዎች፣ በህልም ፈቺዎች ላይ የስነ-ልቦናዊ ጥገና በማድረግ ያለውን ፋይዳ በተለያዩ መንገዶች በህልም አማካኝነት መግለፅ እንደሚቻል በጥናቱ ታይቷል፡፡

በአጠቃላይ ህልም በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ትልቅ ተግባር እና ሚና ካላቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የተለያዩ የሳይንስ ተመራማሪዎች፣ በተለያዩ ነገሮች የሚያምኑ እና የሚያመልኩ አማኞች ( አምላኪዎች)፣ ፈላስፎች፣ የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች፣ ጸሃፊዎች፣ የስነ-ጽሁፍ ሰዎች፣ደራሲዎች፣ ገጣሚዎች፣ የጠፈር ተመራማሪዎች፣ የተማረው፣ ያልተማረው እና የተለያዩ ሀይማኖት ያላቸው ሰዎች የነገሮችን ትርጉም እና ፍቺ ለመስጠት ህልም መሰረታቸው ነው፡፡ ህልም የሌለበት ቦታ የለም፡፡ ህልም ከህጻናት እስከ ታላላቅ ሰዎች፣ ሴት እና ወንድ ጾታን ሳይለይ የሰዎችን ቀለም፣ ቁመት፣ የትምህርት ደረጃ የማይጠይቅ፣ ሃብት፣ ባህሪይ…ወዘተ የመሳሰሉትን ነገሮች የማይጠይቅ በሁሉም የሰው ልጅ ላይ እንደሁኔታው የሚከሰት ሀገረሰባዊ እምነት ነው፡፡ በተለያየ ባህል ለሚኖር ሰው፣ የተለያየ አመለካከት እና አስተሳሰብ ለሚከተል ማህበረሰብ ህልም በርካታ ትርጉም እና ፍቺ አለው፡፡

## የጥናቱ ግኝት

### 1. ህልም የሚታይባቸው ወሳኝ ጊዚያት ያሉት መሆኑ

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም እራሱን የቻለ የተለያየ ፍቺ ያላቸው ህልሞች የሚታለሙበት ወሳኝ ጊዜያት እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ጊዜያት ለህልም ፍቺ ከፍተኛ አስተዋጾ አላቸው፡፡ በተለይም የማህበረሰቡን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ፓለቲካዊ ጉዳይ መሰረት በማድረግ በሚኖረው ወቅታዊ እንቅስቃሴ ላይ ህልም ተግባራዊ እንደሚሆን የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡

### 2. በህልም ትዕምርት ሆነው የሚገቡ ነገሮች አሉታዊ እና አወንታዊ ገፅታ ያላቸው መሆኑ

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ማንኛውም ህልማዊ ትዕምርት ሁለት ገጽታዎች አሉት፡፡ በማህበረሰቡ እምነት አንድ የህልም ትዕምርት ሁለት አይነት አወንታዊ እና አሉታዊ ገጽታዎች ናቸው፡፡ ይኸውም አንዱ የህልም ውስጥ ትዕምርት መጥፎ እና ጥሩ የህልም ፍቺ እንደሚይዝ ነው፡፡ እነዚህም በግለሰቦች ዘንድ ትርጉም የሚሰጣቸው ግለሰባዊ ማንነትን የያዙ እና

በማህበረሰቡ ፍቺ የሚሰጣቸው ማህበረሰባዊ አደራረስ ያላቸው ናቸው፡፡ ትዕምርቶች ህልም በህይወት እንዲቆም የሚያደርጉ እንደሆነ በጥናቱ ታይቷል፡፡

## 3. የህልም ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ከሌሎች ፋይዳዎች ትልቁን ድርሻ የሚይዝ መሆኑ

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ህልም ከምንም በላይ ስነ-ልቦናዊ ፋይዳው ቀዳሚ ነው፡፡ ህልም ለዚህ ማህበረሰብ የደስታው ምንጭ፣ የሃዘኑ መገለጫ፣ የመኖሩ እና የመሞቱ ዋስትና የሆኑትን ነገሮች ያካተተ፣ የማግኘቱ እና የማጣቱ ጠቋሚ ክስተት፣ ጥላቻን የሚያወግዝበት፣ እርቅን የሚፈጽምበት፣ ፍቅርን የሚሰብክበት፣ የመረዳዳን እና የመተሳሰብ ተግባራትን የሚያከናውንበት በአጠቃላይ ጥሩ እና መጥፎ የሆነውን የህይወቱን ትልቅ ጉዳይ የሚለይበት እና የሚወስንበት መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ የተዘረዘሩት ነገሮች በሙሉ በማህበረሰቡ አባላት እያንዳንዳቸው አእምሮ ላይ አንዳች ነገርን ይፈጥራሉ፡፡ የሚፈጠረው ነገርም ደስታ፣ ሃዘን፣ ጭንቀት፣ ብስጭት፣ ጸጸት፣ ሃሳብ…ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች ደግሞ ከማህበራዊ፣ ከኢኮኖሚያዊ፣ ከፖለቲካዊ እና ከባህላዊ የማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት መግለጫዎች ይልቅ ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው ስነ-ልቦናዊ የማህበረሰቡ አስተሳሰብ እና አመለካከት መግለጫ ነው፡፡

## 4. በአንድ ህልም ውስጥ ብዙ የህልም ማህበራዊ ትዕምርቶች ያሉ መሆን

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ በአንድ ህልም ውስጥ ከአንድ በላይ ማህበራዊ ፍቺ ያላቸው እንደ ሰብሎች፣ የሰው ስሞች፣ እንስሳት፣ እጽዋት፣ አልባሳት፣ ምግብ እና መጠጦች…ወዘተ የመሳሰሉት የህልም ውስጥ ትዕምርቶች ተሰበጣጥረው እናገኛቸዋለን፡፡ እነዚህ ትዕምርቶች እያንዳንዳቸው እራሳቸውን የቻለ ትርጉም እና ፍቺ በመያዝ አንዱ ህልም የተለያየ መልክት እንዲይዝ ያደርጉታል፡፡ ከማህበረሰቡ በተገኘው መረጃ እንደተረጋገጠው በአንድ ህልም ውስጥ በርካታ ትዕምርቶች የህልሙን ይዘት በማስፋት የማህበረሰቡን አስተሳሰብ እና አመለካከት ያንጸባርቃሉ፡፡

## 5. በህልም ውስጥ ቀለም ሰፊ ሚና ያለው መሆኑ

በእናርጅ እናውጋ ማህበረሰብ ቀለም በህልም ውስጥ ለህልም ትርጉም እና ፍቺ ትኩረት የሚሰጠው እንደዋና የህልም መታያ መንገድ ይቆጠራል፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ሶስት ያህል ቀለሞች በህልም ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታዩ ሲሆን በማህበረሰቡም አመለካከት፣አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና እንዲሁም የኑሮ ዘይቤ ላይ ትልቅ አስተዋጾ ያላቸው ናቸው፡፡ እነዚህም ቀለሞች ቀይ፣ ጥቁር እና ነጭ ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው በግለሰቦች ህልም ውስጥ የራሳቸው ተግባር እና ህልማዊ ፍቺ አላቸው፡፡ በምዕራፍ አምስት እንደተገለጸው ቀይ ቀለም ቅድስ መላክን እና ውቃቤ መቅረብን የሚወክል ነው፡፡ ነጭ ቀለም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ መቅረብን፣ ፀጋ መልበስን (መጎናጸፍን)፣ ጽድቅ ማግኘትን እና ንጽህናን (ንጹህ መሆንን) የሚያመለክት ሲሆን ጥቁር ቀለም ደግሞ የነጭ ቀለም ተቃራኒ እንደሆነ በማህበረሰቡ የህልም አስተሳሰብ ውስጥ እናገኘዋለን፡፡

## 6. ህልም ያለንበትን እና መጪውን ጉዳይ የሚያሳይ መሆኑ

ህልም ለተጠናው ማህበረሰብ እንደፍሮይድ ያለፈን ያልተሳካ የልጅነት ምኞት፣ ፍላጎት ማሳኪያ እና ማውጫ መንገድ ሳይሆን ማህበረሰቡ አሁን ላይ ሆኖ ለሚያስበው፣ ለሚሰራው ስራ እና ወደፊት ምን ማድረግ እንዳለበት የሚያውቅበት ፣ምልክት የሚያገኝበት እና የወደፊት የኑሮ መመሪያ የሚያወጣበት መንገድ እንደሆነ ከማህበረሰቡ የተገኘው መረጃ ያስገነዝባል፡፡

### እሳቤ ማለት በዚህ ጥናት ምንድን ነው?

እሳቤ በዚህ ጥናት የህልምን ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ትርጉም (ምንነት) የሚመለከት ነው፡፡

### 6.2 ይሁንታ ሃሳብ

የተጠናው ማህበረሰብ ህልም ለማለም እና በህልም ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ያለውን አመለካከት፣ አስተሳሰብ እና ፍልስፍና ለማስፋት እና ለመጨመር፣ ከልዕለ-ተፈጥሮ ሃይል ጋር ለመገናኘት፣የሆነን ትሩፍት ለማምጣት…ወዘተ ለተለያዩ ጠቀሜታዎች በህልም ለማግኘት ሲሉ ‹‹ህልመ ዮሴፍ›› ድጋምን እንደሚጠቀሙ መረጃው ያመለክታል፡፡

ስለዚህ ከዚህ የጥናት ግኝት አንጻር ሌሎች አጥኚዎች የተለያዩ ንድፈ-ሃሳቦችን በመጠቀም ከዚህ በሰፋ እና በበለጠ ሁኔታ ቢያጠኑት በተለይም የተጠናው ማህበረሰብ ህልምን ለማየት ‹‹የህልመ ዩሴፍን›› ድግምት እንደሚጠቀም በአገኘውት መረጃ መሰረት ለመጠቀም ሞክሪያለሁ፡፡ በመሆኑም በይበልጥ ይህ የድግምት መረጃ ከተለያዩ መጽሀፎች ተጽፎ የሚገኘው በግዕዝ ቋንቋ ስለሆነ ቋንቋውን የሚችል ሰው ስለህልም በደንብ ማጥናት ስለሚችል ጥቆማውን በመከተል አዲስ ነገር እንደሚገኝ አምናለሁ፡፡ ስለዚህ ይህን የሚችል ሰው ቢያጠና የሆነ ግኝት በማግኘት ለባህል እውቀት አስተዋጾ ያበረክታልና ትኩረት ተሰጦት ቢጠና የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

## ዋቢ-መጽሀፍት


የማርክሲዝም ሌኒኒዝም፡፡ (1978)፡፡ <u>መዝገበ ቃላት</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ማሬ እና ሌሎች፡፡ (2004 ዓ.ም)፡፡ ‹‹በንፋስ መውጫ ከተማ ሀገረሰባዊ የህልም አፈታት ይዘታዊ ትንተና››፡፡ የመጀመርያ ድግሪ ክፊል ማሟያ ጥናታዊ ጹሁፍ፣ በባህርዳር ዩንቨርስቲ የተጠና፡፡

ሶሎሞን ተሾመ፡፡ (2007 አ.ም)፡፡ <u>የፎክሎር ምንነቱ እና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስ ትሬዲንግ፡፡

ሸህ ሰይድ ሙሀመድ ሳዲቅና ሐጅ ሙሀመድ ሳኒ ሐቢብ/ተርጓሚ/፡፡ (2004ዓ.ም)፡፡ <u>የቅዱስ ቁርዓን የአማረኛ ትርጉም</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ነጃሽ ማተሚያ ቤት፡፡

ሽታው ተገኘ፡፡ (2007 ዓ.ም)፡፡ ‹‹በሰሜን ሸዋ ዞን አንሳሮ እና ዋዩ ወረዳ የህልም አፈታት ትዕምርት ትንተና››፡፡ ለመጀመርያ ድግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ ባህርዳር ዩንቨርስቲ የተጠና፡፡

ቀና ማይጨው፡፡ (1945 ዓ.ም)፡፡ <u>የህልም መፍቻ</u>፡፡ ሰላም ቀ.ኃ.ሥ.ማ/ቤት ታተመ፡፡

ተሾመ ብርሀኑ፡፡ (2001 ዓ.ም)፡፡ <u>ጥንታዊ ዘመናዊና ሀይማኖታዊ የህልም አፈታት</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ሜጋ የግል መተሚያ ድርጅት፡፡

ቴወድሮስ ገብሬ፡፡ (2008 ዓ.ም)፡፡ <u>በይነ-ዲሲፕሊናዊ የስነ-ጹሁፍ ንባብ</u>፡፡ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ፕሬስ

አለም እሸቱ፡፡ (2001ዓ.ም)፡፡ <u>መሰረታዊ የምርምርና ዘገባ አጻጻፍ</u>፡፡ ቅድስት ማሪያም ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋክሊቲ ህትመት፡፡

አባ ቤተ ማሪያም እና ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁባ ጊወርጊስ (ተርጓሚዎች)፡፡ (1991 አ.ም)፡፡ <u>አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ምስለ ሥነ ፍጥረት አንድምታ ትርጉም</u>፡፡ በአክሱም ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡

ኤፍሬም አሰፋ፡፡ (1992 ዓ.ም)፡፡ <u>አዲሱ የአማረኛ መዝገበ ቃላት</u>፡፡ በሜጋ ማተሚያ ኢንተር ፕራይዝ ታተመ፡፡

ከሳቴ ብርሀን ተሰማ። (1951 ዓ.ም)። የዐማረኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። (1918 ዓ.ም)። መጽሐፈ ሰዋሰው ፡ ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ፣ አርቲስት ማተሚያ ቤት።

ወንዳለ ጌታቸው። (2000 ዓ.ም)። ምስባከቅዱሳን። ኃ.የተ.የማ.ማህበር፣ ጉተንበርግ ማተሚያ ቤት።

ዘርጋው። (2010ዓ.ም)። ከፍተኛ የአማረኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ ርኖቦት አታሚዎች።

ስማ ንጋቱ (ፒ.ኤች.ዲ)። (2009)። የፍካሬ ልቦና ትወራ ሚና፤ በተመረጡ ሁለት የግብረ-ወሲብ ተረቶች ማሳያነት። ዶ/ር አንተነህ አወቀ እና ዶ/ር ማረው አለሙ፣ *4ኛው የአማርኛ ቋንቋና የባህል ዘርፎች አገርአቀፍ አውደ ጥናት* ። የአማረኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ተቋም ባህርዳር፣ መጋቢት፣(ገጽ 54-74)። ፔዳ ግቢ፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ።

የኢትዮጲያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር። (2010 ዓ.ም)። የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጲያ ቋንቋዎች ጥናት እና ምርምር ማዕከል። (1993ዓ.ም)። አማረኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጲያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን። (2000ዓ.ም)። መጽሀፍ ቅዱስ። የብሉይ ኪዳን እና የሀዲስ ኪዳን መጽሀፍት። አዲስ አበባ፣ የኢትዮጲያ መጽሀፍ ቅዱሰ ቅዱስ ማህበር።

ያለው እንዳወቀ። (2004ዓ.ም)። የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር። ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ደስታ ተክለ ወልድ። (1962ዓ.ም)። ዐዲስ ዐማረኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዳሳሽ እንዳየው። (2010 ዓ.ም)። ‹‹ የህልም አፈታት ልማድ በእብናት ወረዳ›› ለመጀመሪያ ድግሪ ከፊል ማሙያ የቀረበ ጥናት፤ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ የተጠና።

ጸሐይ ጅምበሩ፡፡ (2008ዓ.ም)፡፡ የአንጎሌ ሁካታ (ህይወቴን ልተንትን)፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማኅበር፣ ባህርዳር፡፡

ጸጋነሽ ሙሉ ጌታ፡፡ (2007 ዓ.ም፣ መስከረም)፡፡ እውነትን መፈለግ እና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ሃላፊነታችን ይሁን! ናይል፣2ኛ ዓመት፣ ቁጥር 8፣ ገጽ9፣ 11እና13፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991ዓ.ም)፡፡ የስነ-ቃል መምርያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር አባይ አታሚዎች፡፡

ABE /American Board of Examiners in Clinical Social Work, Subcommittee of the StandardsCommittee.(2004,january).*Thepractice of Psychoanalysis: A Specialty of Clinical Social Work (*Rev. ed.). Salem, MA: ABE.

Bascom,W. (1954). Four Function of Folklore: Journal of American Folklore.Vol. 67. N. 266.

Bronwen,M. and Felizitas, R. (2000). Dictionary of Semiotics. Cassell Lendon and New York.

Dorson, M. Richard, (Ed). (1972). Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago: Chicago press.

Eric Ackroyd. (2001). A Dictionary of Dream Symbols: with an introduction to dream psychology, Bland Ford.

Green, A. Thomas, (Ed). (1997). Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Atr.

Goldstein, Kenneths. (1962). AGuide fore Field Workers in Folklore. Hatboro Pennsylvania; The American Folklore Society.

Jackson, Bruce. (1987). Field Work. Urbana and Chicago: Unversity of Illinios Press,

Johnf, Putnam. (1964). Folklore; A Key to Cultural Understanding.

Freud, Sigmund. (1920). Dream Psychology; Psycho Analaysis for beginners. New York the jamesa Mccann Company.

Freud, Sigmund. (2010). Interpretation of Dream: A Member of the Perseus books group New York.

Martha, Sims and Stephen, Marthine. (2005). *Living Folklore* ; An Introduction to the study of People and Their Tradition. (Ohio: Utah State University Press,).

Taye Asefa. (1988). *Dreams in Amharic Prose Fiction.* Institiute of Ethiopian studies, P155.

Turner, Victor. (1967). The Forest of Symboles Aspects of Ndembu Ritual, NewYork: Cornell University press.

Tyson Lois. (2006). Critical theory to day: A user friendly guide, New York London.

## አባሪ1፡-ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ የምርምር ጥቄዎች

1. ህልም ማለት ምን ማለት ነው?

2. ህልም ህልምነቱ በምን ይረጋገጣል?

3. ህልም መቼ እና የት ይታለማል (ይታያል)?

4. ህልም ማን ያልማል ህልምን ማን ይፈታል? ህልም ማለም እና መፍታት መሰረታቸው ምንድን ነው?

5. ህልም ምን ፋይዳ አለው?

6. ጥሩ እና መጥፎ ህልም የቱ የቱ ነው?

7. ህልምና ፍቺው ለምን ይለያያል?

8. በህልም ውስጥ ወካይ ነገሮች ምን ምን ናቸው? ውክልናቸው ለምን ለምን ነው?

9. ህልም እና አላሚው ግንኙነት አላቸውን?

10. ህልም የሚታለምባቸው አመቶች፣ ወራቶች፣ ቀናቶች፣ ስአቶች አሉ ወይ?

11. ህልም ምን ገጽታ አለው?

12. ህልም መፍታት እንዴት ይለመዳል?

## አባሪ2፡- አብይ መረጃ ሰጭዎች

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ | ጾታ | ስራ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | መላከ ሰላም ዳምጤ አርገህ | 75 | ወ | አርሶ አደር | ቋሚ ጨርቅ |
| 2. | ጨሰ ገበዝ ደረሰ ገላየ | 80 | ወ | አርሶ አደር | ቋሚጨርቅ |
| 3. | ርዕሰ ደብር መሪጌታ አባተ ንጋቴ | 78 | ወ | አርሶ አደር | ቋሚ ጨርቅ |
| 4 | ወ/ሮ የተመኝ አለሙ | 67 | ሴ | የቤት እመቤት | ቋሚ ጨርቅ |
| 5. | ቄስ ግዛ ደነቀው | 45 | ወ | አርሶ አደር | ቋሚ ጨርቅ |
| 6. | እማሆይ ዋለ ገረመው | 58 | ሴ | የቤተክርስቲያን ግብር አድቃቂ | ቋሚ ጨርቅ |
| 7. | ወ/ሮ የንጉሴ በላይ | 67 | ሴ | የቤት እመቤት | ቋሚ ጨርቅ |
| 8. | አቶ ቢያድጌ ይወጉ | 53 | ወ | አርሶ አደር | ወፊት |
| 9. | አቶ ተሾመ ከበደ | 59 | ወ | አርሶ አደር | ወፊት |
| 10. | መሪጌታ ስማቸው አሞኘ | 46 | ወ | አርሶ አደር | ወፊት |
| 11. | ቄስ ጌታቸው በላይ | 72 | ወ | | ወፊት |
| 12. | እማሆይ አበቡ ተገኝ | 74 | ሴ | የቤት እመቤት | ወፊት |
| 13. | እማሆይ ባሳዝን ሙኔ | 56 | ሴ | የቤተክርስቲያን ግብር አድቃቂ | ወፊት |
| 14. | አቶ ልንገረው ያለው | 84 | ወ | አርሶ አደር | ወፊት |
| 15. | አቶ ባየ መኮነን | 75 | ወ | አርሶ አደር | አንባገር |
| 16. | ወ/ሮ ጥሩ ቀለም ባየ | 39 | ሴ | የቤት እመቤት | አንባገር |
| 17. | እማሆይ የዝና ቸኮል | 72 | ሴ | የቤት እመቤት | አንባገር |
| 18. | አቶ ንጉሴ አንዷለም | 80 | ወ | አርሶ አደር | አንባገር |
| 19. | አቶ አስራቴ ቢተው | 79 | ወ | አርሶ አደር | አንባገር |
| 20. | ወ/ሮ እራቤ ጥሩነህ | 62 | ሴ | የቤት እመቤት | አንባገር |
| 21. | አባ ብሬ ተካ | 60 | ወ | አድሶ አደር | አራራ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 22. | አቶ ቢተው ሰው አገኝ | 67 | ወ | አርሶ አደር | አራራ |
| 23. | እማሆይ ይረብ አወቀ | 75 | ሴ | አርሶ አደር | አራራ |
| 24. | አቶ ፀጋ ይመር | 82 | ሴ | የቤት እመቤት | አራራ |
| 25. | አቶ ብዙነህ ታምራት | 77 | ወ | የቤት እመቤት | አራራ |
| 26. | አቶ አቻም የለው ፈንታሁን | 66 | ወ | አርሶ አደር | አራራ |

## አባሪ3፡- ንውሳን መረጃ ሰጭዎች

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ | ጾታ | ስራ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ቀኑብሽ አለሜ | 46 | ሴ | የቤት እመቤት | ቋሚ ጨርቅ |
| 2. | ብርቱካን ተመስጌን | 18 | ሴ | ተማሪ | ቋሚ ጨርቅ |
| 3. | አቶ ተስፋየ ደጉ | 35 | ወ | ነጋዴ | ቋሚ ጨርቅ |
| 4. | አቶ ባወቀ ምሳኤ | 50 | ወ | አርሶ አደር | ቋሚ ጨርቅ |
| 5. | አቶ በአንተ አምላክ ታደሰ | 68 | ወ | አርሶ አደር | አራራ |
| 6. | ወ/ሮ የሮም ደመቀ | 55 | ሴ | የቤት እመቤት | አራራ |
| 7. | አቶ ፈንቴ እንዳለው | 48 | ወ | አርሶ አደር | አራራ |
| 8. | አቶ አጎልን ታምራት | 85 | ወ | አርሶ አደር | አራራ |
| 9. | አቶ አለባቸው ከበበው | 67 | ወ | አርሶ አደር | አንባገር |
| 10. | ወ/ሮሁልዬ እንዳላማው | 80 | ሴ | የቤት እመቤት | አራራ |
| 11. | ወ/ሮ ጆንበር ቢዘንጋው | 77 | ሴ | የቤት እመቤት | አራራ |
| 12. | ቄስ ሙሉቀን ተገኘ | 38 | ወ | አረሶ አደር | ወፌት |
| 13. | አቶ ሙንዬ ጌትነት | 63 | ወ | አርሶ አደር | ቋሚ ጨርቅ |
| 14. | አቶ ኤርሚያስ ስበር | 32 | ወ | አርሶ አደር | አራራ |
| 15. | ቄስ መንበሩ ጌትነት | 65 | ወ | አርሶ አደር | ቋሚ ጨርቅ |
| 16. | ቄስ አያሌው ወንዴ | 42 | ወ | አርሶ አደር | ወፌት |
| 17. | አቶ ዳኘ ሰሬ | 70 | ወ | አርሶ አደር | ወፌት |
| 18. | አቶ ምንይችል አባተ | 54 | ወ | አርሶ አደር | አራራ |
| 19. | ወ/ሮ ታንጉት የወግነህ | 50 | ሴ | የቤት እመቤት | አንባገር |
| 20 | አቶ ነጋ እሸቱ | 82 | ወ | አርሶ አደር | አንባገር |

## አባሪ 4፡- ያልተተነተኑ የማህበረሰቡ ህልሞች

### ሀብት ማግኘትን የሚመለከቱ

በህልም ፍትፍት መሸከም አዝመራ ነው፡፡ በህልም እበት ማፈስ ሲሳይ ነው፡፡

በህልም ሰገራ (ሽንት ቤት) መንካት ሲሳይ ነው፡፡ በህልም ድንች መብላት ሲሳይ ነው፡፡

በህልም ዳቦ መጋገር እንጀራ (ስራ ማግኘት) ነው፡፡

### ሞትን የሚመለከቱ

በህልም ከዛፍ መውደቅ ሞት ነው፡፡ በህልም ዛፍ መቁረጥ ሞት ነው፡፡

በህልም የዛፍ ቅርንጫፍ መጨፍጨፍ የልጅ ሞት ነው፡፡

በህልም መኪና መሳፈር ሞት ነው፡፡

በህልም ቤተ-ክርስቲያን ስለት መስጠት (መጣል) ልጅ መሞት ነው፡፡

በህልም ዳቦ ደፍቶ ይዞ መሄድ የሙሽራ ሞት ነው፡፡ መህልም መሞሸር (ማግባት) ሞት ነው፡፡

### ደስታን የሚመለከቱ

በህልም ማልቀስ ደስታ ነው፡፡ በህልም ማዘን ደስታ ነው፡፡

በህልም ወንድ ልጅ ማዘል ጥሩ ነገር ነው፡፡ በህልም መጣላት ፍቅር ነው፡፡

### እድሜን የሚመለከቱ

በህልም ከሞተ ሰው ጋር ማድር እድሜ ነው፡፡ በህልም ረጅም መንገድ መሄድ አድሜ ነው፡፡

በህልም ገደል መግባት እድሜ ነው፡፡ በህልም ዛፍ መሰቀል እድሜ ነው፡፡

### ጀግንነትን የሚመለከቱ

በህልም እበት መሸከም ጀግንነት ነው፡፡ በህልም መውደቅ ማለፍ ነው፡፡

## ሀብት ማጣትን የሚመለከቱ

በህልም እራስን መላጨት ሀብት ማጣት (መጥፋት) ነው፡፡

በህልም በውሀ መታጠብ ሀብት ማጣት (መሸሽ) ነው፡፡

## በበሽታ መያዝን የሚወክሉስ

በህልም ቅቤ መቀባት ጉንፋን ነው፡፡ በህልም እራቁት መሆን መታመም ነው፡፡

በህልም ወታደር ማየት መሽታ ነው፡፡ በህልም መደብደብ በበሽታ መያዝ ነው፡፡

## ማዘንን የሚመለከቱ

በህልም በጣም መሳቅ ከባድ ሀዘን ነው፡፡ በህልም ማርገዝ ነገር መያዝ ነው፡፡

በህልም አንዱ በሬ ከሌው በሬ መደነብ አግብቶ ሰተቶ መሄድ ነው፡፡

በህልም መሞት መጥገብ ነው፡፡ በህልም ድልድይ መሰበር የመንግስት ለውጥ ነው፡፡

በህልም ልጅ መታቀፍ ነገር ነው፡፡ በህልም ስፌት መስፋት ትምህርት ነው፡፡

በህልም ጥቁር ሰው ጋር አብሮ ማደር ሰይጣን ነው፡፡ በህልም መውለድ ከሀሳብ መላቀቅ ነው፡፡

በህልም ልጉም ማስለጎም ቅርርብ መፍጠር ነው፡፡ በህልም ጥቁር በሬ አጋንት ነው፡፡

## አባሪ5፡- በመረጃ ስብሰባው ጊዜ የተነሱ ፎቶዎች




**ስዕል1፡-** መረጃ ሰብሳቢዋ በአራራ ቀበሌ ከአጋዥ መረጃ ሰብሳቢዋ ጋር፡፡ **ስዕል2፡-** የአራራ ቀበሌ ነዋሪ ህልም ፈቺ ይራብ አወቀ፡፡




**ስዕል3፡-** መረጃ ሰብሳቢዋ መረጃ በመሰብሰብ ላይ፡፡ **ስዕል4፡-** መረጃ ሰብሳቢዋ በቡድን ውይይት ላይ እያለች፡፡